

ወንሰይኩ መዋዕለ ትካት ተዘከርኩ ዓመተ ዓለም ወአንበብኩ::
የቀድሞውን ዘመን አሰብሁ ዓመተ ዓለምንም ቆጠርሁ አነበብሁም::
(መዝ 76÷5)

ኢትዮጵያ መስከረም 1 ቀን 2004 ዓ.ም. ላይ በራሷ አቈጣጠር 2012 ዓ.ም.፣7504 ዓመተ ዓለም፣ 1728 ዓመተ ሰማዕታት፣4 ዓመተ ወንጌላዊ፤ በጉንዳጉንዲ አቈጣጠሯ 7048 ዓመት፣ በቢዘን 7276 ዓመት፣መቀበሏን ያውቃሉ? ስለነዚህና ሌሎች የጨረቃና ከዋክብት አቈጣጠሮች፣ ስለኢትዮጵያ ሥነ ፈለክ (አስትሮኖሚ) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያገኛሉ:: "በረጋ መንፈስ የሚያነብ የባሕረ ሐሳብን ምሥጢር ይቀስማል::" ደጋግሞ የሚያነብ በባሕረ ሐሳብ ውስጥ ይዋኛል:: ነገር ግን የሚዋኘው ብቻውን ሳይሆን መግቢያና መውጫውን ከሚያውቁት ከአለቃ ያሬድ ፈንታ ጋር ነውና የሚያሰጋው አይኖርም::

**ከዚህ በፊት የታተሙ**

- መጽሐፈ ግጻዌ ሐዲስ ዘተሰናአወ በአርባዕቱ ክፍላተ አዝማን
- ፍኖተ ግእዝ(ዘመናዊ)
- የንግግር ሥርዓቶችና አገባቦች(Rules and Forms of Speech)

**ዋጋ 50.00 ብር**

ህትመት ፋር ኢስት ት...

# ባሕረ ሐሳብ

## የቀመርና የሥነ ፈለክ ምሥጢር



በአለቃ ያሬድ ፈንታ ወልደ ዮሐንስ

www.ethiopianorthodox.org

# ባሕረ ሐሳብ

## የቀመርና የሥነ ፈለክ ምሥጢር

በአለቃ ያሬድ ፈንታ ወልደ ዮሐንስ

17-8-2004 ዓ/ም

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

©የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
7504 ዓመተ ዓለም፣2004 ዓመተ ሥጋዌ (በፀሐይ)፣
2012 ዓመተ ምሕረት (በፀሐይና በጨረቃ)፣
1728 ዓመተ ሰማዕታት፣
ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ።

የሽፋን ዲዛይን፣ ብዙነህ መለሰ
መነሻ ሐሳብ፣ ሔኖክ ያሬድ

**<u>የሽፋን መግለጫ</u>**

ስለዕለታትና ዓመታት መመላለስ (ዐውደ ዕለትና ዐውደ ጳጉሜን)፣
እንዲሁም ስለነፋሳት ባሕርይ የሚያሳይ ከጥንታዊ ብራና የተገኘ የባሕረ ሐሳብ ሥዕልና ከአቡሻህር መጽሐፍ ከተወሰደ የአንድ ገጽ ምንባብ ጋር።

## መክሥት


መክፈቻ ጸሎት ---------- 1
አኰቴት ወክብር ---------- 3
ቀዳሚ ቃል ---------- 5
መቅድም ---------- 6
መፍትሔ ቃላት ---------- 8
መግቢያ ---------- 16
1. ባሕረ ሐሳብ ---------- 19
- የባሕረ ሐሳብ አዋጅ ---------- 20
- የድሜጥሮስ ታሪክ ---------- 27
- የአጽዋማትና በዓላት ሥርዓት ---------- 30

2. መርሐ ዕዉር ---------- 32
- ዓመተ ዓለም ---------- 33
- አዕዋዳት ---------- 34
- ዐውደ ዕለት በጥንታት ሲገለጽ ---------- 39
- ዐውደ ጳጉሜን በሰንበተ ወንጌላውያን ---------- 48
- የዐውደ አበቅቴ ትንተና ---------- 50
- የዘመነ ሐዲስ አጽዋማትና በዓላት ---------- 58
- የብሉይ አጽዋማትና በዓላት ---------- 61
- አምሳል መርገፍ ---------- 63
- የአበቅቴ ትስስር ---------- 65
- የአጽዋማትና በዓላት አወጣጥ ምሳሌ ---------- 69
- የቀመር ጥንታት




www.ethiopianorthodox.org

3. መጽሔተ ሕርግራግ ---------------------------------------- 86
4. እምርት ዕለት---------------------------------------- 128
- ቀመረ አዳም ---------------------------------------- 128
- ዓመተ ሕይወቱ ለአዳም---------------------------------------- 129
- የሺሕ ዓመት መነሻና መድረሻ ዕለት---------------- 133
- ከመዠመርያው አዳም እስከ ሁለተኛው አዳም---- 134
- ዐበይትና ንኡሳን ሰባዕያት ---------------------------- 138
- የጌታችን ሐረገ ትውልድ---------------------------- 144
- የእመቤታችን ሐረገ ትውልድ ---------------------- 145
5. ሐሳበ አቡሻክር ---------------------------------------- 154
- ዓመተ ዓለም በፀሐይና ጨረቃ---------------------- 154
- የጨረቃ የዕለት መንገድና ሕጸጽ ------------------ 157
- የከዋክብት ምግብና---------------------------------- 164
- ቀመረ ዐረብ ---------------------------------------- 172
6. ሐሳበ ፈለክ---------------------------------------- 175
- ዑደተ ፀሐይ---------------------------------------- 175
- የአራቱ ክፍላተ ዓመት ምግብና ---------------------- 177
- ኬክሮስና ኬንትሮስ---------------------------------- 182
7. ሐሳበ ነፋሳት---------------------------------------- 190
8. ሐሳበ ሰዓታት ---------------------------------------- 196
መክደኛ ---------------------------------------- 201
ስምአት ---------------------------------------- 210
ስለደራሲው---------------------------------------- 213





# መክፈቻ ጸሎት

*በስመ እግዚአብሔር አብ መስተሣህል ወመሐሪ በቃሉ ወበመንፈሱ ኵሎ ዓለመ ሣራሪ።*

*ወበስመ እግዚአብሔር ወልድ ቃለ አብ ነባቢ፣ ወቃለ መንፈስ ቅዱስ ተናጋሪ ኵሎ ፍጥረተ በአሐቲ ምክር ገባሪ።*

*ወበስመ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፣ መንፈስ አብ ወወልድ ኅጢአተነ ዘይሰሪ*

*ኅቡዓ ወክሡተ በአሐቲ ሥምረተ ፈጠረ እንዘ አስምክ በዝንቱ ጉንደ ሃይማኖት አስካለ በረከት ዘይፈሪ።*

*እጽሕፍ ለክሙ አበው እስመ አእምርክምዎ ለቀዳማዊ።*
*እጽሕፍ ለክሙ ወራዙት እስመ ሞእክምዎ ለእኩይ።*
*ጸሐፍኩ ለክሙ ደቂቅየ እስመ አእመርክምዎ ለአብ።*

1ዮሐንስ 2.03

## ትርጓሜ

በቃሉና በመንፈሱ ዓለምን ሁሉ ስለመሠረተ፣ መሐሪና ይቅር ባይ ስለሆነው ስለእግዚአብሔር አብ ስም፤ የአብ ቃል ነባቢ፤ የመንፈስ ቅዱስ ቃል ተናጋሪ ስለሆነው፣ ፍጥረትን ሁሉ በአንዲት ምክር ስለፈጠረ ስለእግዚአብሔር ወልድ ስም፣ በአንዲት የፈጣሪ ፈቃድ ሥውርና ግልጽ የሆነውን ኃጢአት ይቅር ስለሚል የአብና የወልድ መንፈስ ስለሆነ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም፣ የበረከት ፍሬን በሚያፈራ በዚህ የሃይማኖት ግንድ አምኜ፦

«አባቶች ሆይ፤ በመጀመርያ የነበረውን ዐውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ፤ ጐልማሶች ሆይ፤ ክፉን ድል ነሥታችሁታልና



www.ethiopianorthodox.org

እጽፍላችኋለሁ፤ ልጆች ሆይ፤ አብን ዐውቃችሁታልና እጽፍላችኋለሁ። (1ኛ ዮሐንስ 2÷13)





# አኰቴት ወክብር

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በሚያስተምሩበት፣ ባሕረ ሐሳብ ተብሎ በተሰየመው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ነው።

በተለይም የባሕረ ሐሳቡን ትምህርት በሚገባ ያስተማሩኝና ምሥጢሩንም የገለጹልኝ መምህራን ባለውለታዎቼ ስለሆኑ ስማቸውን በመጥቀስ ለመጽሐፉ አንባቢዎች ማሳወቅ እወዳለሁ።

1ኛ. መምህር ይኄይስ ወርቁ ዘብሔረ ጐጃም

2ኛ. መምህር ኄራ ወርቅ ገብረ እግዚአብሔር ዘደብረ ዳሞ ገዳም፣

3ኛ. አለቃ ወልደ ኪሮስ ገብረ መድኅን ዘብሔረ ሐረቆ ቅድስት ማርያም ጽዮን እንተ ይእቲ ደብረ ሲና ናቸው።

እኔም ከእነዚህ መምህራን የተማርኩትን ትምህርት በቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ይማሩ ለነበሩ ደቀ መዛሙርት ከ1976 እስከ 2000 ዓ.ም. ለ24 ዓመታት አስተምሬያለሁ።

የባሕረ ሐሳብ ትምህርት በጥቁር ሰሌዳ ላይ እየተጻፈ ደቀ መዛሙርት እንዲማሩት ማድረግ የተገለመረውም በዚሁ ትምህርት ቤት ነው። ደቀ መዛሙርቱ ጥልቅ ዕውቀት ስለነበራቸው ትምህርቱን እጅግ ይወዱት ነበር። እሊህ ደቀ መዛሙርት ባገራቸው ትምህርት የበሰሉና ባለሞያዎች ስለነበሩ በመማር ማስተማሩ ወቅት ከእነርሱ የተረዳኋቸውን ፍሬ ነገሮች በማከል ዛሬ እነሆ መጽሐፉን በዚህ ቅርጽ አቅርቤዋለሁ።

ይህ ጽሑፍ በመገለመርያ ንድፉ ተዘጋጅቶ ከቀረበ በኋላም በ1975 ዓ.ም. በነበረው ጉባኤ ሊቃውንት ታይቶና ተመርምሮ ሊቃውንቱ በሥነ ጽሑፉ ባንድ ቃል ተስማምተው መጽሐፉ እንዲታተም ፈቅደናል በማለት ሰኔ 2 ቀን 1975 ዓ.ም ፈርመውበታል።



www.ethiopianorthodox.org

ላስተማሩኝ መምህራንና የመዠመርያ ጽሑፉን መርምሮ እንዲታተም ለፈቀደልኝ ጉባኤ ሊቃውንት ምስጋና አቀርባለሁ። እንዲሁም ይህን መጽሐፍ ሳዘጋጅ ሔኖክ ያሬድ በአርታዒነት፣ ሙሉጌታ ያሬድ የጽሑፉን ረቂቅ በትጋትና በቅንነት እየተከታተለ በማጻፍና በማባዛት፤ፍጥረት ገረመው ጽሑፉን ተግታ ሳትሰለች በተደጋጋሚ በመጻፍ፣ሐዲስ እስጢፋኖስ ገላጭ ሥዕሎችን በማዘጋጀት፣ ብዙነህ መለሰ ቅርጸ መጽሐፉን በማደራጀት፣ኅሩይ አብዱ ጠቃሚ ሐሳብ በመስጠት፤ሁሉም በየሙያቸው ስለረዱኝ ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርብላቸዋለሁ።
መጽሐፉ መልክ እንዲይዝና የኅትመት ብርሃን እንዲያገኝ ላደረጉት አባ ዳንኤል አሰፋ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።





# ቀዳሚ ቃል

ጊዜ ለሰው ልጅ እጅጉን ቅርብ፥ እጅጉንም ምሥጢራዊ ነው። የሰው ልጅ ሐሳቡ፥ ንግግሩና ተግባሩ የሚከናወነው በጊዜ ውስጥ ነው። የጊዜአትና የዘመናት ቍጥርም ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር የተቆራኘ ነው። የአንድ ማኅበረሰብም ማንነት አንዱ መገለጫም የዘመን አቈጣጠር ነው።

ለመሆኑ ዘመን እንዴት ይቆጠራል? እንዴትስ ይመደባል? የትንሣኤ በዓል አንዴ መጋቢት 26፤አንዴም ሚያዝያ 30 የሚውለው ለምን ይሆን? ለምንስ ይዘዋወራል? ይህ የአለቃ ያሬድ ፈንታ የብዙ ዓመታት ድካም ፍሬ የሆነው መጽሐፍ እነኝህንና እነኝህን ለመሳሰሉ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።
"ለቃለ እግዚአብሔር ጥናት ሰዋስው፥ ለምስጋና ዜማ፥ ለምሥጢራት ቀኖና እንደሚያስፈልግ ሁሉ፥ ለጌታ በዓላት ደግሞ ባሕረ ሐሳብ ያስፈልገናል" ይሉናል ደራሲው።

በረጋ መንፈስ የሚያነብ የባሕረ ሐሳብን ምሥጢር ይቀስማል። ደጋግሞ የሚያነብ በባሕረ ሐሳብ ውስጥ ይዋኛል። ነገር ግን የሚዋኘው ብቻውን ሳይሆን መግቢያና መውጫውን ከሚያውቁት ከአለቃ ያሬድ ፈንታ ጋር ነውና የሚያሰጋው አይኖርም። ይልቁንም ጥበብን በሰፊው ያስተናግዳል እንጂ።

አባ ዳንኤል አሰፋ



www.ethiopianorthodox.org

## መቅድም

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት የሚነገር መሠረታዊ ድንጋጌ አለ። እንደ ቀኖናም ይታሰባል። ድንጋጌውም የሚከተለው ነው።

1) ምሥጢረ አቅማራትንና ሥነ ፈለካትን፣ የቤተ ክርስቲያን በዓላትና አጽዋማት የሚውሉበት ትክክለኛውን ቀን ለማወቅ ባሕረ ሐሳብን፤
2) የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ለማወቅና ወንጌልን ለማስተማር ሰዋስውን፤
3) ቤተ ክርስቲያንን በዜማ ለማገልገል ሦስቱ የዜማ ስልቶችን፤
4) ቤተ ክርስቲያንን ለማስተዳደርና ምሥጢራትን በሚገባ ለመፈጸም የቀኖናን ሕግ መማርና ማወቅ ይገባል። ከዚህ አዕማድ በመነሣትም የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ሐሳብ አጠቃላይ ገጽታ በዚህ መጽሐፍ ለማሳየት ተሞክሯል።

ይህ መጽሐፍ ባሕረ ሐሳብን ለማጥናት መነሻ ይሆን እንደሆነ ነው እንጂ፤ ትምህርቱ እንደ ስሙ እጅግ ጥልቅ ስለሆነ በዚህ ጽሑፍ የሚወሰን አይደለም። ገና ብዙ ይቀረዋል። ስለዚህ ይህ ባሕረ ሐሳብ የተባለው መጽሐፍ የቤተ ክርስቲያን ታላቅ ሙያና ያገርም ቅርስ ስለሆነ፤ መጽሐፈ አቡሻህርንና መርሐ ዕዉርን፣ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ የተባለ መጽሐፍን፣ መጽሐፈ ሔኖክና መጽሐፈ ኩፋሌን እንዲሁም እነዚህን የመሰሉ ሌሎች መጻሕፍትንም ጭምር በማጥናት ተሟልቶ እንዲጻፍ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንድታስብበት ለማሳሰብ ጸሐፊው ይህን መጽሐፍ ያቀርባል።

አለቃ ያሬድ ፈንታ ወልደ ዮሐንስ





### መለብው

ዝንቱ መጽሐፍ ዘያዜክር ቀደምተ አበው፣

ወልደ ያሬድ ሔኖክ በከመ ዜነው፣

በያሬድ ፈንታ ወልደ ዮሐንስ ተሰነዐው፣

ለትውልደ ትውልድ ከመ ይኩን መለብው፣

እስመ በውስቴቱ ምሥጢረ አቅማራት ወሥነ ፈለካት ሀለው።

ያሬድ ፈንታ ወልደ ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

# መፍትሔ ቃላት

**ልበ ምድር**:- የአይሁድ በዓል፣ባሕረ ኤርትራን የተሻገሩበት ደረቅ ምድር የሚታሰብበት፤

**ላዕላይ ቀመር**:- ተዘዋዋሪዎቹ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበት የላይኛው ቀን ወሰን፤

**ሐሳበ ቢዘን**:- አዳም የተፈጠረበት ዕለተ ዓርብን ጥንተ ቀመር ያደረገ የዓመት ስሌት

**ሐሳበ ጉንዳጉንዲ**:- ሰማይና ምድር የተፈጠሩበት ዕለተ እሑድን ጥንተ ቀመር ያደረገ የዓመት ስሌት፤

**ሕጸጽ**:- ጉድለት ፣ ጉዳይ ፣ ቅሬታ ማለት ነው:: ለምሳሌ ጨረቃ በዕለት፣በ15 ቀን፣ በወርና በዓመት ከፀሐይ የምታጉድለው ቀንና ሰዓት ሕጸጽ ይባላል:: ለምሳሌ የፀሐይ ወር 30 ቀን ሲሆን የጨረቃ ግን 29 ነው::
በዚህም ጨረቃ ከፀሐይ አንድ ቀን ስለምታጎድል ሕጸጽ መሰኘቱ ስለዚህ ነው:: የዓመቱ ሕጸጽም እስከ 19 ዓመት ቢሰበሰብ ወይም በ19 ቢበዛ 7 ወር ሆኖ ትራፋተ ዐውድ (የዐውድ ትርፎች) ይገኝበታል::

**ሕርግራግ**:- የአጽዋማትና የበዓላት አወጣጥ ሥርዓት በዝርዝር የተጻፈበት ሠንጠረዥ

**መርሐ ዕዉር**:- አንድ መሪ ማየት የተሳነውን ሰው መርቶ ከሚፈልግበት ቦታ እንዲያደርሰው፣ይህም መጽሐፍ አላዋቂውን ሰው መርቶና አስተምሮ ምስጢረ አቅማርን፣የቁጥር ምስጢርን ከማወቅ ያደርሰዋል ማለት ነው::

**መባጃ ሐመር**:- የአጽዋማትና በዓላት ማስገኛ ልዩ ቁጥር፣መባጊያ ሐመር (የበጋ ማመላለሻ) የመጥቅዕና የዕለታት ተውሳክ ድምር ሆኖ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን ቀን ያመለክታል:: የመጽሐፉን





ስም ባሕረ ሐሳብ፣ወደላይና ወደታች የሚመላለሱበት ሥርዓትም ሐመር (መርከብ) ብለውታል::

**መናዝል**:- አስራ ሁለቱን ወሮች ብርሃን የሚመግቡ (መገብተ አውራኅ) ከሐመል እስከ ሑት ያሉ በእንስሳት ስም የሚጠሩ 12 ከዋክብት::

**መዓልት**:- የብርሃን ጊዜ፤ የፀሐይ ብርሃን የሚታይባቸው 12ቱ ሰዓታት ማለት ነው::

**መጠነ ራብዕት**:- አንድ አራተኛ፤

**መጥቅዕ**:- የአይሁድ አዲስ ዓመት መባቻ፣አዋጅ የሚነገርበት ነጋሪት፣ደወል ማለት ነው:: የዕለታት ተውሳክ ሲደመርበት ውጤቱ መባጃ ሐመር ይሆናል::

**መጸለት**:- ዳስ፣የአይሁድ በዓል፤

**ሚጠተ ብርሃናት**:- የብርሃናት መመላለስ ማለት ነው::ያውም ብርሃናት በ12ቱ የፈለክ ደጃፎች (ኆዋኆወ ፈለክ የሚመላለሱበት ሥርዓት ነው::

**ማኀፈድ**:- አዳራሽ፣ግንብ፣ምሽግ::

**ማዕዶት**:- መሻገርያ፣ድልድይ፣ፋሲካ
**ምሥጢረ አቅማር**:- የዓመታትን ሥራና ሱባዕያቸው የዕለታትን መፈራረቅ የሰንበታትን አከፋፈል በስፍር በቁጥር የሚገለጽበት ስሌት ነው::

**ምዕዛር**:- የብርሃን ወንፊት፣ብርሃን የሚነዛበት ብሱ ነዳላው

**ሠርቀ ሌሊት**:- የሌሊት መባቻ (መገመርያ)

**ሠርቀ መዓልት** :- የመዓልት መባቻ

**ሠርቀ ወርኅ**:- የወር መባቻ



www.ethiopianorthodox.org

**ሠርቅ**:- መባቻ፣ የወር መጀመርያ ቀን

**ሠግር**:-መራመድ፣ስድስተኛዋ ጳጉሜን ሠግረ ዮሐንስ፣ዮሐንስ ተራምዶባት የምትውል፣በየአራት ዓመቱ የምትመጣ

**ሥነ ፈለክ**:- በአየር፣ በጠፈርና በዙርያው ያለ የፍጥረት ሁሉ ዓይነት፤

**ርደተ ማየ አይኅ**:- የጥፋት ውኃ፣ድምሳሴ በኖኅ ዘመን የወረደ፤

ሱባዔ:- ሰባት፣ሰባተኛ ልዩ ልዩ አገባብ ያለው፤

ሳቤላ:- ሕልምን የምትተረጉም ነቢይት፤የዓለምን 7000 ዓመታት በዘጠኝ ፀሐይ (ዘመን) የመደበች።

**ሳኒታ**:- ማግስት፤

**ስቍረት**:- መብሳት፣መበሳት ፣አበሳስ፤

**ሺሕ ዓመት**:- ዐሥር መቶ፤

**ቀመረ ዓረብ** :- 228 ዓመተ ፀሐይን የያዘ የቊጥር መደብ፤ይህም የጨረቃ ዓመተ ዓለም የሚታወቅበት ስሌት ነው።

**ቀመር**:- ቊጥር ፣ ሒሳብ ፣ የቊጥር መደብ ማለት ነው።

**ቀዳምያት**:- የመገናመርያ፤

በዓለ ሰዊት:- የእሸት በዓል፤

በዓለ ናዕት:- የአይሁድ የቂጣ በዓል፤

በኵራት:- ከሰውም ሆነ ከእንስሳ መገናመርያ የተወለደው፤





**በድር**:- የአይሁድ ጾም፣በሠራነው ባለፈው ኃጢአታችን ይቅር በለን ተብሎ የሚጾም

በአተ ጾም:- የጾመ መግቢያ፣ዐቢይ ጾም፣ሁዳዴ፤

**ተውሳክ** :ጭማሪ፣ተጨማሪ፣ማሟያ፣ማስተካከያ፤ለአጽዋማትና በዓላት ማውጫ የሚያገለግል ቁጥር፤

**ታሕታይ ቀመር**:- ተዘዋዋሪ የሆኑ አጽዋማትና በዓላት የማይሻገሩበት የታችኛው ቀመር መስመር፤

**ትራፋተ ዐውድ**:- ከጨረቃ ዑደት የተገኘ የጊዜ ትርፍራፊ፣ከሌሊት ብተት ጋር እየተደመረ የጨረቃ ወር መባቻን የሚያስገኝ፤
**ትስብእት**:- ሰው መሆን፣በተለይ የጌታችችን ዕለተ ጽንስ የሚያመለክት፤

**ኍልቈ ዜና መዋዕል**:- የዘመናት ታሪክ ቁጥር፤

**ኖኅት**:- ደጃፍ፤

**ናጌብ**:-ብርሃናት የሚመላለሱበት፣የሚወጡበትና የሚገቡበት፤

**ንዝሐተ ደም**:- ደምን መርጨት፤

**አምሳል**:- ምሳሌ፣ አምሳያ፤

**አምስት ቀን ተኩል**:- 5500 ዓመታት፤

**አሥርቆት**:- የእያንዳንዱን የሌሊትና የመዓልት መባቻ የሚታወቅበት ሥርዓት፤

**አበቅቴ**:- ተረፈ ዓመት ወይም ተረፈ ጨረቃ፤ሕጸጽና ሠርቀ መዓልት ሲደመርበት ሠርቀ ሌሊትን ያመለክታል።



www.ethiopianorthodox.org

**አቡሻህር:-** አቡሻህር የተባለ ዮሐንስ የጻፈው የቁጥር መጽሐፍ ነው:: መጽሐፉ በደራሲው ስም ተሰይሟል::ሙሉ ስሙ አቡሻህር ኢብን ቡትሩስ ራሒብ ሲሆን በእስክንድሪያ የኖረው በ13ኛው ምእት ዓመት ነው::

**አስተርእዮ:-** መታየት፣መገለጥ፤

**አንቀጸ ብፁአን:-** መምህራን አንብበው፣ተርጉመው የሚያስተምሩት ቃለ ወንጌል (ማቴ5፥1)፤

**አንቀጸ አባግዕ:-** መምህራን አንብበው፣ተርጉመው የሚያስተምሩት ቃለ ወንጌል (ማቴ18፥12)፤

**ኢየዐርግ:-** አጽዋማትና በዓላት የሚመላለሱበት የላይኛው የቀመር መስመር፤

**ኢይወርድ:-** አጽዋማትና በዓላት የሚመላለሱበት የታችኛው የቀመር መስመር፤

**እምርት ዕለት:-** የታወቀች ዕለት ያውም የወሩ መባቻ፤

**ኬክሮስ:-** ብርሃናት የሚመላለሱበት ከሰሜን እስከ ደቡብ የተዘረጋ የሐሳብ መስመር

**ክንትሮስ:-** ብርሃናት የሚመላለሱበት ከምስራቅ እስከ ምዕራብ የተዘረጋ የሐሳብ መስመር

**ወንበር:-** ገባር፣ተረፈ ንኡስ ቀመር፣ ዓመተ አበቅቴ ማለት ነው:: አበቅቴና መጥቅዕ ከወንበር ይገኛሉ::

**ዐውደ ዓመት:-** በፀሐይ 365 ቀን ከ15 ኬክሮስ ከ6 ካልዒት ነው:: በጨረቃ 354 ቀን 22 ኬክሮስ ካል 37 ሣልሲት 52 ራብዒት 48 ኃምሲት ነው:: በከዋክብት 364 ዕለት፤ በሐሳበ ነቢያት 360 ዕለት ወይም 42 ወር ነው:: (ራእ:11:2፣12:14፣ዳን:7:25)

**ዐረፍተ ሣህል:-** ዐሥራ አምስት ኬክሮስ የሚገኝበት የብርሃን ክፍል፤



www.ethiopianorthodox.org



**ዐጽፌ አውራኅ:-** የወሩ 30 ቀን በሱባኤ ሲቀመር የሚቀረው 2 ቀን በሌላው ወር ተደምሮ የሚቈጠር ስለሆነ ነው:: ዐጽፍ ማለት እጥፍ ድርብ ማለት ነው::

**ዓመተ ምሕረት:-** ዘመነ ሐዲስ አንድ ወገን ነው፤ ይህም ከጌታችን ልደት ዠምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለ በፀሐይና በጨረቃ ጥምር አቈጣጠር የሚቈጠር ዓመት ነው:: ያውም ከ5500 ቀመር የሚተርፈው 8 ዓመት ይደመርበታል:: ለምሳሌ በ2004 ዓመተ ሥጋዌ ላይ ሲደመርበት 2012 ዓመተ ምሕረትን ይሰጣል:: የትንሣኤ በዓል የሚውልበት ቀን የሚታወቀውም ከ2012 ዓመት በሚገኘው አበቅቴ ነው::

**ዓመተ ምሕረት:-** ዓመተ ዓለምም ዓመተ ምሕረት ይባላል:: *ወትባርክ አክሊለ ዓመተ ምሕረትከ* -በቸርነትህ ዓመትን ታቀዳጃለህ/ በቸርነትህ ዘመን የሚገኘውን እህሉን ታበዛዋለህ እንዲል፤(መዝ 64:11) ዓመተ ዓለም ስለምን ዓመተ ምሕረት ተባለ ቢባል ሰው በዚህ ዓለም ንስሐ ገብቶ ምግባር ትሩፋት ቢሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን ስለሚያገኝ ነው::

**ዓመተ ምሕረት:-** ዓመተ ዓለም ለዐውደ ቀመር 532 ዓመት ተካፍሎ የሚገኘው ቀሪ ወይም ትርፉ ዓመተ ቀመር፣ ዓመተ ምሕረት ይባላል:: ለምሳሌ 2005 ዓመተ ሥጋዌ በዓመተ ዓለም 7505 ሲሆን፣በዐውደ ቀመር ሲገደፍ 14 ዐውደ ቀመር ሞልቶ 57 ይተርፋል፤ይህ ትርፍ ዓመተ ምሕረት ይባላል::

**ዓመተ ሥጋዌ:-** ዘመነ መሲሕ አንድ ወገን ነው:: ይህም ጌታችን ሰው ከሆነበት ዠምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለ 2004 ዓመተ ፀሐይ ነው:: ከዚህ የመስከረም መባቻ የሚታወቅበት ተረፈ ፀሐይ (አበቅቴ ፀሐይ ፣ ሐሳበ ፀሐይ ፣ ጥንተዮን) ይገኛል::

**ዓመተ ሰማዕታት:-** ክርስቲያኖች በዘመነ ዲዮቅሊጥያኖስ 276 ዓ.ም. ከደረሰባቸው ፍጅት ተነሥቶ የሚቆጥር፤

**ዓመተ ዓለም:-** መዋዕለ ዓለም አንድ ወገን ነው:: ይህም ከፍጥረተ ዓለም እስከ ዛሬ ድረስ ያለ 7504 ዓመት ነው:: ያውም ከጌታ ልደት

በፊት 5500 ከጌታ ልደት በኋላ 2004 ዓመት ያለ የዘመን ድምር ነው:: (5500 + 2004) = 7504)::
***ዕለት ጠቢባን:-*** ጠቢባን መምህራን ተመራምረው ያገኙት ዕለት ማለት ነው:: እነርሱም እሑድና ሰኞ ናቸው::

***ዕለተ ምርያ:-*** 5ኛ ጳጉሜን፤

***ዕለተ ሠግር:-*** 6ኛ ጳጉሜን፤***ዕለተ ዮሐንስ:-*** የመስከረም ወር መባቻ ወይም የዘመን መለወጫ ዕለት (መስከረም 1 ቀን)፤

**የቍጥር ቤት:-** ከኬክሮስ እስከ ሳድሲት የተዘረዘሩት ስድስቱ የቁጥር ስልቶች ናቸው::

**የጨረቃ ጥንተዮን:-** የጨረቃ ዐውደ ዓመት መባቻ የሚታወቅበት ስሌት ነው:: ያውም ተረፈ ጨረቃ ወይም አበቅቴ ወርኀ ይባላል::

**ድሜጥሮስ:-** የዓመተ ዓለም ቁጥር ስሌት አዕማድ የሆኑትን አበቅቴንና መጥቅዕን ተመራምሮ ያገኘ በሥስተኛው ምእት ዓመት የኖረ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት፤

**ግደፍ:-** ለአንድ ዐውድ ተካፍሎ ከሚገኘው ውጤት የሚተርፈው ቁጥር፤

**ጥንተ ዕለት:-** ከእሑድ የሚነሣ፣ ሐሳበ ሰማይ ወምድር፣ዕለተ ዮሐንስ ተብሎም ይታወቃል፤የሦስቱም ትርጓሜያቸው አንድ ነው፤ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ሲዞር ሲመላለስ ይኖራል::

**ጥንተ ቀመር:-** ቀመር የተገፐመረበት ማክሰኞ ነው:: ከማክሰኞ እስከ ሰኞ ሲዞር ሲመላለስ ይኖራል::

**ጥንተዮን:-** ብርሃናት ከተፈጠሩበት ረቡዕ ተነሥቶ የሚቆጥር፤ አበቅቴ ፀሐይ፣ ሐሳበ ፀሐይም ይባላል፤ የሦስቱም ትርጓሜያቸው አንድ ነው:: ያውም ተረፈ ፀሐይ
ማለት ሲሆን የመስከረም መባቻ የሚውልበትን ዕለት ያመለክታል:: ከረቡዕ እስከ ማክሰኞ ሲዞር ሲመላለስ ይኖራል::





**ፈለክ:-** ጠፈር፣አየር፣ ማዕርግ ማለት ነው:: ያውም ፀሐይና ጨረቃ፣ ከዋክብትም የሚታዩበት የኅዋው ክፍል ነው::

www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ታሪካዊና ባህላዊ ለሆነ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሐሳበ ዘመንና የኑልቄ ዜና መዋዕል ትምህርት መሠረትና ምንጭ ነው። መጽሐፉ አራት ዐበይት ክፍሎች አጠቃልሎ የያዘ ነው።

1. መርሐ ዕውር እና ምሥጢረ አቅማር፣
2. አቡሻህር 3. ሥነ ፈለክ 4. ሐሳበ ነፋሳት

የሁሉም ሥርዓተ ትምህርት በአኀዝና በቀመር ስለተወሰነና የትምህርታቸው ምሥጢርም እንደ ባሕር ዕሙቅና ጥልቅ ስለሆነ መምህራን የሁለቱን ክፍል የአንድነት ስም ባሕረ ሐሳብ ብለውታል። የባሕረ ሐሳቡ ትምህርትም በስምንት ምዕራፍ ተከፍሎ በዚህ መጽሐፍ ተጽፏል። ያውም እንዲህ ነው፡-

አንደኛው ምዕራፍ የባሕረ ሐሳብን ምንነትና ክፍሎቹ፣ የአብነት መምህራን አጽዋማትና በዓላት በየዓመቱ የሚውሉበትን ቀን ለማስረዳት የባሕረ ሐሳብን አዋጅ ሲያውጁ፣ በሥነ ፍጥረት ዠምረው በሰባቱ ዕለታት የተፈጠሩትን ፍጥረታት የአዳምና የሔዋንን ተፈጥሮ፣ የድሜጥሮስን ታሪክና የአጽዋማትና በዓላት ሥርዓት በዝርዝር ያስረዳል።

ሁለተኛው ምዕራፍ መርሐ ዕወር ነው። አራተኛው ምዕራፍ ዓመተ ዓለምን በአዕዋዳት እየቀመረ አበቅቴና መጥቅዕን፣ ጥንተዮንና ዕለተ ዮሐንስን ያስገኛል። በጥንተዮን፣ በአበቅቴና በመጥቅዕም አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን ቀን፣ ኢየአርጋቸውና ኢይወርዳቸውን ተውሳካቸውንም ይገልጻል። የብሉይና የሐዲስ ኪዳን በዓላት በማነጻጸርም የአምሳል መርገፋቸውን ምሥጢር ያትታል። የአሥርቆትንም ሥርዓት ቅደም ተከተል እየዘረዘረ በሚገባ ይጽፋል። የሐሳበ ሳቢላ፣ የሐሳበ ቢዘንና የሐሳበ ጉንዳጉንዲ፣ የዓመተ ሰማዕታትንም ልዩነት ያስረዳል።

ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በዘመናት እየተመላለሱ የሐሳበ ዘመን ሥርዓተ ቀመርና ታሪክ የሚፈጸሙና አርእስትን እየዘረዘረ ያስረዳል። እንዲሁም የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ጥንተ በዓላትና አጽዋማት ማክሰኞ ጥንተ ቀመር የሆነችበትን ምክንያት፣ የሰባተኛው ሺሕ ዓመት አበቅቴ ፀሐይ አወጣጥ ስሌት፣ የሰባቱ ዕለታት ጥንታዊነት ምሥጢር ይገልጻል።

ሦስተኛው ምዕራፍ መጽሔተ ሕርግራግ ነው። በአንድ ዐቢይ ቀመር፣ በ19 ዐውደ ፀሐይ፣ በ28 ዐውደ አበቅቴ፣ በ7 ዐውደ ማኅተም፣ በ4 ክፍለ ሰንበታት፣ በ4 ላዕላይ ቀመር፣ በ4 ታሕታይ ቀመር ተመድቦ የተዘጋጀ የምስጢረ አቅማር ሠንጠረዥ በዝርዝር የተጻፈበት ነው። ሠንጠረዡም በሁለት ተከፍሏል።

1. በ19 ንኡስ ቀመር ብቻ የሚመላለሱ አጽዋማትና በዓላት ሠንጠረዥ ለብቻው በመገመርያ አንድ ገጽ፤
2. በ532 ዐቢይ ቀመር የሚመላለሱ አጽዋማትና በዓላት ሠንጠረዥ ከገጽ 99 እስከ 127 ገጽ ድረስ በዚህ ምዕራፍ በዝርዝር ተጽፏል።

አራተኛው ምዕራፍ እምርት ዕለት ይሰኛል። ቀመረ አዳምና ዓመተ ሕይወቱ፣ ዓመተ አዳምና ዓመተ ኖኅ፤ ከሰባት ሺሕ ዓመታት መካከልም የእያንዳንዱን ሺሕ ዓመት መነሻና መድረሻ ዕለት፣ ስምንተኛው ሺሕ የተገመረበትና የሚፈጸምበት ዓመት፣ ከቀዳማዊ አዳም እስከ ዳግማዊ አዳም ያለ ኑልቄ ዜና መዋዕል በዓመታት፣ በዐቢይ ቀመርና በዓመተ ምሕረት ተለይቶ የታወቀበት ስሌትን ያመለክታል። ዳግመኛም ዐበይት ሱባዕያትና ንኡሳን ሱባዕያትን፣ የእመቤታችንና የጌታችን ሐረገ ትውልድን፣ በበዓለ ትስብእትንና በዓለ ትንሣኤ መካከል ያሉ የጌታችን በዓላት የሚውሉበትን ቀን በአበቅቴ ፀሐይና በዕለተ ምርያ፣ በዕለተ ሠግርም እየቀመረ ለይቶ ያሳውቃል።

አምስተኛው ምዕራፍ ሐሳበ አቡሻህር ነው። ዓመተ ዓለምን በፀሐይና በጨረቃ መንገድ እየቀመረ ያስረዳል። 7 የቊጥር ቤቶችን፣ የጨረቃ የዕለት መንገድና ሕጸጽን፣ የጨረቃ የ15 ቀን መንገድና ሕጸጽን፣ የጨረቃ የወር መንገድና ሕጸጽን፤ የጨረቃ የዓመት መንገድና ሕጸጽን፣ ቀመረ ትራፋተ ዐውድን፣ ቀመረ


www.ethiopianorthodox.org

ዐረብን፣ የጨረቃ ጥንተዮንን፣ እነዚህን ሁሉ እንደየአቈጣጠራቸው ሥርዓት እየቀመረ በዝርዝር ይገልጻል፡፡በአራተኛው ቀን፣ረቡዕ ለተፈጠሩት ብርሃናት መነሻ የሆነው ብርሃን ለታላላቅ ብርሃናት ሲሰጥ የሚለካባቸው ሰባቱን መስፈርታት የፀሐይና የጨረቃ ምዕዛራት (ስቍረታት) መከፈትና መዘጋትን ይዘረዝራል፡፡

ስድስተኛው ምዕራፍ ሐሳበ ፈለክ ነው፡፡ ሚጠተ ብርሃናትን ይመለከታል፡፡ ፀሐይ ከደቡብ ዳርቻ እስከ ሰሜን ጫፍ ባሉት 6 ደጃፎች ከጥር እስከ ሰኔ ወር፤ ዳግመኛም ከሰሜን ጫፍ እስከ ደቡብ ዳርቻ ባሉት 6 ደጃፎች ከሐምሌ እስከ ታኅሣሥ ወር እየተመላለሰ ዓለምን የሚመግብ መሆኑ ይገልጻል፡፡ ምግብናውም ብርሃን ነው፡፡ጨረቃም ከብርሃነ ፀሐይ በምታገኘው ሰባተኛ ክፍለ ብርሃን፣ ብርሃንዋ በተገሠመረበት ገጸ ሰማይ ሕጸጽዋን እንደምትገሥምር፣ ብርሃንዋ በተፈጸመበት ገጸ ሰማይም ብርሃንዋን እንደምትፈጽም ገልጾ፣ በዚሁ መሠረት በየቀኑ በብርሃንዋ ላይ ብርሃንን እንደምትጨምርና በ15ኛው ቀንም ሌሊቱን ሁሉ ስታበራ እንደምታድር ያስረዳል፡፡ በተጨማሪም መገብተ አዝማን የሚባሉ አራት ዐበይት ከዋክብት፣12 መገብተ አውራኅና 28 መገብተ ዕለታት፣ ከዋክብት ከፀሐይና ከጨረቃ ጋር ተመድበው በብርሃናቸው ዓለምን እንደሚመግቡ ይገልጻል፡፡

ሰባተኛው ምዕራፍ ሐሳበ ነፋሳትን ይመለከታል፡፡ በአራቱ የሰማይ ማዕዘን 12ቱ ነፋሳት የሚነፍሱባቸው 12 ደጃፎች መኖራቸውን ገልጾ፣ ከእነሱ አራቱ ነፋሳተ ምሕረት፣ 8ቱ ነፋሳተ መዓት መሆናቸውን ያስረዳል፡፡

ስምንተኛው ምዕራፍ የእጅ ወይም የግድግዳ ሰዓት ባልነበረበት ዘመን ዐሥራ ሁለቱ ሰዓተ መዓልት በየወሩ እንዴት እንደሚመላለሱ፣ ቈጣሪው ቀጥ ብሎ ቁሞ የራሱን ጥላ በጫማ እየሰፈረ የጊዜውን ሰዓት መጠን ለይቶ ያስረዳ እንደ ነበር በዝርዝር ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የመዓልትና የሌሊት ስፍረ ሰዓት የመበላለጥ ደረጃን አስረድቶ ሁለቱም መዓልትና ሌሊት እኩል የሚሆኑባቸው ወሮች መስከረምና መጋቢት እንደሆኑ ያመለክታል፡





# ምዕራፍ አንድ

## ባሕረ ሐሳብ

ባሕረ ሐሳብ ማለት ቍጥር ያለው ዘመን ማለት ነው፡፡ ሐሳበ ባሕር ቢል ግን የዘመን ቍጥር ማለት ነው፡፡ ባሕርን ዘመን ብሎ የተረጐመው ሱቱኤል ዕዝራ ነው፡፡ ንባቡም እንዲህ ነው፡- *እስመ በመዳልው ተደልወ ዓለም ወበመሰፈርት ሰፈሮ ለባሕር ወኢያረምምሂ ወኢይነቅህ እስከ ይትፌጸም መስፈርት ዘተውህበ ሎቱ፤* ማለት፣ ይህ ዓለም በሚዛን ተመዝኗልና፣ ባሕርንም በሳዳን ሰፍሮታልና፡፡ የተሰጠው ዘመኑ እስኪፈጸም ድረስ ዝም ይላል፣ አያልፍም ብሏል፡፡ የኢትዮጵያ መተርጉማንም *ወበመስፈርት ሰፈሮ ለባሕር* የሚለውን ንባብ ዘመኑን በስምንት ሺሕ ወስኖታልና ብለው ተርጉመውታል፡፡ (ሱቱኤል ዕዝራ 2፡37)፡፡

ሐሳብንም ቍጥር ብሎ የተረጐመው ነቢዩ ዳዊት ነው፡፡ ንባቡም እንዲህ ነው፡- *ብፁዓን እለ ተኀድገ ሎሙ ኀጢአቶሙ ወእለ ኢሐሰበ ሎሙ ኵነኔ ጌጋዮሙ፤* ማለት ኃጢአታቸው በንስሐ የተሰረየላቸው በደላቸውም በንስሐ ያልተቈጠረባቸው ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው (መዝ. 31፥1) ብሏል፡፡

ዳግመኛም ባሕረ ሐሳብ ማለት ቀድሞ የነበረ፣ አሁንም ያለ፣ ለወደፊቱም የሚኖር ዘለዓለማዊ እግዚአብሔር በዚች ባለንባት ዓለም ሳድሲትን በኃምሲት፣ ኃምሲትን በራብዒት፣ ራብዒትን በሣልሲት፣ ሣልሲትን በካልዒት፣ ካልዒትን በኬክሮስ፣ ኬክሮስን በሰዓት፣ ሰዓትን በዕለት፣ ዕለትን በሳምንት፣ ሳምንትን በወር፣ ወርን ደግሞ በዓመት አጠቃልሎ ሌሊትንና መዓልትን እያፈራረቀ የሚመግበን እግዚአብሔር መሆኑን በቍጥር በስፍር የሚያስረዳ መጽሐፍ ማለት ነው፡፡

የባሕረ ሐሳብ ትምህርት መርሐ ዕዉር፣ ሐሳበ አቡሻህርና ሐሳበ ፈለክ ተብሎ በሦስት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

መርሐ ዕዉር ማለት አላዋቂዎችን መርቶ ወደ ዕውቀት ደረጃ የሚያደርስ መጽሐፍ ማለት ነው፡፡ በውስጡም የአጽዋማትንና የበዓላትን አወጣጥ መንገድ፣ የኢየዓርጋቸውንና የኢይወርዳቸውን

www.ethiopianorthodox.org

ሥርዓት የአቅማራትንና የሰንበታትን የሱባዕያትንም ሥርዓት አጠቃልሎ የያዘ ነው:: በተጨማሪም ስለአበቅቴ ወርኀና መጥቅዕ፣ ስለአበቅቴ ፀሐይና ሐሳበ ሰማይ ወምድር ወይም ዕለተ ዮሐንስ አቈጣጠር ሥርዓት በዝርዝር የሚያስረዳ መጽሐፍ ነው::

ዜና አርእስተ ሐሳብ ማለት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ቀድሞ የሆነውንና በኋላም የሚሆነውን የሐሳበ ዘመን ሥርዓት ታሪክ የሚናገር ነው:: በዘመናት እየተመላለሱ ይህን ሥርዓት የፈጸሙና የሚፈጽሙ አርእስትም አሉት:: የአቅማራትና የዓመታት ተግባር፣ ነቢያት እንደ ከፈሉት መጠንም የሰንበታትና የሱባዕያቸው ሥርዓት ይዘረዝርበታል::

የአቡሻህርን መጽሐፍ የጻፈም አቡሻህር የተባለ ሊቅ ስለሆነ መጽሐፉ በስሙ ተሰይሟል:: በውስጡም የፀሐይን፣ የጨረቃንና የከዋክብትን፣ የሥነ ፈለክንም ነገር በጠቅላላው ይናገራል:: በተጨማሪም ቀመረ ትራፋተ ዐውድን፣ ቀመረ ዐረብን፣ በጨረቃ ዓመት ፍጻሜ የጨረቃ ጥንተዮን የሚታወቁባቸው ሰባት የቍጥር ቤቶችን አጠቃልሎ የያዘ ነው::

ሐሳበ ፈለክ የብርሃናቱን ፀሐይ፣ጨረቃ፣ከዋክብት መመላለስ (ሚጠተ ብርሃናትን) እንዲሁም ሐሳበ ነፋሳትን ይመለከታል::

ስለዚህ ከዚህ በላይ በሦስት አርእስት የተከፈለው የባሕረ ሐሳብ ትምህርት እንደ ባሕር አዝዋሪት ውስጡ ጥልቅ፣ ምሥጢሩ ረቂቅ ስለሆነ የሐሳበ ዘመን መተርጉማን ሦስቱን አርእስት አንድ መጽሐፍ አድርገው የመጽሐፉ ስም ባሕረ ሐሳብ ብለው ሰይመውታል::

## የባሕረ ሐሳብ አዋጅ

ይህ አዋጅ ከጥንት ጀምሮ የአብነት መምህራን የባሕረ ሐሳብን አዋጅ በመስከረም 1 ቀን ዕለተ ዮሐንስ ሲያሰሙበት የነበረ ስለሆነ አብነት እንዲሆን ገጸ ንባቡ ሳይለወጥ እንደ ነበረው ተጽፏል:: ያውም እንዲህ ነው:-



www.ethiopianorthodox.org



እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት እንደ ዛሬ ሁሉ አንድነቱ ሦስትነቱን ሳይጠቀልለው ሦስትነቱ አንድነቱን ሳይከፍለው በአንድነት በሦስትነት ሲሠለስ ሲቀደስ ይኖር ነበር:: *እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም ሀሎ እግዚአብሔር በትሥልስቱ እግዚአብሔር በመለኮቱ እግዚአብሔር በመንግሥቱ፤* ማለት እግዚአብሔር ከዓለም በፊት እስከ ዘለዓለምም ድረስ በሦስትነቱ አለ:: እግዚአብሔር በመለኮቱ፣ እግዚአብሔር በመንግሥቱ አለ ይላል (ዲዮስቆሮስ ቅዳሴ):: *ይሤለሱ በአካላት ወይትወሐዱ በመለኮት እንዘ አሐዱ ሠለስቱ ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ፤*ማለት እግዚአብሔር በአካላት ሦስት በመለኮት አንድ ነው:: አንድ ሲኾን ሦስት፣ ሦስት ሲሆን አንድ ነውና ይላል (ባስልዮስ)::

ዓለም ሳይፈጠር እግዚአብሔርን ማን ያመሰግነው ነበር ቢሉ ባሕርዩ ምስጉን ነው:: አንድም በኀሊና ሥላሴ ያሉ መላእክት ደቂቀ አዳም ያመሰግኑት ነበር ብለው ይመልሳሉ:: *እምቅድመ ይፍጥር መላእክተ ለቅዳሴ ኢተፀርዐ ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤* ማለት መላእክትን ለምስጋና ከመፍጠሩ በፊት የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ምስጋና አልተቋረጠም ነበር ይላል (ጎርጎርዮስ ሊቁ):: ነቢዩ ዳዊትም *እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም፤* ማለት እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ንጉሥ ነበር ብሏል (መዝ. 73.12)::

## የእሑድ ፍጥረታት

ለእግዚአብሔር ጥንት አስገኝ የለውም:: በዚህ ጌትነት ሳለ ዓለምን ልፍጠር ብሎ አሰበ:: አስቦም አልቀረ:: ቅዳሜ ማታ ለእሑድ አጥቢያ ሰማይንና ምድርን፣ እሳትንና ነፋስን፣ ውሀንና ጨለማን መላእክትንና ብርሃንን ፈጠረ:: *በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ፤* እንዳለ ሙሴ በኦሪት፤ በኩፋሌ *ወገብረ አርባዕተ ዘመደ፤* ማለት አራት ፍጥረታትን ፈጠረ ይላልሳ ቢሉ፣ ሰማይ ለሰማያውያን፣ ምድር ለምድራውያን ቦታቸው ስለኾነ እንዲህ አለ እንጂ የፈጠራቸውስ ስምንት ናቸው ይላሉ::

## የሰኞ ፍጥረታት

በሰኞ ዕለት የተፈጠሩ ፍጥረታት የሚከተሉት ናቸው:: ከዚህ ዠምሮ እስከ ብሩህ ሰማይ ውሀ መልቶ ተፈጥሯል:: እሑድ ማታ ለሰኞ አጥቢያ:- *ለይትጋባዕ ማይ ውስተ ምዕላዲሁ ወያስተርኢ የብስ*፤ ውሀው ባንድ ቦታ ይሰብሰብ፣ ደረቁም ይገለጥ ብሎ ውሀውን ሰበሰበ:: ያን ከአራት ከፍሎ በየቦታው አዘጋጀው:: አንዱ ይህ የምናየው ሰማይ ነው:: ኹለተኛውን ከጠፈር በላይ ወስኖታል:: ሐኖስ ይባላል:: ይኸውም ኃያል ተሐዋኪ ማለት ነው:: *ወማይ ዘመልዕልተ ሰማይ ተናዕታይ ውእቱ*፤ ከጠፈር በላይ ያለው ውሀ ተባዕት ነው እንዳለ ሔኖክ (13.32):: *ማይኒ ዘመልዕልተ ሰማያት*፤ከሰማያት በላይ ያለ ውሀም፤እንዳለ ዳዊት (መዝ.148):: ሦስተኛውን በአድማስና በናጌብ መካከል ዙርያውን አጐድጉዶ ወስኖታል (አስፍሮታል):: ይኸውም ውቅያኖስ ይባላል:: ጠፈርን ከእብነ አድማስ ጋር አያይዞታል:: *ወአስተጣበቅዋ ዲበ እብነ ኰኵሕ* እንዳለ ኢዮብ፤ በጠፈር በዙርያዋ 12 እልፍ (120000) ደጃፎችን አወጣ:: ከቅዱስ ሚካኤል ሰራዊትም፣ 24 እልፍ (240000) መላእክትን አምጥቶ በያንዳንዱ ደጃፍ ሁለት ሁለት ጠባቂዎችን ሾመ:: *ወሤመ ክልኤተ ክልኤተ ርኡሳነ ለለ አሐዱ አንቀጽ* እንዲል፤ ጠባቂዎቹም ከሥላሴ ማኅተም ያለበት ደብዳቤ ያልያዘውን አያስወጡም አያስወርዱም::

በምድር በዙርያዋ ሁለት ተራራዎችን አስገኘ:: የወድያኛውን አድማስ አለው:: ከዚያም 12 መስኮት በምሥራቅ፣ 12 መስኮት በምዕራብ አወጣለት:: ነፋሳት የሚወጡበት ነው:: የወዲህኛውን ናጌብ አለው:: ዐረፍተ ሣህል ማለት ነው:: ለዚህም 6 መስኮት በምሥራቅ 6 መስኮት በምዕራብ አወጣለት:: ይኸም ብርሃናት የሚመላለሱበት ነው:: አራተኛውን እጅ ውሀ ከምድር በታች አጽንቶታል:: *ዘአጽንዓ ለምድር ዲበ ማይ* እንዳለ ክቡር ዳዊት (መዝ. 23.2):: ነገር ግን ከምድር ጋር ተራርቃለች:: *ወሰቀላ ለምድር ዲበ ወኢምንት ዕራቃ* እንዳለ ኢዮብ (26.7):: ይህም ምድሪቱን በታችዋ አንዳች አልባ አንጠለጠላት ማለት ነው::





## የማክሰኞ ፍጥረታት

ምድር ሁለንተናዋ ጭቃ ነበርና ሰኞ ማታ ለማክሰኞ አጥብያ ከእግረ አድማስ ነፋሳትን አውጥቶ ሲያስማማት አደረ:: እንደ ሠኔ እርሻ ስትኾን *ለታብቍል ምድር ዘርዐ፣ ወሐመልማለ፣ ዘይዘራዕ በበዘርዑ፣ወበበጽጌሁ፣ወበበፍሬሁ*፤ ምድር በየዘሩና በየአበባው፣ በየፍሬውም የሚያፈራ ዘርንና ልምላሜን ታውጣ ብሎ ባዘዘ ጊዜ በመጥረቢያ የሚቈረጡ ዕፀዋት፣በማጭድ የሚታጨዱ አዝርእት፣ በጥፍር የሚለቀሙ አትክልት ሦስት ፍጥረታት ተገኝተዋል:: *ወበሠሉስ ዕለት ገብረ እግዚአብሔር ዕፀወ ዐቢየ ወንእሳነ እግዚአብሔር*፤ በሦስተኛው ቀን ታላላቆችንና ታናናሾችን ዛፎች ፈጠረ:: እንዳለ ኤጴፋንዮስ አክሲማሮስ:: የዕፀ ሕይወትም ተፈጥሮ በዚሁ ቀን ነው:: ከዚህም ከዕፀ ሕይወት ሥር አራት አፍላጋት(ወንዞች) ይወጣሉ:: እነሱም ኤፌሶን፣ ግዮን፣ ጤግሮስ፣ ኤፍራጥስ ናቸው::

## የረቡዕ ፍጥረታት

ማክሰኞ ማታ ለረቡዕ አጥቢያ *ሊይኩኑ ብርሃናት በጠፈረ ሰማይ*፤ ማለት ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ላይ ይሁኑ ባለ ጊዜ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት ተገኝተዋል:: ጨረቃን ሲፈጥራት ስሌዳዋን ከነፋስና ከውሀ የወደደውን ያህል ነሥቶ ብርሃን ሥሎባታል:: ቅርዕዋም በሰው አምሳል አድርጎታል:: *በዕሥራ ሠርቀ ሌሊት ታስተርኢ ወርኅ በአርአያ ብእሲ ሌሊተ ወመዓልተ በሰማይ*፤ ማለት *በሃያኛው ሠርቀ ሌሊት ጨረቃ በሌሊትና በመዓልት በሰው አምሳል በሰማይ ትታያለች*፤ እንዳለ ሔኖክ:: የፀሐይንም ስሌዳ ከእሳትና ከነፋስ የወደደውን ያህል ነሥቶ ብርሃን ሥሎበታል:: ቅርፁም እንደ ጨረቃ ነው:: የሁለቱም መጠናቸው እኩል ነው:: የከዋክብት የሠሌዳቸው መጠን ግን ይነስም ይብዛም አልተጻፈም:: በብርሃን እንዲበላለጡ ግን *ኮከብ እምኮከብ ይኄይስ ክብሩ*፤ ኮከብ ከኮከብ በክብር ይበልጣል ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሯል:: *ወነሥአ ብርሃነ እምዚአሁ ብርሃን መጠነ ኀጠተ ሥርናይ* እንዲል (ቅዳሴ ግሩም):: ብርሃን ይሁን ብሎ ከፈጠረው ከደገኛው ብርሃን የስንዴን ቅንጣት ያህል ብርሃንን አመጣ:: ይህ ብርሃን ለታላላቅ ብርሃናት ሲሰጥ የሚለካባቸው ሰባት መስፈርታት አሉ:: (ስለነዚህ መስፈርታት ዝርዝር በምዕራፍ አምስት ተመልከት)

www.ethiopianorthodox.org

## የኀሙስ ፍጥረታት .

ረቡዕ ማግሥ ለኀሙስ አጥቢያ ለታውፅእ ባሕር ዘመደ ዓሣት ወኵሎ ዘይትሐወስ ዘቦ መንፈሰ ሕይወት፤ ባሕር የዓሣትን ወገንና የሕይወት መንፈስ ያለው የሚንቀሳቀሰውም ሁሉ ታውጣ ብሎ እግዚአብሔር በተናገረ ጊዜ በልባቸው የሚሳቡ፣ በእግራቸው የሚሽከረከሩ፣ በክንፋቸው የሚበሩ ሦስት ፍጥረታት ተገኝተዋል። ከነዚሁም የሚበሉ የማይበሉም አሉ። ኢትብላዕ ኵሎ ዘአልቦ ክንፈ ወቅሣረ ዘውስተ ማይ፤ በውሀ ውስጥ ካለው ክንፍና ቅርፊት የሌለውን ሁሉ አትብላ ብሎ ሙሴ እንደተናገረ (ዘሌ.11፥10-12)። ከርከዴን የምትባል ወፍ በገነት ኃሮ ትኖራለች። ከባሕር ስትገባ ባሕሩ ከሁለት ይከፈላል። በፀሐይ ፀዳል ዕንቍን ትፀንሳለች። የሌዋታንም ተፈጥሮ በዚህ ቀን ነው።

## የዓርብ ፍጥረታት

ኀሙስ ማግሥ ለዓርብ አጥቢያ ለታውፅእ የብስ ዘመደ እንስሳት፤ ምድር የእንስሳትን ወገን ሁሉ ታውጣ ብሎ እግዚአብሔር በተናገረ ጊዜ በልባቸው የሚሳቡ፣ በእግራቸው የሚሽከረከሩ፣በክንፋቸው የሚበሩ ሦስት ፍጥረታት ተገኝተዋል። ከነዚሁም የሚበሉ የማይበሉም አሉ። ብልዑ ኵሎ እንስሳ ዘንፋቅ ሰኰናሁ ወስጡቅ ጽፍሩ፤ ሰኰናው የተከፈለ፣ ጥፍሩ የተሰነጠቀ፣ የሚያመስኳም እንስሳ ሁሉ ብሉ ብሎ ሙሴ እንደተናገረ (ዘሌ.11፥1-3)። የብሔሞትም ተፈጥሮ በዚሁ ቀን ነው። እስከዚህ ድረስ 21 ፍጥረት ነው። እነዚህንስ ለምን ፈጠራቸው ቢሉ፤ ለሰው መማርያ ማወቅያ መመርመርያ ሊሆኑ ፈጥሯቸዋል። ወኵሉ ዘተፈጥረ ለመፍቅደ ነባብያን ቦ እምኔሆሙ ለምህሮ ወቦ እምኔሆሙ ለተዘክሮ፤ ከተፈጠረውም መካከል ለትምህርት ለተዘክሮ የሚኾኑ አሉ ብሎ አረጋዊ መንፈሳዊ እንደተናገረ፤ ወለእመ ፈቀድከ ታእምር ዘንተ እምአፍአ ብከ መምህር ወሰማዕት ካልዕ ዘይመርሐከ ኀበ አንክሮተ እግዚአብሔር፤ ይህን ታውቅ ዘንድ ብትሻ እግዚአብሔርን ወደ ማድነቅ የሚመራሕ መምህር ሌላም ምስክር ከውጭ አለልህ ብሎ ማር ይስሐቅ እንደ ተናገረ። ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትዐወቅ በፍጥረቱ ለፍጥረቱ፤ ከፍጥረተ ዓለም ዠምሮ የማይታይ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ለፍጥረቱ ይታወቃል ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረ (ሮሜ 1፥20)። በሐዋርያት





ሥራም፣ አንዘ ኢየኀድግ ርእሶ ዘ እንበለ ሰማዕት፤ ራሱን ያለምስክር አልተወም ተብሎ ተጽፏል (ሐዋ. 14፥15-17)።

## የአዳምና የሔዋን ተፈጥሮ

እግዚአብሔር በዕለተ ዓርብ በነግህ ከማእከለ ምድር መሬትን ነሥቶ አዳምን ፈጠረ (ዘፍ. 2፥7፣19)። ሔዋንንም በሳምንቱ ፈጥሯታል (ኵፋሌ 4፥7፣8)። እርሱን በ40 ቀን፣ እርስዋን በ80 ቀን በመንፈስ ቅዱስ አክብሮ ሰባቱ ሀብታትን አሳድሮ ብርሃን አልብሶ፣ ብርሃን አጐናጽፎ ገነት አግብቷቸዋል። ሰባት ሀብታት የተባሉም ኃይል፣ ኩነኔ፣ መንግሥት፣ ንጽሕና፣ ክህነት፣ ትንቢትና አሚን ናቸው። በዕለተ ቀዳሚት ግን አልፈጠረም። ይህ የተፈጠረው ፍጥረት እያንዳንዱ ቢቈጠር ፍጡር ተናግሮ ባልፈጸመውም ነበር። እየወገን እየወገኑ ብዙውን አንድ ብዙውን አንድ እያሉ ቢቈጥሩ ግን ከእሑድ እስከ ዓርብ ድረስ የተፈጠረው ፍጥረት 22 ነው። ወኮነ ኵሉ እስራ ወክልኤተ ዘመደ፤ እንዳለ ኩፋሌ (ኩፋ.3፥2)።

ከዚህ በኋላ አዳም ሰባት ዓመት ሲሆነው ምክረ ከይሲ ሰምቶ፣ አምላክነትን ሽቶ፣ ዕፀ በለስን በልቶ ከገነት ወጣ። በፈታሒነቱ አንጻር መሐሪነቱን ተመራምሮ ንስሐ ገባ። ጌታም ንስሐውን ተቀብሎ በኀሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ፣ ወእድኅከ ውስተ መርህብከ ወእትቤዘወከ በመስቀልየ ወበምትየ፤ በአምስት ቀን ተኩል ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በግቢህ እድሐለሁ፣ በመስቀሌና በሞቴም እቤዥሃለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ሰጠው። በዚህ ምክንያት ቍጥር ተዠመረ።

ልጆቹ ነቢያት ይህን ይዘው እኩሉ በፀሐይ፣ እኩሉ በጨረቃ፣ እኩሉ በከዋክብት ዘመናትን መቍጠር ዠመሩ። ከዚህ በኋላ ትንቢት ሲነገር፣ ሱባዔ ሲቍጠር ኖሯል። ቀን ሲደርስ አንባ ይፈርስ እንዲሉ 5 ሺሕ 500 ዘመን ሲፈጸም በዘመነ ዮሐንስ እሑድ መጋቢት 29 ቀን ሰው ኾነ። በዘመነ ማቴዎስ ማክሰኞ ታኅሣሥ 29 ቀን በዐሥረኛው ሰዓተ ሌሊት ተወለደ። ተወልዶም ሕግ ጠባይዓዊን፣ ሕግ መጽሐፋዊን ሲፈጽም አደገ። ሕግ ጠባይዓዊ እንደምን ነው ቢሉ፣ ተወልጄ ዕለቱን ልደግ ሳይል በየጊዜው በየጥቂቱ ማደግ ነው። ወልሕቀ ልሕቀ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ ወለይእቲ እሙ እንዲል (ድጓ፣ ሉቃ 2፥40)። ሕግ መጽሐፋዊስ እንደምን ነው ቢሉ ሕገ ኦሪትን መፈጸም፣ በ8 ቀን ቤተ ግዝረት፣ ባርባ ቀን ዕጕለ ርግብ



www.ethiopianorthodox.org

(የርግብ ጫጩት)፣ ፡ዘውገ ማዕነቅ (ቡላል/ዋኔ) ይዞ ቤተ እግዚአብሔር መግባት፣ በዓመት ሦስት ጊዜ ለገቢረ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም መውጣት ነው:: *ለያስተርኢ ተባዕትከ ሠለስተ ጊዜያተ ለለዓመት* (ዘፀ. 23፥14-17፣ ዘዳ. 16፥16):: *ዘሰ ኢዐርገ ለበዓል ርጉም ውእቱ* እንዲል፤በሌሎቹ ሌዋውያን ከሃያ ዓመት በፊት እንዳይወጡ ሥርዓት ተሠርቶላቸዋል:: ጌታ ግን በ12 ዓመት መውጣቱ ለማስተማር ነው እንጂ ለሌላ አይደለም:: እንዲህ እያለ ሠላሳ ዘመን ሲሆነው በእደ ዮሐንስ፣ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቆ የባሕርይ ልጅነቱን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አስመስክሮ ገዳም ኼዶ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ጾመ:: መዋዕለ ጾሙ ሲፈጸም ሰይጣን በሦስት ነገር ተፈታተነው:: በምንና በምን ቢሉ በትዕቢት፣ በስስእት እና በአፍቅሮ ንዋይ:: በትዕቢት ቢመጣበት በትሕትና፣ በስስእት ቢመጣበት በትሕርምት፣ በአፍቅሮ ንዋይ ቢመጣበት በጸሊአ ንዋይ ድል ነሥቶታል:: የሰይጣን ሦስት ዐበይት ጦሮቹ እሊህ ናቸው:: ሰውም እነዚህን ድል ከነሣ ሌላው ኃጢአት አይቆምለትም::

ከዚህ በኋላ ምድረ እስራኤል ገብቶ ትምህርት ተአምራት ዠመረ፤ አደረገ:: የእጁን ተአምራት አይተው የቃሉን ትምህርት ሰምተው ከብዙ መንደር ከዐሥር አህጉር ተወጣጥተው አምስት ገበያ ያህል ሰዎች ተከተሉት:: ከሲሁም መቶ ሃያ ቤተ ሰዎችን መረጠ:: *ወረሰየ ሐዋርያተ እምሰብእ ዘአሁ* እንዲል፤ አስቀድሞ ዐሥራ ሁለት ሐዋርያትን፣ ቀጥሎ *ወኀረየ ካልዓነ ሰብዓ*፤ ይላል ሰብዓ ሁለት አርድእትን፣ ቀጥሎ ሠላሳ ስድስት ቅዱሳት አንስትን መረጠ:: መቶ ሃያ ቤተሰብ የሚያሰኙ እሊህ ናቸው:: በእሊህ ትምህርት ተአምራት አይከፈልባቸውም:: ከዋለበት ይውላሉ፣ ካደረበት ያድራሉ:: ሌሎቹን ግን ምሴት ይከለክላቸዋል:: ከዚህ በኋላ ለዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል በየዕፃቸው ገብቶ ወር፣ ወር ሰብኮላቸዋል:: ሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስተምሮ ትምህርት ተአምራት ሲረዳለት ለመድኃኒተ ዓለም በማእከለ ምድር በቀራንዮ ተሰቀለ (የዓለም መድኃኒት ሆኖ በመካከለኛው ምድር በቀራንዮ ተሰቀለ):: *ወገብረ መድኃኒተ በማእከለ ምድር*፤ እንዲል (መዝ. 73፥12):: *ወኢይደልዎ ለነቢይ መዊት በአፍአ ዘእንበለ በኢየሩሳሌም* እንዲል፤ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ተነሣ:: እስከዚያ ወዴት ኖሯል ቢሉ:- በሲኦል ለነበሩ ነፍሳት ዐሥራ አምስቱን አህጉረ ገነት ርስት አድርጎ ሲያካፍል ቈይቶ፣ ተነሥቶም ለሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን ሰጥቶ አርባ ቀን መጽሐፈ ኪዳንን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አስተምሯቸዋል:: ለነፍሳትም ምሥጢረ መንግሥተ ሰማያትን



www.ethiopianorthodox.org



አስተምሯቸዋል:: *ወነበረ ምስሌሆሙ አርብዓ መዋዕለ እንዘ ይሜህሮሙ ምሥጢረ መንግሥተ ሰማያት* እንዲል፤ በአርባ ቀን ፓትሪያርክነት (በትሪያርክነትን) ሹሟቸው ዐረገ:: ባረገ ባሥረኛው ቀን፣ በተነሣ በኀምሳኛው ቀን ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ሰደደላቸው:: እስከዚያ ወዴት ኖሯል ቢሉ በትርጓሜ ወንጌል እንደታተተው ባሥረኛው ማዕርግ የኀባን እኛ ነበርንና ከጥንት ቦታችን እንደመለሰን ለማጠየቅ ባሥረኛው ቀን ሰደደላቸው:: አንድም በዘጠኙ ከተማ ያሉ መላእክት ሥጋዌውን አያውቁም ነበርና እነዚያን ሲያስተምር ኖሯል:: ይህ እንዳይሆን ፈጣሪ ፍጡር ይመስል አንዱን ሥራውን ሲሠራ አንዱ ሥራ ይከፈልበታል:: ወዲያስ ቢያስተምራቸው ወዲያስ ቢሰዳቸው ይሳነዋል ብሎ ሐተታ ከቀደመው ይገባል:: አንድም ዐሥሩን ቃላት ዐሥሩን ሕዋሳት ጠብቁ ሰጠኋችሁ:: እናንተም ብትጠብቁ ይሰጣችኋል ለማለት ባሥረኛው ቀን ሰደደላቸው:: ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ፍሩሃን የነበሩ ጥቡዓን ሆኑ፣ ከብሌት ታደሱ በአእምሮ ጐለመሱ፣ ምሥጢር አወቁ፣ አንድ ቋንቋ ያወቁ የነበር ሰባ ሁለት ቋንቋ ተገለጸላቸው:: *ወተናገሩ በነገረ ኵሉ በሐውርት* (በአገሩ ሁሉ ቋንቋ ተናገሩ) እንዲል::

ከዚህ በኋላ በኅብረት መዲናቸው ኢየሩሳሌም ዓመት አስተማሩ:: *ወነበሩ ዓመተ ፍጽምተ በኢየሩሳሌም* እንዲል:: ከዚህም በኋላ በኢየሩሳሌም ካሉ ምእመናን ጋራ አንድ ሆነው ጾምን መጾም፣ በዓለ ትንሣኤን ማክበር ዠመሩ:: ለስብከተ ወንጌል ይፋጠኑ ነበርና ሥርዓቱን አልወሰኑትም:: ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሡ ሊቃውንት ግን ሥርዓተ ጾም ቢጠፋባቸው በአተ ጾምን በጥር በ12 ቀን ዠምረው በየካቲት 21 ቀን እየፈጸሙ በዓልን ሳያብሉ (ሳያከብሩ) ያርፉ ነበር:: ሰሙነ ሕማማትንም በመጋቢት 22 ቀን ዠምረው በ28 ቀን እየፈጸሙ በ29 ቀን ትንሣኤን ያከብሩ ነበር:: ይህ ሥርዓት ሲያያዝ ከዘመነ ድሜጥሮስ ደረሰ::

## የድሜጥሮስ ታሪክ

ድሜጥሮስ ጌታችን ባረገ በመቶ ሰማንያ ዘመን በእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስነት ተሾመ:: በተሾመ በ27 ዘመን መንፈስ ቅዱስ ባሕረ ሐሳብ የተባለ የቍጥር መጽሐፍን ገለጸለት:: ታሪኩም እንዲህ ነው:- አርማስቆስ ደማስቆስ የሚባሉ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ:: በረኀብ ምክንያት ብሔረ ሞዓብ ተሰደው ይኖሩ ነበር::

ሚጠታቸው ሳይደርስ (ከመመለሳቸው በፊት) የልዕልተ ወይን አባት ሞተ:: ከአጉትዋ ቤት ከድሜጥሮስ ጋር አደገች:: አካለ መጠን ሁለቱም ሲያደርሱ አሕዛብ የበዙበት ምእመናን ያነሱበት ወራት ነበርና ንጽሐ ነፍስ ኪፈርስ ንጽሐ ሥጋ ይፍረስ ብለው አጋቧቸው:: ከዚህ በኋላ ሥርዓተ መርዓዊ ወመርዓት (የሙሽሮች ሥርዓት) ያድርሱ ብለው መጋረጃ ጥለውባቸው ወጡ:: እርስዋም ወንድሜ ይህን ነገር ያሰብከው እኔን ንቀህ ነው ወይስ ተዘምዶውን አለችው:: እኔስ አንቺንም ተዘምዶውንም ንቄ አይደለም:: የእናቴና ያባቴ ፈቃድ እፈጽማለሁ ብዬ ነው እንጂ አላት:: ፈቃድሽማ ከኾነ በድንግልና አንኖርምን አላት:: ይሁን አለችው:: እንኪያውስ የተፋታን እንደሆን አንቺንም ለሌላ፣ እኔንም ለሌላ ያጋቡናልና ባንድ እንኑር አላት:: እሺ አለችው:: ከዚህ በኋላ ባንድ አልጋ ተኝተው፣ አንድ ምንጣፍ አንጥፈው፣ አንድ ልብስ ለብሰው 48 ዘመን ኑረዋል:: ይኸውም ይታወቅ ዘንድ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ቀኝ ክንፉን ለሱ ግራ ክንፉን ለርስዋ አልብሷቸው አድሮ ጧት በአምሳለ ርግብ በመስኮት ወጥቶ ሲኼድ ያዩት ነበር:: *ንሕነሰ ንሬኢ ዘከመ ገጸ መልአከ እግዚአብሔር ንስረ ወይጼልል ክንፎ ዘየማን ላዕሌየ ወክንፎ ዘፀጋም ላዕሌሃ እምጊዜ ንነውም እስከ ጊዜ ጽባሕ ወውእተ ጊዜ ይትነሣእ፤* እንዲል::

ከዚህ በኋላ ዩልያኖስ የሚባል የማርቆስ ዐሥራ አንደኛ ሊቀ ጳጳስ ነበር፤ ሕዝቡ ተሰብስበው ወጥተው አባታችን አንተ አረጀህ ካንተ ቀጥሎ የሚሾመውን ንገረን አሉት:: እናንተም እዘኑ እኔም አዝናለሁ ብሎ ሱባዔ ገባ:: መልአክ መጥቶ ያለጊዜው የደረሰ ሦስት የወይን ዘለላ ይዞ የሚመጣ ሰው አለ ካንተ ቀጥሎ የሚሾመው እሱ ነው ብሎ ነግሮታል:: እርሱም ሱባዔውን ሲፈጽም አገኛቹህ? አላቸው:: እኛስ አላገኘንም አሉት:: እኔ አግኝቻለሁ፤ ያለ ጊዜ የደረሰ ሦስት የወይን ዘለላን ይዞ የሚመጣ ሰው አለ:: ከእኔ ቀጥሎ የሚሾመው እሱ ነው ብሏቸዋል::

ይህም ድሜጥሮስ ድኮ ታጣቂ ሞፈር አራቂ፣ ወይን አጽዳቂ ነበር:: ከዕለታት ባንድ ቀን ወይን ለማቃናት ከወይን ቦታ ቢገባ ያለ ጊዜው የደረሰ ሦስት የወይን ዘለላ አገኘ:: ወስዶ ለሚስቱ ሰጣት:: እስዋም ይህ ለእኛ አይገባም ወስደህ ለሊቀ ጳጳሱ አበርክተህ አቡነ ዘበሰማያት ተቀብለህበት ና አለችው:: እርሱም ወስዶ ለሊቀ ጳጳሱ አበርክቶ አቡነ ዘበሰማያት ተቀብሎበት ሲወጣ ከኔ ቀጥሎ የሚሾመው ይህ ነው ብሏቸዋል:: አንድም ሊቀ ጳጳሱ አልዋለም፣ አላደረም:: ዕለቱን





ሙቷል:: ቀብረው ሲመለሱ ደረሰ:: ተሾምልን አሉት:: እኔ ደንቆሮ በሊቁ ወንበር እኔ ባለሕጉ በንጹሑ ወንበር እንደምን አድርጎ ይኾንልኛል አላቸው:: አባታችን ነግሮናልና ተሾምልን አሉት:: በሀገራችሁ ሊቀ ጳጳስ ሲሾም ምን ሠርቶ ይሾማል አላቸው:: አንቀጸ አባግዕን፣አንቀጸ ብፁዓንን አንብቦ ተርጉሞ ይሾማል አሉት:: አንቀጸ ብፁዓንን አንቀጸ አባግዕን አንብቦ ተርጉሞ ተሹሟል:: ወዲያው 81 መጻሕፍት ተገልጸውለታል::

ከዚህ በኋላ የሕዝቡ ኀጢአት ተገልጸለት አንተ በቅተሃል ቊረብ፤ አንተ አልበቃህም አትቊረብ እያለ ይከለክላቸው (ነበር) ገ[ዘ]መር:: እጨገነት ከሚስት እንዲሉ፣ እርሱ በማይገባው በንጹሑ በማርቆስ ወንበር ተቀምጦ እኛን አንተ በቅተሃል ተቀበል፤ አንተ አልበቃህም አትቀበል እያለ ይከለክለን ገ[ዘ]መር ብለው አሙት:: አምተውም አልቀሩ የሐሰት ምስክር ዋጅተው፣ ከሳሽ አስነሥተው ለንጉሡ ሰደዱለት:: እርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት በአገልግል አድርጎ ለንጉሡ በውሀው ላይ ዳመጠ፣ በዳመጠው ላይ እሳት አድርጎ ለንጉሡ ላከለት:: ንጉሡም ዳመጠውን እሳቱ ሳያቃጥለው እሳቱን ውሀው ሳያጠፋው አይቶ ሰዎቹን አስጠርቶ ይህ ሰው ደግ ነው፤ በእኔ ጊዜ አይከሰስም አይወቀስም ብሏቸዋል:: የእነሱ መልእክተኞች በፊት ተነሥተው በሠላሳ ቀን ደርሰዋል:: የርሱ መልክተኞች በኋላ ተነሥተው በሰባት ቀን ደርሰዋል:: የነሱ መልእክተኞች በፊት ተነሥተው በሠላሳ ቀን መድረሳቸው በሠላሳ የመገደፉ ምሳሌ ነው:: የሱ መልእክተኞች በኋላ ተነሥተው በሰባት ቀን መድረሳቸው በሰባት የመገደፉ ምሳሌ ነው::

ከዚህ በኋላ መልአኩ መጥቶ ሕዝቡ አንተን እያሙ የሚጉዱ ኹኖአልና ባንተና በሚስትህ መካከል ያለውን ምሥጢር ለሕዝቡ ግለጽላቸው አለው:: *ክሥት ዘሀሎ ማእከሌከ ወማእከለ ብእሲትከ* እንዲል፤ እርሱም ሕዝቡን ዕንጨት እየያዛችሁ ተሰብሰቡ ብሎ አዋጅ ነገረ:: ሕዝቡም ዕንጨት እየያዙ ተሰበሰቡ:: ያን እንደ ደመራ ደምሮ ሊቀ ዲያቆኑን ስወጣ በእሳት እንድታቃጥለው ብሎት ቅዳሴ ገባ:: ከቅዳሴ ከወጣ በኋላ ኼዶ ከፍሕሙ መካከል ይጸልይ ገ[ዘ]መር:: ሕዝቡም በምን ይሞትልናል ስንል ዛሬስ በገዛ እጁ ከእሳት ገብቶ ሊሞትልን ነው አሉት:: ሚስቱም ከቤተ ደናግል ነበረችና ልዕልተ ወይን ልዕልተ ወይን ብሎ ጠርቶ ስፍሂ ዐጽፈኪ (ነጠላሽን ዘርጊ) አላት:: ፍሕሙን በእጁ እየታፈነ ከልብስዋ ላይ አደረገላት:: እርስዋም ወንዱን ሴቱን እጅ ነሥታ ብታራግፈው ልብሷ ከዘሐው



www.ethiopianorthodox.org

ከማት አንድ እንኳ ሳይቀነብር ተገኝቷል፡፡ ሕዝቡም ይህ ነገር ምንድን ነው አባታችን ሆይ ግለጽልን አሉት፡፡ እርሱም እንዲህ አለ፤ ከተጋባን 48 ዘመናችን ነው፡፡ ከአንድ አልጋ ተኝተን፣ አንድ ምንጣፍ አንጥፈን፣ አንድ ልብስ ለብሰን ስንኖር በግብረ ሥጋ አልተዋወቅንም አላቸው፡፡ ሕዝቡም ኀድግ ለነ ስረይ ለነ (ኀጢአታችንን ተውልን፤ይቅርም በለን) ብለው ከጫማው ወደቁ፡፡ እርሱም ይፍታሕ ወይኅድግ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ (ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር ይበላችሁ፤ ከኀጢአታችሁ የተፈታችሁ ሁኑ) ብሎ ናዝዟቸዋል፡፡ ኑዛዜም ያን ጊዜ ተገሮምሯል፡፡

## የአጽዋማትና በዓላት ሥርዓት

ከዚህ በኋላ ድሜጥሮስ እንዲህ አለ፡፡ እኔስ የጌታዬ ፈቃድ ቢሆን ጾመ ነነዌ፣ ዐቢይ ጾም፣ ጾመ ሐዋርያት ከሰኞ፣ ደብረ ዘይት፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ ጰራቅሊጦስ ከእሑድ፣ ረክበ ካህናት፣ ጾመ ድኅነት ከረቡዕ፣ ዕርገት ከኀሙስ፣ ስቅለት ከዓርብ ባይወጣ መልካም ነበር ብሎ ተመኘ፡፡ መልአኩ መጥቶ ሁልጊዜ በተምኔት ይፈጸማል? ከቀኑ 7 ሱባዔ፣ ከሌሊቱ 23 ሱባዔ ገብተህ እየው አለው፡፡ ስለምን የቀኑን አሳንሶ የሌሊቱን አበዛው ቢሉ ቀን ሲፈርድ ሲተች፣ የተጣላ ሲያስታርቅ፣ የተበደለ ሲያስክስ፣ የተቀማ ሲያስመልስ ይውላል፡፡ ሌሊት ግን ይህ ኹሉ የለበትምና ስለዚህ ነው፡፡ የመዓልቱ 7 ሱባዔ ሲባዛ 49 ይሆናል፡፡ ከዚህ 30 ሲቀነስ 19 ይተርፋል፡፡ ይህን መጥቅዕ ብለህ ከዕለታት ተውሳክ ጋር ደምረህ የአጽዋማት፣ የበዓላት ማውጫ ይሁንህ ብሎታል፡፡ የሌሊቱ 23 ሱባዔ ሲባዛ 161 ይሆናል፡፡ ይህ በ30 ሲቀመር 5 ሱባዔ ሆኖ 11 ይተርፋል፡፡ ይህን አበቅቴ ብለህ ከሕጸጽና ከዕለት ጋር ደምረህ የሌሊት ማውጫ ይሁንህ ብሎታል፡፡

## የድሜጥሮስ መልእክት

ቅዱስ ድሜጥሮስ የአጽዋማትና የበዓላት ኢየዐርጋቸውንና ኢይወርዳቸውን በአንድ ዐቢይ ቀመር ቀምሮ ለሦስቱ ሊቃነ ጳጳሳት፣ አራተኛም በኢየሩሳሌም ላለው ኤጲስቆጶስ ሰደደላቸው፡፡ እነርሱም ተቀብለው ሐዋርያት በዲድስቅልያ ካስተማሩት ጋር አንድ ኾኖ ቢያገኙት ደስ ብሎአቸው አስተምረውበታል፡፡ ከሁሉ ደርሷል፡፡ ሠለስቱ ምእትም ጉባኤ ሠርተው አስተምረውበታል፡፡





*ወአስተላጸቅዎ ለጾመ አርብዓ ቅድስት፤ ምስለ ሰሙነ ሕማማት ወሠርዑ አበቅቴ ውስተ አብያተ ክርስቲያናት* (አርባ ጾምን ከሰሙነ ሕማማት ጋራ አዛመዱት) እንዲል፡፡ ቍጥርም ቢሳሳት የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ይመስክር ብለዋል፡፡ *ወአዘዙ ኵሉ ዘስሕተ አበቅቴ ወሐሳበ ይትመራሕ በሊቀ ጳጳሳት ዘእእስክንድርያ* እንዲል፡፡

ይህንም መጽሐፍ ቢኾን ክርስቲያን ኹሉ፣ ባይኾን ካህን ኹሉ ሊማረው ይገባል፡፡ *ካህን ወመነኮስ ዘኢየአምር መጽሐፈ ሐሳብ ይከውን ከመ ፈለግ ዘአልቦ ማይ፣ ወከመ ሀገር ዘአልቦ ሰብእ* እንዲል፡፡ ባሕረ ሐሳብን ያልተማረ ካህንና መነኰሴ ውሀ በሌለው ወንዝ፣ ሰው በሌለው ሀገር ይመሰላል፡፡ ውሀ የሌለው ወንዝ ዛፉ አምሮ ለምልሞ አብቦ ይታያል፡፡ ነጋድያን ከሩቅ ሆነው አሻግረው አይተው ከዚህ ወንዝ አርፈን ውሀ ጠጥተን ከብቶቻችንም አጠጥተን እያሉ እያሰቡና ተስፋ እያደረጉ ይመጣሉ፡፡ አስበውም አይቀሩ ከዚያ ይደርሳሉ፡፡ ውሀ የሌለው ሆኖ ቢያገኙት አዝነው ተክዘው ከቀቢጸ ተስፋ ደርሰው ይኼዳሉ፡፡ ምእመናንም እንዲሁ ባሕረ ሐሳብን ያልተማረ ካህን አምሞ ጠምጥሞ ሰናፊሉን አንሰርትቶ ሲኼድ የዩታል፡፡ አባታችንን አጽዋማት በዓላት የሚውሉበትን ቀን እንጠይቃቸው ብለው ያስባሉ፡፡ አስበውም አይቀሩ ይጠይቁታል፡፡ አሳውቅም ያላቸው እንደሆን አዝነው ተክዘው ከቀቢጸ ተስፋ ደርሰው ይኼዳሉና፡፡ ስለዚህ ውሀ በሌለው ወንዝ ይመሰላሉ፡፡ እንዲሁም ሰው የሌለው ሀገር ቢኼዱ ቢኼዱ ዱር እንጂ ሰው አይገኝበትም፡፡ ባሕረ ሐሳብ ያልተማረ ካህንም ሕጸጽ እንጂ ዕውቀት አይገኝበትም፡፡ በብሉይና በሐዲስ የተሠሩ አጽዋማት በዓላት የሚውሉበት ቀን፣ ታሕታይና ላዕላይ ቀመራቸውን ለይቶ አያውቅምና፡፡ ተከራክሮም ሥርዓተ በዓላትንና አጽዋማትን አያጸናምና፡፡ ስለዚህ ሰው በሌለው ሀገር ይመሰላል፡፡ የዚህም መጽሐፍ ደግነቱ ይታወቅ ዘንድ በአራቱ መዓዝን ያሉ ምእመናን በአተ ጾምን በአንድ ሰኞ ዠምረው በአንድ እሑድ ትንሣኤን ያከብራሉ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

## · ምዕራፍ ሁለት

# መርሐ ዕዉር

የባሕረ ሐሳብ መምህራን ከብዙ ክፍል ከፍለው በማሳጠር ያዘጋጁትን መርሐ ዕዉር የተባለውን መጽሐፍ መሐሪና ይቅር ባይ በሆነው በእግዚአብሔር ስም ረዳትነት መጻፍን እንገርምራለን። ይህም ሕዝብ ሁሉ የብሉይና የሐዲስ አጽዋማትና በዓላትን ለማወቅ ቃል በቃል ይማሩት ዘንድ የተዘጋጀ ነው። ምክንያቱም የአይሁድ በዓል ከምእመናን ሐዲስ በዓል ጋራ ማክበር የማይገባ መሆኑን እንዲያውቁ ነው።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ዘለዓለም። እግዚአብሔር ቅድመ ዓለም ባንድነት በሦስትነት ሳለ ክብሩ በባሕርዩ እንደቀረ አይቶ ዓለምን ልፍጠር ብሎ አሰበ። አስቦም አልቀረም። ሰውና መላእክትን ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ፤ የቀረው ለአንክሮ ለተዘክሮ ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ ፈጠረ። *ወኵሉ ዘተፈጥረ ለመፍቅደ ነባብያን። ቦ እምኔሆሙ ለምህሮ፣ ወቦ እምኔሆሙ ለተገብሮ እንዘ ኢየኀድግ ርእሶ ዘእንበለ ሰማዕት። ወለእመ ኀሠሥከ ሰማዕተ አማናዌ ብከ መምህር ወሰማዕት እምአፍአ ዘይመርሐከ ኀበ አንክሮተ እግዚአብሔር። ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም በፍጥረቱ ለፍጥረቱ። እስመ ኬንያ ይትዐወቅ በኪኑ ወእሙራንኒ በተግባሮሙ፤* እንዲል (አክሲማሮስ፣ ፊልክስዩስ፣ ማር ይስሐቅ)።

የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ለነባብያን ፍላጎት ነው። ከተፈጠረው ፍጥረትም ለትምህርት የሚሆን አለ። ለግብርና ሥራም የሚሆን አለ። ራሱን ያለምስክር አልተወምና አንተ እውነተኛ ምስክርን ከፈለግህ ወደ እግዚአብሔር ድንቅ ሥራ የሚመራሕ መምህርና ምስክር የሚሆን ከውጭ አለልህ፣ ታገኛለህም።እግዚብሔር ከፍጥረተ ዓለም ዠምሮ ለፍጥረቱ፣ በፍጥረቱ የማይታይ ነው። ጥበበኛ ሰው በጥበቡ፣ አዋቂዎችም በዕውቀታቸው ይታወቃሉና።





እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት እያንዳንዱ ቢቈጠር በፍጡር ቃል ተቈጥሮ ባልተፈጸመም ነበር። ነገር ግን እየወገን እየወገኑ ብዙውን አንድ ብዙዉን አንድ እያሉ ቢቈጥሩ ከእሑድ እስከ ዓርብ የተፈጠረው ፍጥረት 22 ነው። ዓለም የተፈጠረበት እሑድ ጥንተ ዕለት ይባላል። አዝርዕት አትክልት፣ዕፀዋት የተፈጠሩበት ዕለተ ሠሉስ (ማክሰኞ) ጥንተ ቀመር ይባላል። ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት የተፈጠሩበት ዕለተ ረቡዕ ጥንተዮን ይባላል። *ያን ይእቲ ሀገረ ፀሐይ፤* እንዲል።

የሐሳበ ዘመን ስሌት በአቅማራትና በአዕዋዳት ተቈጥሮ ተሰፍሮ የተወሰነ ስለሆነ ስሌቱ ከታወቀ አያሳስትም። መንገዱ አንድ ነውና።

### ዓመተ ዓለም

ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለ ዘመን ዓመተ ፍዳ፣ ዓመተ ኵነኔ ዘመነ ብሉይ ይባላል። ከልደተ ክርስቶስ ዠምሮ እስከ ዛሬ ያለ ዘመን ዓመተ ምሕረት፣ ዓመተ ሥጋዌ፣ ዘመነ ሐዲስ ይባላል። መላው ዓመተ ዓለም፣ መዋዕለ ዓለም ይባላል። ዓመተ ዓለም ባለው ዓመተ ምሕረት ይላል። ምክንያቱም ሰው በዚህ ዓለም ሳለ ኃጢአት ሠርቶ ንስሐ ቢገባ፣ ምግባር ትሩፋት ቢሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን የሚያገኝ ስለሆነ ነው። *በዕለት ኅሪት ሰማዕኩከ፣ ወበዕለተ መድኃኒት ረዳእኩከ፤ ወናሁ ይእዜ ዕለት ኅሪት፣ወናሁ ዮም ዕለተ አድኅኖት፤* እንዲል (2ቆሮ፡ 6፥2)። የተመረጠች ቀን እነሆ ዛሬ ናት። ድኅነት የሚገኝባትም ቀን እነሆ ዛሬ ናት።

### አስረጅ

ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ የዘመነ ሐዲስ ሦስተኛው ሺሕ ዓመት እስከባተበት 2001 ዓ.ም. ድረስ ያለ ዘመን ቢቈጠር በፀሐይ 7501 ዓመት፣ በጨረቃ 7730 ዓመት፣ 8 ወር በ8 ቀን ይሆናል። ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለ ዘመን ቢቈጠር በፀሐይ 5500 ዘመን፣ በጨረቃ 5668 ዓመት ከ10 ወር ከ9 ቀን ይሆናል። ከክርስቶስ ልደት ዠምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለ ዘመን

www.ethiopianorthodox.org

በፀሐይ 2001 ዓመቱ በጨረቃ 2061 ዓመት፣ 9 ወር ከ29 ቀን ይሆናል።

## አዕዋዳት

ዐውድ ማለት ዙርያ፣ክበብ፣ከበር እስከ በር ካመት እስካመት ያለ፣ለተወሰነ ክበብ ላለው ሁሉ የሚነገር ነው።በብዙ ቁጥር ሲነገር አዕዋዳት ይባላል። (ኪዳነ ወልድ)

ለዓመተ ዓለም መቍጠርያ መስፈርያ የሚሆኑ ሰባት አዕዋዳት አሉ። እነርሱ ዐውደ ዕለት፣ ዐውደ ወርኅ፣ ዐውደ ዓመት፣ ዐውደ አበቅቴ፣ ዐውደ ፀሐይ፣ ዐውደ ማኅተም፣ ዐውደ ቀመር ናቸው። ዐውደ ጳጉሜን ሲታከልበት ስምንት ይሆናሉ።

1. ዐውደ ዕለት፡- የሰባት ዕለታት ዑደት ነው።

ጥንተ ዕለት (የዕለት መገርመርያ) ከሚባለው ከእሑድ ተነሥቶ ሰኞ፣ማክሰኞ፣ረቡዕ፣ሐሙስ፣ዓርብ ብሎ ቅዳሜ ላይ ያበቃል። እሊህ ሰባቱ ዕለታት አውራኅን ለማስገኘት በዚህ ሲመላለሱ ይኖራሉ።

2. ዐውደ ወርኅ፡- በፀሐይ ዘወትር 30 ዕለት ነው። በጨረቃ አንድ ጊዜ 29 ቀን፣ አንድ ጊዜ 30 ቀን ይሆናል። ይህም ዓመታትን ለማስገኘት በዚህ ሲመላለስ ይኖራል። በፀሐይ መደብ ወር ተብለው የሚጠሩ እነዚህ ናቸው።1ኛ መስከረም፣ 2ኛ ጥቅምት፣ 3ኛ ኅዳር፣4ኛ ታኅሣሥ፣5ኛ ጥር፣6ኛ የካቲት፣7ኛመጋቢት፣ 8ኛሚያዝያ፣9ኛ ግንቦት፣ 10ኛ ሰኔ፣11ኛ ሐምሌ፣12ኛ ነሐሴ፣13ኛ ጳጉሜን፤እነዚህ አንድ ዓመት ይሆናሉ።በጨረቃ መደብ በዑደቱ ልክ በወሩ ስም ላይ የጨረቃ የሚል ቅጥያ ይደረግላቸዋል። የጨረቃ መስከረም፣የሚያዝያ መስከረም እንዲል።

## የወሮች ብተት

መስከረም በሚብትበት ዕለት ማግስት ጥር ይብታል። ጥቅምት በሚብትበት ዕለት ማግስት የካቲት፣ ኅዳር በሚብትበት ዕለት ማግስት መጋቢት፣ ታኅሣሥ በሚብትበት ዕለት ማግስት ሚያዝያ ይብታል።

ዳግመኛም መስከረም በሚብትበት ዕለት ሚያዝያ ይብታል። ጥቅምት በሚብትበት ዕለት ግንቦት ይብታል። ኅዳር በሚብትበት ዕለት ሠኔ፣ ታኅሣሥ በሚብትበት ዕለት ሐምሌ፣ ጥር በሚብትበት ዕለት ነሐሴ፣ የካቲት በሚብትበት ዕለት ጳጉሜን ይብታል። መጋቢት ግን ተመሳሳይ ወር ስለሌለው ለብቻው ይያዛል።

3. **ዐውደ ዓመት፡-** በፀሐይ 365 ዕለት፣ በጨረቃ 354 ዕለት ይሆናል። ዐውደ ዓመት በፀሐይ 365 ዕለት ከ15 ኬክሮስ፣ ከ6 ካልዒት አይደለምን? በጨረቃስ 354 ዕለት 22 ኬክሮስ፣ ከ1 ካልዒት፣ ከ37 ሣልሲት፣ ከ52 ከብዒት ከ48 ኃምሲት አይደለምን? ቢሉ፣ *ወውስተ ውጉድኒ ንብል ሕልቦ ወኢሕሐዱ፤* እንዲል 60 ካልሞላ ብሎ ትርፉን ትቶ መናገር ነው እንጂ ቍጥሩስ አለ ተብሎ ይመለሳል። ከፀሐይ ወሮች ዐጽፌ አውራኅ፣ ከጨረቃ ወሮች ሕጸጸ አውራኅ ይገኛል።

4. **ዐውደ ጳጉሜን፡-** 4 ዓመት ነው።እያንዳንዱ ዓመትም በአራቱ ወንጌላውያን ስም እንደቅደም ተከተላቸው ተሰይሟል። የመገርመርያው ማቴዎስ፣ ሁለተኛው ማርቆስ፣ ሦስተኛው ሉቃስ፣ አራተኛው ዮሐንስ ነው። በዐውደ ጳጉሜን ውስጥ ዓመተ ወንጌላውያን ይገኝበታል።

## ዓመተ ወንጌላውያን

ዓመተ ወንጌላውያን ማለት ዓመተ ዓለም ለአራት ክፍል ሲከፈል ትርፍ ሆኖ የሚገኘው ዓመት ነው። ያውም እንዲህ ነው፡-



www.ethiopianorthodox.org

ዓመተ ወንጌላውያንን ለማወቅ ዓመተ ዓለም ለአራት ክፍል ይከፈላል:: ክፍያው እኩል ሆኖ ምንም ባይተርፍ ያንጊዜ ወንጌላዊው ዮሐንስ፣ ጳጉሜን 6 ይሆናል:: ከክፍያው አንድ ዓመት ቢተርፍ ግን ወንጌላዊው ማቴዎስ፣ ጳጉሜን 5 ይሆናል:: 2 ዓመት ቢተርፍ ወንጌላዊው ማርቆስ፣ ጳጉሜን 5 ይሆናል:: 3 ዓመት ቢተርፍ ወንጌላዊው ሉቃስ፣ ጳጉሜን 5 ይሆናል:: ሦስቱ ወንጌላውያን እያንዳንዳቸው አምስቱን ጳጉሜን ይዘው እየተከታተሉ በየአራቱ ዓመት ይመላለሳሉ:: ዮሐንስ ግን ለብቻው ስድስቱን ጳጉሜን ይዞ ይመላለሳል::

ማቴዎስ ምግብናውን በሠርክ ይጀምራል:: ከሠርክ እስከ መንፈቀ ሌሊት መግቦ በ6 ሰዓት በ15 ኬክሮስ ይፈጽማል:: ማርቆስ ምግብናውን በመንፈቀ ሌሊት ይገሮምራል:: ከመንፈቀ ሌሊት እስከ ነግህ መግቦ በ6 ሰዓት በ15 ኬክሮስ ይፈጽማል:: ሉቃስ ምግብናውን በነግህ ይጀምራል:: ከነግህ እስከ ቀትር መግቦ በ6 ሰዓት በ15 ኬክሮስ ይፈጽማል:: ዮሐንስ ምግብናውን በቀትር ይጀምራል:: ከቀትር እስከ ሠርክ መግቦ በ6 ሰዓት በ15 ኬክሮስ ይፈጽማል:: 15 ኬክሮስ በ4 ሲበዛ (15x4) =60 ኬክሮስ ሆኖ አንድ መዓልት ይባላል:: በአራተኛው ዘመን 6ኛ ጳጉሜን የሚባል ይህ ነው:: በዚሁ ላይ የሌሊቱ ሲደመር 24 ሰዓት ይሆናል:: ይህም አንድ ዕለት ነው::

የመዓልቱና የሌሊቱ ሰዓት ሐተታ ሲዘረዘርም እንዲህ ነው:- ከመጀመርያው ከዘመነ ማቴዎስ 3 ሰዓተ መዓልት 3 ሰዓተ ሌሊት ይገኛል:: ይህ ሲደመር 6 ሰዓት ይሆናል:: ከሁለተኛው ከዘመነ ማርቆስ 3 ሰዓተ መዓልት 3 ሰዓተ ሌሊት ይገኛል:: ይህ ሲደመር 6 ሰዓት ይሆናል:: ከሦስተኛው ከዘመነ ሉቃስ 3 ሰዓተ መዓልት 3 ሰዓተ ሌሊት ይገኛል:: ይህ ሲደመር 6 ሰዓት ይሆናል:: ከአራተኛው ከዘመነ ዮሐንስ 3 ሰዓተ መዓልት 3 ሰዓተ ሌሊት ይገኛል:: ይህ ሲደመር 6 ሰዓት ይሆናል:: 6 ሰዓት በ4 ሲባዛ (6 x4) =24 ሰዓት ሆኖ አንድ ዕለት ይባላል:: 6ኛ ጳጉሜን የሚባለው ይህ ነው::

ይህ ትክክለኛ ስሌት መሆኑ የሚታወቀውም እንዲህ ነው:: ከመጋቢት 26 ቀን እስከ ሠኔ 25 ቀን ያለው ዕለት 91 ይሆናል:: ያንጊዜ መዓልት እየረዘመ ሌሊት እያጠረ ይኼዳል:: *መዓልት ይስሕቦ ለሌሊት ይነውኅ መዓልት*





*ወየሐጽር ሌሊት*፤ እንዲል ከዚህ 3 ሰዓተ መዓልት ይገኛል:: ዘመኑ በእኛ ጸደይ በዕብራውያን መፀው ነው:: መጋቢው ኮከብ ምልክኤል ይባላል:: መሬትን ይመግባል::

ከሠኔ 26 እስከ መስከረም 25 ቀን ያለው ዕለት 91 ነው:: ይህ መዓልቱም ሌሊቱም ዕሩይ ነው:: *ወታገብእ መዓልት አሐደ ሰዓተ ለሌሊት*፤ እንዲል:: ዘመኑም በእኛ ክረምት በዕብራውያን ሐጋይ ነው:: መጋቢው ኮከብ ሕልመልሜሌክ ይባላል:: ውሀን ይመግባል::

ከመስከረም 26 እስከ ታኅሣሥ 25 ያለው ዕለት 91 ነው:: ያንጊዜ መዓልት እያጠረ ሌሊት እየረዘመ ይኼዳል:: *ሌሊት ይስሕቦ ለመዓልት ይነውህ ሌሊት ወየሐጽር መዓልት*፤ እንዲል:: ከዚህ 3 ሰዓተ ሌሊት ይገኛል:: ዘመኑ በእኛ መፀው በዕብራውያን ጸደይ ነው:: መጋቢው ኮከብ ሚካኤል ይባላል:: ነፋስን ይመግባል::

ከታኅሣሥ 26 እስከ መጋቢት 25 ያለው ዕለት 91 ነው:: ይህ ሌሊቱም መዓልቱም ዕሩይ ነው:: *ወታገብእ ሌሊት አሐደ ሰዓተ ለመዓልት*፤እንዲል:: ዘመኑ በእኛ ሐጋይ በዕብራውያን ክረምት ነው:: መጋቢው ኮከብ ናርኤል ይባላል:: እሳትን ይመግባል:: በአንድ ዓመት የተገኘው 3 ሰዓተ መዓልትና 3 ሰዓተ ሌሊት በአራት ዓመት 24 (6x4) ሰዓት ሆኖ አንድ ዕለት ይባላል:: ይኸውም 6ኛው ጳጉሜን ነው::

5. **ዐውደ አበቅቴ**:- 19 ዘመን ነው:: በዚህ ፀሐይና ጨረቃ፣ ዐውደ ዓመታቸውን ፈጽመው በተፈጠሩበት ኆኅት ተራክቦ ያደርጉበታል:: በየ19 ዓመት መስከረም አንድ ቀን እኩል ዐውደ ዓመታቸውን ይጀምራሉ:: ነቢየ ኦሪት ሙሴ፣ መምህራነ ወንጌል ሐዋርያት፣ ሊቀ ጳጳሳት ድሜጥሮስ ከ20ው አንድ፣ ከ40ው 2፣ ከ60ው 3፣ ከ80ው 4፣ ከ100ው 5 ነሥታችሁ ቊጠሩ ያሉት ስለዚህ ነው:: ከዚህ 7 የጨረቃ ወር ይገኛል::

6. **ዐውደ ፀሐይ**:- 28 ዓመት ነው:: በዚህ ዕለት፣ ወንጌላዊ ይገናኙበታል:: ዕለቱ ረቡዕ፣ ወንጌላዊው ማቴዎስ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

ዕለቱን ፀሐይ አለው:: *ወበትእዛዝከ ይቀውም ዕለት*፤ እንዲል:: ወንጌላዊውን ፀሐይ አለው *አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም*፤ ካላቸው አንዱ እርሱ ነውና:: ከዚህ አበቅቴ ፀሐይ ይገኛል::

7. **ዐውደ ማኅተም**፡- 76 ዓመት ነው:: በዚህ አበቅቴና ወንጌላዊ ይገናኙበታል:: አበቅቴ 18፣ ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው:: ማኅተም አለው አበቅቴው ለአበቅቴ ፍጻሜ እንደሆነ ወንጌላዊውም ለወንጌላውያን ፍጻሜ ነውና::

8. **ዐውደ ቀመር**፡- 532 ዓመት ነው:: በዚህ ዕለት፣ አበቅቴ፣ ወንጌላዊ ይገናኙበታል:: አበቅቴው 18፣ ወንጌላዊው ዮሐንስ፣ ዕለቱ ሠኑይ (ሰኞ) ነው:: አይለወጥም፤ *ሠሉሱ ማቴዎስ* የሚል ነውና:: ዐውዱ በዘመነ ማቴዎስ በማክሰኞ ዕለት አንድ ብሎ ይጀምርና በ532ኛ ዓመት ላይ በዘመነ ዮሐንስ በሰኞ ዕለት ይፈጸማል::

ከእሊህ ከስምንቱ አዕዋዳት ሦስቱ በዕለት ይቈጠራሉ:: በዕለት የሚቈጠሩት ሦስቱ ዐውደ ዕለት ዐውደ ወርኅ፣ ዐውደ ዓመት ናቸው:: በዓመት የሚቈጠሩ አምስቱ ዐውደ ጳጉሜን፣ ዐውደ አበቅቴ፣ ዐውደ ፀሐይ፣ ዐውደ ማኅተም፣ ዐውደ ቀመር ናቸው::

ዕለታትን አዕዋድ አላቸው:: አውራኅን የሚያስገኙ ስለሆነ፣ አውራኅን አዕዋድ አላቸው:: ዓመታትን የሚያስገኙ ስለሆነ፣ *በከመ ይትወለዳ አውራኅ እምዕለታት፣ ወዓመታት እምአውራኅ ከማሁ ይትወለዳ አእምሮታት እምግባራት፣ ወእመከራት ዘቦቱ ያነጽሕ ዐውደ እክሉ*፤ እንዲል::

ዳግመኛም ቀመርን ለሦስት ስም በሰጡ ጊዜ ዐውደ ቀመር ዐቢይ ቀመር፣ ዐውደ ማኅተም ማእከላዊ ቀመር፣ ዐውደ አበቅቴ ንኡስ ቀመር ይባላል:: በዐውደ ማኅተም ቦታ ዐውደ ፀሐይ፣ በዐውደ ፀሐይ ቦታ ዐውደ ማኅተም የሚል አብነት ይገኛል:: ከሁለቱ አንዱ ቢታጣ ከቀመር ገብቶ ይቈጠራል::

ሌሎች ዐውዶችም በየ15 ዓመት የሚመላለሰው ዐውደ እንድቅትዮን፣ በየ49 ዓመት የሚመላለሰው ዐውደ ኢዮቤልዩ፣ አሉ::



www.ethiopianorthodox.org



## 1. ዐውደ ዕለት በጥንታት ሲገለጽ

ጥንት ማለት መነሻ መገኘመርያ ማለት ነው:: ሲበዛ ጥንታት ይሰኛል:: የፀሐይ ጥንታት ሦስት ናቸው:: እነርሱም ዓለም የተፈጠረበት እሑድ ጥንተ ዕለት፣ ዕፀዋት አዝርዕት የተፈጠሩበትና ቀመር የተገኘመረበት ማክሰኞ (ሠሉስ) ጥንተ ቀመር፣ ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብትም የተፈጠሩበት ረቡዕ ጥንተዮን ይባላል:: *ያን ይእቲ ሀገረ ፀሐይ*፤እንዲል (ዘፀ. 1፥11)::

ዳግመኛም የጥንታት ሐተታ ተዘርዝሮ ሲጻፍ እስከ ሰባት ይደርሳል:: ይኸውም እሑድ ጥንተ ዕለት፣ ጥንተ ጽልመት፣ ጥንተ መላእክት፣ ጥንተ ብርሃን፣ ጥንተ ቅዳሴ፣ ሰኞ ጥንተ ሳኒታ፣ ጥንተ አስተርእዮ፤ ማክሰኞ ጥንተ ዘርዕ፣ ጥንተ ልደት፣ ጥንተ ጥምቀት፣ ጥንተ ቀመሩ ለማቴዎስ፤ ረቡዕ ጥንተዮን፣ ጥንተ ቀመሩ ለማርቆስ፣ ኀሙስ ጥንተ ወርኅ፣ ጥንተ ፍሥሕ፣ ጥንተ ቀመሩ ለሉቃስ፣ ዓርብ ጥንተ አዳም፣ ጥንተ ቀመሩ ለሠግር፣ ቅዳሜ ጥንተ ዕረፍት፣ ጥንተ ቀመሩ ለዮሐንስ ማለት ነው::

## የጥንተ ዓለም ቀመር

ሌሊትንና መዓልትን የሚለዩ ጨረቃና ፀሐይ የተፈጠሩበት ዕለት ረቡዕ ቢሆንም እንኳ የሐሳበ ዘመን መምህራን ጥንተ ዓለም ወይም ጥንተ ቀመር ያደረጉት ዕለት ማክሰኞን ነው:: ምክንያቱም ከፍሬና ከአበባ ጋር ዛፎች ሁሉ የበቀሉበት፣ የብስ የታየበት፣ ማያት (ውኃ) የተከፈሉበት፣ የመገኘመርያው ወር የባተበት ዕለት ማክሰኞ ነውና:: ስለዚህ መፀውንና ጸደይን (በልግ)፣ ክረምትንና ሐጋይን (በጋ) የምትለይ ማእከላዊት፣ ኮከባዊት የሆነች አንዲት ቀን ከንቱ ሆና እንዳትቀር ቀመራቸውን በማክሰኞ እንደ ገኘመሩ መምህራት ያስረዳሉ (ዘፍ 1÷14-19)::

*ወዘረሰዩሰ ጥንተ ዓለም በሠሉስ ይቤሉ እስመ በሠሉስ አስተርአየ የብስ፣ ወተከፍሉ ማያት፣ ወሠረቀ ቀዳማይ ወርኅ (ሚያዝያ) በዕለተ ሠሉስ* እንዲል(መርሐ ዕዉር)::

በዚሁ አንጻርም ማክሰኞን ጥንተ ቀመር ያደረጉ የሐሳበ ዘመን መምህራን የሐዲሱ ዓለም ጥንትና መሠረት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ5,500 ዓመት በዕለተ እሑድ በዘመነ ዮሐንስ ተፀንሶ፣ በ5,501 ዓመት በዕለተ ሠሉስ በዘመነ ማቴዎስ ተወለደ ብለው ያስተምራሉ።

ኢትዮጵያውያንና ግብጻውያንም እንደ ዕብራውያን አቈጣጠር ዐውደ ዓመታቸውን በስድስተኛው ወር በመስከረም መባቻ ያደረጉት በመስከረምና በመጋቢትና ወር በሚያዝያ ፀሐይ የሚወጣበትና የሚገባበት ማኅፈድ (ደጃፍ) አንድ ስለሆነ ነው። ያውም አራተኛው ኆኅት ወይም ደጃፍ ነው።

## ጥንተ ቀመር

ቀመር የቁጥር መደብ ሲሆን፣ ጥንተ ቀመርም ቀመር የተጀመረበት ቀን ማለት ነው። ያም ቀን ማክሰኞ ነው። ዐቢይ ቀመር በማክሰኞ ተገምሮ በተጀመረ በ532 ዓመት በሰባተኛው ቀን ሰኞ በዘመነ ዮሐንስ ይፈጸማል። ዐቢይ ቀመር በሚባለው በዚህ ባንዱ ቀመር በሌሊትና በመዓልት ብተት የሚውሉ በዓላትና አጽዋማት ከዚህ ሥርዓት ለዘለዓለሙ ሳይፋለሱና ሳይለወጡ፣ ሳይናወጹም በሌሎቹ አቅማራት ሁሉ እንዲሁ ይውላሉ። በአንዱ ቀመር የተጻፈው የበዓላትና የአጽዋማት ሁሉ ሥርዓትም በአቅማራተ ዓለም ሁሉ የሚፈጸም ነው እንጂ የአንድ ቀመር ሥርዓት ብቻ አይደለም።

ጥንተ ቀመርን ለማወቅ ዓመተ ዓለም ለአራት ይከፈላል። አራተኛው ክፍል መጠነ ራብዕት ይባላል። በመጠነ ራብዕት ላይ ዓመተ ዓለም ተደምሮ ለ7 ዐውደ ዕለት ይከፈላል። ከክፍያው የተረፈው ዕለተ ቀመር ይሆናል። 1 ቢተርፍ ዕለተ ቀመር ማክሰኞ ይሆናል። 2 ቢተርፍ ዕለተ ቀመር ረቡዕ ነው። 3 ቢተርፍ ኀሙስ፣ 4 ቢተርፍ ዓርብ፣ 5 ቢተርፍ ቀዳም፣ 6 ቢተርፍ እሑድ፣ 7 ቢሆን ዕለተ ቀመር ሰኞ ይሆናል። የጥንተ ቀመር መመላለሻ 7 ነው። ያውም ከማክሰኞ እስከ ሰኞ ነው።





## ጥንተዮን

ጥንተዮን ማለት ጥንተ ፀሐይ፣ ዕለተ ተረክቦቶሙ ለብርሃናት ማለት ነው። ስማ ለፀሐይ ዖን ይእቲ፤ እንዲል (ዘፀ፦ 1፡11)።ለዕለተ ቀመር ከወጣው ላይ 1 ሲቀነስ ጥንተዮን ይገኛል። ተቀንሶ የተገኘው ውጤት 1 ቢሆን ጥንተዮን ረቡዕ ይሆናል። 2 ቢሆን ኀሙስ፣ 3 ቢሆን ዓርብ፣ 4 ቢሆን ቀዳም፣ 5 ቢሆን እሑድ፣ 6 ቢሆን ሰኞ፣ 7 ቢሆን ማክሰኞ ጥንተ ዮን ይሆናል። የጥንተዮን መመላለሻ 7 ነው። ያውም ከረቡዕ እስከ ማክሰኞ ነው። መስከረም አንድን የሚያመለክተው ጥንተዮን አበቅቴ ፀሐይም ይባላል።

## ዕለተ ዮሐንስ

ዕለተ ዮሐንስ ማለት በዮሐንስ ወንጌላዊ የተጀመረ፣ መጥምቁ ዮሐንስ የሚከበርበት፣ ዕለት ማለት ነው። መነሻውም እሑድ ነው። ይህም ጥንተ ዕለት ይባላል። በመጀመርያ ሰማይና ምድር የተፈጠረበት ዕለት ስለሆነም ሐሳበ ሰማይ ወምድር ይባላል።

ለዕለተ ቀመር በወጣው ላይ 2 ዕለተ ጠቢባን (ከማክሰኞ በፊት ያሉት ሁለቱ ቀኖች እሑድና ሰኞ) ሲደመር ዕለተ ዮሐንስ ይገኛል። የተገኘው ውጤት 1 ቢሆን ዕለተ ዮሐንስ እሑድ ይሆናል። 2 ቢሆን ዕለተ ዮሐንስ ሰኞ ይሆናል። 3 ቢሆን ማክሰኞ፣ 4 ቢሆን ረቡዕ 5 ቢሆን ኀሙስ፣ 6 ቢሆን ዓርብ፣ 7 ቢሆን ዕለተ ዮሐንስ ቀዳም ይሆናል። ዕለተ ዮሐንስ ማለትም የመስከረም መባቻ ማለት ነው። የዕለተ ዮሐንስ መመላለሻ 7 ነው። ያውም ከእሑድ እስከ ቀዳም ነው። በሰባቱ ዕለታት ብተት በየሰባቱ ዓመት የሚመላለሱ፦ ጥንተዮን የሚባለው ሐሳበ ፀሐይ፣ጥንተ ዕለት የሚባለው ሐሳበ ሰማይ ወምድር ናቸው።

### አስረጅ

የ7000 ዓ.ዓ. አበቅቴ ፀሐይን ለማወቅ ከ7 ሺሕ ዓመት ዕለተ ምርያን (5ኛ ጳጉሜን) እና ዕለተ ሠግርን (6ኛ ጳጉሜን) ለይቶ አውጥቶና ደምሮ ለ7 ዐውደ ዕለት ይከፈላል። ከ7 ዐውደ ዕለት የተረፈው አበቅቴ ፀሐይ ይሆናል። ያውም እንዲህ ነው፦



www.ethiopianorthodox.org

የ7000 ዓመት፡-

| | |
|---|---|
| ዕለተ ምርያ 7000 x 1 = | 7000 ዕለት |
| ዕለተ ሠግር 7000 ÷ 4 = | 1750 ዕለት |
| ድምር | 8750 ዕለት |

ከ8750 ዕለት አንድ ሲቀነስ 8749 ዕለት ይሆናል። ይህ በ7 ዐውደ ዕለት ሲቀመር 1249 ሱባዔ ዕለት ሆኖ 6 ይተርፋል። ስለዚህ ያንጊዜ ጥንተዮን 6፣ ዕለተ ዮሐንስ 2 ሆኖ ነበር። ቀኑም ሰኞ ነው። ስለዚህ በዚሁ ስሌት መሠረት መምህራኑ፡-ሰባተኛው ሺሕ የተፈጸምበት ዕለት ሰኞ፣

| | |
|---|---|
| ጥንተዮን ወይም አበቅቴ ፀሐይ | 6 |
| ዕለተ ዮሐንስ ወይም ሐሳበ ሰማይ ወምድር | 2 |
| አበቅቴ ወርኅ | 17 |

መሆኑን አውቀው ተረድተዋል።

## ሰባቱ ሺሕ ዓመት በተለያዩ ዐውዶች ሲሰፈር

ብፁዕ አባ ዘሲማስ *በሳብዕ ሲሕ የሐልቅ ዓለም* ብሎ እንደ ጻፈው (ራእ. 16፣17) (*መጽሐፈ ዘሲማስ* ገጽ 409) በቀድሞ ዘመን ዓለም በሰባት ዕለታት እንደ ተፈጠረ እንዲሁም 7 ሺሕ ዓመት ሲፈጸም ዓለሙ ያልፋል የሚል ትውፊታዊ ትምህርት ስለነበር የሐሳበ ዘመን መምህራን ሰባተኛው ሺሕ ዓመት የሚፈጸምበትን ዕለት ለማወቅ፣ በሰባቱ ዕለታት ብተት በየሰባቱ ዓመት የሚመላለሱትን ሐሳበ ፀሐይ የሚባለው ጥንተዮንንና ሐሳበ ሰማይ ወምድር የሚባለው ዕለተ ዮሐንስን፣ እንዲሁም አበቅቴ ወርኅን ለይቶ ለማወቅ 7ቱን ሺሕ በ15 ዐውደ እንድቅትዮን፣ በ4 ዐውደ ጳጉሜን፣ በ19 ዐውደ አበቅቴ ቀምረውት ነበር። ያውም እንዲህ ነው፡-





ከአዳም ዠምሮ እስከ 7 ሺሕ ዓመት ፍጻሜ ያለው ዘመን፡-

በ15 ዐውደ እንድቅትዮን ሲቀመር 466 አንቀጽ ሆኖ 10 ይተርፋል። ስለዚህ ያንጊዜ እንድቅትዮን 10፣ ጳጉሜን 5 ሆኖ ነበር።

በ4 ዐውደ ጳጉሜን ሲቀመር 1750 አንቀጽ ሆኖ ምንም የተረፈ ስለሌለ ያንጊዜ ጳጉሜን 6 ሆኖ ነበር።

በ19 ዐውደ አበቅቴ ሲቀመር 368 አንቀጽ ሆኖ 8 ተርፎ ነበር። ከ8 ዓመት አንድ ተቀንሶ፣ ቀሪው በ11 ተባዝቶ ለ30 ሲከፈል 17 ተረፈ። ስለዚህ ያንጊዜ አበቅቴ ወርኅ 17፣ ጳጉሜን 5 ቀን ሆኖ ነበር።

ሰባተኛው ሺሕ ዘመን አልፎ አሁን ስምንተኛው ሺሕ ዘመን ከገባ 503 ዓመት አብቅቶ በ2004 ዓመት 504ኛው ዓመት ላይ እንገኛለን። ዓመተ ዓለሙም ከአዳም ተነሥተን ስንቆጥረው 7504 ዓመት ላይ ደርሰናል።

ከዚህ በላይ በተጻፈው ስሌት መሠረት እኛም የመስከረምን መባቻ ዕለት ከሰባቱ ዕለታት ለይቶ ለማውጣት ጥንተዮንን አስቀድመን ማወቅ ይገባናል። ለምሳሌ በ2004 ዓመተ ሥጋዌ የመስከረም መባቻ ዕለት ሰኞ እንደሆነ ሁላችንም አውቀናል። ነገር ግን ማወቃችን በልማድ ሳይሆን በርግጥ ሰኞ መሆኑ እንዴት ይታወቃል? የመስከረም መባቻ ሰኞ መሆኑ የታወቀው በ2004 ዓመት የተገኘው ጥንተዮን 6 ስለሆነ ነው። የተገኘበት መንገድም እንዲህ ነው፡-

2004 ዓመት በ28 ዐውደ ፀሐይ ሲቀመር 71 ዐውደ ፀሐይ ሆኖ 16 ዓመት ይተርፋል።

ከ16 ዓመት፡-

| | |
|---|---|
| ዕለተ ምርያ 16 x 1 = | 16 ቀን |
| ዕለተ ሠግር 16 ÷ 4 = | 4 ቀን |
| ድምር | 20 ቀን ይሆናል። |



www.ethiopianorthodox.org

20 ቀን በ7 ዐውደ ዕለት ሲቀመር 2 ሱባዔ ሆኖ 6 ይተርፋል:: ይህ ጥንተዮን ይባላል::

ስለዚህ በ2004 ዓመተ ሥጋዌ የተገኘው ጥንተዮን 6 ስለሆነ የመስከረም መባቻ ወይም ዕለተ ዮሐንስ ሰኞ መሆኑ እንዲህ ይታወቃል:: ይህ የአሠራር ሥርዓት የመስከረምን መባቻ ለማግኘት በየዓመቱ የሚሠራበት ቋሚ ሕግ ነው:: አይለወጥም::

ምሳሌ፣

7504 ዓመተ ዓለም ለ4 ሲከፈል ለያንዳንዱ ወንጌላዊ 1876 ደርሶ ምንም አይተርፍም:: ስለሆነም ወንጌላዊው ዮሐንስ መሆኑ በዚህ ይታወቃል:: ይህ 1876 መጠነ ራብዕት ለወንጌላውያን በዓመት ይቈጠራል:: ለ6ኛ ጳጉሜን ሲሆን ግን የሚቈጠረው በዕለት ነው:: ምክንያቱም ወንጌላዊ ባመት ጳጉሜን በዕለት ድርሻቸው አንድ ስለሆነ ነው::

የ2004 ዓመት ዕለተ ቀመርን ለማወቅ ከ7504 ዓመት ዕለተ ምርያንና ዕለተ ሠግርን ለይቶ አውጥቶና ደምሮ ለ7 ዐውደ ዕለት ይከፈላል:: ከሱባዔ የተረፈው ዕለተ ቀመር ይሆናል:: ያውም እንዲህ ነው የ7504 ዓመተ ዓለም:-

| | |
|---|---|
| ዕለተ ምርያ | 7504 ዕለት |
| ዕለተ ሠግር | 1876 ዕለት |
| ድምር | 9380 ዕለት:: |

9380 ዕለት በ7 ሲቀመር (9380÷7) =1340 ሱባዔ ይደርሳል:: ባለመትረፉ 7 ስለሆነ የ2004 ዓመት ዕለተ ቀመር ሰኞ መሆኑ በዚህ ይታወቃል:: ምክንያቱም ከጥንተ ቀመር ከማክሰኞ ዠምሮ ሲቈጠር ሰኞ 7ኛ ቀን ነውና::

የ2004 ዓመት ጥንተዮን ለማወቅ ለዕለተ ቀመር ከወጣው 7 ላይ 1 ሲቀነስ 6 ይተርፋል:: የተረፈው 6 ስለሆነ የ2004 ጥንተዮን ሰኞ ይሆናል:: ምክንያቱም ከጥንተዮን ከረቡዕ ዠምሮ ሲቈጠር ሰኞ 6ኛ ቀን ነውና::





የ2004 ዓመት ዕለተ ዮሐንስ (ጥንተ ዕለት) ለማወቅ ለዕለተ ቀመር በወጣው 7 ላይ 2 ዕለተ ጠቢባን ሲደመር 9 ይሆናል::በ7 ሲገድፉት 2 ስለሚተርፍ በ2004 ዓመት ዕለተ ዮሐንስ ሰኞ እንደሆነ በዚህ ይታወቃል:: ምክንያቱም ከጥንተ ዕለት ከእሑድ ዠምሮ ሲቈጠር ሰኞ ሁለተኛ ቀን ነውና::

## ዕለተ ምርያ

የፀሐይ ዐውደ ዓመት በ4 ክፍል ቢከፈል 91፣ 91 ዕለት ደርሶ አንዲት ቀን ትተርፋለች:: ወይም በ7 ቢከፈል 52 ሱባዔ ሆኖ አንዲት ቀን ትተርፋለች:: ዕለተ ምርያ የምትባል ይህች ናት:: ዕለተ ምርያ ማለት ዕለተ መድኃኒት፣ አዕዋዲት ማለት ነው:: ዕለተ መድኀኒት ማለት ጌታችን የተወለደባትን ቀን የምታስታውቅ ማለት ነው:: አዕዋዲትም ማለት ዓመቱን የምታዘዋውር የምታለዋውጥ ማለት ነው:: አምስተኛይቱ ጳጉሜን ዕለተ ምርያ አዕዋዲት ትባላለች:: 6ኛይቱ ጳጉሜን መጠነ ራብዕት ሠግረ ዮሐንስ ትባላለች:: ሠግረ ዮሐንስ ማለትም ዮሐንስ ተራምዶ የሚውልበት ቀን ማለት ነው::

ዳግመኛም ዕለተ ምርያን፣ አዕዋዲትን ለማወቅ የዓመቱ ዕለት በሱባዔ ሲቀመር 1 ዕለት ከ15 ኬክሮስ ይተርፋል:: ከ1 ዓመት 1 ዕለት ከ15 ኬክሮስ፣ ከ2 ዓመት 2 ዕለት ከ30 ኬክሮስ፣ ከ3 ዓመት 3 ዕለት ከ45 ኬክሮስ፣ ከ4ኛው ዓመት 5 ዕለት ከ60 ኬክሮስ ይገኛል:: 5ኛይቱ ጳጉሜን ዕለተ ምርያ፣ አዕዋዲት ትባላለች:: 60ው ኬክሮስ 1 መዓልት ሆኖ 6ኛ ጳጉሜን፣ መጠነ ራብዕት ወይም ሠግረ ዮሐንስ ይባላል::

## ዕለተ ጠቢባን

ያለ ትምህርት ጥበብ፣ ያለ ምርምር ርቀት አይገኝም:: ዕለተ ጠቢባን ማለት ጠቢባን መምህራን ተመራምረው ያገኙት ዕለት ማለት ነው:: ያውም እሑድና ሰኞ ነው:: ዳግመኛም ጠቢባን ሥላሴ ከዕለታት መርጠው ዓለምን የፈጠሩበት ዕለት ማለት ነው:: በኋላም ጌታችን የተፀነሰባት፣ ከሙታንም ተለይቶ የተነሣባት፣ ዓለምን የሚያሳልፍባት ዕለት ማለት ነው::



www.ethiopianorthodox.org

## ዐጽፌ አውራኅ

የፀሐይ ወር 30 ቀን ነው:: ይህ በ7 ሲቀመር 4 ሱባዔ ሆኖ 2 ቀን ይተርፋል:: ዐጽፌ አውራኅ የሚባል ይህ ነው:: ዐጽፌ አውራኅ ማለት የአንዱ ወር ከሌላው ወር ተደርቦ የሚቈጠር ማለት ነው:: ይህም የመስከረም ከጥቅምት፣ የጥቅምት ከኅዳር ጋር ይቈጠራል::

የመንፈቁ 12፣ የዓመቱ 24 ዐጽፌ አውራኅ ይሆናል:: ይህም በሠርቀ መዓልት ከዕለተ ጠቢባን፣ ከጥንተዮን ጋራ አንድ ሆኖ ይቈጠራል:: መቈጠሩም በተገኘ ጊዜ ነው:: መገኘቱም ከ28 ቀን በኋላ ነው:: እስኪገኝ ድረስ ግን በሠርቀ መዓልት፣ በዕለተ ጠቢባን፣ በጥንተዮን ይቈጠራል::

## ሰንበተ ክርስቲያንና ዕለተ በዓላት

ያለፈውንና የሚመጣውን ዕለተ በዓልና ሰንበተ ክርስቲያንን ለማወቅ በየዓመቱ የሚወጣውን ጥንተዮን በየወሩ ያለውን ዐጽፌ አውራኅ ከወሩ መባቻ ዝምሮ እስከ ደረሱበት ያለውን ሠርቀ መዓልት፣ ሁለቱን ዕለተ ጠቢባን እሊህ አራቱን አንድ አድርጎ ቈጥሮ ድምሩ በ7 ሲቀመር 1 ቢተርፍ እሑድ አሚሩ፣ 2 ቢተርፍ ሰኞ ሰኑዩ፣ 3 ቢተርፍ ማክሰኞ ሠሉሱ፣ 4 ቢተርፍ ሮብ ረቡዑ፣ 5 ቢተርፍ ኀሙስ ኀሙሱ፣ 6 ቢተርፍ ዓርብ ሰዱሱ፣ 7 ቢተርፍ ቀዳም ሰቡዑ:- ሰንበተ ክርስቲያን ወይም ዕለተ በዓል ይባላል:: አሚሩ በሦስት ወገን ይነገራል:: ይህም *አመ አሚሩ፣ አመ ዐሡሩ ወአሚሩ፣አመ ዕሥራ ወአሚሩ* ማለት ነው::

## ሰንበተ ሰንበታት

ሰንበተ ሰንበታት ማለት ጸሎትን ወደ እግዚአብሔር የሚያሳርጉበት ዕለት ነው:: *ዝኒ ዘያዐርጉ ቦቱ ጸሎተ ኀበ እግዚአብሔር፣* እንዲል:: የሰንበተ ሰንበታትን ቀን ለማወቅ ሥርዓቱ እንዲህ ነው:: ዕለተ ዮሐንስ ሰኞ ቢሆን ከዚያው ዠምሮ በሌላው ቀን ቢሆን ካለፈው ወይም ከሚመጣው ሰኞ ዠምሮ ቈጥሮ በ133 በ133 ቀን ይውላል:: ዕለቱም እሑድ ነው:: በዓመት ሦስት ጊዜ ይውላል:: 3ኛው ግን በ99 ዕለት ብቻ ይውላል::



www.ethiopianorthodox.org



በዚሁ አንቀጽ ሰንበተ ሰንበታት ማለት በዓመቱ ከሚውሉት ሌሎች ሰንበታት ተለይታ በመቶ ሠላሳ ሦስት ቀን ካህናት ጸሎትን ወደ እግዚአብሔር የሚያሳርጉባት ዕለተ እሑድ ናት:: ይህችም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ለሚመጣባት ሰንበተ ሰንበታት አምሳል ናት:: የሰንበት ሰንበት ማለት ነው::

## ሰባተኛዪቱ ሰንበትና እሑድ ሰንበት

ሰባተኛዪቱ ሰንበት ቀድሞ እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ፣ በኋላም ዓለም የሚድንበትን ሥራ ሁሉ ፈጽሞ ያረፈባት ዕለት ስለሆነች፣ ምእመናን ሁሉ ከነቢያት ማኅበር ጋር ሆነው ያከብሯታል፤ ይዘምሩላታል::

እሑድ ሰንበትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት ዕለት ስለሆነች፣ ክርስቲያኖች ሁሉ ከማኅበረ ሐዋርያት ጋር ሆነው በየሳምንቱ ያከብሯታል፤ ይዘምሩላታል:: የዚህን ዓለም ተድላ ደስታ ንቆ፣ እግዚአብሔርን በማምለክ እነዚህን ሁለት ሰንበታት በቅን ልቡና፣ በንጹሕ ኅሊና የሚያከብር፣ ዳግመኛ ጌታ ወደሚመጣባት ሰንበተ ሰንበታት በክብር በመላእክትም ዝማሬ ይገባል:: ይህች ዳግም ምጽአት የሚሆንባት ሰንበተ ሰንበታት፣ ፀሐይና ጨረቃ፣ ጎሕና ምሽት፣ ቀንና ሌሊት፣ በጋና ክረምት የማይፈራረቁባት ዕለተ እግዚአብሔር ናት::

እስራኤል ከግብጽ ምድር በወጡበት ጊዜ እስራኤልና ግብጻውያን በአንድ ቦታ ሳሉ ለግብጻውያን ጨለማ እንደሆነባቸው ለእስራኤል ግን ብርሃን እንደሆነላቸው፤ ያንጊዜ እንዲሁ ለበደለኛው የኃጢአቱ ጨለማ እንደ ዕውር ያደነባብረዋል፤ ለጻድቁም ከበጎ ሥራው የተነሣ ብርሃን እንደመብረቅ ብልጭታ ያበራለታል::

ይህች ሰንበተ ሰንበታት በቀኖች ሱባዔ አትቈጠርም፤ በኢዮቤልዩም ሰንበታት (ሱባዕያት) አትስፈርም፤ የሰንበታት ሰንበት ናትና::, እግዚአብሔር የንጉሦች ንጉሥ፣ የጌቶች ጌታ እንዲባል፤ እንዲሁም እርስዋ ለዘለዓለሙ ጸንታ የምትኖር ስለሆነች የሰንበታት ሰንበት ትባላለች::



www.ethiopianorthodox.org

ይች ሰንበተ ሰንበታት የምትባል ዕለት፣ ቀድሞ እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረባት፣ በኋላም የተፀነሰባት፣ ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት፣ ዳግመኛም ዓለምን ለማሳለፍ የሚመጣባትና ሐዲስ ሰማይ፣ ሐዲስ ምድር የሚገለጽባት ዕለተ እሑድ ናት:: ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር ንትፌሣሕ ወንትሐሠይ ባቲ፤(ይህች ዕለት እግዚአብሔር ፍጥረትን የፈጠረባት ናትና በርስዋ ፈጽሞ ደስ ይበለን) መዝ. 117፣ ራእ. 21፥1-27፣ 2ኛ ጴጥ. 3፥13፤ መጽሐፈ ምሥጢር ገጽ 324-25::

## ሰንበተ ረቡዕ

ሰንበተ ረቡዕ ማለት ጸሎትን ወደ እግዚአብሔር የሚያሳርጉበት ዕለት ነው:: ገዘኒ ዘያዐርጉ ቦቱ ጸሎተ ኀበ እግዚአብሔር፤ እንዲል የሰንበተ ረቡዕን ቀን ለማወቅ ሥርዓቱ እንዲህ ነው:: ዕለተ ዮሐንስ ኀሙስ ቢሆን ከዚያ ዠምሮ በሌላ ቀን ቢሆን ካለፈው ወይም ከሚመጣው ኀሙስ ዠምሮ ቈጥሮ በ91፣ በ91 ዕለት ይውላል:: ዕለቱም ረቡዕ ነው:: በዓመት 4 ጊዜ ይውላል::

## ርኅወ ሰማይ

ርኅወ ሰማይ ማለት፣ የሰማይ መስኮት መከፈትን ያመለክታል:: ዕለቱም በውሀና በዘይት ላይ የሚጸልዩበት፣ ውሀውንም ዘይቱንም ለፈውስና ለረድኤት የሚቀቡበትና የሚጠጡበት ዕለት ነው:: ገዘኒ ዘይጼልዩ ቦቱ ላዕለ ማይ ወዘይት ወይትቀብዑ ወይስትዩ ለፈውስ ወለረድኤት፤ እንዲል:: የርኅወ ሰማይ ዕለት ለማወቅም ሥርዓቱ እንዲህ ነው:: ከጳጉሜን 2 ወይም 3 ቀን ዠምሮ ቈጥሮ በ52፣ በ52 ዕለት ይውላል:: በዓመት 7 ጊዜ ይውላል::

## 2. ዐውደ ጳጉሜን በሰንበተ ወንጌላውያን

አራቱ ወንጌላውያን በዐውደ ጳጉሜን በሚመላለሱ አራት ዓመታት ስማቸው ሲጠራ የሚኖረው የክርስቶስን ሥርዓተ ትስብእት ስለጻፉና ስላስተማሩ፣ በአራቱ መዓዝነ ዓለምም ወንጌልን ስለሰበኩ ነው እንጂ እንዲያው ለከንቱ የተጠሩ አይደለም:: እነዚህ



www.ethiopianorthodox.org



ወንጌላውያን አንዱን ዐቢይ ቀመር ከአራት ክፍል አድርገው በተካፈሉት ጊዜ ለያንዳንዳቸው በዘመን 133፣ በቀመር 7 ይደርሳቸዋል:: አራቱም ክፍሎች ሰንበታት ይባላሉ:: ሰንበት ማለት በዚሁ ገጽ ሱባዔ ማለት ነው::

ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከአዳም ዠምሮ እስከ ኅልፈተ ዓለም ድረስ መዠመርያይቱ ክፍለ ሰንበት በማቴዎስ ስም ስለተሰየመች ሰንበተ ማቴዎስ ትባላለች:: ሁለተኛይቱ ክፍለ ሰንበት በማርቆስ ስም ስለተሰየመች ሰንበተ ማርቆስ፣ ሦስተኛይቱ ክፍለ ሰንበት በሉቃስ ስም ስለተሰየመች ሰንበተ ሉቃስ አራተኛይቱ ክፍለ ሰንበት በዮሐንስ ስም ስለተሰየመች ሰንበተ ዮሐንስ ትባላለች:: እያንዳንድዋ ክፍለ ሰንበት 7 አናቅጸ አበቅቴን ትፈጽማለች:: እያንዳንድዋ አንቀጸ አበቅቴም 19 ምዕዋደ ዓመትን ትፈጽማለች:: የአንቀጸ አበቅቴ ሁሉ መነሻ አልቦ አበቅቴ ነው:: ፍጻሜውም 18 አበቅቴ ነው::

ዳግመኛም አራቱ ወንጌላውያን ያራቱ ኪሩቤል አምሳል ናቸው:: ቤተ ክርስቲያንም የመንበረ መንግሥት አምሳል ናት:: እግዚአብሔር አራት ማዕዘን ባለው በኪሩቤል መንበር ላይ በሰማየ ሰማያት እንዲቀመጥ፣ በምድርም ባራቱ ወንጌላውያን ማዕዘንነት በተሠራች ቤተ ክርስቲያን ቀመር ራስ ላይ ይቀመጣል:: ኪሩቤል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ እንዲያመሰግኑ፣ የመለኮትን ቃል የሚናገሩ አራቱ ወንጌላውያንም ከሕያው አምላክ ልጅ አንደበት ከሚመነጭ ጥሩ የምስጋና ፈሳሽን እየቀዱ ዓመተ ዓለምን ባራት ክፍል መድበው በማጠጣት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ይኖራሉ:: አርባዕቱ ወንጌላውያን እለ ይትናገሩ ቃለ ዘመለኮት ወይቀድሑ አስራበ ስብሐት ጽሩየ እምነቅዐ አፉሁ ለወልደ አምላክ ሕያው፤ እንዲል (ሰዓታት ዘሌሊት፤መጽሐፈ ምሥጢር ገጽ 271)

## አምሳልነታቸው

ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም ብሎ የጻፈና ያስተማረ ማቴዎስ በገጸ ሰብእ ይመሰላል:: አዲስ ትምህርትን በማስተማር የግብጽ ሰዎችን ያስደነገጠና ያስፈራ ማርቆስ በገጸ አንበሳ ይመሰላል:: ስለሚሰዋው ፍሪዳ ያስተማረና የጻፈ ሉቃስ በገጸ ላሕም ይመሰላል:: ቃል ሥጋ ሆነ ብሎ ረቂቅ ምሥጢርን ያስተማረ ዮሐንስ በገጸ ንስር ይመሰላል::

## 3. የዐውደ አበቅቴ ትንተና

አበቅቴ የዘመን ቁጥር ትርፍ ማለት ነው።በሌላ አነጋገርም ተረፈ ዓመት፣ ተረፈ ጉልቊም ይባላል። በፀሐይ ዓመት 365 ቀንና በጨረቃ ዓመት 354 ቀን መካከል ያለው የ11 ቀን ልዩነት አበቅቴ ይባላል። መጥቅዕ ማለት አዋጅ መንገርያ ነጋሪት ማለት ነው። ተዘዋዋሪዎቹ አጽዋማትና በዓላት የሚታወጁት፣ የሚነገሩት በመጥቅዕ አማካይነት ነው። ዘሌዋ.23:4፤24፤ኢዮኤ. 2:15።

የመጥቅዕ ትርጓሜው እንዲህ ከሆነ በዘመነ ብሉይ የተሠሩ አጽዋማት በዓላት ከሚውሉባቸው ዕለታት ተለይቶ ዕለቱ ስለምን መጥቅዕ ተባለ ቢሉ፣ ቀድሞ እስራኤል ዓመተ ሥጋዌን፣ ዓመተ ኅድገትን ለመማር ወደ ደብተራ ኦሪት ይገቡ ዘንድ ሌዋውያን ነጋሪት (መጥቅዕ) የሚመቱበት ስለሆነ ነው። ዳግመኛም መጥቅዕ በተመታ ጊዜ ሰዉን የሩቁን ከቅርብ፣ የቅርቡን ከሩቅ ሰብስቦ በአንድ ቦታ እንዲያስገኝ እርሱም አጽዋማትንና በዓላትን ሰብስቦ ያስገኛልና። ይህም ነነዌ፣ በአተ ጾም፣ ጾመ ሐዋርያት ሰኞ፤ ረክብ፣ ምሕላ ድኅነት ረቡዕ፤ ዕርገት ኀሙስ፤ ስቅለት ዓርብ፤ ደብረ ዘይት፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ ጰራቅሊጦስ እሑድ መዋላቸውን ያመለክታል። *ወበሂለ መጥቅዕሂ አስተጋባኢ ብሂል እስመ ከመ መጥቅዕ ዘብርት፣ ወዘሐፂን፣ ዘዕፅ ወዘእብን ያስተጋብእ ሰብአ ከማሁ ውእቱኒ ያስተጋብእ በዓላተ ወአጽዋማተ ዘኵሎን ዕለታት ወዓመታት፤* እንዲል (መርሐ ዕዉር)።

### የቀመር መዠመርያ

የቀመር ሁሉ መዠመርያ አልቦ አበቅቴ ነው። ፍጻሜው ግን 18 አበቅቴ ነው። እንዲህ ከሆነ አበቅቴ አልቦ በሆነ ጊዜ ሠርቀ ሌሊት በመዓልትና በሕጸጸ አውራኅ እንዴት ይቈጠራል ቢሉ? ከተገኘ በኋላ አለመግባቱን መናገር ነው፡- *ወሶበ ኮነ አልቦ አበቅቴ አሜሃ ይትሐሰብ ሠርቀ ሌሊት በመዓልት ወበመናፍቅ ዘውእቱ ሕጸጸ አውራኅ፤* እንዲል።

ለአበቅቴ ዐሥራ አንድ፣ ዐሥራ አንድ መንሳት ስለምን ነው ቢሉ? የፀሐይ ዐውደ ዓመት 365 ዕለት ነው። ከዚህ ጨረቃ 354 ዕለት በኼደችለት ጊዜ 11 ዕለት ይተርፋልና ስለዚህ ነው። ከዚህ በኋላ



www.ethiopianorthodox.org



ፀሐይ ዐውደ ዓመቱን ሳያደርስ፣ ጨረቃ ከ11 ዕለታት አስቀድሞ ሌላውን ዓመት ይዠምርበታል። *ወእምዝ ዘእንበለ ያብጽሕ ፀሐይ ዐውደ ዓመት ይዌጥን ቦቱ ወርኅ ካልአ ዓመተ እምቅድመ ዐሠርቱ ወአሐዱ ዕለት ዘውእቶሙ 6 ሕጸጸ አውራኅ ወ5ቱ ጳጉሜን፤* እንዲል (መርሐ ዕዉር)። 11 ዕለታትም የ6 ሕጸጽና የጳጉሜን 5 ድምር ናቸው።

### የአበቅቴ አዋጅ

ልደተ አበቅቴ በኋላ ይዘረዘራል። አዋጁ እንዲታወቅ ግን ከዚህ ይነገራል። ልደተ አበቅቴ ከነሐሴ 8 ቀን በታች አይወርድም። ከጳጉሜን 5 ቀን በላይ አይወጣም። ከነሐሴ 30 ቀን 7 ቢቀነስ 23 ቀን ይተርፋል። 23 በ5 ጳጉሜን ላይ ሲደመር 28 ይሆናል። በዚህ ሲመላለስ ይኖራል። ልደተ አበቅቴ ከነሐሴ 8 በታች አይወርድም። ከጳጉሜን 5 በላይ አይወጣም።

6ኛው ጳጉሜን ግን እንደ አምስተኛው ጳጉሜን ለያንዳንዱ ወንጌላዊ የማይደርስ ስለሆነ አራቱ ወንጌላውያን በሰዓት በኬክሮስ ከአራት አድርገው ይካፈሉታል እንጂ ከአበቅቴ ገብቶ አይቈጠርም። አከፋፈሉም እንዲህ ነው፡-

### ልደተ አበቅቴ

1ኛ ዓመት አልቦ አበቅቴ በሆነ ጊዜ የጨረቃ ዐውደ ዓመት በመስከረም መባቻ ይዠመራል። ይህም ነሐሴ 24 ቀን በመፈጸሙ ይታወቃል። ከመስከረም እስከ ሐምሌ 330 ዕለት ነው። በዚሁ ላይ ከነሐሴ 24 ሲደመርበት 354 ዕለት ይሆናል። ይህ የጨረቃ ዐውደ ዓመት ነው። ያንጊዜ ልደተ አበቅቴ ነሐሴ በባተ በ25ኛው ቀን ይሆናል። ከነሐሴ 30 ቀን 24 ሲቀነስ 6 ይተርፋል። በዚሁ ላይ 5 ጳጉሜን ሲደመር 11 ይሆናል። ይህ የመዠመርያው ዓመት አበቅቴ ነው።

ፀሐይ ከጨረቃ የምታተርፈው 11 ዕለት ብቻ አይደለም። 22 ኬክሮስ፣ 1 ካልዒት፣ 37 ሣልሲት፣ 52 ራብዒት 48 ኃምሲት ጭምር ነው እንጂ። ድሜጥሮስ ግን አጽዋማትና በዓላት የሚውሉባቸው ዕለታትንና አውራኀን ለማግኘት 11 ዕለታትን ብቻ አድርጎ የቀሩትን አልሻቸውም ነበር። አቡሻህር ግን በኋላ ሠርቀ

ሌሊትና ልደተ ወርኅ ባይተካከልላት ከኬክሮስ እስከ ኃምሲት ያሉትን ዕለታት አጠራቅሞ ዕለታትን አገኘ:: ስማቸውም ትራፋተ ዐውድ አላቸው:: ከዐውደ አበቅቴ የተረፉ ማለት ነው:: እሊህ ዕለታት እስከ ዛሬ ድረስ 4 ዕለታት ሆነዋል:: ባለው አበቅቴ ላይ እሊህን ዕለታት ካልጨመሩ እውነተኛ ልደተ ወርኅና ሠርቀ ሌሊት አይገኝም:: ስለዚህ ባለው አበቅቴ ላይ አራቱን ዕለታት መጨመር የግድ ነው::

2ኛ ዓመት ከመስከረም እስከ ሐምሌ 330 ዕለት ነው:: በዚሁ ላይ 11 አበቅቴና 13 ከነሐሴ ሲደመር 354 ይሆናል:: ይህ የጨረቃ ዐውደ ዓመት ነው:: ያንጊዜ ልደተ አበቅቴ ነሐሴ በባተ በ14ኛው ቀን ይሆናል:: ከነሐሴ 30 ቀን 13 ሲቀነስ 17 ይተርፋል:: በዚሁ ላይ 5 ጳጉሜን ሲደመር 22 ይሆናል:: ይህ የሁለተኛው ዓመት አበቅቴ ነው:: አበቅቴ ከ20 በላይ ሲሆን ሠግር ነው::

3ኛ ዓመት ከመስከረም እስከ ሐምሌ 330 ዕለት ነው:: በዚሁ ላይ አበቅቴ 22፣ 30 ቀን ነሐሴ፣ ከጳጉሜ 2 ሲደመሩ 384 ዕለት ይሆናሉ:: ከዚሁም 30ው የሠግር ወር ብሎ 354ቱ ዕለት የጨረቃ ዐውደ ዓመት ይሆናል:: ያንጊዜ ልደተ አበቅቴ ጳጉሜን በባተ በ3ኛው ቀን ይሆናል:: ከጳጉሜን 5 ቀን 2 ሲቀነስ 3 ይተርፋል:: ይህ የሦስተኛው ዓመት አበቅቴ ነው:: ድምሩ በዝቶ 384 ሲሆን 30ው ሠግር፣ የቀረው የጨረቃ ዐውደ ዓመት ይባላል:: ድምሩ 354 ሲሆን ግን እንዳለ ተይዞ እስከ አልቦ ድረስ ይቈጠራል:: በ5 ዓመት፣ በ8 ዓመት፣ በ10ኛው ዓመት ሠግር ይሆናል:: በ10ኛው ዓመት 20 አበቅቴ ይገኛል:: አበቅቴ ከ20 በላይ ሲሆን ሠግር ነው::

11ኛው ዓመት ከመስከረም እስከ ሐምሌ 330 ዕለት ነው:: በዚሁ ላይ አበቅቴ 20፣ 30 ነሐሴ፣ ከጳጉሜን 4 ሲደመር 384 ዕለት ይሆናል:: ከዚህ 30ው የሠግር ወር ብሎ 354ቱ የጨረቃ ዐውደ ዓመት ይሆናል:: ያንጊዜ ልደተ አበቅቴ ጳጉሜን በባተ በ5ኛው ቀን ይሆናል:: ከጳጉሜን 5 ቀን 4 ሲቀነስ 1 ይተርፋል:: የ11ኛው ዓመት አበቅቴ ይህ ነው:: በዚህ ጊዜ ኢየዓርግ ነው:: በዚህ ስሌት እስከ 18 ዓመት ይቈጠራል:: በ18ኛው ዓመት 18 አበቅቴ ይገኛል::

19ኛ ዓመት ከመስከረም እስከ ሐምሌ 330 ዕለት ነው:: በዚሁ ላይ 18 አበቅቴ 6 ከነሐሴ ሲደመር 354 ዕለት ይሆናል:: ይህ የጨረቃ ዐውደ ዓመት ነው:: ያንጊዜ ልደተ አበቅቴ ነሐሴ በባተ በ7ኛው ቀን ይሆናል:: ልደተ አበቅቴ ከነሐሴ 8 አይወርድም ተብሎ ነበር:: ወደ





7 ስለምን ወረደ ቢባል አልቦ አበቅቴ የሚሆንበት ዓመት ስለሆነ ነው ይባላል:: ከነሐሴ 30 ቀን 6 ሲቀነስ 24 ይተርፋል:: በዚሁ ላይ ጳጉሜን ሲደመር 29 ይሆናል:: ይህ ሕጹጽ ወርኅ ተብሎ ከሠግር ወሮች ጋር ይቈጠራል:: ያንጊዜ አልቦ አበቅቴ ይሆናል:: ከዚህ ከአንዱ ንኡስ ቀመር 7 የሠግር ወር ይገኛል:: ከሁለት ንኡስ ቀመር 1 ዓመት ከ2 ወር ይገኛል:: ከፍጥረተ ዓለም እስከ ዛሬ ድረስ እንዲህ እየተቈጠረ ቢሰላ ጨረቃ ከፀሐይ የምታርፈው ዘመን ይታወቃል::

አልቦ በሆነ ባመቱ 11 አበቅቴ ይሆናል:: በሁለተኛው ዓመት 22 አበቅቴ፣ በሦስተኛው ዓመት 3 አበቅቴ፣ በ4ኛው ዓመት 14 አበቅቴ፣ በ5ኛው ዓመት 25፣ በ6ኛው ዓመት 6፣ በ7ኛው ዓመት 17፣ በ8ኛው ዓመት 28፣ በ9ኛው ዓመት 9፣ በ10ኛው ዓመት 23፣ በ14ኛው ዓመት 4፣ በ15ኛው ዓመት 15፣ በ16ኛው ዓመት 26፣ በ17ኛው ዓመት 7፣ በ18ኛው ዓመት 18 አበቅቴ ይሆናል:: በ19ኛው ዓመት 29 አበቅቴ ይገኛል:: ይህ አልቦ ነው:: ከመመላለሻው ተላልፎ በሕጹጽ ወርኅ ልክ ስለሆነ ባለው ይያዛል:: ወደ 20ኛው ዓመት አይተላለፍም:: *ትገድፎ ወኢታመጽእ ኀበ ዕሰራ እስመ ኮነ መጠነ ጉልቄ ወርኀ ሕጹጽ*፤ እንዲል:: ባለው አበቅቴ ላይ 11 ቢደመር የሚመጣው ዓመት አበቅቴ፣ 19 ቢደመር ያለፈው ዓመት አበቅቴ ይታወቃል:: አበቅቴና መጥቅዕ አንድ ላይ ቢደመሩ 30 ይሆናሉ:: ከ30 አይወርዱም፣ ከ30 አይበልጡም::

## በዓለ መጥቅዕ

አልቦ አበቅቴ በኾነ ጊዜ በዓለ መጥቅዕ በመስከረም ይውላል:: በዚህ ጊዜ አጽዋማትና በዓላት መስከረም በባተ በ30ኛው ዕለት ተውሳክ ይወጣሉ:: ተውሳኩ መባጃ ሐመር ሆኖ ይባጃል:: ሠርቀ ሌሊትም በሕጸጽና በሠርቀ መዓልት ብቻ ይወጣል:: በ11 አበቅቴ ጊዜ በዓለ መጥቅዕ መስከረም 19 ቀን ይሆናል:: በ22 አበቅቴ ጊዜ በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት 8 ቀን ይሆናል:: በ3 አበቅቴ ጊዜ በዓለ መጥቅዕ መስከረም 27 ቀን ይውላል:: ሁሉም እንዲህ እየተቀመረ እስከ አልቦ ድረስ ይቈጠራል:: በ17 አበቅቴ ጊዜ በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት 13 ቀን ይሆናል:: በዚህ ጊዜ ኢየዓርግ ነው:: ይህን ጊዜ አጽዋማትና በዓላት በላዕላይ ቀመራቸው ይውላሉ:: ይሁን እንጂ መጥቅዕ የዋለበት ቀን ቀዳም (ቅዳሜ) ካልሆነ ላዕላይ ቀመር አይሆንም:: በ15 አበቅቴ ጊዜ በዓለ መጥቅዕ መስከረም 15 ቀን ይሆናል:: በዚህ ጊዜ ኢይወርድ ነው:: ይህን ጊዜ አጽዋማትና

www.ethiopianorthodox.org

ዕላት በታሕታይ ቀመራቸው ይውላሉ:: በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ቀን ዓርብ ካልሆነ ግን ታሕታይ ቀመር አይሆንም:: በዓለ መጥቅዕ ከመስከረም 15 በታች አይወርድም:: ከጥቅምት 13 በላይ አይወጣም:: ከመስከረም 16፣ ከጥቅምት 13 ቀን ሲደመር 29 ይሆናል:: በዓለ መጥቅዕ በዚህ ሲመላለስ ይኖራል:: በዘመነ ብሉይ የተሠሩ አጽዋማትና በዓላት መመላለሻቸው 29 ነው የሚባለው ስለዚህ ነው::

በዓለ መጥቅዕ የሚውልባቸው ዕለታት ግን 19 ናቸው:: ከእነርሱም 11ዱ በመስከረም 8ቱ በጥቅምት የሚገኙ ናቸው:: በመስከረም ከ15 በላይ በ17፣ በ20፣ በ22፣ በ25፣ በ28 በዓለ መጥቅዕ አይውልባቸውም:: ከ16 እሊህ 5 ሲቀነሱ 11 ይቀራል:: 11ዱ በመስከረም ይገኛሉ የተባሉት እሊህ ናቸው:: በጥቅምት ከ13 በታች በ1፣ በ3፣ በ6፣ በ9፣ በ11 መጥቅዕ አይውለባቸውም:: ከ13 እሊህ 5 ቢቀነሱ 8 ይተርፋል:: 8 በጥቅምት ይገኛሉ የተባለው ይህ ነው::

## ተረፈ መጥቅዕ

ባለፈውና በሚመጣው መጥቅዕ መካከል አንዳንድ ጊዜ 19፣ አንዳንድ ጊዜ 49 ይገኛል:: *ማእከለ መጥቅዕ ዘኀለፈ ወማእከለ መጥቅዕ ዘይመጽእ ቦ ጊዜ ዘበበዐሥርቱ ወተሰዓቱ ይትረከብ፣ ወቦ ጊዜ ዘበበአርብዓ ወተሰዓቱ ይትረከብ፤* እንዲል:: 19 ቢገኝ ባለው ይያዛል:: 49 ቢገኝ 30ው ተቀንሶ 19ኙ ይያዛል:: ለመጥቅዕ 19 መንሣት ስለዚህ ነው::

በአልቦ አበቅቴ ጊዜ በዓለ መጥቅዕ መስከረም በባተ በ30ኛው ቀን ይውላል:: አልቦ በሆነ ባመቱ በዓለ መጥቅዕ መስከረም 19 ይውላል:: ከጥቅምት እስከ ነሐሴ 11 ወር ነው:: ከመስከረም 30 ቀን 19 ሲቀነስ 11 ይተርፋል:: ማእከል የተባለ ይህ ነው:: ማእከል ማለት ተረፈ መጥቅዕ ማለት ነው:: ከጥቅምት እስከ ነሐሴ 11 ወር ነው::

አልቦ በሆነ በ2ኛው ዓመት በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት 8 ቀን ይውላል:: ማእከል (ወይም ተረፈ መጥቅዕ) የተባለው 11ና 8 ከጥቅምት ቢደመር 19 ይሆናል:: አንዳንድ ጊዜ 19 ይገኛል ያለው ይህ ነው:: *ቦ ጊዜ ዘበበ ዐሠርቱ ወተሰዓቱ ይትረከብ፤* እንዲል ለመጥቅዕ 19 መንሣት ስለዚህ ነው:: ከጥቅምት 30 ቀን 8 ሲቀነስ





22 ይተርፋል:: ማእከል የተባለ ይህ ነው:: ከጥቅምት እስከ ነሐሴ 11 ወር ነው::

በ3ኛው ዓመት በዓለ መጥቅዕ መስከረም 27 ይውላል:: ማእከል የተባለው 22ና 27 ከመስከረም ሲደመር 49 ይሆናል:: አንዳንድ ጊዜ 49 ይገኛል ያለው ይህ ነው:- *ቦ ጊዜ ዘበበ አርብዓ ወተሰዓቱ ይትረከብ፤* እንዲል:: ከ49ኙ 30ው ተቀንሶ 19 ይያዛል:: ለመጥቅዕ 19 መንሣት ስለዚህ ነው:: ከመስከረም 30 ቀን 27 ሲቀነስ 3 ይተርፋል:: ማእከል የተባለው ይህ ነው:: ከጥቅምት እስከ ነሐሴ 11 ወር ነው:: እንዲህ እየተቀመረ እስከ አልቦ ድረስ ይቈጠራል::

በ4ኛው ዓመት በዓለ መጥቅዕ መስከረም 16 ቀን ይውላል:: በ5ኛው ዓመት ጥቅምት 5 ቀን፤ በ6ኛው ዓመት መስከረም 24 ቀን፤ በ7ኛው ዓመት ጥቅምት 13 ቀን፤ በ8ኛው ዓመት ጥቅምት 2 ቀን፤ በ9ኛው ዓመት መስከረም 21 ቀን፤ በ10ኛው ዓመት ጥቅምት 10፤ በ11ኛው ዓመት መስከረም 29 ቀን፤ በ12ኛው ዓመት መስከረም 18 ቀን፤ በ13ኛው ዓመት ጥቅምት 7 ቀን፤ በ14ኛው ዓመት መስከረም 26 ቀን፤ በ15ኛው ዓመት መስከረም 15 ቀን፤ በ16ኛው ዓመት ጥቅምት 4 ቀን፤ በ17ኛው ዓመት መስከረም 23 ቀን፤ በዓለ መጥቅዕ ይሆናል:: ከመስከረም 30 ቀን 23 ሲቀነስ 7 ይተርፋል:: ማእከል የተባለ ይህ ነው:: ከጥቅምት እስከ ነሐሴ 11 ወር ነው::

በ18ኛው ዓመት በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት 12 ቀን ይውላል:: ማእከል የተባለው 7 ና 12 ከጥቅምት ሲደመር 19 ይሆናል:: አንዳንድ ጊዜ 19 ይገኛል ያለው ይህ ነው:: *ቦ ጊዜ ዘበበ ዐሠርቱ ወተሰዓቱ ይትረከብ፤* እንዲል ከጥቅምት 30 ቀን 12 ሲቀነስ 18 ይተርፋል:: ተረፈ መጥቅዕ (ማእከል) የሚባል ይህ ነው:: ከጥቅምት እስከ ነሐሴ 11 ወር ነው::

በ19ኛው ዓመት አበቅቴ 29 ይሆናል:: በዓለ መጥቅዕ መስከረም በባተ በ30ኛው ቀን ይውላል:: በዚህ ጊዜ መጥቅዕ ሙሉ ወር ሆኖ ወደ 11 ወር ይጨመራል:: ምሉ ዓመት ሆኖ ይቀራል:: ያንጊዜ አልቦ መጥቅዕ ይባላል:: 29ኙም አበቅቴ ሕጹጽ ወርኀ ሆኖ ይቀራል:: በዚህ ጊዜ አልቦ አበቅቴ ይሆናል:: ባለው መጥቅዕ ላይ 19 ቢጨመር የሚመጣው 11 ቢጨመር ያለፈው መጥቅዕ ይታወቃል::



www.ethiopianorthodox.org

## የአንድ ዐውደ አበቅቴ ጓዝ

| ዓመተ አበቅቴ | አበቅቴ | መጥቅዕ | ልደተ አበቅቴ |
|---|---|---|---|
| 1ኛ | አልቦ(0) | መስከረም 30 | መባቻ(0) |
| 2ኛ | 11 | መስከረም 19 | ነሐሴ 25 |
| 3ኛ | 22 | ጥቅምት 8 | ነሐሴ 14 |
| 4ኛ | 3(33) | መስከረም 27 | ጳጉሜን 3 |
| 5ኛ | 14(44) | መስከረም 16 | ነሐሴ 22 |
| 6ኛ | 25(55) | ጥቅምት 5 | ነሐሴ 11 |
| 7ኛ | 6(65) | መስከረም 2 | ነሐሴ 30 |
| 8ኛ | 17(77) | ጥቅምት 13 | ነሐሴ 19 |
| 9ኛ | 28(88) | ጥቅምት 2 | ነሐሴ 8 |
| 10ኛ | 9(99) | መስከረም 21 | ነሐሴ 27 |
| 11ኛ | 20(110) | ጥቅምት 10 | ነሐሴ 16 |
| 12ኛ | 1(121) | መስከረም 29 | ጳጉሜን 5 |
| 13ኛ | 12(132) | መስከረም 18 | ነሐሴ 24 |
| 14ኛ | 23(143) | ጥቅምት 7 | ነሐሴ 13 |
| 15ኛ | 4(154) | መስከረም 26 | ጳጉሜን 2 |
| 16ኛ | 15(165) | መስከረም 15 | ነሐሴ 21 |
| 17ኛ | 26(176) | ጥቅምት 4 | ነሐሴ 10 |
| 18ኛ | 7(187) | መስከረም 23 | ነሐሴ 29 |
| 19ኛ | 18(198) | ጥቅምት 12 | ነሐሴ 18 |

## ዕለተ መጥቅዕ

መጥቅዕ ማለት 7ኛ ወር 7ኛ ጨረቃ ማለት ነው:: ዝንቱ ወርኅ ይኩንክሙ ቀዳማየ አውራኀ፤ ተብሏልና:: ከሚያዝያ ዠምሮ ጥቅምት 7ኛ ወር ነው:: የመጥቅዕ ትርጓሜ እንዲህ ከሆነ ዕለቱ ስለምን መጥቅዕ ተባለ ቢባል ኦሪት፣ አመ ርእሰ ሳብዕ ሠርቀ ወርኅ ግበሩ መጥቅዓ፤ ትላለችና :: በዚህ ቀን ሌዋውያን ዓመተ ኅድገትን ለመናገር ሰው ሰብስበው ነጋሪት ይመቱበት ነበር:: ዛሬም መምህራን በዚህ ቀን ሰው ሰብስበው አጽዋማትን በዓላትን ይናገሩበታልና ጊዜያ ቦታ ስለገባ ዕለቱ መጥቅዕ ተባለ::



www.ethiopianorthodox.org



## የመጥቅዕ አዋጅ

ከ14 በላይ ያለ መጥቅዕ በመስከረም፣ ከ14 በታች ያለ መጥቅዕ በጥቅምት ይውላል:: መጥቅዕ ከዕለታት ተውሳክ ጋር ተደምሮ ሲቈጠር ከ30 ቢተርፍ ትርፉ መባጃ ሐመር ሆኖ ይባጃል:: አማራጭ የሚሆን ሌላም መንገድ አለ:: ይህም ከ2 እስከ 13 ያለ መጥቅዕ በጥቅምት ላይ ይወድቃል:: ከ15 በላይ ያለ መጥቅዕ ዳግሞ በመስከረም ላይ ይወድቃል (ይውላል):: 14 መጥቅዕ ስለሌለ 14ትን ፈጽሞ አይነካም:: መጥቅዕ በመስከረም ላይ ሲወድቅ ጾመ ነነዌ ጥር ላይ ይውላል:: መጥቅዕ ጥቅምት ላይ ሲወድቅ ግን ነነዌ የካቲት ላይ ይውላል:: መጥቅዕ መስከረም ላይ ወድቆ ተውሳክ ዕለት ተጨምሮበት ከ30 በላይ ሆኖ ቢተርፍ ተረፉ መባጃ ሐመር ይሆናል:: በዚህ ጊዜ ጾመ ነነዌ በየካቲት እንጂ በጥር አይውልም:: አልቦ አበቅቴ በሆነ ጊዜም አጽዋማትና በዓላት መጥቅዕ አያስፈልጋቸውም:: መስከረም በባተ በሠላሳኛው ቀን ተውሳክና በተውሳካቸው ብቻ ይወጣሉ::

## የሰባቱ ዕለታት ተውሳክ

ሰባቱ ዕለታት የሚባሉት ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉ ዕለታት ናቸው:: እነርሱም እሑድ፣ሰኞ(ሰኑይ)፣ ማክሰኞ (ሠሉስ)፣ ረቡዕ፣ ኀሙስ፣ ዓርብና ቅዳሜ (ቀዳም) ናቸው:: ለሁሉም ተውሳክ አላቸው:: ተውሳካቸው የሚዠምረው በቅዳሜ ነው::

| ዕለት | ተውሳክ | ዕለት | ተውሳክ |
|---|---|---|---|
| ቅዳሜ | 8 | ረቡዕ | 4 |
| እሑድ | 7 | ኀሙስ | 3 |
| ሰኞ | 6 | ዓርብ | 2 |
| ማክሰኞ | 5 | | |

የዕለታት ተውሳክ ከየት እንደተገኘ የሚታወቅበት መንገድም እንዲህ ነው:: መጥቅዕ ቅዳሜ ቢሆን ከሳኒታ መጥቅዕ እስከ ነነዌ ያለው ዕለት 128 ነው:: እሑድ ቢሆን 127፣ ሰኞ ቢሆን 126 ቀን፣ ማክሰኞ ቢሆን 125፣ ረቡዕ ቢሆን 124፣ ኀሙስ ቢሆን 123 ቀን፣

ዓርብ ቢሆን 122 ዕለት ይገኛል። ይህ ሁሉ በ30 ዐውደ ወርኅ ተቀምሮ የሚተርፈው የያንዳንዱ ዕለት ተውሳክ ይሆናል።

## የዘመነ ሐዲስ አጽዋማትና በዓላት

በዘመነ ሐዲስ የተሠሩ ተዘዋዋሪ አጽዋማትና በዓላት 11 ናቸው። እነርሱም ጾመ ነነዌ፣ በአተ ጾም (ዐቢይ ጾም)፣ ደብረ ዘይት ሆሣዕና፣ ስቅለት፣ ትንሣኤ፣ ረክበ ካህናት፣ ዕርገት፣ ጰራቅሊጦስ፣ ጾመ ሐዋርያት ጾመ ድኅነት ይባላሉ። የሊህ መሠረታቸው ነነዌ ነው። ለሁሉም ተውሳክ አላቸው። ለጾመ ነነዌ ተውሳክ የለውም። በመባጃ ሐመር ብቻ ይታወቃል። የሌሎቹ አጽዋማትና በዓላት ተውሳክ በበአተ ጾም ይገኘምራል።

| በዓል/ጾም | ተውሳክ | በዓል/ጾም | ተውሳክ |
|---|---|---|---|
| በአተ ጾም | 14 | ረክበ ካህናት | 3 |
| ደብረ ዘይት | 11 | ዕርገት | 18 |
| ሆሣዕና | 2 | ጴራቅሊጦስ | 28 |
| ስቅለት | 7 | ጾመ ሐዋርያት | 29 |
| ትንሣኤ | 9 | ጾመ ድኅነት | 1 |

የዘመነ ሐዲስ አጽዋማትና በዓላት ተውሳክ የሚገኝበት መንገድም እንዲህ ነው። በዘመነ ሐዲስ ለተሠሩ አጽዋማትና በዓላት መሠረታቸው ጾመ ነነዌ ነው። ከሳኒታ (ማግስት) ነነዌ እስከ በአተ ጾም 14 ዕለት ይገኛል። ይህ የበአተ ጾም ተውሳክ ነው። እስከ ደብረ ዘይት 41 ዕለት ይገኛል። እስከ ሆሣዕና 62 ይገኛል። እስከ ትንሣኤ 69 ቀን ይገኛል። እስከ ረክበ ካህናት 93 ዕለት ይገኛል። እስከ ዕርገት 108 ዕለት ይገኛል። እስከ ጰራቅሊጦስ 118፣ እስከ ጾመ ሐዋርያት 119 ዕለት ይገኛል። እስከ ምሕላ ድኅነት 121 ዕለት ይገኛል። ይህ ሁሉ በ30 ዐውደ ወርኅ ተቀምሮ የሚተርፈው የያንዳንዱ ጾምና በዓል ተውሳክ ይሆናል። የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ 6 ነው የሚሉ አሉ። አቡሻህር ተውሳክ የለውም ይላል። የጾመ ሐዋርያት መሠረቱ ግንቦት 25 ነው። በዓለ 50 ከ25 በታች ቢወርድ እስከ 25 ያለው





ዕለት ጾመ ሐዋርያት አይደለም። ከ25 በላይ ቢወጣ ጾመ ሐዋርያት በበዓለ ኀምሳ ምክንያት ይበላል። ሮብና ዓርብ እንደተበሉ። በዚህ በዓለ ኀምሳ ሲፈጸም በሳኒታ ጰራቅሊጦስ ሰኞ መጦም ይገባል። ጾመ ሐዋርያት ቀድሞ አልፏልና ይላል። እንዲህ ከሆነ የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ የኢትዮጵያ ውሳኔ እንጂ የድሜጥሮስ እንዳይደለ ይታወቃል ይባላል።

## ኢየዐርግና ኢይወርድ

የሐዲስ አጽዋማትና በዓላት የሠርቀ መዓልታቸው ኢየዐርግ፣ ኢይወርድ መመላለሻ ቀጥሎ ይነገራል። ኢይወርዳቸው 17 ኢየዐርጋቸው 21፣ መመላለሻቸው 35 ነው።

መጥቅዕ 15 ሆኖ በዓለ መጥቅዕ ዓርብ መስከረም 15 ቀን ቢውል ያን ጊዜ አጽዋማትና በዓላት በታሕታይ ቀመራቸው ይውላሉ። የዓርብ ተውሳክ 2ና 15 መጥቅዕ ሲደመር 17 የሆናል። ጾመ ነነዌ ከጥር 17 በታች አይወርድም።

መጥቅዕ 13 ሆኖ በዓለ መጥቅዕ ቅዳሜ ጥቅምት 13 ቢውል ያን ጊዜ አጽዋማትና በዓላት በላዕላይ ቀመራቸው ይውላሉ። የቅዳሜ ተውሳክ 8ና 13 መጥቅዕ ሲደመር 21 ይሆናል። ነነዌ ከየካቲት 21 በላይ አይወጣም። ከጥር 30 ቀን 16 ሲቀነስ 14 ይተርፋል። ይህ በ21 ላይ ሲደመር 35 ይሆናል። ጾመ ነነዌ በዚህ ሲመላለስ ይኖራል።

የበአተ ጾም ተውሳክ 14ና 17 ሲደመር 31 ይሆናል። 31 በ30 ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 1 ብቻ ይተርፋል። በአተ ጾም ከየካቲት 1 በታች አይወርድም። 14ና 21 ሲደመር 35 ይሆናል። ይህ በ30 ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 5 ይተርፋል። በአተ ጾም ከመጋቢት 5 በላይ አይወጣም። በየካቲት 30 ቀን ላይ ከመጋቢት 5 ሲደመር 35 ይሆናል። በዚህ ሲመላለስ ይኖራል።

የደብረ ዘይት ተውሳክ 11ና 17 ሲደመር 28 ይሆናል። ደብረ ዘይት ከየካቲት 28 በታች አይወርድም። 11ና 21 ሲደመር 32 ይሆናል። ይህ በ30 ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 2 ይተርፋል። ደብረ ዘይት ከሚያዝያ 2 በላይ አይወጣም። ከየካቲት 30 ቀን 27 ሲቀነስ 3 ይተርፋል። ከየካቲት 3፣ መጋቢት 30፣ ከሚያዝያ 2 ሲደመር 35 ይሆናል። በዚህ ሲመላለስ ይኖራል።

www.ethiopianorthodox.org

የሆሣዕና ተውሳክ 2ና 17 ሲደመር 19 ይሆናል:: ሆሣዕና ከመጋቢት 19 በታች አይወርድም:: 2ና 21 ሲደመር 23 ይሆናል:: ሆሣዕና ከሚያዝያ 23 በላይ አይወጣም:: ከመጋቢት 30 ቀን 18 ሲቀነስ 12 ይተርፋል:: መጋቢት 12 ከሚያዝያ 23 ሲደመር 35 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::

የስቅለት ተውሳክ 7 ና 17 ሲደመር 24 ይሆናል:: ስቅለት ከመጋቢት 24 በታች አይወርድም:: 7 ና 21 ሲደመር 28 ይሆናል:: ስቅለት ከሚያዝያ 28 በላይ አይወጣም:: ከመጋቢት 30 ቀን 23 ሲቀነስ 7 ይተርፋል:: ከመጋቢት 7 ከሚያዝያ 28 ሲደመር 35 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::

የትንሣኤ ተውሳክ 9ና 17 ሲደመር 26 ይሆናል:: ትንሣኤ ከመጋቢት 26 ቀን አይወርድም:: 9ና 21 ሲደመር 30 ይሆናል:: ትንሣኤ ከሚያዝያ 30 በላይ አይወጣም:: ከመጋቢት 30 ቀን 25 ሲቀነስ 5 ይተርፋል:: ከመጋቢት 5 ከሚያዝያ 30 ሲደመር 35 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::

የረክበ ካህናት ተውሳክ 3 በ17 ላይ ሲደመር 20 ይሆናል:: ረክበ ከሚያዝያ 20 በታች አይወርድም:: 3 በ21 ላይ ሲደመር 24 ይሆናል:: ከግንቦት 24 በላይ አይወጣም:: ከሚያዝያ 30 ቀን 19 ሲቀነስ 11 ይተርፋል:: በሚያዝያ 11 ላይ 24 ሲደመር 35 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::

የዕርገት ተውሳክ 18 በ17 ላይ ሲደመር 35 ይሆናል:: ይህ በ30 ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 5 ይተርፋል:: ዕርገት ከግንቦት 5 በታች አይወርድም:: 18 በ21 ላይ ሲደመር 39 ይሆናል:: ይህ በ30 ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 9 ይተርፋል:: ዕርገት ከሠኔ 9 በላይ አይወጣም:: ከግንቦት 30 ቀን 4 ሲቀነስ 26 ይተርፋል:: በ26 ላይ 9 ሲደመር 35 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::

የጰራቅሊጦስ ተውሳክ 28 በ17 ላይ ሲደመር 45 ይሆናል:: ይህ በ30 ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 15 ይተርፋል:: ጰራቅሊጦስ ከግንቦት 15 በታች አይወርድም:: 28 በ21 ላይ ሲደመር 49 ይሆናል:: ይህ በ30 ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 19 ይተርፋል:: ጰራቅሊጦስ ከሠኔ 19 በላይ አይወጣም:: ከግንቦት 30 ቀን 14 ሲቀነስ 16 ይተርፋል:: በ16 ላይ 19 ሲደመር 35 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::





የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ 29 በ17 ላይ ሲደመር 46 ይሆናል:: ይህ በ30 ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 16 ይተርፋል:: ጾመ ሐዋርያት ከግንቦት 16 በታች አይወርድም:: 29 በ21 ላይ ሲደመር 50 ይሆናል:: ይህ በ30 ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 20 ይተርፋል:: ጾመ ሐዋርያት ከሠኔ 20 በላይ አይወጣም:: ከግንቦት 30 ቀን 15 ሲቀነስ 15 ይተርፋል:: 15ና 20 ሲደመር 35 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::

የጾመ ድኅነት ተውሳክ 1 በ17 ላይ ሲደመር 18 ይሆናል:: ጾመ ድኅነት ከግንቦት 18 በታች አይወርድም:: 1ና 21 ሲደመር 22 ይሆናል:: ከሠኔ 22 ቀን በላይ አይወጣም:: ከግንቦት 30 ቀን 17 ሲቀነስ 13 ይተርፋል:: በ13 ላይ 22 ሲደመር 35 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::

## የብሉይ አጽዋማትና በዓላት

በዘመነ ብሉይ የተሠሩ አጽዋማትና በዓላት ዘጠኝ ናቸው:: እነርሱም መጥቅዕ፣ በድር፣ መጸለት፣ ጾመ አይሁድ፣ ፍሥሕ፣ ልበ ምድር፣ በዓለ ሰዊት፣ ጾመ አስቴር፣ ጾመ ዮዲት ይባላሉ:: መነሻቸውም እንዲህ ነው:: በዓለ መጥቅዕ በኖኅ፣ የሐዘን ቀን የሚባለው ጾመ አይሁድ (በድር) በያዕቆብ፣በዓለ መጸለትና በዓለ ናዕት፣ በዓለ ፍሥሕ በአብርሃም፣ ንዝሐተደምና በሲዓ ናዕት ፍሥሕ የሚደረግበት ዕለት በሙሴ ተጀምረዋል:: በዓለ ሰዊት የእሸቱ አሥራት የሚገባበት፣ ልበ ምድር ባሕረ ኤርትራን የተሻገሩበትን ዕለት የሚያከብሩበት ነው:: ጾመ አስቴር በሐማ ጊዜ፣ጾመ ዮዲት ደግሞ በሆሎፎርኒስ ጊዜ ተጀምረዋል::

ከእሊህም ሦስቱ መጥቅዕ፣ በድርና መጸለት ተለይተው በመስከረምና በጥቅምት ይውላሉ:: ጾመ አይሁድ በጥርና በየካቲት ይውላል:: ፍሥሕ በመጋቢትና በሚያዝያ ይውላል:: ልበ ምድር በሚያዝያና በግንቦት ይውላል:: በዓለ ሰዊት በግንቦትና በሠኔ ይውላል:: ጾመ አስቴርና ጾመ ዮዲት በነሐሴና በጳጉሜን ይውላሉ:: ጾመ ዮዲት ተለይታ በ8፣ በ10፣ በ12፣ በ13 መጥቅዕ ጊዜ በመስከረም አራት ጊዜ ትውላለች::

ለብሉይ አጽዋማትና በዓላት መሠረታቸው መጥቅዕ ነው:: ለመጥቅዕ ተውሳክ የለውም:: በገንዘቡ ይወጣል:: የቀሩት ግን ተውሳክ አላቸው:: የበድር ተውሳክ 9 ነው:: የመጸለት 14፣ የጾመ



www.ethiopianorthodox.org

አይሁድ 15፣ የፍሥሕ 10፣ የልበ ምድር 3፣ የበዓለ ሰዊት 30፣ የጾመ አስቴር 21፣ የጾመ ዮዲት ተውሳክ 28 ነው:: ፍሥሕን መሠረት ያደረጉ እንደሆነ ግን የልበ ምድር ተወሳክ 23፣ የበዓለ ሰዊት 20፣ የጾመ አስቴር 11፣ የጾመ ዮዲት 18፣ የመጥቅዕ 20፣ የበድር 29፣ የመጸለት 4፣ የጾመ አይሁድ ተውሳክ 5 ይሆናል::

ሠርቀ ሌሊታቸውም እንዲህ ነው:- የመጥቅዕ ሌሊት 1 ነው፣ የበድር ሌሊት 10፣ የመጸለት ሌሊት 15፣ የጾመ አይሁድ 18፣ የፍሥሕ 14፣ የልበ ምድር በሚያዝያ ቢውል 7፣ በግንቦት ቢውል 8 ይሆናል:: የበዓለ ሰዊት ሌሊት 5፣ የጾመ አስቴር 27፣ የጾመ ዮዲት ሌሊት 4 ነው:: ጾመ ዮዲት ተለይታ በመስከረም የዋለች እንደሆን ባለፈው አበቅቴ፣ ባለፈው ሕጸጽ ጳጉሜን አውጥተው ቢቴጥሩ 29 ሌሊት፣ ጳጉሜንን አግብተው ቢቴጥሩ 34 ይሆናል:: ከዚህ 30ው ሲቀነስ 4 ይተርፋል:: ከጥንተ ሌሊቱ ይገባል::

## የብሉይ አጽዋማትና በዓላት ተውሳክ

የዘመነ ብሉይ አጽዋማትና በዓላት ተውሳክ ከየት እንደ መጣ የሚታወቅበት መንገድም እንዲህ ነው:: የብሉይ አጽዋማትና በዓላት መሠረታቸው መጥቅዕ ነው:: ከሳኒታ መጥቅዕ እስከ በድር 9 ዕለት ይገኛል:: ይህ የበድር ተውሳክ ነው:: እስከ መጸለት 14 ዕለት ይገኛል:: ይህ የመጸለት ተውሳክ ነው:: ከሳኒታ መጥቅዕ እስከ ጾመ አይሁድ (ሙሴ) 135 ዕለት ይገኛል:: እስከ ፍሥሕ 190 ዕለት፣ እስከ ልበምድር 213፣ እስከ በዓለ ሰዊት 240 ዕለት፣ እስከ ጾመ አስቴር 321፣ እስከ ጾመ ዮዲት 328 ዕለት ይገኛል:: ይህ ሁሉ በ30 ዐውደ ወርኀ ተቀምሮ የሚተርፈው የያንዳንዱ ጾምና በዓል ተውሳክ ይሆናል::

በንለ ፍሥሕ መሠረታቸው የሆነ እንደሆነ ግን ከሳኒታ ፍሥሕ እስከ ልበ ምድር 23 ዕለት ይገኛል::ይህ የልበ ምድር ተውሳክ ነው:: እስከ በዓለ ሰዊት 50 ዕለት ይገኛል:: እስከ ጾመ አስቴር 131 ይገኛል:: እስከ ጾመ ዮዲት 138 ዕለት ይገኛል:: ይህ ሁሉ በ30 ተቀምሮ የሚተርፈው የያንዳንዱ ጾምና በዓል ተውሳክ ይሆናል::

## ኢይዐርግና ኢይወርድ

የብሉይ አጽዋማትና በዓላት የሠርቀ መዓልታቸው፣ ኢየዐርግ፣ ኢይወርድ መመላለሻ ቀጥሎ ይነገራል:: ኢይወርዳቸው



www.ethiopianorthodox.org



15 መጥቅዕ ኢየዐርጋቸው 13 መጥቅዕ መመላለሻቸው 29 ነው:: የበድር ተውሳክ 9 በ15 መጥቅዕ ላይ ሲደመር 24 ይሆናል:: በድር ከመስከረም 24 በታች አይወርድም:: 9ና 13 ሲደመር 22 ይሆናል:: በድር ከጥቅምት 22 በላይ አይወጣም:: ከመስከረም 30 ቀን 23 ሲቀነስ 7 ይተርፋል:: ይህ በጥቅምት 22 ላይ ሲደመር 29 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::

የበዓለ መጸለት ተውሳክ 14ና 15 መጥቅዕ ሲደመር 29 ይሆናል:: በዓለ መጸለት ከመስከረም 29 በታች አይወርድም:: 14ና 13 ሲደመር 27 ይሆናል:: በዓለ መጸለት ከጥቅምት 27 በላይ አይወጣም:: ከመስከረም 30 ቀን 28 ሲቀነስ 2 ይተርፋል:: ይህ በጥቅምት 27 ላይ ሲደመር 29 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::

የጾመ አይሁድ (ሙሴ) ተውሳክ 15ና 15 ሲደመር 30 ይሆናል:: ጾመ አይሁድ ከጥር 30 በታች አይወርድም:: 15ና 13 ሲደመር 28 ይሆናል:: ጾመ አይሁድ ከየካቲት 28 በላይ አይወጣም:: ከጥር 30 ቀን 29 ሲቀነስ 1 ይተርፋል:: ይህ በየካቲት 28 ላይ ሲደመር 29 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::

የፍሥሕ ተውሳክ 10ና 15 ሲደመር 25 ይሆናል:: ፍሥሕ ከመጋቢት 25 በታች አይወርድም:: 10ና 13 ሲደመር 23 ይሆናል:: ፍሥሕ ከሚያዝያ 23 በላይ አይወጣም:: ከመጋቢት 30 ቀን 24 ሲቀነስ 6 ይተርፋል:: ይህ በሚያዝያ 23 ላይ ሲደመር 29 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል::

የልበ ምድር ተውሳክ 3 በ15 መጥቅዕ ላይ ሲደመር 18 ይሆናል:: ልበ ምድር ከሚያዝያ 18 በታች አይወርድም:: 3ና 13 መጥቅዕ ሲደመር 16 ይሆናል:: ልበ ምድር ከግንቦት 16 በላይ አይወጣም:: ከሚያዝያ 30 17 ሲቀነስ 13 ይተርፋል:: ይህ በግንቦት 16 ላይ ሲደመር 29 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል:: የቀሩት አጽዋማትና በዓላትም ኢየዐርጋቸውና ኢይወርዳቸው በዚህ መንገድ ይታወቃል::

## አምሳል መርገፍ

በዘመነ ብሉይ የተሠሩ አጽዋማት በዓላትን ጾማቸውን እንጾመው፣ በዓላቸውን እናከብረው፣ ስለምን እንማራቸዋለን፣ እናስተምራቸዋለን? ቢሉ ኦሪት ለወንጌል አምሳል መርገፍ

እንደሆነች፣ በዘመነ ብሉይ የተሠሩ አጽዋማትና በዓላትም በዘመነ ሐዲስ ለተሠሩ አጽዋማትና በዓላት አምሳል መርገፍ ናቸውና:: ስለዚህ እንማራቸዋለን እናስተምራቸዋለን:: ምሳሌነታቸውም እንዲህ ነው:-

በዓለ መጥቅዕ የበዓለ ዮሐንስ ምሳሌ ነው:: ምሳሌነቱም ቀድሞ ሌዋውያን ዓመተ ኅድገት፣ ዓመተ ሥጋዌ ሊሆን ይህን ያህል ዘመን ቀረ እያሉ ያስተምሩ እንደነበር መምህራንም ጾመ ነነዌ፣ ዐቢይ ጾም፣ ትንሣኤ፣ ጾመ ድኅነት ሊሆን ይህን ያህል ቀርቷል፤ እያሉ የሚያስተምሩበት ቀን ስለሆነ ነው::

በድር የጾመ ንስሐ ምሳሌ ነው:: ምሳሌነቱም እስራኤል በዚሁ ቀን ኃጢአታችንን ይቅር በለን፣ ዕዳ በደል አትበልብን እያሉ ይጸልዩ እንደነበር፣ ምእመናንም ኃጢአታችንን ይቅር በለን እያሉ የሚያዝኑበት ቀን ስለሆነ ነው::

በሠርቀ ወርኀም የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ገብቶበታል:: መጸለት የበዓለ ጥምቀት ምሳሌ ነው:: ምሳሌነቱም እስራኤል በዚሁ ቀን ጃንጥላ ጥለው፣ ድንኳን ተክለው፣ ከባሕር ወርደው ያከብሩት እንደ ነበር ምእመናንም በበዓለ ጥምቀት ከባሕር ወርደው ጃንጥላ ጥለው፣ ድንኳን ተክለው የሚያከብሩት ዕለት ስለሆነ ነው::

ጾመ ሙሴ (አይሁድ) የበአተ ጾም ምሳሌ ነው:: ምሳሌነቱም ሙሴ ከሰው ተለይቶ፣ ደብረ ሲና ወጥቶ እህል ውሀ ትቶ የጾመው ጾም እንደሆነ፣ ጌታም ከሰው ተለይቶ ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ እህል ውሀ ትቶ የጾመው ስለሆነ ነው::

በዓለ ፍሥሕ የስቅለት ምሳሌ ነው:: ምሳሌነቱም በዚሁ በዓል እስራኤል በግ ይሠውበት እንደነበር *በግዐ ንጹሕ ዘበአማን ኢየሱስ ክርስቶስም* የተሠዋበት ዕለት ስለሆነ ነው::

ልበ ምድር የማዕደት (የትንሣኤ) ምሳሌ ነው:: ምሳሌነቱም እስራኤል ከግብጽ የወጡበት ባሕረ ኤርትራን የተሻገሩበት ዕለት እንደኾነ፣ ማዕደትም (ትንሣኤ) ነፍሳት ከሲኦል ከገሃነም የወጡበት ባሕረ እሳት የተሻገሩበት ዕለት ስለሆነ ነው::

በዓለ ሰዊት የበዓለ ጰራቅሊጦስ ምሳሌ ነው:: ምሳሌነቱም ሌዋውያን የእሸቱን ቀዳምያት፣ ዓሥራት፣ በኩራት የሚቀበሉበት እንደሆነ፣



www.ethiopianorthodox.org



ሐዋርያትም ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የተቀበሉበት ስለሆነ ነው:: *ሃዲ ንቴክዝ ንሕነሂ እስመ ነሣእነ ጸጋሁ ለመንፈስ ቅዱስ*፤ እንዲል::

ጾመ አስቴር የጾመ ረቡዕ ምሳሌ ነው:: ምሳሌነቱም የእስራኤል ምክረ ሞታቸው የተፈጸመበት ዕለት እንደሆነ ረቡዕም የጌታ ምክረ ሞቱ የተፈጸመበት ስለሆነ ነው::

ጾመ ዮዲት የጾመ ዓርብ ምሳሌ ነው:: ምሳሌነቱም እስራኤል የዳኑበት ሆሎፎርኒስ የተቀጣበት ዕለት እንደሆነ ዓርብም ነፍሳት የዳኑበት፣ ዲያብሎስ የተቀጣበት ዕለት ስለሆነ ነው:: ስለዚህ እኛ የምንማራቸው ለማወቅ፣ ለምእመናን የምናስተምራቸው ለማሳወቅ ነው እንጂ አጽዋማቱን የምንጾማቸው በዓላቱን የምናከብራቸው ሆኖ አይደለም::

## የአበቅቴ ትስስር

### ከብሉይ አጽዋማት በዓላት

አበቅቴና መጥቅዕ ሲደመሩ ዘወትር 30 ናቸው:: አበቅቴና በድር ሲደመሩ ቢበዙ 29፣ ቢያንሱ 9 ይሆናል:: አበቅቴና መጸለት ቢበዙ 44፣ ቢያንሱ 14 ይሆናሉ:: አበቅቴና ጾመ አይሁድ (ሙሴ) ቢበዙ 45፣ ቢያንሱ 15 ይሆናሉ:: አበቅቴና ልበ ምድር ቢበዙ 33፣ ቢያንሱ 3 ይሆናሉ:: አበቅቴና በዓለ ሰዊት ዘወትር 30 ናቸው:: አበቅቴና ጾመ አስቴር ቢበዙ 51፣ ቢያንሱ 21 ይሆናሉ:: አበቅቴና ጾመ ዮዲት ሲደመሩ ቢበዙ 58 ቢያንሱ 28 ይሆናሉ:: አበቅቴና ፍሥሕ ቢበዙ 40፣ ቢያንሱ 10 ይሆናሉ:: አበቅቴ ወፍሥሕ እመ ይበዝኁ አርብዓ፣ ወእመ ይውኅዱ ዐሥረ ይከውኑ እንዲል (መር.ዕውር)::

### ከዕለተ ፍሥሕ

በአልቦ አበቅቴ ጊዜ ፍሥሕ በሚያዝያ 10 ቀን ይውላል:: አልቦ በሆነ ባመቱ፣ በ11 አበቅቴ ጊዜ ፍሥሕ በመጋቢት በ29 ቀን ይውላል:: 11 ና 29 ሲደመር 40 ይሆናል:: ቢበዙ 40 ይሆናሉ ያለው ይህ ነው:: በ22 አበቅቴ ጊዜ ፍሥሕ ሚያዝያ 18 ቀን ይሆናል:: 18 እና 22 ሲደመር 40 ይሆናል:: ቢበዙ 40 ይሆናሉ ያለው ይህ ነው:: በ3 አበቅቴ ጊዜ ፍሥሕ በሚያዝያ 7 ቀን

ይሆናል:: 3 ና 7 ሲደመሩ 10 ይሆናል:: ቢያንሱ 10 ይሆናሉ ያለው ይህ ነው:: እንዲህ እየተሰላ እስከ አልቦ ድረስ ይቈጠራል::

በ11፣ በ12፣ በ14፣ በ15 አበቅቴ ጊዜ ፍሥሕ በመጋቢት ትውላለች:: የቀረው ግን በሚያዝያ ይሆናል:: ፍሥሕ ከመጋቢት 25 በታች አይወርድም:: ከሚያዝያ 23 በላይ አይወጣም:: ከመጋቢት 6፣ ከሚያዝያ 23 ሲደመር 29 ይሆናል:: በዚህ ሲመላለስ ይኖራል:: በአበቅቴ ፍሥሕ በፍሥሕ አበቅቴ ይታወቃል:: ከፍሥሕ ቀጥሎ ያለው እሑድ ትንሣኤ ነው::

ፍሥሕን አራት ነገሮች ይጠብቁታል:: ገቦ መጥቅዕ፣ 190 ዕለት፣ ሰሙነ ሕማማት፣ 14 ሌሊት እሊህ አራቱ ይጠብቁታል:: ፍሥሕን ሳያልፉ ትንሣኤን ቢያደርጉ እንደገና ትንሣኤን ማድረግ ያሻል:: ስለዚህም ነገር ቀድሞ ሐዋርያት በዲድስቅልያ፣ በኋላም ጉባኤ ኒቅያ፣ *በሁለተኛው ሱባዔ ትንሣኤ አታድርጉ፤ እስከ 21 ጨረቃ ጠብቁ፤ ከአይሁድ በዓል ጋራ እንዳትገናኙ ተጠንቀቁ:: ፍሥሕ ዓርብና ቅዳሜ ቢውል እሑድ ትንሣኤ አታድርጉ:: በዓለ አይሁድ ነው:: በሁለተኛው እሑድ አድርጉ፤* ብለዋል:: በስድስት ሺሕ ከአንድ ፻ዘመን ፍሥሕ ቅዳሜ ሆኖ ምእመናን አይሁድ ከፍሥሐቸው ጋራ እንዲሆንላቸው እሑድ ትንሣኤ እናድርግ አሉ:: ማርቆስ ወልደ ቀንበር አይገባም:: ቀድሞ አባቶቻችን ሐዋርያት ኋላም በጉባኤ ኒቅያ ከአይሁድ በዓል ጋራ አትገናኙ 21 ጨረቃ ጠብቁ ብለዋል ብሎ ተነሣባቸው:: ምእመናን አይሁድ መንፈሳዊ ትምህርት የጐደላቸው አልከኞች ሰዎች ናቸውና ቀጥቅጠው ገደሉት:: በዚህም እርሱ ሰማዕት ተብሎበታል:: ዛሬም ፍሥሕን በቀዳም ስዑር ያደርጋሉ:: እውነተኛ ፍሥሕ አይደለም:: እውነተኛው ፍሥሕ ግን አስቀድሞ በሕማማት ረቡዕ ይሆናል:: በምን ይታወቃል ቢሉ? ፍሥሕ የታዘዘበት 14ኛው ጨረቃ ነው:: በቀዳም ስዑር 18 ጨረቃ ይሆናል:: ስለዚህ ፍሥሕ ካለፈ በኋላ ሁለተኛ ፍሥሕ ማድረግ ይሆናል:: አውነተኛስ ሆኖ ቢሆን በነጋው ትንሣኤ ባልሆነም ነበር:: ያለ እውቀት ያለ መማር የተደረገ ነገር ነው:: እውነተኛውን ፍሥሕ ለማግኘት ከመጥቅዕ 4 ነሥቶ ባበቅቴ ላይ 4 መጨመር ያስፈልጋል:: ስለምን ቢሉ? በአንቀጸ አበቅቴ በተናገርናቸው በኬክሮስና በካልዒት ምክንያት የመጥቅዕ ብተት ወደ ታች 4 ቀን ወርደዋል:: አበቅቴ 4 ቀን ሰቧል:: ይህንም ለማወቅ ከአቡሻህር ቃል ትምህርት በጥቂቱ መማር ያስፈልጋል:: የፍሥሕም ኢየዐርግ ከጸሎተ ኀሙስ አይወጣም:: ኩተዕዊኖ ዓርብ አይወርድም:: ይህም መለዋለጥ በሔኖክና በኩፋሌ ተነግሯል::



www.ethiopianorthodox.org



## አበቅቴና ወንጌላዊ

ባለው አበቅቴ ላይ 14 ቢደመር ባራት፣ ባራት ዓመት የሚመጣ ወንጌላዊ አበቅቴ ይታወቃል:: በማቴዎስ ላይ ቢጨመር የማቴዎስ፣ በማርቆስ ላይ ቢጨመር የማርቆስ፣ በሉቃስ ላይ ቢጨመር የሉቃስ፣ በዮሐንስ ላይ ቢጨመር የዮሐንስ ይታወቃል:: ዳግመኛም ባለው አበቅቴ ላይ 16 ቢጨመር ባራት፣ ባራት ዓመት የሆነው፣ ያለፈው ወንጌላዊ አበቅቴ ይታወቃል::

በአልቦ አበቅቴ፣ በ11 አበቅቴ፣ በ22 አበቅቴ የተነሣ ወንጌላዊ በአንድ ንኡስ ቀመር አምስት፣ አምስት ጊዜ ይመላለሳል:: በ3 አበቅቴ የተነሣ ወንጌላዊ ግን በአንድ ንኡስ ቀመር አራት ጊዜ ተመላልሶ በአምስተኛው አልቦን ይቀበላል::

በአልቦ አበቅቴ የተነሣ ወንጌላዊ በ2ኛው 14 አበቅቴ፣ በ3ኛው 28 አበቅቴ፣ በ4ኛው 12 አበቅቴ፣ በ5ኛ 26 አበቅቴ ይደርሰዋል:: በ11 አበቅቴ የተነሣ ወንጌላዊ በ2ኛው 25 አበቅቴ፣ በ3ኛው 9 አበቅቴ፣ በ4ኛው 23 አበቅቴ፣ በ5ኛው 7 አበቅቴ ይደርሰዋል:: በ22 አበቅቴ የተነሣ ወንጌላዊ በ2ኛው 6 አበቅቴ፣ በ3ኛው 20 አበቅቴ፣ በ4ኛው 4 አበቅቴ፣ በ5ኛው 18 አበቅቴ ይደርሰዋል:: በ3 አበቅቴ አተነሣ ወንጌላዊ በ2ኛው 17 አበቅቴ፣ በ3ኛው 1 አበቅቴ፣ በ4ኛው 15 አበቅቴ፣ በ5ኛው 29 አበቅቴ ደርሶት አልቦን ይቀበላል::

## አልቦና ወንጌላዊ

አልቦን የሚቀበል ወንጌላዊ በአራት አራተኛው ዓመት ነው:: ከማቴዎስ ዮሐንስ፣ ከዮሐንስ ሉቃስ፣ ከሉቃስ ማርቆስ፣ ከማርቆስ ማቴዎስ ይቀበላል:: ማቴዎስ ቀመሩን ማክሰኞ ዘምሮ በሳኒታው ረቡዕ ይፈጽማል:: ከርሱ የሚቀበል ወንጌላዊ በፊቱ ሠግር አለና ባራተኛው ቀን ዓርብ ቀመሩን ይቀበላል:: ዮሐንስ ቀመሩን ዓርብ ዘምሮ በሳኒታው ቅዳሜ ይፈጽማል:: ሉቃስና ማርቆስ ርእሰ አንቀጽ በሆኑ ጊዜ ቀመራቸውን በ3ኛው ቀን ይፈጽማሉ ከርሳቸው የሚቀበል ወንጌላዊ በአራተኛው ቀን ይቀበላል::

የቀመር መዠመርያው ማክሰኞ ነው:: ማክሰኞ ማቴዎስ አንድ፣ እሑድ ማቴዎስ 5፣ ዓርብ ማቴዎስ 9፣ ረቡዕ ማቴዎስ 13፣ ሰኞ ማቴዎስ 17፣ ማክሰኞ ማርቆስ 18፣ ረቡዕ ሉቃስ 19፣ እንድ አልቦ ደረሰ:: ኀሙስ ሠግር ነው::

ዓርብ ዮሐንስ አንድ፣ ረቡዕ ዮሐንስ 5፣ ሰኞ ዮሐንስ 9 ቅዳሜ ዮሐንስ 13፣ ኀሙስ ዮሐንስ 17፣ ዓርብ ማቴዎስ 18፣ ቅዳሜ ማርቆስ 19 2 አልቦ ደረሰ:: እሑድ ሉቃስ አንድ፣ ዓርብ ሉቃስ 5፣ ረቡዕ ሉቃስ 9፣ ሰኞ ሉቃስ 13፣ ቅዳሜ ሉቃስ 17፣ እሑድ ሠግር ነው:: ሰኞ ዮሐንስ 18፣ ማክሰኞ ማቴዎስ 19፣ 3 አልቦ ደረሰ::

ረቡዕ ማርቆስ አንድ፣ ሰኞ ማርቆስ 5፣ ቅዳሜ ማርቆስ 9፣ ኀሙስ ማርቆስ 13፣ ማክሰኞ ማርቆስ 17፣ ረቡዕ ሉቃስ 18፣ ኀሙስ ሠግር ነው:: ዓርብ ዮሐንስ 19፣ 4 አልቦ ደረሰ::

## አበቅቴና ጾመ ነነዌ

በአልቦ አበቅቴ ጊዜ መስከረም ኀሙስ ብቶ ዓርብ ቢያልቅ ያንጊዜ ጾመ ነነዌ የካቲት በባተ በ2 ቀን ይውላል፣ መስከረም ሮብ ብቶ ኀሙስ ቢያልቅ ያንጊዜ ጾመ ነነዌ የካቲት በባተ በ3 ቀን ይውላል:: መስከረም ማክሰኞ ብቶ ሮብ ቢያልቅ ያንጊዜ ጾመ ነነዌ የካቲት በባተ በ4 ቀን ይውላል:: መስከረም ሰኞ ብቶ ማክሰኞ ቢያልቅ ያንጊዜ ጾመ ነነዌ የካቲት በባተ በ5 ቀን ይውላል:: መስከረም እሑድ ብቶ ሰኞ ቢያልቅ ያንጊዜ ጾመ ነነዌ የካቲት በባተ በ6 ቀን ይውላል:: መስከረም ቅዳሜ ብቶ እሑድ ቢያልቅ ያንጊዜ ጾመ ነነዌ የካቲት በባተ በ7 ቀን ይውላል:: መስከረም ዓርብ ብቶ ቅዳሜ ቢያልቅ ያንጊዜ ጾመ ነነዌ የካቲት በባተ በ8 ቀን ይውላል::





## *የበዓላትና አጽዋማት አወጣጥ ምሳሌ በዓመተ ዓለም*

የባሕረ ሐሳብ መግቢያ በር፣ መክፈቻ ቁልፍም የመስከረም መባቻ ነው:: ስለዚህ በፀሐይም ሆነ በጨረቃ አቈጣጠር መንገድ የያንዳንዱ ዓመት የመስከረም መባቻ ዕለት የሚታወቀው የአበቅቴ ፀሐይንና የአበቅቴ ወርኅን አወጣጥ ሥርዓት ለይቶ በማወቅ ነው:: ምክንያቱም የፀሐይና የጨረቃ ብርሃን የዘመናት መስፈርያ ነውና::

በ2001 ዓመተ ሥጋዌ አበቅቴ ፀሐይ 2፣ አበቅቴ ወርኅ 4 ነው:: አበቅቴ ፀሐይ የመስከረም አንድ ሠርቀ መዓልት፣ አበቅቴ ወርኅ የመስከረም አንድ ሠርቀ ሌሊት ስንት እንደሆነ ተለይቶ የሚታወቅበት ስሌት ነው:: መዓልቱ ለብቻ ሌሊቱ ለብቻ የሚቈጠረውም ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ነው:: ምክንያቱም ሙሴ በሲና ተራራ ላይ፣ ጌታችን በምድረ በዳ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት እንደ ቈዩ ተጽፏልና ነው (ዘፀ. 24፥17፣ ማቴ. 4፥2)::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ሌሊቱን ለብቻ፣ መዓልቱን ለብቻ መድባ የመዓልቱን መባቻ ሠርቀ መዓልት፣ የሌሊቱን መባቻ ሠርቀ ሌሊት ብላ እየቈጠረች በየቀኑ የአሥርቆቱን ሥርዓት የምታደርሰው ጌታችንንና ሙሴን ዐብነት በማድረግ ነው::

ስለዚህ ሦስተኛው ሺሕ በባተበት በ2001 ዓመተ ሥጋዌ የተገኘው አበቅቴ ፀሐይ 2 ስለሆነ የመስከረም መባቻ ኀሙስ፣ ሠርቀ መዓልቱ 1 ነው:: እንዲሁም የወጣው አበቅቴ ወርኅ 4 ስለሆነ የጨረቃ መስከረም መባቻ ጳጉሜን 2 ቀን ሆኖ ከዚያ ገሮምሮ ሲቈጠር የመስከረም አንድ ሠርቀ ሌሊት 6 ይሆናል::

እሊህ አበቅቴ ፀሐይና አበቅቴ ወርኅ የተባሉ የሐሳበ ዘመን አርእስት፣ እግዚአብሔር ጠቢባን ለሆኑ አገልጋዮቹ ካህናት የገለጸላቸው መቅድመ ሐሳብ ናቸው:: ካህናቱ በእነርሱ እየተመሩ ለሰው ልጆች መድኃኒትና ሕይወት የሚሆኑ የታወቁ በዓላት በየዓመቱ የሚውሉባቸውን ዕለታት ያውቁና ያስተውሉም ዘንድ ነው:: መቅድመ ሐሳብ ዘከሠተ ሎሙ እግዚአብሔር ለካህናቲሁ



www.ethiopianorthodox.org

ጠቢባን ከመ ያእምሩ ወይለብዉ ኅበ ይውዕሉ በዓላት እሙራት ዘበዕለታቲሆሙ ከነ መድኅኒት ወሕይወት ለሰብእ እንዲል፡፡ (መርሐ ዕዉር)

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሐሳበ ዘመን እነዚህ የቍጥር አርእስት የሚታወቁባቸው ሁለት መንገዶች አሉ፡፡

1ኛ. ዘመኑ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተቈጠረ እንደሆነ ሁለቱም ከ7501 ዓመተ ዓለም ይገኛሉ፡፡ ስሌቱም እንዲህ ነው፡፡ 7501 ዓመተ ዓለም በዐቢይና በንኡስ ቀመር ሲቀመር 14 ወንበር ይገኛል፡፡ ከዚህ 4 አበቅቴ ወርኅ፣ 26 መጥቅዕ ይወጣል፡፡ ዳግመኛም ከ7501 ዓ.ዓ. የሚገኝ የዕለተ ምርያና የዕለተ ሠግር ድምር በሱባዔ ሲቀመር 2 አበቅቴ ፀሐይ ስለተረፈ በዚህ የመስከረም መባቻ ኀሙስ መሆኑ ይታወቃል፡፡

2ኛ. ዘመኑ ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ ሲቈጠር ግን፡-

ሀ. በፀሐይ 2001 ዓመት ይሆናል፡፡ ይህ ዓመተ ሥጋዌ ዘመነ መሢሕ ይባላል፡፡ ከዚህ አበቅቴ ፀሐይ ይገኛል፡፡ አበቅቴ ፀሐይ ማለት ተረፈ ፀሐይ፣ ጥንተዮን ማለት ነው፡፡ ስሌቱም እንዲህ ነው፡፡ 2001 ዓመት በ28 ዐውደ ፀሐይ ሲቀመር 71 ዐውደ ፀሐይ ሆኖ 13 ዓመት ይተርፋል፡፡ ከ13 ዓመት ዕለተ ምርያ 13 ቀን፣ ዕለተ ሠግር 3 ቀን ድምር 16 ቀን ይገኛል፡፡ ይህ በሱባዔ ሲቀመር 2 አበቅቴ ፀሐይ ይተርፋል፡፡ በዚህ የመስከረም መባቻ ኀሙስ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ለ. በፀሐይና በጨረቃ ጥምር አቈጣጠር 2009 ዓመት ይሆናል፡፡ ይህ ዓመተ ምሕረት ዘመነ ሐዲስ ይባላል፡፡ ከዚህ አበቅቴ ወርኅ ይወጣል፡፡ አበቅቴ ወርኅ ማለት ተረፈ ጨረቃ ማለት ነው፡፡ ስሌቱም እንዲህ ነው፡፡ 2009 ዓመት በ19 ንኡስ ቀመር ሲቀመር 105 ንኡስ ቀመር ሆኖ 14 ወንበር ይተርፋል፡፡ ከ14 ወንበር 4 አበቅቴ ወርኅ፣ 26 መጥቅዕ ይገኛል፡፡

1. ከ7501 ዓመተ ዓለምና ከ2009 ዓመተ ምሕረት የተገኘው ወንበር፣ አበቅቴ ወርኅና መጥቅዕ፣



www.ethiopianorthodox.org



2. ከ7501 ዓመተ ዓለምና ከ2001 ዓመተ ሥጋዌ የተገኘው አበቅቴ ፀሐይ አንድ ዓይነት ስለሆነ በኢትዮጵያና በአውሮፓ ሐሳበ ዘመን መካከል ልዩነት የሌለ መሆኑን ይህ ስሌት ያስረዳል፡፡

የአውሮፓ ሐሳበ ዘመን ግን ከክርስቶስ ልደት ብቻ ጀምሮ ዘመኑን የሚቈጥር ስለሆነ አበቅቴ ወርኅ የሚገኝበትን 2009 ዓመተ ወርኅን ቈጥሮ ያስረዳል እንጂ አበቅቴ ፀሐይ የሚገኝበትን 2001 ዓመተ ፀሐይን ቈጥሮ አያስረዳም፡፡ ስለዚህ የቀመሩን መንገድ ባለመገንዘብ በልማድ በኢትዮጵያና በአውሮፓ የዘመን አቈጣጠር መካከል የ8 ዓመት ልዩነት አለ ተብሎ ይነገራል እንጂ እንኳን የ8 ዓመት የአንድ ዓመት ያህል ልዩነት እንደሌለ ሥርዓተ ቀመሩ ያስረዳል፡፡

የ8ቱ ዓመት ልዩነት ግን በፀሐይና በጨረቃ የዘመን አቈጣጠር መካከል ያለ ልዩነት ነው እንጂ በኢትዮጵያና በአውሮፓ ሐሳበ ዘመን መካከል እንዳይደለ የባሕረ ሐሳብ መምህራንና መጻሕፎቻቸው ይመሰክራሉ፡፡ (አቡሻህር አንቀጽ 26፡፡)

## ዓመተ ምሕረት

ዳግመኛም በዓመተ ምሕረት ብቻ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበት ቀን ማወቅ ይቻላል፡፡ «ወለእመ ፈቀድከ ታእምር አበቅቴ ወርኅ እምዓመተ ሥጋዌ ትዌስከ ለዕሌሁ ተሰዓተ ዓመተ ዘልፈ ዘይተርፍ እምዓመተ ፍዳ ወእምዝ ትገድፍ አሐደ ዘልፈ፡፡ ወዘተርፈ ትቄምር በዐሠርቱ ወተሰዓቱ ዓመት ዘውእቱ ንኡስ ቀመር» አበቅቴ ወርኅን ከዓመተ ሥጋዌ ለማግኘት ከፈለግህ ከዓመተ ፍዳ የተረፈውን 9 ዓመት በዓመተ ሥጋዌ ላይ ሁልጊዜ ትደምራለህ፡፡ ከዚህ በኋላ ከድምሩ አንዱን ዓመት ለዘመን ቀንሰህ የተረፈውን በ19 ንኡስ ቀመር ትቀምረዋለህ ይላል (አቡሻ.አን. 26)፡፡ ያውም እንዲህ ነው፡- 5500 ዓመት በ19 ሲቀመር 289 ንኡስ ቀመር ሆኖ 9 ዓመት ይተርፋል፡፡ ከዚህ 9 ዓመት አንዱን ለዘመን ቀንሶ 8ቱ ዓመት በዓመተ ሥጋዌ ላይ ሁልጊዜ ይደመራል የተባለው ይህ ነው፡፡

ከክርስቶስ ልደት ዠምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለ ዘመን ሲቈጠር በፀሐይ 2001 ዓመት ነው፡፡ ይህ ዓመተ ሥጋዌ ዘመነ መሢሕ ይባላል፡፡ ከዚህ አበቅቴ ፀሐይ ይገኛል፡፡ አበቅቴ ፀሐይ ማለት

ጥንተዮን ማለት ነው:: በፀሐይና በጨረቃ ጥምር አቈጣጠርም (2001+8)=2009 ዓመት ይሆናል:: ይህም ዓመተ ምሕረት ዘመነ ሐዲስ ይባላል:: ከዚህ አበቅቴ ወርኅ ይገኛል:: 2009 ዓመተ ምሕረት በ19 ንኡስ ቀመር ሲቀመር (2009÷19)=105 ንኡስ ቀመር ሆኖ 14 ዓመተ አበቅቴ ይተርፋል:: ይህ የ2001 ዓመተ ሥጋዌ ወንበር ነው::

የዘመኑን አበቅቴ ለማግኘት 14 ወንበር በ11 ጥንተ አበቅቴ ተባዝቶ (14×11)ለ30 ዐውደ ወርኅ ሲከፈል 5 ወር ሆኖ 4 ቀን ይተርፋል:: ይህ የ2001 ዓመተ ሥጋዌ አበቅቴ ነው::

ዳግመኛም የዘመኑን መጥቅዕ ለማግኘት 14 ወንበር በ19 ጥንተ መጥቅዕ ተባዝቶ (14×19) ለ30 ዐውደ ወርኅ ሲከፈል 8 ወር ሆኖ 26 ቀን ይተርፋል:: ይህ የ2001 ዓመተ ሥጋዌ መጥቅዕ ነው::

በ2001 ዓመተ ሥጋዌ የመስከረም መባቻ ኀሙስ፣ ወንጌላዊው ማቴዎስ፣ አበቅቴ 4፣ መጥቅዕ 26 መሆኑ ታውቋል:: ስለዚህ በዓለ መጥቅዕ መስከረም በባተ በ26ኛው ቀን ሰኞ ይውላል:: የሰኞ ተውሳክ 6 በ26 መጥቅዕ ላይ ሲደመር 32 ይሆናል:: 32 ለ30 ሲከፈል 1 ወር ሆኖ 2 ይተርፋል:: ይህ የ2001 ዓመተ ሥጋዌ መባጃ ሐመር ነው:: የካቲት እሑድ ይብታል:: የካቲት በባተ በ2ኛው ቀን ሰኞ ጾመ ነነዌ ይገባል:: ሌሎቹ አጽዋማትና በዓላትም እስከ ጾመ ድኅነት ድረስ በዚሁ መንገድ ይታወቃሉ::

እንባቢ ሆይ! ከ7501 ዓመተ ዓለምና ከ2009 ዓመተ ምሕረት የተገኘው ውጤት:-

1ኛ ወንበር 14
2ኛ አበቅቴ 4
3ኛ መጥቅዕ 26
4ኛ መባጃ ሐመር 2 ነው::

ከሁለቱም የተገኘው ውጤት አንድ መሆኑ በዚህ ስሌት ስለተረጋገጠ በኢትዮጵያና በአውሮፓ ዘመን አቈጣጠር መካከል ፈጽሞ ልዩነት እንደሌለ ልንገነዘብ ይገባናል:: 8ቱ ዓመት ግን የፀሐይና የጨረቃ አቈጣጠር ልዩነት ነው እንጂ የኢትዮጵያና የአውሮፓ አቈጣጠር ልዩነት እንዳይደለ ሥርዓተ ቀመሩ ያስረዳል::





## ትንሣኤን በአበቅቴ (የአበቅቴ ወርኅ አዋጅ)

አበቅቴ ወርኅ ማለት ተረፈ ጨረቃ ወይም በቁሙ አበቅቴ ማለት ነው:: በአበቅቴ ወርኅ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበት ቀን ማወቅ ይቻላል:: አዋጁም እንዲህ ነው:- አበቅቴና ፍሥሐ ሲደመሩ ማወቅ ውጤታቸው ቢበዛ 40፣ ቢያንስ 10 ይሆናል:: በዘመኑ የተገኘው አበቅቴ ከ10 በላይ ከሆነ ከ40፣ ከ10 በታች ከሆነ ከ10 ተቀንሶ የሚገኘው ውጤት ከ1 እስከ 23 ቢሆን በሚያዝያ፣ ከ25 እስከ 30 ቢሆን በመጋቢት በዓለ ፍሥሐ ይውላል:: ከፍሥሐ ቀጥሎ ባለው እሑድም ሁልጊዜ ትንሣኤ ይውላል:: ሌሎቹ አጽዋማትና በዓላትም የላዕላይ ቀመራቸው ቀን ከትንሣኤ ቀን ጋራ ተደምሮ በሚገኘው ውጤት የሚውሉበት ቀን ይታወቃል:: ያውም እንዲህ ነው:-

### የአጽዋማትና በዓላት የላዕላይ ቀመራቸው ቀን

| ተቁ | ጾም/በዓል | ላዕላይ ቀመር |
|---|---|---|
| 1 | ጾመ ነነዌ | የካቲት 21 |
| 2 | ዐቢይ ጾም | መጋቢት 5 |
| 3 | ደብረ ዘይት | ሚያዝያ 2 |
| 4 | ሆሣዕና | ሚያዝያ 23 |
| 5 | ስቅለት | ሚያዝያ 28 |
| 6 | ትንሣኤ | ሚያዝያ 30 |
| 7 | ረክበ ካህናት | ግንቦት 24 |
| 8 | ዕርገት | ሠኔ 9 |
| 9 | ጰራቅሊጦስ | ሠኔ 19 |
| 10 | ጾመ ሐዋርያት | ሠኔ 20 |
| 11 | ጾመ ድኅነት | ሠኔ 22 |
| | | |

በ2001 ዓመተ ሥጋዌ የተገኘው አበቅቴ 4 ነው:: ይህ በአዋጁ መሠረት ከ10 ሲቀነስ 6 ይተርፋል:: ሚያዝያ ኀሙስ ይብታል:: ሚያዝያ በባተ በ6ኛው ቀን ማክሰኞ በዓለ ፍሥሐ፣ በ11ኛው ቀን እሑድ ትንሣኤ ይውላል::



www.ethiopianorthodox.org

በላዕላይ ቀመር ጊዜ ጾመ ነነዌ የሚውልበት ቀን የካቲት 21 ነው:: ይህ በአዋጁ መሠረት ትንሣኤ ከዋለበት ከሚያዝያ 11 ቀን ጋር ሲደመር 32 ቀን ይሆናል:: ይህ በዐውደ ወርኅ ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 2 ይተርፋል:: የካቲት እሑድ ይብታል:: የካቲት በባተ በ2ኛው ቀን ሰኞ ጾመ ነነዌ ይገባል::

በላዕላይ ቀመር ጊዜ ዐቢይ ጾመ መጋቢት 5 ቀን ይውላል:: ይህ ከሚያዝያ 11 ቀን ጋር ሲደመር 16 ይሆናል:: የካቲት በባተ በ16ኛ ው ቀን ሰኞ በአተ ጾም ይሆናል::

በላዕላይ ቀመር ጊዜ ደብረ ዘይት ሚያዝያ 2 ቀን ይውላል:: ይህ ከሚያዝያ 11 ቀን ጋር ሲደመር 13 ይሆናል:: መጋቢት ማክሰኞ ይብታል:: መጋቢት በባተ በ13ኛው ቀን እሑድ ደብረ ዘይት ይውላል::

በላዕላይ ቀመር ጊዜ ሆሣዕና ሚያዝያ 23 ቀን ይውላል:: ይህ ከሚያዝያ 11 ቀን ጋር ሲደመር 34 ይሆናል:: 34 በዐውደ ወርኅ ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 4 ይተርፋል:: ሚያዝያ ኀሙስ ይብታል:: ኀሙስ በባተ በ4ኛው ቀን እሑድ ሆሣዕና ይውላል::

በላዕላይ ቀመር ጊዜ ስቅለት የሚውልበት ቀን ሚያዝያ 28 ቀን ነው:: ይህ ከሚያዝያ 11 ቀን ሲደመር 39 ይሆናል:: 39 በዐውደ ወርኅ ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 9 ይተርፋል:: ሚያዝያ በባተ በ9ኛው ቀን ዓርብ ስቅለት ይውላል::

በላዕላይ ቀመር ጊዜ ትንሣኤ የሚውልበት ቀን ሚያዝያ 30 ቀን ነው:: ይህ በሚያዝያ 11 ላይ ሲደመር 41 ይሆናል:: 41 በዐውደ ወርኅ ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 11 ይተርፋል:: ሚያዝያ በባተ በ11ኛው ቀን ትንሣኤ ይውላል::

በላዕላይ ቀመር ጊዜ ረክበ ካህናት የሚውልበት ቀን ረቡዕ ግንቦት 24 ቀን ነው:: ይህ በሚያዝያ 11 ላይ ሲደመር 35 ይሆናል:: 35 በዐውደ ወርኅ ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 5 ቀን ይተርፋል:: ግንቦት ቅዳሜ ይብታል:: ግንቦት በባተ በ5ኛው ቀን ረቡዕ ረክበ ካህናት ይውላል::





በላዕላይ ቀመር ጊዜ ዕርገት የሚውልበት ቀን ኀሙስ ሠኔ 9 ቀን ነው:: ይህ በሚያዝያ 11 ላይ ሲደመር 20 ይሆናል:: ግንቦት በባተ በ20ኛው ቀን ኀሙስ ዕርገት ይውላል::

በላዕላይ ቀመር ጊዜ ጰራቅሊጦስ የሚውልበት ቀን እሑድ ሠኔ 19 ቀን ነው:: ይህ በሚያዝያ 11 ላይ ሲደመር 30 ይሆናል:: ግንቦት በባተ በ30ኛው ቀን እሑድ ጰራቅሊጦስ ይውላል::

በላዕላይ ቀመር ጊዜ ጾመ ሐዋርያት የሚውልበት ቀን ሰኞ ሠኔ 20 ቀን ነው:: ይህ በሚያዝያ 11 ላይ ሲደመር 31 ይሆናል:: 31 በዐውደ ወርኅ ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 1 ቀን ይተርፋል:: ሠኔ ሰኞ ይብታል:: ሠኔ በባተ በ1ኛው ቀን ጾመ ሐዋርያት ይገባል::

በላዕላይ ቀመር ጊዜ ጾመ ድኅነት የሚውልበት ቀን ረቡዕ ሠኔ 22 ቀን ነው:: ይህ በሚያዝያ 11 ላይ ሲደመር 33 ይሆናል:: 33 በዐውደ ወርኅ ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 3 ቀን ይተርፋል:: ሠኔ በባተ በ3ኛው ቀን ረቡዕ ጾመ ድኅነት ይገባል::

ከ7501 ዓመተ ዓለም በተገኘው መባጃ ሐመርና ከ2009 ዓመተ ምሕረት በተገኘው አበቅቴ ወርኅ የታወቁት አጽዋማትና በዓላት በ2001 ዓመተ ሥጋዌ ሁሉም በሠርቀ ሌሊትና በሠርቀ መዓልት የዋሉባቸው ዕለታት ከላይ እንደተገለጸው ተመሳሳዮች ናቸው:: ይኸውም በኢትዮጵያና በአውሮፓ የዘመን አቈጣጠር መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ በድጋሚ ያረጋግጣል::

በ2001 ዓመተ ሥጋዌ የመስከረም መባቻ ኀሙስ፣ ወንጌላዊው ማቴዎስ፣ አበቅቴ 4፣ መጥቅዕ 26 መሆኑ ታውቋል:: ስለዚህ በዓለ መጥቅዕ መስከረም በባተ በ26ኛው ቀን ሰኞ ይውላል:: የሰኞ ተውሳክ 6 በ26 መጥቅዕ ላይ ሲደመር 32 ይሆናል:: ይህ በ30 ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 2 ይተርፋል:: ይህ የ2001 ዓ.ም. መባጃ ሐመር ነው::

የካቲት እሑድ ይብታል:: የካቲት በባተ በ2ኛው ቀን ሰኞ ጾመ ነነዌ ይገባል:: የበአተ ጾም ተውሳክ 14 በ2 መባጃ ሐመር ላይ ሲደመር 16 ይሆናል:: የካቲት በባተ በ16ኛው ቀን ሰኞ በአተ ጾም ይገባል:: የደብረ ዘይት ተውሳክ 11 በ2 መባጃ ሐመር ላይ ሲደመር 14 ይሆናል:: መጋቢት ማክሰኞ ይብታል:: መጋቢት በባተ በ13ኛው ቀን እሑድ ደብረ ዘይት ይውላል:: የሆሣዕና ተውሳክ 2 በ2 መባጃ



www.ethiopianorthodox.org

ሐመር ላይ ሲደመር 4 ይሆናል:: ሚያዝያ ሐሙስ ይብታል:: ሚያዝያ በባተ በ4ኛው ቀን እሑድ ሆሣዕና ይውላል:: የስቅለት ተውሳክ 7 በ2 መባጃ ሐመር ላይ ሲደመር 9 ይሆናል:: ሚያዝያ በባተ በ9ኛው ቀን ዓርብ ስቅለት ይውላል::

የትንሣኤ ተውሳክ 9 በ2 መባጃ ሐመር ላይ ሲደመር 11 ይሆናል:: ሚያዝያ በባተ በ11ኛው ቀን ትንሣኤ ይውላል:: የረክብ ተውሳክ 3 በ2 መባጃ ሐመር ላይ ሲደመር 5 ይሆናል:: ግንቦት ቅዳሜ ይብታል:: ግንቦት በባተ በ5ኛው ቀን ረቡዕ ረክበ ካህናት ይውላል:: የዕርገት ተውሳክ 18 በ2 መባጃ ሐመር ላይ ሲደመር 20 ይሆናል:: ግንቦት በባተ በ20ኛው ቀን ኀሙስ ዕርገት ይውላል:: የጰራቅሊጦስ ተውሳክ 28 በ2 መባጃ ሐመር ላይ ሲደመር 30 ይሆናል:: ግንቦት በባተ በ30ኛው ቀን እሑድ ጰራቅሊጦስ ይውላል:: የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ 29 በ2 መባጃ ሐመር ላይ ሲደመር 31 ይሆናል:: 31 በ30 ሲቀመር 1 ወር ሆኖ 1 ይተርፋል:: ሠኔ በባተ በ1ኛው ቀን ሰኞ ጾመ ሐዋርያት ይገባል:: የጾመ ድኅነት ተውሳክ 1 በ2 መባጃ ሐመር ላይ ሲደመር 3 ይሆናል:: ሠኔ በባተ በ3ኛው ቀን ረቡዕ ጾመ ድኅነት ይገባል::

## የ2001 ዓመት አጽዋማትና በዓላት

ከዓመተ ዓለም በተገኘው መጥቅዕ ጾመ ነነዌን መሠረት በማድረግ፣ ከዓመተ ምሕረት በተገኘው አበቅቴ ወርኅ! ትንሣኤን መሠረት በማድረግ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበት ቀንና ወር በሁለቱም መንገድ ከዚህ በላይ በዝርዝር ተጽፏል:: አሁን ደግሞ የአሥርቆትን ሥርዓት ለማሳየት አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን ወርና ቀን ከዚህ በታች ባጭሩ እንጽፋለን::

በ2001 ዓመተ ሥጋዌ የተገኘው መባጃ ሐመር 2 ነው::
ስለዚህ ጾመ ነነዌ የካቲት በባተ በ2ኛው ቀን ሰኞ ይገባል::
ዐቢይ ጾም ሰኞ የካቲት 16 ቀን ይገባል::
ደብረ ዘይት እሑድ መጋቢት 13 ቀን ይውላል::
ሆሣዕና እሑድ ሚያዝያ 4 ቀን ይውላል::
ስቅለት ዓርብ ሚያዝያ 9 ቀን ይውላል::
ትንሣኤ እሑድ ሚያዝያ 11 ቀን ይውላል::
ረክበ ካህናት ረቡዕ ግንቦት 5 ቀን ይውላል::
ዕርገት ኀሙስ ግንቦት 20 ቀን ይውላል::
ጰራቅሊጦስ እሑድ ግንቦት 30 ቀን ይውላል::



www.ethiopianorthodox.org



ጾመ ሐዋርያት ሰኞ ሠኔ 1 ቀን ይገባል::
ጾመ ድኅነት ረቡዕ ሠኔ 3 ቀን ይገባል::

## አሥርቆት

አሥርቆት ማለት ከአንድ ዕለት የሚገኙትን ሌሊትና መዓልትን እያፈራረቀ ለሚመግበን ለእግዚአብሔር የሌሊቱን ብተት፣ የመዓልቱን ብተት ስንት እንደሆነ ለይተን አውቀን እርሱን የምናመሰግንበት ሥርዐት ነው:: ያውም እንዲህ ነው:-

*ነአኵቶ ለገባሬ ሠናያት ሳዕሌነ እግዚአብሔር መሐሪ አቡሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ:: እስመ ሠወረነ ወረድአነ ዐቀበነ ወአቅረበነ ወተወክፈነ ኀቤሁ ወተማኅፀነነ፣ ወአጽንዐነ ወአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት ንስአሎ እንከ ከመ ይዕቀበነ በዛቲ ዕለት ቅድስት ኵሎ መዋዕለ ሕይወትነ ወበኵሉ ሰላም አኃዜ ኵሉ እግዚአብሔር አምላክነ (ጸልዩ::)*

*እግዚእ እግዚአ እግዚአብሔር አኃዜ ኵሉ አቡሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነአኵተከ ለዕለ ኵሉ ግብር፣ ወውስተ ኵሉ ግብር፣ በእንተ ኵሉ ግብር እስመ ሠወርከነ ወረዳእከነ፣ ዐቀብከነ ወአቅርብከነ ወተወከፍከነ ኀቤከ፣ ወተማኅፀንከነ ወአጽናዕከነ፣ ወአብጻሕከነ እስከ ዛቲ ሰዓት::*

*ኀሡ ወአስተብቍዑ ከመ ይምሐረነ እግዚአብሔር ወይሣህል ላዕሌነ፣ ወይትወከፍ ጸሎተ ወስእለተ እምነ ቅዱሳኒሁ በእንቲአነ፣ በዘይሤኒ ኵሎ ጊዜ ይረስየነ ድልዋነ ከመ ንንሣእ እምሱታፌ ምሥጢር ቡሩክ ወይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ ኪርያላይሶን::*

*በእንተ ዝንቱ ንስእለከ ወንኅሥሥ እምነ ኂሩትከ ኦ መፍቀሬ ሰብእ ሀበነ ከመ ንፈጽም ዛተ ዕለተ ቅድስተ ኵሎ መዋዕለ ሕይወትነ ወበኵሉ ሰላም ምስለ ፈሪሆትከ ኵሎ ቅንዓተ ወኵሎ መከራ ወኵሎ ግብረ ሰይጣን፣ ወምክረ ሰብእ እኩያን፣ ወትንሣኤ ፀር ዘኅቡዕ ወዘገሀድ አርኅቅ እግዚኦ እምኔየ ወእምነ ኵሉ ሕዝብከ ወእምዝንቱ መካን ቅዱስ ዘዚአከ ወላዕለ እለ ሀለው በምሥዋዕ ኵሎ ሠናያተ ዘይሤኒ ወዘይኄይስ አዝዝ ለነ እስመ አንተ ዘወሀብከነ ሥልጣነ ከመ ንኪድ ከይሴ ወአቃርብተ ወዲበ ኵሉ ኃይለ ጸላኢ:: ኢታብአነ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ በጸጋ ወሣህል ዘለፍቅረ ሰብእ፣ ዘበወልድከ ዋሕድ እግዚእነ*

ወአምላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ስብሐት ወክብር ወእዘዝ ይደሉ ምስሌሁ ወምስለ መንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ ዘዕሩይ ምስሌክ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለም ዓለም አሜን።

ሃሌ ሉያ ዮም በዘንዜከር ሐሳባተ ሕጉ እምትእዛዛቲሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ወሐሳባተ አዝማነ ዓለም ወዓመታት ወሠርቀ አውራኅ ዘሌሊት ወዘመዓልት እንዘ ሀሎነ በዘመነ ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌላዊ ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ዘመነ ቅዱስ ማርቆስ ዜናዊ አሜን።

በሠርቀ ፀሐይ ፸ወ፭፻ወ፩ ዓመተ፣ በሠርቀ ወርኅ ፸ወ፭፻ወ፴ ዓመተ ፳ አውራኃ፣ ወ፳፫ ዕለተ ኮነ ዓመተ ዓለም መዋዕለ ዓለም ወእምኔሁ፦

- በሠርቀ ፀሐይ ፶ወ፭፻ ዓመተ፤ በሠርቀ ወርኅ ፶ወ፭፻፳ወ፫ ዓመተ ፲ አውራኃ ወ፱ ዕለተ ኮነ ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ ዘመነ ብሉይ
- በሠርቀ ፀሐይ ፳፻ወ፩ ዓመተ፣ በሠርቀ ወርኅ ፳፻፳ወ፩ ዓመተ አውራኃ ፳ወ፱ ዕለተ ኮነ ዓመተ ሥጋዌ ዘመነ መሢሕ
- በሠርቀ ዕምረተ ፀሐይ ወወርኅ ፳፻ወ፱ ዓመተ ኮነ ዓመተ ምሕረት ዘመነ ሐዲስ።

ዮም በዛቲ ዕለት በፀሐይ ሠረቀ ለነ ወርኃ መስከረም ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ወርኃ ጥቅምት ሰላመ እግዚአብሔር አሜን።

- ሰዱሱ ሠርቀ ሌሊት፣
- ዐሡሩ ሠርቀ ወርኅ፣
- አሚሩ ሠርቀ መዓልት፣
- ኀሙሱ ጥንተ ዕለት (ሐሳበ ሰማይ ወምድር)፣
- ሠሉሱ ጥንተ ቀመር
- ሰኑዩ ጥንተዮን (ሐሳበ ፀሐይ)

ኮነ በዛቲ ዕለት እንዘ አበቅቴ ወርኅ አርባዕቱ፣ ወአበቅቴ ፀሐይ ክልኤቱ ለሕልመልሜሌክ በዘመነ ዕብሬቱ ወእንዘ ሀሎ ፀሐይ በአሐዱ መዓርግ እመዓርጋት ዐቢያን በማኅፈደ ሚዛን በራብዕ ጦኅት ወለእግዚአብሔር አኮቴት አሜን።



www.ethiopianorthodox.org



ወኀለይኩ መዋዕለ ትካት ተዘከርኩ ዓመተ ዓለም ወአንበብኩ። ሌሊተ ተዛዋዕኩ ምስለ ልብየ ወአንቃሕክዋ ለነፍስየ። ቦኑ ለዓለም ይገጽፍ እግዚአብሔር። ወኢይደግምኑ እንከ ተሣህሎ ወቦኑ ለግሙራ ይመትር ምሕረቶ ለትውልደ ትውልድ። ወይረስዕኑ እግዚአብሔር ተሣህሎ። ወይደፍንኑ ምሕረቶ በመዓቱ። ወእቤ እምይእዜ ወጠንኩ። ከመ ዘያስተብረ የማኖ ልዑል። ወተዘከርኩ ግብር ለእግዚአብሔር። እስመ እዜከር ዘትካት ምሕረተከ። (መዝ.76) ወትባርክ አክሊለ ዓመተ ምሕረትከ። ይጸርሑ እንዘ ይሴብሑ። (መዝ. 64) ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም። ዝ ጸሎት ወዝዕጣን ይዕርግ በእንተ ስመ እግዚአብሔር አብ መስተሣህል ወመሐሪ በቃሉ ወበመንፈሱ ኩሎ ዓለመ ሣራሪ፣ ወበእንተ ስመ እግዚአብሔር ወልድ ቃለ አብ ነባቢ፣ ወቃለ መንፈስ ቅዱስ ተናጋሪ ኩሎ ፍጥረተ በአሐቲ ምክር ገባሪ። ወበእንተ ስመ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መንፈስ አብ ወወልድ ኀጢአተነ ዘይሰሪ ኀቡዓ ወክሡተ በአሐቲ ሥምረተ ፈጣሪ። እንዘ ናስምክ በዝ ጉንደ ሃይማኖት አስካለ በረከት ዘይፈሪ። ወበእንተ ስማ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ እመ መሐሪ አሜን።

ስብሐት ለአብ፣ ስብሐት ለወልድ፣ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ (ሦስት ጊዜ) ስብሐት ለእግዝእትነ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ስብሐት ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ክርስቶስ በምሕረቱ ይዘክረነ፣ አመ ዳግም ምጽአቱ ኢያተስተኀፍረነ፣ ለስብሐተ ስሙ ያንቅሐነ ወበአምልኮቱ ያድንዓነ። እግዝእትነ ማርያም አዕርጊ ጸሎተነ፣ ወአስተሰርዪ ኩሎ ኃጢአተነ፣ ቅድ መንበሩ ለእግዚእነ። ለዘአብልዐነ ዘንተ ኅብስተ ወለዘአ ስተየነ ዘንተ ጽዋዓ፣ ወለዘሠርዐ ለነ ሲሳየነ ወአራዘነ ወለዘተ ዐገሠ ለነ ኩሎ ኃጢአተነ፣ ወለዘወሀበነ ሥጋሁ ቅዱስ ወደሞ ክቡረ ወለዘአብ ጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት።

ነሀብ ሎቱ ስብሐተ ወአኰቴተ ለእግዚአብሔር ልዑል ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር። ይትአኰት ወይሳባሕ ስሙ ለእግዚአብሔር አምላክነ ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት፤ የሚለው የምስጋና ጸሎት ሲፈጸም፣ታላቁ ካህን ጸሎተ ቡራኬን አድርሰው አቡነ ዘበሰማያት እንዲጸለይ ያዛሉ። ቀጥሎም የብቡ ለእግዚአብሔር በኵሎ ምድር፤ የሚለው መዝሙር 99 ከተነበበ

በኋላ፣ የነበረው ወንጌላዊ ዘመን አለፈ፤ የሚመጣው ወንጌላዊ ዘመን ተተካ ተብሎ ሲታወጅ፣ የብቡ ለእግዚአብሔር ተብሎ እንደተነገረው ሁሉም ሕዝብ ከዚህ ላደረሰን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ብሎ እልል፣ እልል ይላል። እግዚአብሔርንም ያመሰግናል።

## የአሥርቆት ሥርዓት በአማርኛ

አሥርቆት ማለት የሌሊቱን መባቻ በጨረቃ የመዓልቱን መባቻ በፀሐይ ቈጥሮ ለይቶ መናገር ነው። የአሥርቆቱ ሥርዓት በልሳነ ግእዝ ተጽፏል። አሁን ደግሞ ከግእዝ ወደ አማርኛ ተርጉመን የ2003 ዓ.ም. ምሳሌ አድርገን ከዚህ በታች እናሳያለን።

## የምስጋና ጸሎት

በጎ ነገር ያደረገልንን ቸር ይቅር ባይ የሚሆን የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አባት እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። ከመከራ ሰውሮ ረድቶናልና፣ ጠብቆናልና፣ በረድኤትም ተቀብሎናልና፣ አጽንቶ ጠብቆ እስከዚች ሰዓት አድርሶናልና። አሁንም ባለ ዘመናችን ሁሉ ይጠብቀን ዘንድ ክብርት በምትሆን በዚች ቀን ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔርን በፍጹም ፍቅር እንለምነው።

ጸልዩ፡- (በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ... ይጸለያል)

ሁሉን የምትገዛ አቤቱ ጌታችን እግዚአብሔር የጌታችን የመድኃኒታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት በሁሉ ላይ፣ ስለ ሁሉም በምትሠራው ሥራ እናመሰግንሃለን። ከመከራ ሠውረኸናልና፣ በመከራም ጊዜ ረድተኸናልና፣ ከመከራ ጠብቀኸናልና፣ በልጅነትም አቅርበኸናልና፣ በረድኤት ጠብቀኸናልና፣ አጽንተህ ጠብቀህ እስከዚች ሰዓት አድርሰኸናልና።

እግዚአብሔር ይምረን ዘንድ ይቅርታውም በላያችን ያደርግ ዘንድ እሹ ለምኑ። ስለእኛ ጸሎቱን ልመናውን ከቅዱሳን ይቀበል ዘንድ። ሁልጊዜ በጎ ነገር በሚያደረግልን ገንዘብ ክቡር ከሚሆን





ከመንፈሳዊ ምሥጢር አንድነቱን እንድንቀበል የበቃን ያደርገን ዘንድ ኃጢአታችንንም ይቅር ይለን ዘንድ። ኪርያላይሶን።

ስለዚህም ከቸርነትህ እንሻለን እንማልዳለን። ሰውን የምትወድ አቤቱ! ክብርት የምትሆን ይህችን ዕለት እንፈጽም ዘንድ መፈጸሙን ስጠን። ያለ ዘመናችን ሁሉ በፍጹም ፍቅር አንተን ከመፍራት ጋራ ቅንዓትን ሁሉ፣ መከራውንም ሁሉ፣ የሰይጣንን ሥራ ሁሉ፣ የክፉ ሰዎችንም፣ የሰይጣንን ጦር፣ የተሠወረውንም፣ የተገለጸውንም አቤቱ ከእኔ አርቅ። ከሕዝብህም ሁሉ አርቅላቸው። ያንተ ማደሪያ ከሚሆን ከዚህም ቦታ አርቅ። በጎዉን ነገር ሁሉ ያማረውን የሚሻለዉን ስጠን።

ዲያብሎስን ድል እንነሣ ዘንድ ሥልጣንን የሰጠኸን አንተ ነህና። ወደ መከራ አታግባን፣ ከክፉ ነገር ሁሉ አድነን እንጂ። አንድ ልጅህ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ፍቅር ብሎ ባደረገው ቸርነት ክብር ምስጋና ያለው ጽንዕ ይገባዋል። ከርሱ ጋር መድኀኒት ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጋር ካንተ ጋር የሚተካከል ቀድሞም፣ ዛሬም መቸውንም ለዘለዓለሙ አሜን።

ከጌታችንና ከአምላካችን ከመድኃኒታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግና ትእዛዝ የተገኘው የዘመናትና የዓመታት ቍጥር፣ የሌሊትና የመዓልት ወሮች መባቻ አቈጣጠር ሥርዓት በምንናገርበት በዛሬው ቀን ለእግዚአብሔር ምስጋናን እያቀረብን፣ አሁን ካለንበት ከወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ዘመን እንዳደረሰን እንዲሁም ወደ ዜናዊው ቅዱስ ዮሐንስ ዘመን እንዲያደርሰን ፈቃዱ ይሁን አሜን።

ዓመተ ዓለም በፀሐይ 7503 ዓመት፣ በጨረቃ 7732 ዓመት ከ9 ወር ነው። ይህ ዓመተ ዓለም መዋዕለ ዓለም ይባላል። ከዚሁም፡- በፀሐይ 5500 ዓመት፣ በጨረቃ 5668 ዓመት 10 ወር ከ9 ቀን ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኵነኔ ዘመነ ብሉይ ይባላል። እንዲሁም በፀሐይ 2003 ዓመት፣ በጨረቃ 2063 ዓመት 10 ወር 21 ቀን ዓመተ ሥጋዌ ዘመነ መሢሕ ይባላል። በፀሐይና በጨረቃ ጥምር



www.ethiopianorthodox.org

አቈጣጠርም 2011 ዓመት ይሆናል፡፡ ይህም ዓመተ ምሕረት ዘመነ ሐዲስ ይባላል፡፡ (አቡሻህር አንቀጽ 26)፡፡

ዛሬ በዚሁ ቀን ከመስከረም ወር መባቻ እንደደረሰን እንዲሁም ወደ ጥቅምት ወር መባቻ በሰላም እንዲያደርሰን ፈቃዱ ይሁን አሜን፡፡

| | |
|---|---|
| የሌሊት መባቻ | 28፣ |
| የጨረቃ መባቻ | 2፣ |
| የመዓልት መባቻ | 1፣ |
| ዕለተ ዮሐንስ | 7፣ |
| ጥንተ ቀመር | 5፣ |
| ጥንተዮን | 4 ነው፡፡ |

ፀሐይ ከታላላቆቹ መዓርጋት በአንደኛው ማዕርግ በአራተኛው ደጃፍ በሚዛን ማኀፈድ፣ በሕልመልሜሴክ የምግብና ወራት በፀጋመ ሰማይ ሳለ፣ የጨረቃ ተረፍ 26፣ የፀሐይ ተረፍ 4 ሆነ፡፡ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡፡ አሜን፡፡ ይህ የመስከረም 1 ቀን የአሥርቆት ሥርዓት ነው፡፡ የሌሎቹ ዕለታት አሥርቆትም በዚሁ መንገድ ማውጣት ይቻላል፡፡

ስብሐት ለእግዚአ አዝማን ወዓመታት፣ ወመዋዕል ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

## የቀመር ጥንታት

የቀመር ጥንታት ማለት ዐቢይ ቀመር የሚነሣባቸው ዕለታት ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በሐሳበ ድሜጥሮስ፣ በሐሳበ ቢዘን፣ በሐሳበ ጉንዳጉንዲና በሐሳበ ሳቤላ ዓመተ ዓለም ሲቈጠር ዐቢይ ቀመር የሚነሣባቸው ዕለታት የተለያዩ ስለሆኑ ነው፡፡ ያውም እንዲህ ነው፡-



www.ethiopianorthodox.org



የሐሳበ ድሜጥሮስ ጥንተ ቀመር ማክሰኞ ነው፡፡ ማክሰኞ ደረቅ ምድር የታየበት፣ መዠመሪያው ወር ሚያዝያ የባተበት፣ ዕፅዋት አዝርዕት አትክልት የበቀሉበት ዕለት ነውና፡፡ ስለዚህም ዕለተ ጠቢባን የሚባሉትን እሑድና ሰኞን ወደኋላ ትቶ ቀመሩን በማክሰኞ ይዠምራል፡፡

የሐሳበ ቢዘን ጥንተ ቀመር እሑድ ነው፡፡ እሑድ ዓለም የተፈጠረበትና የዕለታትም ጥንት ስለሆነ የቀመር መነሻ ሊሆን የሚገባ እሑድ ነው እንጂ ሌላ ቀን አይደለም ብለው የደብረ ቢዘን ገዳም ሊቃውንት ስለወሰኑ ነው፡፡ ስለዚህም ሊቃውንቱ ዐሥራ ሁለቱን ንኡስ ቀመር ወደኋላ ትተው እሑድ ርእሰ አንቀጽ ከሆነበት ከ13ኛው አንቀጸ አበቅቴ ዠምረው ቀመራቸውን ይቈጥራሉ፡፡

የሐሳበ ጉንዳጉንዲ ጥንተ ቀመር ዓርብ ነው፡፡ ምክንያቱም ዓርብ አዳም የተፈጠረበት ቀን ስለሆነና መጽሐፍ ቅዱስም የአበውን ዕድሜ ሲቈጥር ከአዳም ዠምሮ ስለሆነ የጉንዳንጉንዲ ገዳም ሊቃውንት የቀመር መዠመሪያ ሊሆን የሚገባ ዓርብ ነው እንጂ ሌላ ቀን አይደለም ብለው ስለወሰኑ ነው፡፡ ስለዚህ ሊቃውንቱ ስድስቱን ማእከላዊ ቀመር ወደኋላ ትተው ዓርብ ርእሰ አንቀጽ ከሆነበት ከ25ኛው አንቀጸ አበቅቴ ዠምረው ቀመራቸውን ይቈጥራሉ፡፡

ሐሳበ ሳቤላ አንዱን ንኡስ ቀመር ወደኋላ ትቶ ዘመነ ዮሐንስና ዕለተ ዓርብ በሚገናኙበት በሁለተኛው አንቀጸ አበቅቴ ቀመሩን ይዠምራሉ፡፡ ምክንያቱም የጌታችንን ቅድምና ለማስረዳት ዮሐንስ ወንጌላዊ በመዠመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበር ብሎ የዳግማዊ አዳም የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቅድምና ስለጻፈና ዓርብም ቀዳማዊ አዳም የተፈጠረበት ዕለት ስለሆነ የሁለቱን ቅድሞና ለማነጻጸር ወንጌላዊውና ዕለተ ዓርብ በሚገናኙበት ርእሰ አንቀጽ ቀመሩን ይዠምራል፡፡

ይህ ሐሳብ ፈካሪተ ሕልም የሆነች ሳቤላ ወለተ ሕርቃል የምትባል ሴት የተናገረችው ነው፡፡ ታሪኩ እንዲህ ነው፡፡ በሰማይ

ዘጠኝ ፀሐይ በሕልማችን አይተናልና ምሥጢሩ ምንድን ነው ብለው ለጠየቅዋት ሰዎች ዘጠኝ ፀሐይ ማለት ዘጠኝ ክፍለ ዘመን ነው፡፡ እግዚአብሔር በዘመናት የሚሆነውን ሁሉ ገልጾላችኋል ብላ በያንዳንዱ ፀሐይ ማለት በያንዳንዱ ክፍለ ዘመን የሚሆነውን ነገር ሁሉ አስረድታቸዋለች፡፡

በተለይም በስድስተኛው ፀሐይ ማለት በስድስተኛው ክፍለ ዘመን በአርያም የሚኖር ልዑል በድንግል ማኅፀን ተፀንሶ በይሁዳ አገር ይወለዳል ብላ ትንቢት ተናግራለች፡፡ (መጽሐፈ ሳቤላ)፡፡

መምህራንም ይህ ራእይ ምሥጢረ ሥጋዌን የሚገልጽ ስለሆነ፣ 7 ሺህ ዓመት በ9 ቀምረው ከዘጠኙ ፀሐይ ስምንቱ ለያንዳንዳቸው 778 ዓመት ሲደርሳቸው የዘጠነኛው ፀሐይ ድርሻ ግን 776 ዓመት ሆኖ ጠቅላላው ድምር 7000 ዓመት በመሆኑ ከቀመር ገብቶ እንዲቈጠር ወስነዋል፡፡

በዚህ ውሳኔ መሠረት የጐንደር ሊቃውንት በ7 ሺህ 177 ዓመተ ዓለም አጼ ኢያሱ በነገሡ በ3ኛው ዓመት በ1677 ዓ.ም. የሐሳበ ሳቤላን፣ የሐሳበ ቢዘንን፣ የሐሳበ ጉንዳጉንዲን ልዩነት መርምረውና አጥንተው ውጤቱን በግእዝ ቋንቋ መዝግበውታል፡፡ ያውም እንዲህ ነው፡፡

*ሐሳበ ሳቤላ ፸ወ፩፻፶ወ፰ ውእቱ፡፡ ሶበ ይትቄመር ዝንቱ ይከውን ፲ወ፫ ቀመረ ተረፈ ቀመሩ ይከውን ፪፻፵ወ፪ ዓመት፡፡ ወእም ዓመተ ዚአነ ፲ወ፱ ዓመት የሐጽጽ፡፡*

*ሐሳበ ቢዘን ፷ወ፱፻፵ወ፱ ዓመት ውእቱ ሶበ ይትቄመር ዝንቱ ይከውን ፲ወ፫ ቀመረ፡፡ ወተረፈ ቀመሩሂ ይከውን ፴ወ፫ ዓመት ወእም ዓመተ ዚአነ ፪፻፳ወ፰ ዓመት የሐጽጽ፡፡*

*ሐሳበ ጐንዳጉንዲ ፷ወ፯፻፳ወ፩ ዓመት ውእቱ ወሶበ ይትቄመር ይከውን ፲ወ፪ ቀመረ ወተረፈ ቀመሩሂ ይከውን ፪፻፴ወ፯ ዓመት፡፡ ወእም ዓመተ ዚአነ ፬፻፶ወ፮ ዓመት የሐጽጽ፡፡*





*ሐሳበ ግብጻውያን ዘውእቱ ዓመተ ሰማዕታት ፲ወ፬፻ ዓመት ወሶበ ይትቄመር ይከውን ፪ ቀመረ፡፡ ወተረፈ ቀመሩሂ ፫፻፴ወ፮ ዓመት ወእም ዓመተ ዚአነ ፶ወ፯፻፸ወ፯ ዓመት የሐጽጽ፡፡* ማለትም፡-

እሊህ የሐሳበ ዘመን መምህራን እንዲህ ዘመናትን በልዩ ልዩ ሐሳብና ቀመር እየቀመሩ የተነገረውን ትንቢት የተቈጠረውን ሱባዔ ሐተታ ያስተምራሉ፡፡

ይህ ወደ አማርኛ ሲተረጐምም እንዲህ ነው
ሐሳበ ሳቤላ የሚባለው የዘመን ቊጥር 7158 ዓመት ነው፡፡ ይህ በ532 ዐቢይ ቀመር ሲቀመር 13 ዐቢይ ቀመር ሆኖ 242 ዓመት ይተርፋል፡፡ ከተቀመረበት 7177 ዓመተ ዓለም 19 ዓመትን ያጐድላል፡፡

ሐሳበ ቢዘን የሚባለው የዘመን ቊጥር 6949 ዓመት ነው፡፡ ይህ በዐቢይ ቀመር ሲቀመር 13 ቀመር ሆኖ 33 ዓመት ይተርፋል፡፡ ከተቀመረበት 7177 ዓመተ ዓለም 228 ዓመትን ያጐድላል፡፡

ሐሳበ ጉንዳጉንዲ የተባለው የዘመን ቊጥር 6721 ዓመት ነው፡፡ ይህ በዐቢይ ቀመር ሲቀመር 12 ዐቢይ ቀመር ሆኖ 237 ዓመት ይተርፋል፡፡ ከተቀመረበት 7177 ዓመተ ዓለም 456 ዓመትን ያጐድላል፡፡

ሐሳበ ግብጻውያን የተባለው ዓመተ ሰማዕታት 1400 ዓመት ነው፡፡ ይህ በዐቢይ ቀመር ሲቀመር 2 ዐቢይ ቀመር ሆኖ 336 ዓመት ይተርፋል፡፡ ከተቀመረበት 7177 ዓመተ ዓለም 5777 ዓመትን ያጐድላል፡፡

ይህን ስሌት ያጠኑና የመረመሩ መምህራን ዓመተ ዓለምን በዐቢይ ቀመር እየቀመሩ ልዩ ልዩ መነሻ ባላቸው ሐሳባት መካከል ያለውን ልዩነት ያስተምራሉ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሦስት

## መጽሔተ ሕርግራግ

| 7945 | 2445 | 497 | 3 | 2 | ቅ | ማቴ | 4 | 22 | 8 | የ/14 | የ/28 | መ/25 | ሚ/16 | ሚ/21 | ሚ/23 | ግ/17 | ሰ/02 | ሰ/12 | ሰ/13 | ሰ/15 |
| 7946 | 2446 | 498 | 4 | 3 | እ | ማር | 5 | 3 | 27 | ጥ/29 | የ/13 | መ/10 | ሚ/01 | ሚ/06 | ሚ/08 | ግ/02 | ግ/17 | ግ/27 | ግ/28 | ግ/30 |
| 7947 | 2447 | 499 | 5 | 4 | ሰ | ሉቃ | 6 | 14 | 16 | ጥ/21 | የ/05 | መ/02 | መ/23 | መ/28 | መ/30 | ሚ/24 | ግ/09 | ግ/19 | ግ/20 | ግ/22 |
| 7948 | 2448 | 500 | 6 | 5 | ረ | ዮሐ | 1 | 25 | 5 | የ/10 | የ/24 | መ/21 | ሚ/12 | ሚ/17 | ሚ/19 | ግ/13 | ግ/28 | ሰ/08 | ሰ/09 | ሰ/11 |
| 7949 | 2449 | 501 | 7 | 6 | ሐ | ማቴ | 2 | 6 | 24 | የ/02 | የ/16 | መ/13 | ሚ/04 | ሚ/09 | ሚ/11 | ግ/05 | ግ/20 | ግ/30 | ሰ/01 | ሰ/03 |
| 7950 | 2450 | 502 | 8 | 7 | ዓ | ማር | 3 | 17 | 13 | የ/15 | የ/29 | መ/26 | ሚ/17 | ሚ/22 | ሚ/24 | ግ/18 | ሰ/03 | ሰ/13 | ሰ/14 | ሰ/16 |
| 7951 | 2451 | 503 | 9 | 8 | ቅ | ሉቃ | 4 | 28 | 2 | የ/07 | የ/21 | መ/18 | ሚ/09 | ሚ/14 | ሚ/16 | ግ/10 | ግ/25 | ሰ/05 | ሰ/06 | ሰ/08 |
| 7952 | 2452 | 504 | 10 | 9 | ሰ | ዮሐ | 6 | 9 | 21 | ጥ/28 | የ/12 | መ/09 | መ/30 | ሚ/05 | ሚ/07 | ግ/01 | ግ/16 | ግ/26 | ግ/27 | ግ/29 |
| 7953 | 2453 | 505 | 11 | 10 | ማ | ማቴ | 7 | 20 | 10 | የ/18 | መ/02 | መ/29 | ሚ/20 | ሚ/25 | ሚ/27 | ግ/21 | ሰ/06 | ሰ/16 | ሰ/17 | ሰ/19 |
| 7954 | 2454 | 506 | 12 | 11 | ረ | ማር | 1 | 1 | 29 | የ/03 | የ/17 | መ/14 | ሚ/05 | ሚ/10 | ሚ/12 | ግ/06 | ግ/21 | ሰ/01 | ሰ/02 | ሰ/04 |
| 7955 | 2455 | 507 | 13 | 12 | ሐ | ሉቃ | 2 | 12 | 18 | ጥ/25 | የ/09 | መ/06 | መ/27 | ሚ/02 | ሚ/04 | ሚ/28 | ግ/13 | ግ/23 | ግ/24 | ግ/26 |
| 7956 | 2456 | 508 | 14 | 13 | ቅ | ዮሐ | 4 | 23 | 7 | የ/14 | የ/28 | መ/25 | ሚ/16 | ሚ/21 | ሚ/23 | ግ/17 | ሰ/02 | ሰ/12 | ሰ/13 | ሰ/15 |
| 7957 | 2457 | 509 | 15 | 14 | እ | ማቴ | 5 | 4 | 26 | ጥ/29 | የ/13 | መ/10 | ሚ/01 | ሚ/06 | ሚ/08 | ግ/02 | ግ/17 | ግ/27 | ግ/28 | ግ/30 |
| 7958 | 2458 | 510 | 16 | 15 | ሰ | ማር | 6 | 15 | 15 | ጥ/21 | የ/05 | መ/02 | መ/23 | መ/28 | መ/30 | ሚ/24 | ግ/09 | ግ/19 | ግ/20 | ግ/22 |
| 7959 | 2459 | 511 | 17 | 16 | ማ | ሉቃ | 7 | 26 | 4 | የ/11 | የ/25 | መ/22 | ሚ/13 | ሚ/18 | ሚ/20 | ግ/14 | ግ/29 | ሰ/09 | ሰ/10 | ሰ/12 |
| 7960 | 2460 | 512 | 18 | 17 | ሐ | ዮሐ | 2 | 7 | 23 | ጥ/25 | የ/09 | መ/06 | መ/27 | ሚ/02 | ሚ/04 | ሚ/28 | ግ/13 | ግ/23 | ግ/24 | ግ/26 |
| 7961 | 2461 | 513 | 19 | 18 | ዓ | ማቴ | 3 | 18 | 12 | የ/15 | የ/29 | መ/26 | ሚ/17 | ሚ/22 | ሚ/24 | ግ/18 | ሰ/03 | ሰ/13 | ሰ/14 | ሰ/16 |

## ሰንጠረዥ 7

| ዓመተ ዓለም | ዓመተ ምሕረት | ዐውደ ቀመር | ዐውደ ወርኅ | ዐውደ ወንበር | ዐውደ ዓመት: ዕለተ ዮሐንስ | ዐውደ ዓመት: ወንጌላዊ | ጥንተ ዮን | አበቅቴ | መጥቅዕ | ጾመ ነነዌ | በዓተ ጾም | ደብረ ዘይት | ሆሣዕና | ስቅለት | ፋሲካ | ረክበ ካህናት | ዕርገት | በዓለ 50 (ጰራቅሊጦስ) | ጾመ ሐዋርያት | ጾመ ድኅነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7962 | 2462 | 514 | 1 | አ | ቅ | ማር | 4 | አ | 30 | የ/07 | የ/21 | መ/18 | ሚ/09 | ሚ/14 | ሚ/16 | ግ/10 | ግ/25 | ሰ/05 | ሰ/06 | ሰ/08 |
| 7963 | 2463 | 515 | 2 | 1 | እ | ሉቃ | 5 | 11 | 19 | ጥ/22 | የ/06 | መ/03 | መ/24 | መ/29 | ሚ/01 | ሚ/25 | ግ/10 | ግ/20 | ግ/21 | ግ/23 |
| 7964 | 2464 | 516 | 3 | 2 | ማ | ዮሐ | 7 | 22 | 8 | የ/11 | የ/25 | መ/22 | ሚ/13 | ሚ/18 | ሚ/20 | ግ/14 | ግ/29 | ሰ/09 | ሰ/10 | ሰ/12 |
| 7965 | 2465 | 517 | 4 | 3 | ረ | ማቴ | 1 | 3 | 27 | የ/03 | የ/17 | መ/14 | ሚ/05 | ሚ/10 | ሚ/12 | ግ/06 | ግ/21 | ሰ/01 | ሰ/02 | ሰ/04 |
| 7966 | 2466 | 518 | 5 | 4 | ሐ | ማር | 2 | 14 | 16 | ጥ/18 | የ/02 | የ/29 | መ/20 | መ/25 | መ/27 | ሚ/21 | ግ/06 | ግ/16 | ግ/17 | ግ/19 |
| 7967 | 2467 | 519 | 6 | 5 | ዓ | ሉቃ | 3 | 25 | 5 | የ/08 | የ/22 | መ/19 | ሚ/10 | ሚ/15 | ሚ/17 | ግ/11 | ግ/26 | ሰ/06 | ሰ/07 | ሰ/09 |
| 7968 | 2468 | 520 | 7 | 6 | እ | ዮሐ | 5 | 6 | 24 | ጥ/29 | የ/13 | መ/10 | ሚ/01 | ሚ/06 | ሚ/08 | ግ/02 | ግ/17 | ግ/27 | ግ/28 | ግ/30 |
| 7969 | 2469 | 521 | 8 | 7 | ሰ | ማቴ | 6 | 17 | 13 | የ/19 | መ/03 | መ/30 | ሚ/21 | ሚ/26 | ሚ/28 | ግ/22 | ሰ/07 | ሰ/17 | ሰ/18 | ሰ/20 |
| 7970 | 2470 | 522 | 9 | 8 | ማ | ማር | 7 | 28 | 2 | የ/04 | የ/18 | መ/15 | ሚ/06 | ሚ/11 | ሚ/13 | ግ/07 | ግ/22 | ሰ/02 | ሰ/03 | ሰ/05 |
| 7971 | 2471 | 523 | 10 | 9 | ረ | ሉቃ | 1 | 9 | 21 | ጥ/26 | የ/10 | መ/07 | መ/28 | ሚ/03 | ሚ/05 | ሚ/29 | ግ/14 | ግ/24 | ግ/25 | ግ/27 |
| 7972 | 2472 | 524 | 11 | 10 | ዓ | ዮሐ | 3 | 20 | 10 | የ/15 | የ/29 | መ/26 | ሚ/17 | ሚ/22 | ሚ/024 | ግ/18 | ሰ/03 | ሰ/13 | ሰ/14 | ሰ/16 |
| 7973 | 2473 | 525 | 12 | 11 | ቅ | ማቴ | 4 | 1 | 29 | የ/07 | የ/21 | መ/18 | ሚ/09 | ሚ/14 | ሚ/16 | ግ/10 | ግ/25 | ሰ/05 | ሰ/06 | ሰ/08 |
| 7974 | 2474 | 526 | 13 | 12 | እ | ማር | 5 | 12 | 18 | ጥ/22 | የ/06 | መ/03 | መ/24 | መ/29 | ሚ/01 | ሚ/25 | ግ/10 | ግ/20 | ግ/21 | ግ/23 |
| 7975 | 2475 | 527 | 14 | 13 | ሰ | ሉቃ | 6 | 23 | 7 | የ/12 | የ/26 | መ/23 | ሚ/14 | ሚ/19 | ሚ/21 | ግ/15 | ግ/30 | ሰ/10 | ሰ/11 | ሰ/13 |
| 7976 | 2476 | 528 | 15 | 14 | ረ | ዮሐ | 1 | 4 | 26 | የ/03 | የ/17 | መ/14 | ሚ/05 | ሚ/10 | ሚ/12 | ግ/06 | ግ/21 | ሰ/01 | ሰ/02 | ሰ/04 |
| 7977 | 2477 | 529 | 16 | 15 | ሐ | ማቴ | 2 | 15 | 15 | ጥ/18 | የ/02 | የ/29 | መ/20 | መ/25 | መ/27 | ሚ/21 | ግ/06 | ግ/16 | ግ/17 | ግ/19 |
| 7978 | 2478 | 530 | 17 | 16 | ዓ | ማር | 3 | 26 | 4 | የ/08 | የ/22 | መ/19 | ሚ/10 | ሚ/15 | ሚ/17 | ግ/11 | ግ/26 | ሰ/06 | ሰ/07 | ሰ/09 |
| 7979 | 2479 | 531 | 18 | 17 | ቅ | ሉቃ | 4 | 7 | 23 | ጥ/30 | የ/14 | መ/11 | ሚ/02 | ሚ/07 | ሚ/09 | ግ/03 | ግ/18 | ግ/28 | ግ/29 | ሰ/01 |
| 7980 | 2480 | 532 | 19 | 18 | ሰ | ዮሐ | 6 | 18 | 12 | የ/19 | መ/03 | መ/30 | ሚ/21 | ሚ/26 | ሚ/28 | ግ/22 | ሰ/07 | ሰ/17 | ሰ/18 | ሰ/20 |

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አራት

# እምርት ዕለት

እምርት ዕለት ማለት የታወቀች ዕለት ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የተከናወኑ ታሪኮች የተፈጸሙበትን ዓመትና ዕለት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ሐሳብ መሠረት ጠንቅቆ የሚያሳይ ነው።

## ቀመረ አዳም

አዳም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ 7 ሺሕ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ ያለ ዘመን ቀመረ አዳም ይባላል። *ናሁ ሐልቀ ቀመርነ ዘተውህበ ለአቡነ አዳም ዘውእቱ ሰብዓ ምእት ዓመት*። ለአዳም ተሰጥቶት የነበረ ቀመርም 7 ሺሕ ዓመት ነበር። እርሱም እነሆ አለቀ እንዲል (ትውፊታዊ ሐሳበ ዘመን ገጽ 4)።

እግዚአብሔር *ለይኩን ብርሃን*- ብርሃን ይሁን ብሎ በሦስቱ የብርሃን ዕለታት የተፈጠሩትን ፍጥረታት ፈጠረ። እግዚአብሔርም ያንን መልካም እንደሆነ አየ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ሦስተኛ ቀን፤ እስከዚህ ድረስ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት አልተፈጠሩም ነበር። በአራተኛው ቀን በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ ሁለት ታላላቅ ብርሃናትን በሰማይ ጠፈር ላይ አደረገ። እግዚአብሔርም ያንን መልካም እንደ ሆነ አየ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አራተኛ ቀን። በአምስተኛው ቀን እግዚአብሔር እንዲሁ *ሥራውን* ሠራ። እግዚአብሔርም ያንን መልካም እንደሆነ አየ። ዓለም ከተፈጠረበት ከእሑድ ጀምሮ እስከ ኀሙስ ያሉትን ቀኖች የጳጉሜን ዕለታት ናቸው። እስከዚህ ድረስ ሰው አልተፈጠረም ነበር። በስድስተኛውም ቀን እግዚአብሔር ሰውን ፈጠረ። በመልኩ በእግዚአብሔር መልክ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ባረካቸውም፣ ፍጥረት ሁሉ ይገዙ ዘንድም *ሥልጣን* ሰጣቸው። እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ። እነሆም እጅግ መልካም ሆነ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ስድስተኛ ቀን (ዘፍ. 1፥3-31)።





## ዓመተ ሕይወቱ ለአዳም

በመጀመርያው የአዳም ዓመተ ሕይወት አልቦ አበቅቴ ነበር። በ2ኛው የአዳም ዓመተ ሕይወት 1 ወንበር፣ 11 አበቅቴ፣ 19 መጥቅዕ ነበር። በ3ኛው የአዳም ዓመተ ሕይወት 2 ወንበር፣ 22 አበቅቴ፣ 8 መጥቅዕ ነበር። በ4ኛው የአዳም ዓመተ ሕይወት 3 ወንበር 3 አበቅቴ፣ 27 መጥቅዕ ነበር። እንዲህ እየተቀመረ እስከ 18 ዓመተ አበቅቴ ይቈጠራል። በ19ኛው የአዳም ዓመተ ሕይወት አልቦ አበቅቴ ሆነ። ይህ የዓመተ አበቅቴ መመላለሻ የሆነው 19 ዓመት *ንኡስ ቀመር*፣ ዐውደ አበቅቴ ወይም ዐውደ ወርኀ ይባላል። *እስመ ለዛቲሰ ዓመት ፲ወ፱ ገብራ ሙሴ በጥበበ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል ዘውእቱ ፲ወ፱ ዓመት ዘይገብሩ ባቲ ፍሥሐ አይሁድኒ ወክርስቲያንኒ*። (አቡሻህር አንቀጽ ፵፬) ማለት ይህ 19 ዓመት ሙሴ በእግዚአብሔር ጥበብ ለእስራኤል ልጆች የሠራላቸው የቀመር ሥርዓት ነው። ይህም 19 ዓመት አይሁድና ክርስቲያኖች በዓለ ፍሥሕ የሚውልበትን ዕለት ለይተው የሚያውቁበት ስሌት ነው።

አንድ ንኡስ ቀመር አራት ጊዜ ሲመላለስ አንድ ማእከላዊ ቀመር ይሆናል። የማእከላዊ ቀመር ቊጥሩ (19×4)=76 ዓመት ነው። አንድ ማእከላዊ ቀመርም ሰባት ጊዜ ሲመላለስ አንድ ዐቢይ ቀመር ይሆናል። የዐቢይ ቀመር ቊጥሩ (76×7)=532 ዓመት ነው። ቀመረ አዳም የተባለው 7 ሺሕ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ እንዲሁ እየተቀመረ ይቈጠራል።

እሊህ ሰባት ሺሕ ዓመታት ከ7 ዕለታት የተገኙ ናቸው። *እሊህ ሰባት ሺሕ ዓመታት እማንቱ ወተውህቦን ለለአሐቲ ዓለም ብሂል ሰባቱ ዕለታት በበዐሠርቱ ምእት ዓመት*። ዓለም ማለት:- ሰባቱ ዕለታት ናቸው። ለያንዳንዳቸውም አንዳንድ ሺሕ ዓመት ተሰጥቷቸዋል እንዲል (መርሐ ዕዉር)። ቅዱስ ዳዊትም *እስመ ዐሠርቱ ምእት ዓመት በቅድሜከ ከመ ዕለት እንተ ትማልም ኀለፈት፣ ወሰዓተ ሌሊት* በቅድሜከ- በሰው ዘንድ ሺሕ ዓመት ባንተ ዘንድ *ምኑን ዓመታት በቅድሜከ*- በሰው ዘንድ ሺሕ ዓመት ባንተ ዘንድ ትናንት እንደ አለፈች እንደ አንዲት ቀን ናት። በሰው ዘንድ ሺሕ ሌሊትና ብዙ ዘመን ባንተ ዘንድ እንደ ተናቀች እንዳንዲት ሰዓት ናት ብሏል (መዝ. 8፥94-5)። መጽሐፈ ኩፋሌም *እስመ ዐሠርቱ ምእት ዓመት ከመ አሐቲ ዕለት ውስተ ስምዐ ሰማያት*፤ አንድ ሺሕ ዓመት በሰማይ ጽላት እንደአንዲት ቀን ናት (ኩፋሌ 6፥4) ብሏል። ከዚህ በላይ እንደ ተገለጸው አንድ ሺሕ ዓመት በ7 ዕለታት ሲበዛ



www.ethiopianorthodox.org

(1000x7)=7000 ዓመት ይሆናል:: ሰባቱ ሺሕ ዓመት ከ7 ዕለታት የተገኘ መሆኑ በዚህ ይታወቃል::

ዳግመኛም፣

*ወወሀቦ እግዚአብሔር ሰቡዓ መዋዕለ ለዕጓለ እመሕያው ይንበር ዲበ ምድር እስመ ዐሠርቱ ምእት ዓመት አሐቲ ዕለት በኀበ እግዚአብሔር በእንተ ዝንቱ ተጽሕፈ በእንተ ዕፀ አእምሮ እስመ በዕለተ ትበልዑ እምኔሁ ትመውቱ:: ወሶበ ዐለወ አዳም ዘንተ ትእዛዘ በጽሐ ሥልጣነ ሞት ላዕሌሁ በተሰዓቱ ምእት ወሠላሳ ዓመተ ሕይወቱ ወበእንተዝ ኢፈጸመ አዳም ዓመታቲሃ ለዛቲ ዕለት:: ወአሕጸጸ ሰብዓ ዓመተ እምዕለተ እግዚአብሔር ወውእቱ መቅድመ ተቀብረ ውስተ ምድር ::*

ይህም ማለት፣

እግዚአብሔር በምድር ላይ ይኖር ዘንድ ለሰው ልጅ ሰባት ዕለታትን ሰጠው ሺሕ ዓመት በሰው ዘንድ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ አንዲት ቀን ናትና:: ስለዚህም መልካሙንና ክፋውን ከምስታስታውቅ ዛፍ በበላችሁበት ቀን ትሞታላችሁ ተብሎ ተጻፈ:: አዳም ይህን ትእዛዝ በተላለፈ ጊዜ በዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት ዕድሜው ሞት በርሱ ላይ ሠለጠነ:: ስለዚህም አዳም የዚች ዕለት ዓመታትን አልፈጸመም:: ከእግዚአብሔር ዕለት ሰባ ዓመትን አጐደለ እንጂ:: እርሱም አስቀድሞ በምድር ውስጥ ተቀበረ (ኩፋሌ 6፥3፣ 4)::

ነገር ግን አዳም እስከ ሺሕ ዓመት ድረስ በጽድቅና በርትዕ፣ በንጽሐ ጠባይዕ ጸንቶ ኑሮ ቢሆን ብልየትና ሞት ሳያገኙት ረቆ ታድሶ ከዓለመ ሥጋ ወደ ዓለመ ነፍስ ሲያርግ መንግሥተ ሰማያትንም ሊገባ ነበር:: ነገር ግን አዳም በሕይወተ ሥጋ በኖረበት ዘመን በጽድቅና በርትዕ ጸንቶ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ትእዛዝ ስላልፈጸመ በርሱና በልጆቹ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ ተፈረደባቸው:: ስለዚህም ቅ.ጳውሎስ በሮሜ 5፥14 *ነገር ግን በአዳም ኃጢአት ምክንያት ከአዳም እስከ ሙሴ የበደሉትንም ያልበደሉትንም ሞት ገዛቸው:: ሁሉ በአዳም አምሳል ተፈጥረዋልና* ብሎ ጻፈ::





## ዓመተ አዳም ወኖኅ

*ወከሠተ እግዚአብሔር ለሙሴ ከመ ትልቁ ኃምስቱ አውራኅ ምእት ወኀምሳ ዕለት ውእቱ:: ወበዝንቱ ቃል አንቅሖ ለአእምሮ ዓመተ አዳም ወኖኅ::*

ይህም ማለት:- እግዚአብሔር ያምስት ወር ቀን ቍጥር 150 ዕለት እንደሆነ ለሙሴ ገልጾለታል:: በዚሁም ቃል የአዳምንና የኖኅን ዓመት ለማወቅ አነቃቃው ማለት ነው (አቡሻህር)::

ዳግመኛም የወሮቹ ቀን በጨረቃ ወር ቢቈጠር አንዱ ወር 30፣ አንዱ ወር 29 ሆኖ የመዠመሪያዎቹ 5 ወሮች ቀን ጠቅላላ ቍጥር 148 ዕለት ይሆናል:: የቀደምት ሮማውያን ሰዎችም የዓመታቸው ወሮች ቍጥር የያንዳንዱ ወር ቀን 36 ሆኖ 10 ወር ይሆናል:: በዚሁ ስሌት ያምስት ወሮች ቀን ጠቅላላ ድምር 180 ቀን ይሆናል:: እንዲሁም በዮናናውያንና በሶርያውያን ዓመትም ላንዱ ወር 31፣ ላንዱ ወር 30 ቀን ይደርሰዋል:: በዚሁ ስሌት ያምስት ወር ቀን ቍጥር በእነርሱ ዘንድ 153 ቀን ይሆናል::

በኦሪት ዘፍጥረት 8፥3 የተጠቀሱት 150 ዕለታት ግን 5 ወሮች እንደሆኑ በስሌት ተረጋግጧል:: የእነዚህ 5 ወሮች ቀን ቍጥር እንዲህ ተስተካክሎ የተገኘው የያንዳንዱ ወር ቍጥር 30 በሆነው በግብጻውያንና በኢትዮጵያውያን ወሮች እንጂ በጨረቃ ወር ወይም በዮናናውያንና በሮማውያን በሶርያውያንም ወሮች ቀን ቍጥር እንዳይደለ ከዚህ በላይ በተጻፈው ሐተታ ተገልጿል::

የግብጻውያን (ኮፕት/ቅብጥ) እና የኢትዮጵያውያን ዓመት መዠመሪያም የመስከረም ወር መባቻ ነው:: የዓመታቸው መነሻም የዓመተ ዓለም መዠመርያ (ዘፀ 12፥2) ከሆነው ወር በ208 ዕለት ትቀድማለች:: መነሻዋ ዕለተ ሠሉስ መድረሻዋ ዕለተ ሰንበት ነው:: የዓመተ ዓለም መዠመሪያ የተባለውም እሑድ መጋቢት 29 ዕለት ነው:: እሑድም የዕለታት መነሻ ወይም ጥንት ናት:: ይህንንም የሚያስረዳ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 7 ቍጥር 11 ይገኛል:: ያውም እንዲህ ነው:-

በኖኅ ዕድሜ በ6ኛው መቶ ዓመት በ2ኛው ወር ከወሩም በ17ኛው ቀን የጥፋት ውሀ ሆነ ከ150 ቀን በኋላም ውሀው ጐደለ:: መርከቢቱም በ7ኛው ወር ከወሩም በ17ኛው ቀን በአራራት ተራሮች ላይ ዐረፈች ይላል::



www.ethiopianorthodox.org

ኖኅ ከመርከብ ከወጣ በኋላም ልጆቹ ልጆችን ወለዱ ተባዙም:: ከእነርሱም መካከል ተለይቶ የከነዓን ልጅ የካም ልጅ የኖኅ የልጅ ልጅ የሆነው ስሙ ናምሩድ የሚባል ሰው በእነርሱ ላይ ነገሠ:: እርሱም የባቢሎን ሰዎች ለሆኑ ለከለዳውያን አባታቸው ሆነ:: በምድር ላይ የነገሠ የመጀመርያ ንጉሥ እርሱ ነበር::

እንዲሁም የምስር አገር ሰዎች ስሙ መንቅዕ የሚባለውን ሰው በምስር አገራቸው ላይ አነገሡት:: የምስርን ከተማ በኒል ባሕር ወሰን ላይ መንፍ በሚባል ቦታ የመሠረታት እርሱ ነው:: እርሱም የመስሪም ልጅ የካም ልጅ የኖኅ የልጅ ልጅ ነው:: ከተማይቱንም ባባቱ ስም መስሪም ብሎ ሰየማት:: በምድር ላይ የነገሠው ሁለተኛው ንጉሥ እርሱ ነበር:: ታሪክንና ሕግን የሠሩና የመሠረቱ እሊህ ሁለቱ ነገሥታት ናቸው ይባላል::

ይህን ታሪክ የገለጸና ያስረዳ የፀሐይንና የጨረቃን የከዋክብትንም አቈጣጠር መርምሮ የጻፈ በጥሊሞስ የሚባል ጸሐፊ እንደ ሆነ በመጽሐፈ አቡሻህር ተገልጿል:: በተጨማሪም ይህ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የምስራውያን ወሮችና ዓመታት መጠን እንደ ኖኅና ሴት እንደ አዳምም ወሮችና ዓመታት እንደሆኑ ያስረዳል:: ይህም አቈጣጠር በአይሁድ የሌሊት መባቻ በሚያዝያ ወር (ኒሳን) በ14ኛው ሠርቀ ሌሊት ለኅሙስ አጥቢያ እስራኤል በሌሊት ከግብጽ እስከ ወጡ ድረስ ጸንቶ የቈየ ነው:: ንጉሡ እስክንድር የዐውደ ዓመታቸውን መጀመርያ እርሱ ወደ ነገሠበት ዕለት ወደ ታሰረን ቀዳማይ (ጥቅምት) መባቻ እስኪለውጠው ድረስ የእስራኤል የቀን አቈጣጠር እንዲሁ ነበር:: እንዲሁም የምስር ሰዎች መጀመሪያ ዓመት ከንጉሦቻቸው አንዱ እርሱ ወደ ነገሠበት ወደ መስከረም (ተውት) መባቻ ቀን ለወጠው:: ዳግመኛም በዐውደ ጳጉሜን ከሚመላለሱት አራት ዓመታት ሦስቱ የያንዳንዱ ዓመት ዕለት ቍጥር 365 ቀን ሲሆን፣ ያራተኛው ዓመት ዕለት ቍጥር ግን በሠግር ምክንያት 366 ይሆናል:: የዓመታቸው መጀመርያም በነሐሴ (አብ) በ29ኛው ቀን ያውም የመስከረም (ተውት) መባቻ ዕለት ነው:: በሠግር ጊዜ ግን መባቻው በዚሁ ወር በ30ኛው ቀን ይሆናል::

ኢትዮጵያውያንም የዓመታቸው መጀመርያ የመስከረም መባቻን ያደርጋሉ:: እነርሱም ሁለት ታሪኮችን ይከተላሉ:: እነዚህም ታሪከ ሥጋዌና ታሪከ ዲዮቅልጥያኖስ ናቸው (አቡሻህር አንቀጽ 8)::





## የሺሕ ዓመት መነሻና መድረሻ ዕለት

የብሉይና የሐሳበ ዘመን መምህራን ጥንተ ቀመር ማክሰኞን መነሻ በማድረግ በዐውደ ፀሐይና በሰባዔ እየቀመሩ ከሰባቱ ሺሕ ዓመት የያንዳንዱን ሺሕ መነሻና መድረሻ ቀን በነበራቸው የሐሳበ ዘመን ስሌት ችሎታ ለይተው ዐውቀውና ተረድተው ከዚያ ያደረሳቸውን አምላክ በማመስገን የያንዳንዱን ሺሕ መፈጸሚያ ዕለት በጸሎትና በምሕላ እያሰቡት ይውሉ ነበር:: ስለዚህ የሺሕ ዓመት በዓልን ማክበር ከጥንት የነበረ ሥርዓት ነው እንጂ በዘመናችን የተጀመረ አይደለም:: ከቀዳማይ አዳም ጀምሮ የያንዳንዱ ሺሕ ዓመት መነሻና መድረሻ የሚሆኑ ዕለታትም ተለይተው ሲነገሩ እንዲህ ነው::

| ሺሕ ዓመት | መነሻ ዓመት | መነሻ ዕለት | ፍጻሜ ዓመት | ፍጻሜ ዕለት |
|---|---|---|---|---|
| 1ኛው | 1 ዓ.ዓ. | ማክሰኞ | 1000ዓ.ዓ. | ዓርብ |
| 2ኛው | 1001ዓ.ዓ. | ቅዳሜ | 2000ዓ.ዓ. | ማክሰኞ |
| 3ኛው | 2001ዓ.ዓ. | ረቡዕ | 3000ዓ.ዓ. | ቅዳሜ |
| 4ኛው | 3001ዓ.ዓ. | እሑድ | 4000ዓ.ዓ. | ረቡዕ |
| 5ኛው | 4001ዓ.ዓ. | ሐሙስ | 5000ዓ.ዓ. | እሑድ |
| 6ኛው | 5001ዓ.ዓ. | ሰኞ | 6000ዓ.ዓ. | ሐሙስ |
| 7ኛው | 6001ዓ.ዓ. | ዓርብ | 7000ዓ.ዓ. | ሰኞ |
| 8ኛው | 7001ዓ.ዓ. | ማክሰኞ | 8000ዓ.ዓ. | ዓርብ |

ይህ የ7 ሺሕ ዓመት ዑደት በጥንተ ቀመር ማክሰኞ ተጀምሮ በሰባተኛው ቀን ሰኞ መፈጸሙን መምህራኑ በነበራቸው የሐሳበ ዘመን ችሎታ አስልተው፣ ዐውቀውና ተረድተው ለመጭው ትውልድ መዝግበው ያቈዩት ነውና ምስጋና ይገባቸዋል::

### የዘመነ ሐዲስ ሺሕ ዓመታት መነሻና መድረሻ

ከዳግማይ አዳም እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጀምሮ እስካለንበት ሦስተኛው ሺሕ ድረስ ያሉት ሺሕ ዓመታት መነሻና መድረሻ የሚሆኑ ዕለታትም ተለይተው ሲነገሩ እንዲህ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

| ሺሕ ዓመት | መነሻ ዓመት | መነሻ ዕለት | ፍጻሜ ዓመት | ፍጻሜ ዕለት |
|---|---|---|---|---|
| 1ኛው | 1ዓ.ም. | ረቡዕ | 1000ዓ.ም. | ቅዳሜ |
| 2ኛው | 1001ዓ.ም. | እሑድ | 2000ዓ.ም. | ረቡዕ |
| 3ኛው | 2001ዓ.ም. | ሐሙስ | 3000ዓ.ም. | እሑድ |

## ከመጀመርያው አዳም እስከ ሁለተኛው አዳም

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የብሉይና የቊጥር መምህራን ግን የዘመን አቈጣጠራቸውን ታሪክ በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ለማቃናት እጅግ ይተጉ፣ ይደክሙም ነበርና አዳም ከተፈጠረበት ጊዜ ዠምሮ ክርስቶስ በሥጋ እስከ ተገለጸበት ዘመን ድረስ 5500 ዓመት እንደሆነ በእነርሱ ዘንድ ታውቆ፤ ተረዳ:: ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘርዕ መካከል ዋነኛ በሆነው አራተ ሊቃናት ላይ የተመሠረተ ነው:: ይህ ዘርዕ ከ5240 ዓመተ ዓለም እስከ 5278 ዓ.ዓ. (ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ260 እስከ 222 ዓመት) ድረስ ነግሦ በነበረው ፊላደልፍስ በጥሊሞስ ትእዛዝ በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት (መተርጕማን) ከዕብራይስጥ ወደግሪክ የተተረጎመ ነው:: የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ከመጀመርያው ሰው አዳም አንሥቶ እስከ ሁለተኛው አዳም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድረስ የነበረውን፣የተቈጠረውንና በዘመናት መካከል ያሉ ታሪኮችንም በአንዝ ለይቶ ለማስረዳት 5500ውን ዓመት እየደመሩና እየሚሉ ተርትረውና ቈጥረው በክፍል በክፍል መድበውታል:: አከፋፈሉም እንዲህ ነው፡

| መደብ | ታሪክ | ዓመት |
|---|---|---|
| 1 | ከአዳም እስከ ርደተ አይኅ | 2256 |
| 2 | ከርደተአይኅ እስከ ሕንጻ ማኅፈድ | 571 |
| 3 | ከሕንጻ ማኅፈድ እስከ አብርሃም | 501 |
| 4 | ከአብርሃም እስከ ሙሴ | 425 |
| 5 | ከሙሴ እስከ ዳዊት | 694 |
| 6 | ከዳዊት እስከ ናቡከደነፆር | 469 |
| 7 | ከናቡከደነፆር እስከ እስክንድር | 265 |
| 8 | ከእስክንድር እስከ ክርስቶስ | 319 |
| | ድምር | 5500 |



www.ethiopianorthodox.org



ከአዳም እስከ ልደተ ክርስቶስ 5500 ዓመት ነው ተብሎ የተቈጠረው የተስፋ ዘመን በዚሁ ስሌት የተረጋገጠ ሆኖ ተገኝቷል:: ይህም ስሌት የሴቲቱ ዘር የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል ተብሎ የተሰጠው የተስፋ ቃል ኪዳንም በዚሁ ጊዜ መፈጸሙን ያመለክታል (ዘፍ. 3፥15)::

ዳግመኛም አበው ሊቃውንት በ5500 ዓመት የተፈጸሙ ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ክፍለ ጊዜን በዓመታት፣ በዐቢይ ቀመርና በዓመተ ምሕረት ከፍለው የመደቡትን ዝርዝር ከዚህ በታች እንመለከታለን:: በዚህ አገባብ ዓመተ ምሕረት ማለት ዓመተ ዓለሙ ለዐቢይ ቀመር 532 ተካፍሎ የሚገኘውን ቀሪ የሚያመለክት ነው::

| ታሪክ | በታሪኮች መካከል ያለ ክፍለ ጊዜ | | |
|---|---|---|---|
| | ዓመታት | ዐቢይ ቀመር | ዓመተ ምሕረት |
| ከአዳም እስከ ርደተ አይኅ | 2256 | 4 | 128 |
| ከአዳም እስከ ሕንጻ ማኅፈድ | 2827 | 5 | 167 |
| ከአዳም እስከ አብርሃም | 3328 | 6 | 136 |
| ከአዳም እስከ ሙሴ | 3753 | 7 | 29 |
| ከአዳም እስከ ዳዊት | 4447 | 8 | 191 |
| ከአዳም እስከ ናቡከደነጾር | 4916 | 9 | 128 |
| ከአዳም እስከ እስክንድር | 5181 | 9 | 393 |
| ከአዳም እስከ ክርስቶስ | 5500 | 10 | 180 |

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው መምህራኑ ከአዳም እስከ ክርስቶስ ልደት ያለውን ዘመን በዓመታት፣ በዐቢይ ቀመርና በዓመተ ምሕረት ከፍለውና መድበው ዳግመኛ ቢቈጥሩትም 5500 ዓመት ሆኖላቸዋል:: በዚያም ሆነ በዚህ ቢቈጠር የዘመኑ የቍጥር ሚዛን ትክክል ሆኖ ተገኝቷል:: በስምዐ ክልኤቱ ወሠለስቱ ይቀውም ነገር:: በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ነገር ጸንቶ ይኖራል እንዲል (ዘዳ. 17፥6፣ ዮሐ. 8፥17)::

ዳግመኛም፣ *ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ግበር ታቦተ ዘመርጡል እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ዘክዕበ እመት ወመንፈቀ እመት ኑኁ፣ እመት ወመንፈቀ እመት ራኅቡ፣ እመት ወመንፈቀ እመት ቆሙ::* ማለት፣ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ከስንዝር ወርዱ አንድ ክንድ ከስንዝር ቁመቱ አንድ ክንድ ከስንዝር የሚሆን የማይነቅዝ እንጨት ቈርጠህ ታቦትን ሥራ እኔ በዚያ ላይ ሆኜ እገለጽልሀለሁና ብሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ነግሮታል:: የታቦቱ ትርብዕት መጠን ሲደመርም 5 ተኩል ክንድ ይሆናል:: በእግዚአብሔር ዘንድ አንዲቱ ቀን በሰው ዘንድ ሺሕ ዘመን ነው:: ብሎ ዳዊት እንደተናገረው፣ በእግዚአብሔር ዘንድ 5 ተኩል ክንድም በሰው ዘንድ 5500 ዓመት ይሆናል:: (መዝ. 89፥4፣ 2ጴጥ. 3፥8፣ ዘኁል. 14፥34) ይህም ምሳሌ ነው ብለው መምህራን ከአዳም እስከ ክርስቶስ ያለውን ዘመን እንደሚያመለክት በትርጓሜያቸው ገልጸውታል:: ያውም እንዲህ ነው::





ርዝመቱ ሁለት.ክንድ ከስንዝር ማለት ከአዳም እስከ ኖህ ያለ ዘመን ነው:: ይህም ሲቈጠር 2256 ዓመት ይሆናል:: በሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ዘመን አርአያ ድንግል የሆነች ታቦተ ኖኅ ለመገኘትዋ ምሳሌ ነው:: ወርዱ አንድ ክንድ ከስንዝር ማለት ከኖኅ እስከ ሙሴ ያለው ዘመን ነው:: ይህ ሲቆጠር 1622 ዓመት ይሆናል:: በአንድ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ሁለት ዘመን አርአያ ድንግል የሆነች ታቦተ ሙሴ ለመገኘትዋ ምሳሌ ነው:: ቁመቱ አንድ ክንድ ከስንዝር ማለት ከሙሴ እስከ አማናዊት ድንግል ያለው ዘመን ነው:: ይህም ሲቆጠር 1622 ዓመት ይሆናል:: በሺህ ስድስት መቶ ሃያ ሁለት ዘመን አርአያ ድንግል ታቦተ ኖኅ፣ አርአያ ድንግል ታቦተ ሙሴ ምሳሌዎቿ የሆኑ አማናዊት ድንግል ለመገኘትዋ ምሳሌ ነው:: መላው ሲደመር 5500 ዘመን ይሆናል:: እነዚህ ምሳሌዎች ሁሉ አማናዊት ድንግል በሆነች በእመቤታችን ማርያም በዚህ ዘመን ተፈጽመዋል (ዘፀ. 25፥10፣ 21፥22)::

ዳግመኛም «ወውስተ ታቦት ትወዲ ትእዛዘ ዘአነ እሁበከ» ማለት ከዚህ አስቀድሞ እኔ የሰጠሁህ ዐሠርቱ ቃላት የተጻፉባቸው ሁለቱን ጽላቶች በታቦቲቱ ውስጥ አኑር ብሎታል:: ይህም ምሳሌ ነው:: ታቦት የእመቤታችን ምሳሌ፣ ሁለቱ ጽላቶች የሥጋዋ የነፍስዋ ምሳሌ፣ በጽላቶቹ የተጻፈው ቃል አካላዊ ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ሰው የሚሆንበትን ምሥጢር የሚያመለክት ምሳሌ ነው:: *ወውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወኃደረ ላዕሌነ፣* ማለት ቃል ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በኛ አደረ እንዲል:: (ዮሐ. 1፥14)

ምሥጢረ ትስብእትን ከሚመራመሩ መምህራን አንዱ ቅዱስ ያሬድ ማሕሌታይ ነው:: እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ5 ሺሕ 5 መቶ ዘመን ሰው መሆኑን ለማስረዳት ሃሌን አምስት ጊዜ ሉያን ሁለት ጊዜ ጽፎና አዚሞ በዚሁ ቍጥር መሠረት የጌታ ሰው የመሆን ምክር ተፈጸመ:: መልአኩ ገብርኤልም ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ:: ከርሱ በኋላም ንትሆ ሰላም መድኀኔ ዓለም መጣ ብሎ ድምፁን አሰምቶ ዘምሯል:: ምሥጢሩም እንዲህ ነው:: አምስት ጊዜ «ሃሌ» ማለቱ 5 ሺሕ ዓመት፣ ሁለት ጊዜ «ሉያ» ማለቱ አምስት መቶ ዓመት ማለት ነው:: ሁለቱ ሲደመርም 5500 ዓመት



www.ethiopianorthodox.org

ይሆናል:: ይህም በ5 ሺሕ 5 መቶ ዘመን ጌታችን ሰው ሆነ ማለት ነው::

የግእዙ ንባብም እንዲህ ነው፤ *ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ፣ ሃሌ ሃሌ ሉያ በዝንቱ ቀጸር ኮነ ዝንቱ ምክር ተፈነወ ገብርኤል መልአክ እምኀበ እግዚአብሔር መጽአ እምድኅሬሁ ንጉሠ ሰላም መድኃኔ ዓለም፤* እንዲል (ድጓ ታኅሣሥ 22)::

*በዝንቱ ቀጸር ኮነ ዝንቱ ምክር* ማለት:- ይህ ምክር ሰውን በአርአያችንና በአምሳላችን እንፍጠር እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ብለው የመከሩና የተናገሩ የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስም ምክር ነው:: በዚህ ምክር መሠረትም የሰላም ንጉሥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ ፈቃድ፣ ባባቱ ፈቃድ፣ በመንፈስ ቅዱስም ፈቃድ 5500 ዘመን ሲፈጸም ሰው ሆኖ ሊያድነን መጣ ብለው መምህራን ያስተምራሉ፤ ይተርጉማሉ:: *እስመ በፈቃዱ ወበሥምረተ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ መጽአ ወአድኀነነ* እንዲል (ውዳሴ ዘሠሉስ፤ዘፍ. 1፥26፣ 3፥22)::

ዐበይትና ንኡሳን ሱባዕያት

*ቀመረ ምጽአት*

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፣

> "የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱ ምንድር ነው? ይህ መቼ ይሆናል? ንገረን" አሉት:: ኢየሱስም "ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና:: ብዙዎችንም ያስታሉ" ብሎ መለሰላቸው (ማቴ. 24፥3-5)::

*ዳግመኛም* እነሆ ሁሉን ገለጥሁላችሁ ያንጊዜ ነገሥታትና ሌሎችም ወገኖች የሚመጡ መሆናቸውን ነግሬያችኋለሁ:: እናንተ ግን ነገሬን አትርሱ:: በመገናኛ ሰማያትንና ምድርን እንደፈጠርሁ፣ በሰባቱ ዕለታትም ሥራዬን ሁሉ እንደፈጸምሁ እወቁ:: እንዲሁም የዓለም መኖር በዚች ዓለም ባሉ ዘመናት ውስጥ





ከሚገኙ 7 ሺሕ ዓመታት ይሆናል:: የዚች ዓለም ኀልፈትም ከዕለታት ተለይታ መገናኛ በሆነችው ዕለት ይሆናል:: በርስዋ ዓለምን ፈጥሬያታለሁና ኀልፈትዋም በዚያች ዕለት ይሆናል:: በዚያች ዕለት ከመቃብር እንደተነሣሁም ሙታንን በዚያች ዕለት ከመቃብራቸው አስነሣቸዋለሁ:: ከእንቅልፌ በነቃሁበት ጊዜም እንዲሁ ሙታን ከመቃብራቸው ይነሣሉ:: በዚያች ዕለትም ነጋሪትን ይመታ ዘንድ ሚካኤልን አዘዋለሁ:: የካህናቶቹ አለቃ ገብርኤልንም በመጠኑ አሰምቶ ይጮህ ዘንድ አዝዘዋለሁ:: በዚያች ዕለት የነቢያት ትንቢት፣ የኦሪት ሕግ ይፈጸማልና ዕወቁ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ ለፍርድ እስከምመጣበት ጊዜ ድረስ 250 ሱባዕያት ዐበይት ይሆናልና ዕወቁ ብሎ ለሰባክያን ነግሯቸዋል:: በ71 ንኡሳን ሱባዕያትና በ3 ዓመታት ጊዜ ውስጥ የወንድሞቻቸውን በደል የሚተው ወንድሞቼ የተመሰገኑ ናቸው:: በደላቸውንም እደመስስላቸዋለሁ፣ ወንድሞቼ ሆይ ንጹሐን ለሆኑ መላእክቶቼ ያልገለጽሁትን ለናንተ ገልጫለሁና የነገርኋችሁን ሁሉ ጠብቁ:: ይህ 71 ሱባዕያት ከ3 ዓመት የሆነው 500 ዓመትም የስምንተኛው ሺሕ ዘመን ግማሽ ነው (መርሐ ዕዉር)::

ሰባት ሺሕ ዓመት በሱባዔ ሲቀመር ሺሕ ሱባዔ ይሆናል:: ሺሕ ሱባዔ በ4 ሲቀመር 250 ሱባዕያት ዐበይት ይሆናል:: 500 ዓመት በሱባዔ ሲቀመር 71 ሱባዕያት ንኡሳን ሆኖ 3 ዓመት ይተርፋል::

*ዳግመኛም* 250 ሱባዕያት ዐበይት በ7 ሲባዛ 1750 ይሆናል:: 1750 በ4 ሲባዛ 7000 ዓመት ይሆናል:: 71 ሱባዕያት ንኡሳንም በ7 ተባዝቶ 3 ዓመት ሲደመርበት 500 ዓመት ይሆናል:: ስለዚህም መላው ሱባዔ 7500 ዓመት ነው::

*ሐሳበ ዕዝራ*

ሱቱኤል ዕዝራ የነበረው ይህ ዓለም በተፈጠረ በ5 ሺሕ ዓመት ነው (ዕዝራ 14፥48):: ይህ ዓለም የሚያልፍበትን ጊዜ በቀመር ሲያስረዳም እንዲህ ይላል:- *ዓለምሰ ኀለፈ ውርዙቱ ወረሰዐ መዋዕሊሁ እስመ ለዐሠርቱ ክፍል ተሠርዐ ዓለም፤ ወበጽሐ ውስተ ዐሥር ወተርፈ መንፈቀ ዐሥር::* ማለት ይህ ዓለም የሕፃንነቱ ወራት አልፎ ዘመኑ አርጅቷል:: ይህ ዓለም የሚያልፍበት ዘመኑ ከዐሥር ተከፍሎ እስከ ዐሥር ደርሷል:: የዐሥሩ እኩሌታ ቀርቷል ይላል (ዘዕዝ. 14፥10-42):: ምሥጢሩም እንዲህ ነው:-



www.ethiopianorthodox.org

የዕዝራ መስፈርያ 500 ነው። የቈጠረበት ዘመንም ከ5 ሺሕ ዓመተ ዓለም ዠምሮ ነው። 5000 ዓመት በ500 ሲቀመር 10 ክፍል ይሆናል። እስከ ዐሥር ደረሰ ያለው ይህ ነው። ዐሥር ክፍል የሆነው 5000 ዓመት ለ2 ሲከፈል 2500 ዓመት ይሆናል። የዐሥሩ እኩሌታ ቀረ ያለውም ይህ ነው። ዐሥር ክፍል የሆነው 5000 ዓመትና የዐሥር እኩሌታ የሆነው 2500 ዓመት ሲደመር 7500 ዓመት ይሆናል። ሱቱኤል ዕዝራ ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ እስከ ዳግም ምጽአት የቈጠረው ዘመን ይህ ነው።

ይህ ዓለም የሚያልፍበትን ጊዜ ለማስረዳት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሱባዔ፣ ሱቱኤል ዕዝራ በቀመር በተለያየ ስሌት ሁለቱ ቢቈጥሩትም ውጤቱ አንድ ሆኖ ተገኝቷል። ያውም 7500 ዓመት ነው።

7500 ዓመት አልፏል። ዓለም ግን አላለፈችም የሚል ጠያቂ ቢኖር ጌታችን የሰጠውን ምልክት አስተውሎ ሊመለከት ይገባዋል። ያውም ምልክቱ እንዲህ ነው:- ጦርነትን የጦርነትንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፣ ይህ ሊሆን የግድ ነውና ተጠንቀቁ አትደንግጡ። ነገር ግን ፍጻሜው ገና ነው። ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነሣሉ። በየሀገሩም ረኀብ፣ ቸነፈርም፣ የምድር መናወጥም ይሆናል። እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መዠመርያ ናቸው (ማቴ. 24፥6-8)። የሚለው ንባብ አሁን ዓለም የደረሰችበት የመዠመሪያ ማስጠንቀቅያ መስሎ ይታያል። ስለዚህ ነገ የሚሆነውን አናውቀውምና ተጠንቀቁ አትደንግጡ፣ ፍጻሜው ገና ነው በሚለው የጌታችን ቃል አምነን ዳግም ምጽአቱን በተስፋ ልንጠብቅ ይገባናል።

ዳግመኛም በዘፍጥረት 15፥13፣ በገላትያ 3፥17 እንደተጻፈው ትርፋን ትቶ ኀርምሩን መልቶ መቍጠር ልማደ መጽሐፍ ስለሆነ ስምንተኛው ሺሕ ባይፈጸምም ኀርምሩን መልተው ቈጥረዉታል ብለው የሐሳብ ዘመን መምህራን ያትታሉ።

ሱባዔ ነቢያት

ከአዳም እስከ ክርስቶስ ድረስ የተቈጠረው 5500 ዓመት ነቢያት እንደገና በሱባዔ እየቀመሩ በመቍጠር ጌታችን





የተወለደበትን ዓመትና ቀን ለይተው ያመለክታሉ። ያውም እንዲህ ነው:-

ኤርምያስ ነቢይ ከፍጥረት እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለውን ዘመን በሱባዔ ቈጥሮ አስረድቷል። ሱባዔውን የዠመረበት ራእዩን ያየበት፣ ትንቢቱን የተናገረበት ዘመን ዓለም በተፈጠረ በ5053 ዓመት ነው። ኤርምያስ ሱባዔውን የቈጠረው በዕለት ነው። ሰባቱ ዕለት በ7 ሲባዛ ዕለታት በ10 ሲባዙ (7 x10)=70 ይሆናሉ። ሰባው ዕለት በ7 ሲባዛ (70x7)=490 ዕለት ይሆናል። በኤርምያስ ቀመር ይህ አንድ ሱባዔ ይባላል። በዚሁ ቀመር ሲቀመር መላው የኤርምያስ ሱባዔ 333 ነው። ወይከውን ምጽአቱ ውስተ ምድር በ፻፴፫ ሱባዔ፤ ማለት ጌታ ሰው ሊሆን ሥጋ ሊለብስ ወደዚህ ዓለም ሊመጣ የቀረው ዘመን ሦስት መቶ ሠላሳ ሦስት የዕለት ሱባዔ ነው እንዲል (ተረፈ ኤር.11፥48)።

333 ሱባዔ በ490 ሲባዛ 16 እልፍ 3 ሺሕ 170 (163170) ዕለት ይሆናል። ይህ ወደ ዓመት ሲጠቀለል 447 ዓመት ሆኖ 15 ቀን ይተርፋል። ትርፋን ትቶ ኀርምሩን ሞልቶ መቈጠር ልማደ መጽሐፍ ነውና (ዘፍ. 15፥13፣ ገላ. 3፥17) 15 ቀን ቀርቶ 447 ዓመት ብቻ ይያዛል። ስለዚህ:-

| | |
|---|---|
| ሱባዔው የተዠመረበት ዓለም በተፈጠረ | በ5053 ዓመት |
| ሱባዔው ከተዠመረበት እስከ ክርስቶስ ልደት | 447 ዓመት |
| ድምር | 5500 ዓመት ይሆናል። |

ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተነገረው ትንቢት በተቈጠረው ሱባዔ መሠረት መወለዱን ያረጋግጣል።

ዳንኤል ነቢይም ኤርምያስ በተናገረው ትንቢት መሠረት ሰባው (70) የምርኮ ዘመን (ኤር. 25፥11-12) መፈጸሙን አውቆ ወገኖቹ እስራኤል ወደ አገራቸው እንዲመለሱ «አቤቱ ልመናችንን ስማን፣ አቤቱ ይቅር በለን» እያለ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ ሳለ መልአኩ ገብርኤል በሰው አምሳል ተገልጦ ኤርምያስ ከተናገረው ሰባ ዓመት ሌላ ከኢየሩሳሌም መታደስ እስከ መሢሕ ድረስ ገና ሰባ ሱባዔ የቀረ መሆኑን ገለጸለት። ሰብዓ ሰንበታተ አድምሙ



www.ethiopianorthodox.org

ለሕዝብከ፤ እንዲል (ዳን. 9፥24)። ወገኖችህ እስራኤልን ሰባ ሱባዔ ቅጠራቸው ማለት በሰባ ሱባዔ ጌታ ይወለዳል ብለህ ንገራቸው ማለት ነው።

የሰባው ሱባዔ ቀጠሮ ምክንያትም በቅድስት አገርህ ላይ ዐመፃና ኃጢአት ይፈጸም ዘንድ፣ በደልም ይጠፋ ዘንድ፣ የዘለዓለም ጽድቅ ይመጣ ዘንድ፣ ራእይና ትንቢትም ይገለጥ ዘንድ፣ ቅዱስ ቅዱሳን ጌታም የባሕርይ ክብሩን ገንዘብ ያደርግ ዘንድ ነውና ነገሩን መርምር። ራእዩንም አስተውል ብሎታል።

ዳግመኛም ሰባውን ሱባዔ በሦስት ክፍል ከፍሎ ምጥጢሩን አስረድቶታል። የመገርመርያው ክፍል ሰባት ሱባዔ ወይም 49 ዓመት ነው። የዚህ ሱባዔ ዋና ተግባር ከፋርስ ነገሥታት ከቂሮስና ከዳርዮስ፣ ከአርጤክስስም በወጣው ትእዛዝ መሠረት የኢየሩሳሌም መታደስና መሠራት መሆኑን ገልጾለታል (ዕዝራ 6፥14)። ስለዚህ በትእዛዙ መሠረት በኢየሩሳሌም የነበረው ቤተ እግዚአብሔር በዚህ ሱባዔ ተሠርቶ ተፈጽሟል።

ሁለተኛው ክፍል 62 ሱባዔ ነው። ይህም ከዳግም ሕንጸ እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለውን ጊዜ ያመለክታል። ያውም እንዲህ ነው፦

| | |
|---|---|
| ከዳግም ሕንጸ እስከ ልደተ ክርስቶስ (62x7) | 434 ዓመት |
| ዳግም ሕንጸ የተፈጸመበት ዓመተ ዓለም | <u>5066 ዓመት</u> |
| ድምር | 5500 ዓመት ይሆናል (አቡሻህር አንቀጽ 20)። |

ከ62 ሱባዔ በኋላም መሢሕ የሚገደል መሆኑን ገልጾለታል (ዳን. 9፥26)። 7 ሱባዔና 62 ሱባዔ ሲደመር (7+62)=69 ሱባዔ ወይም 483 ዓመት ይሆናል። ይህም ትንቢቱ ከተነገረበት ሱባዔው ከተቈጠረበት ጊዜ ገምሮ ጌታችን እስከ ተጠመቀበት ዓመት ያለውን ጊዜ ያመለክታል።

ሦስተኛው ክፍል ሰባኛው ሱባዔ ወይም 7 ዓመት ነው። ይህ ሱባዔ ከጌታችን ጥምቀት ገምሮ ያለው 7 ዓመት ነው። በዚሁ ሱባዔ እኩሌታ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕገ ኦሪት ፈንታ ሕገ ወንጌልን ሠራ። የመጨረሻውን ፋሲካ አክብሮ በመሥዋዕተ ኦሪት ፈንታ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በመስቀል ላይ ተሰቀለ። «መሢሕ





ይገደላል» ተብሎ እንደተነገረ። በዚህ ጊዜ ጌታችን አምላክነቱን ሲቀ ካህናትነቱን ንጉሥነቱን ገለጠ።

ዳግመኛም ጊዜው ደረሰ፣ ዘመኑ ተፈጸመ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ ብሎ ጌታችን አስተምሯል (ማር. 1፥14-15)። ዘመኑ ተፈጸመ ማለቱ ዳንኤል የቈጠራቸውን ሱባዕያት መፈጸማቸውን ሲያስረዳ ነው። የዳንኤል ሱባዔ ዓለም ከተፈጠረ ገምሮ እስከ ጌታችን ስቅለት ሲቈጠርም እንዲህ ነው።

| | |
|---|---|
| ከፍጥረተ ዓለም እስከ ሕንጸ ቤት ቀዳማይ | 4981 ዓመት |
| ዘመነ ዕረፍት ወይም ዘመነ ፂዋዌ | 70 ዓመት |
| ስድሳ ዘጠኝ ሱባዔ (69 x 7) | <u>483 ዓመት</u> |
| ድምር | 5534 ዓመት ነው። |

ዳንኤል ከፍጥረት እስከ ክርስቶስ ስቅለት ያለውን ዘመን 5534 ዓመት መሆኑን በሱባዔ ቈጥሮና ቀምሮ ያስረዳውን ከዚህ በላይ ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ይህ ነቢይ ከፍጥረት እስከ ዳግም ምጽአት ያለውን ዘመን በሱባዔ ቈጥሮና መርምሮ የገለጸውን ጠቅሶ የመልክዓ ኢየሱስ ደራሲ ሲጽፍ እንዲህ ይላል፦ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞገስ ዳንኤል ነቢየ ሱሳ፣ ድኅረ ተፈጸመ ሱባዔ ሰንበታት ስድሳ፣ በምጽአትከ ተንትመ አበሳ ማለት የሱሳ ነቢይ ዳንኤል ክብርና ሞገስ የሆንህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ስድሳው ሱባዔ ከተፈጸመ በኋላ በደልና ኃጢአት ሁሉ ባንተ መምጣት ይደመሰሳል ማለት ነው።

የሐሳብ ዘመን መምህራንም የስድሳውን ሱባዔ ምሥጢር ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ። አንዱ ዐቢይ ቀመር ማለት 532 ዓመት ለአራቱ ወንጌላውያን ሲከፈል ለያንዳንዳቸው 133 ዓመት ይደርሳቸዋል። ይህም ሰንበተ ማቴዎስ፣ ሰንበተ ማርቆስ፣ ሰንበተ ሉቃስ፣ ሰንበተ ዮሐንስ ይባላል። ሰንበት ማለት በዚሁ ገጽ ሱባዔ ማለት ነው። ስለዚህ በአንድ ዐቢይ ቀመር አራት ሰንበታት ከተገኙ በ15 ቀመረ ድሜጥሮስ (4x15)=60 ሰንበታት ይገኛሉ። አንዱ ሰንበት 133 ዓመት ከሆነም 60 ሰንበታት (60x133)=7980 ዓመት ይሆናል። ስለዚህ የጌታችን ዳግም መምጣት 7980 ዘመን ሲፈጸም መሆኑን የዳንኤል ሱባዔ ያስረዳል ብለው መምህራን ያትታሉ።



www.ethiopianorthodox.org

ከአዳም እስከ ክርስቶስ ልደት ያለውን ዘመን ነቢያት በሱባዔ፣ የብሉይና የሐሳበ ዘመን መምህራንም በልዩ ልዩ ቀመርና ስሌት እየቀመሩ ቢቈጥሩትም ውጤታቸው አንድ ነው፡፡ ያውም 5500 ዘመን ነው፡፡ ምክንያቱም የሱባዔውንና የቀመሩን ምሥጢር የሚገልጽላቸው መንፈስ ቅዱስ አንድ ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስን «ባሕርያዊ አካላዊ ሕይወት ነው፡፡ እንደ ነፍስ ፍጡር፣ እንደ ነፋስ ዝርው ያይደለ፣ የሥላሴ ሦስተኛ አካል፣ ከአብ የሚሠርፅ፣ ከወልድ የሚነሣ፣ ለሰው ለመላእክት ጸጋ ሀብት ሆኖ የሚሰጥ» እያለች ዘወትር ስታመሰግነው ትኖራለች (ዮሐ. 15፥26፣ 16፥14፣ መ/ሰዋ.ወግስ ገጽ 648)፡፡

## የጌታችን ሐረገ ትውልድ

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐረገ ትውልድና የአምላክ ሰው መሆንን ምሥጢር በቅዱሳት መጻሕፍት በልዩ ልዩ መንገድ ተገልጿል፡፡ በብሉይ ኪዳን ይወርዳል፣ ይወለዳል ተብሎ ይነገር የነበረ በሐዲስ ኪዳን ወረደ ተወለደ ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣ ወይም መልአከ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ነገረኝ፣ ወይም እንዲህ ያለ ራእይ እየሁ ብለው ሲጽፉ፣ የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ግን ጌታችን ያስተማረውን ትምህርት ሰምተው፣ ያደረገውን ተአምራት አይተው የጻፉ ስለሆነ የአምላክ ሰው መሆንን ምሥጢር ሲገልጹ ቃል ሥጋ ሆነ፣ ተወለደ በሚል የኃላፊ አንቀጽ ዘይቤ ገልጸውታል፡፡

አራቱ ወንጌላውያንም ስለጌታችን ሰው የመሆን ምሥጢርና ትውልድ ሲጽፉ እንዲህ ይላሉ፡፡ ማቴዎስ መጽሐፈ ልደቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ ዳዊት፣ ወልደ አብርሃም፣ ማርቆስ ቀዳሚሁ ለወንጌለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር፣ ሉቃስ ወልደ አዳም ወልደ እግዚአብሔር፣ ዮሐንስ ቃል ሥጋ ሆነ ብለው የአምላክ ሰው መሆንን ምሥጢር ባንድነት አስረድተዋል፡፡

ማቴዎስ የጌታችንን ሐረገ ትውልድ ሲጽፍ ወልደ ዳዊት፣ ወልደ አብርሃም፣ ... ብሎ ዠምሮ አልዓዛር ማታንን፣ ማታን ያዕቆብን፣ ያዕቆብ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስ የወለደች የማርያም እጮኛ ዮሴፍን ወለደ ብሎ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ መሆኑን ለማስረዳት በዮሴፍ አማካይነት ወይም አንጻር ትወልዱን ወደ እመቤታችን ድንግል ማርያም አደረሰው፡፡ ምክንያቱም በዕብራውያን ዘንድ ሐረገ ትውልድ በሴቶች በኩል የማይቈጠር ስለሆነ ነው (ማቴ.





1፥16)፡፡ የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ ማለቱ ግን ክርስቶስ ከሁለቱ እንዲወለድ፡- *ለአብርሃም በዘርዕከ ይትባረኩ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር*፣ ለዳዊት፡- *እስመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ*፤ ተብሎ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸው ተስፋ ጌታችን በመወለዱ የተፈጸመ መሆኑን ያመለክታል (ዘፍ. 12፥3፣ መዝ. 131)፡፡

ማቴዎስ የዮሴፍን ሐረገ ትውልድ የሰሎሞንና የዳዊት ዘር በሆነው በማትያን ልጅ በያዕቆብ በኩል እንዲህ አድርጎ ቈጥሮ ሲጽፍ ሉቃስ ደግሞ የናታንና የዳዊት ዘር በሆነው በማጣት (ማቲ) ልጅ በኤሊ በኩል መወለዱን ጽፎለታል፡፡ ምክንያቱም ዮሴፍ ከያዕቆብ በሥጋ፣ ከኤሊ በሕግ የተወለደ ስለሆነ ሁለቱም አባቶቹ ናቸውና፡፡ *አቅም ዘርዐ ለእኁከ*፤ ለወንድምህ ዘር ተካለት እንዲል (ዘዳ. 25፥5-6፣ ሉቃ. 3፥24፣ ማቴ. 1፥14-16)፡፡ የዮሴፍና የኤሊ ወንድማማችነትም እንዲህ ነው፡- የሰሎሞንና የዳዊት ዘር የሆነው ማትያን እሸታ የምትባለውን ሴት አግብቶ ያዕቆብን ከወለደ በኋላ ሞተ፡፡ ከርሱ በኋላ ሚስቱ እሸታ የናታንና የዳዊት ዘር የሆነውን ማጣትን (ማቲን) አግብታ ኤሊን ወለደች፡፡ ኤሊ ሳይወልድ ስለሞተ በኦሪቱ ሕግ መሠረት ዘር ይተካለት ዘንድ ሚስቱን ወንድሙ ያዕቆብ ስላገባት ከርስዋ ዮሴፍ ተወለደ፡፡ ስለዚህ ዮሴፍ በሥጋ የያዕቆብ ልጅ በሕግ የኤሊ ልጅ ተባለ፡፡

## የእመቤታችን ሐረገ ትውልድ

የእመቤታችን ድንግል ማርያም ሐረገ ትውልድም እንዲህ ነው፡- የእመቤታችን አባት ስም ዮናኪር የተባለ ሳዶቅ ነው፡፡ የእናትዋም ስም ሐና ወይም ዲና ይባላል፡፡ የዳዊትና የሰሎሞን ዘር የሆነው አልዓዛር ኢዮአታም የተባለ ቅስራን፣ ቅስራ ሳዶቅን፣ ሳዶቅ እመቤታችን ድንግል ማርያምን ይወልዳል፡፡ ሳዶቅ የተባለ ዮናኪርና የዮሴፍ አባት ያዕቆብ የወንድማማች ልጆች ናቸው፡፡ ያውም እንዲህ ነው፡- እመቤታችን ድንግል ማርያም የአልዓዛር ልጅ የኢዮአታም (ቅስራ) ልጅ የሳዶቅ ልጅ ናት፡፡ ዮሴፍም የአልዓዛር ልጅ የያዕቆብ ልጅ ነው፡፡ ዮሴፍና እመቤታችን ሐረገ ትውልዳቸው ከዳዊትና ከሰሎሞን ዘር የወረደ ስለሆነ የዳዊት ልጆች ይባላሉ፡፡

በእናትዋም በኩል ያለው ሐረገ ትውልድ እንዲህ ነው፡- ሜልኪ ሌዊን፣ ሌዊ ማቲን (ማጣትን) ይወልዳል፡፡ ማቲ ሦስት ሴቶች ልጆችን ወለደ፡፡ እነርሱም ማርያም፣ ሶፊያና ሐና ይባላሉ፡፡ ማርያም የሰሎሜ መወልዲት እናት ናት፡፡ ሶፍያ የዮሐንስ እናት



www.ethiopianorthodox.org

ኤልሳቤጥን ወልዳለች። ሐና ኢያቄም የተባለ ሳዶቅን አግብታ እመቤታችን ድንግል ማርያምን ወልዳለች። ስለዚህ እመቤታችን፣ ሰሎሜና ኤልሳቤጥ የእኅትማማች ልጆች ናቸው (ስንክሳር ኅዳር 11)።

## ብሥራተ ገብርኤል

ገብርኤል መልአክ በስድስተኛው ወር ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ፣ *ማርያም ሆይ እነሆ ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ፣ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፤* ብሎ የምሥራች በነገራት ጊዜ *ነየ ዓመተ እግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ/ እነሆኝ የእግዚአብሔር ባርያው እንደ ቃልህ ይሁንልኝ* ብላ ስትመልስለት፣ ያን ጊዜ የቃል ገንዘብ፦ አምላክነት፣ ንጉሥነት፣ ነቢይነት፣ ካህንነት ለሥጋ፣ የሥጋ ገንዘብ፦ ሕማም፣ ሞት፣ መቃብር ለቃል ስለሆነ፣ ሥግው ቃል በተዋሕዶ ከበረ ብለን እናምናለን። ከበረ ማለትም ተመሰገነ ማለት ነው። *አማኑኤል ሞተ ከመ ሞተ ዘአነ ዘውእቱ ተፈልጦተ ነፍስ እምሥጋ፤* እንዲል። አማኑኤል የተዋሕዶ፣ ኢየሱስ የቤዛነት፣ ክርስቶስ የፈራጅነት ስሙ ነው (ትር. ወንጌል ዘመ.መን.ገብርኤል)፣ (ሉቃ. 1፥26-38)። ስድስተኛ ወር ማለቱ ግን ኤልሳቤጥ ከፀነሰችበት ወር ዠምሮ ላለው ጊዜ ነው እንጂ ለዓመቱ ስድስተኛ ወር ለሆነው ለየካቲት አይደለም። ኤልሳቤጥ ከፀነሰችበት ከጥቅምት ወር ዠምሮ ሲቈጠር ስድስተኛ ወር የሚሆነው በፀሐይ መጋቢት፣ በጨረቃ ሚያዝያ ነው። ስለዚህ መልአኩ ትፀንሻለሽ ብሎ ለእመቤታችን የምሥራች የነገራት በፀሐይ አቈጣጠር መጋቢት 29 ቀን፣ በጨረቃ አቈጣጠር ሚያዝያ 10 ቀን መሆኑ ነው። ምክንያቱም መልአኩ ለዘካርያስ የምሥራች የነገረው (ሉቃ. 1፥13) በጨረቃ አቈጣጠር ጥቅምት 10 ቀን ስለሆነ ነው። *እስመ ለዘካርያስስ ኢያብሠርዎ ዘእንበለ አመ ዐሡሩ ለወርኃ ታስሪን ቀዳማይ በሐሳበ ወርኅ፤* እንዲል ማለት ለዘካርያስ የምሥራች የተነገረው በጨረቃ አቈጣጠር ታስሪን ቀዳማይ (ጥቅምት) በባተ በዐሥረኛው ቀን ይላልና (ትርጓሜ ወንጌል ዘመንበረ መንግሥት ገብርኤል)።

እመቤታችን ድንግል ማርያም በአራተኛው ወይም በአምስተኛው ወር ሳይሆን በስድስተኛው ወር እንድትፀንስ የተነገረበት ምክንያትም ፈጢረ ፍጥረታት በስድስተኛው ቀን እንደ ተፈጸመ የፍጥረታት ተሐድሶም በዚሁ ዕለት እንዲሆን የፈጣሪ ፈቃድ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ሰውን በስድስተኛው ቀን





እንደፈጠረውና ሰውም በራሱ ፈቃድ በዚሁ ዕለት ወደ ኃጢአት አዘቅት እንደወደቀ የተሐድሶው መፀነስ የምሥራችም በዚሁ ዕለት እንዲነገር የፈጣሪ ፈቃድ ሆነ። በተጨማሪም ዓለም በተፈጠረ በስድስተኛው ሺሕ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት መሆኑን ያስረዳል። ድርጊቱ በሚያዝያ ወር እንዲሆን የተደረገበት ምክንያትም ሚያዝያ የወሮች መዠመርያ ስለሆነና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የዳግማዊት ዓለም ወጣኒ ስለሆነ ነው (ዘፍ 12፥2)።

ዳግመኛም እግዚአብሔር ፈጢረ ፍጥረትን በዚሁ ወር እንደዠመረ ሐዳሴ ፍጥረት የሆነው መድኀኒታችን ክርስቶስም የመዠመርያውን ፋሲካ በርሱ አደረገ። ያውም ስለእኛ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ምሥጢርን ያመለክታል። በርስዋም እንዲታመምና እንዲነሣ ፈቃዱ ሆነ። መድኀኒታችን ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜም በርስዋ ትንሣኤ ይሆናል ብለው መምህራን ያስተምራሉ።

ብሥራቱ እንደ ጨረቃ አቈጣጠር ወሩ በባተ በዐሥረኛው ቀን መሆኑም ዐሥር ቍጥር ሙሉ ስለሆነ ነው። ዳግመኛም እስራኤል አስቀድሞ የተሰጠውን ምልክት ለመፈጸም ነው። ያውም እስራኤል ከግብጽ በወጡበት ጊዜ በዚሁ ወር በዐሥረኛው ቀን ለአንድ ቤት አንድ በግ ለመሥዋዕት እንዲመደብ መታዘዙን ለማስረዳት ነው (ዘፍ. 12፥3)። የዓለምን ኃጢአት እንዲሸከም በዚያ በግ የተመሰለውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው።

## ጥንተ ፅንሰቱ ለክርስቶስ

ዓለም በተፈጠረ በ5500 ዓመት፣ በ11ኛው ዐቢይ ቀመር፣ በሰንበተ ማርቆስ፣ በ180 ዓመተ ምሕረት (ቀመር)፣ በሣልስተኛ አንቀጽ፣ በ9 ዓመተ አበቅቴ፣ በዘመነ ዮሐንስ፣ እሑድ መጋቢት 29 ቀን መልአኩ ገብርኤል በተናገረው የምሥራች መሠረት ጌታችን በድንግል ማርያም ማኅፀን ተፀነሰ። ዕለቱ እሑድ ጊዜው 3 ሰዓት እንደሆነም ሐዋርያት አስተምረዋል። ያንጊዜ አበቅቴ ወርኀ 28፣ አበቅቴ ፀሐይ 7፣ ሐሳበ ሰማይ ወምድር 3 ዞኖ ነበር።

## ጥንተ ልደቱ ለክርስቶስ

ዓለም በተፈጠረ በ5501 ዓመት በ11ኛው ዐቢይ ቀመር፣ በሰንበተ ማርቆስ በ181 ዓመተምሕረት (ቀመር) በሣልስተኛው አንቀጽ



www.ethiopianorthodox.org

በ10 ዓመተ አበቅቴ በዘመነ ማቴዎስ ማክሰኞ ታኅሣሥ 29 ቀን ተወለደ:: ያንጊዜ አበቅቴ ወርኅ 9፣ አበቅቴ ፀሐይ 1፣ ሐሳበ ሰማይ ወምድር 4 ሆኖ ነበር::

## ጥንተ ጥምቀቱ ለክርስቶስ

ዓለም በተፈጠረ በ5531 ዓመት በ11ኛው ዐቢይ ቀመር በሰንበተ ማርቆስ በ211 ዓመተ ምሕረት (ቀመር)፣ በአምስተኛው አንቀጽ በ2 ዓመተ አበቅቴ በዘመነ ሉቃስ ማክሰኞ ጥር 11 ቀን ተጠመቀ:: ያንጊዜ አበቅቴ ወርኅ 11፣ አበቅቴ ፀሐይ 3፣ ሐሳበ ሰማይ ወምድር 6 ሆኖ ነበር::

## ምሥጢረ መለኮቱ ለክርስቶስ

ዓለም በተፈጠረ በ5533 ዓመት በ11ኛው ዐቢይ ቀመር በሰንበተ ማርቆስ በ214 ዓመተ ምሕረት (ቀመር) በአምስተኛው አንቀጽ፣ በ4 ዓመተ አበቅቴ በዘመነ ማቴዎስ እሑድ ነሐሴ 13 ቀን ምሥጢረ መለኮቱን ታቦር በሚባል ተራራ ላይ ገለጠ (ማቴ. 17፥1-2):: ያንጊዜ አበቅቴ ወርኅ 3፣ አበቅቴ ፀሐይ 6፣ ሐሳበ ሰማይ ወምድር 2 ሆኖ ነበር::

## ጥንተ ስቅለቱ ለክርስቶስ

ዓለም በተፈጠረ በ5534 ዓመት በ11ኛው ዐቢይ ቀመር በሰንበተ ማርቆስ በ214 ዓመተ ቀመር (ዓ.ም.) በአምስተኛው አንቀጽ፣ በ5 ዓመተ አበቅቴ በዘመነ ማርቆስ ጌታችን ዓርብ መጋቢት 27 ቀን፣ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ጸዋትወ መከራን ሁሉ ፈጸመ:: *ወይቤ ተፈጸመ ኵሉ* እንዲል (ዮሐ. 19፥30):: ያንጊዜ አበቅቴ ወርኅ 14፣ አበቅቴ ፀሐይ 7፣ ሐሳበ ሰማይ ወምድር 3 ሆኖ ነበር::

ፍሥሕ የሚባል የአይሁድ በዓልም ጌታችን በተሰቀለበት ዓመት ኀሙስ መጋቢት 26 ቀን ውሎ ነበር:: በዚሁ ዕለት ማታ ጌታችን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ፋሲካን በላ:: ከራት በኋላም በ1ኛው ሰዓተ ሌሊት የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ:: በ2ኛው ሰዓተ ሌሊት ይህ ሥጋዬ ነው፣ ይህ ደሜ ነው ብሎ ኅብስቱንና ጽዋዉን ሰጣቸው (መ.ምሥጢር ምዕ. 15)::





## ጥንተ ትንሣኤሁ ለክርስቶስ

ዓለም በተፈጠረ በ5534 ዓመት፣ በ11ኛው ዐቢይ ቀመር፣ በሰንበተ ማርቆስ፣ በ214 ዓመተ ምሕረት (ቀመር)፣ በአምስተኛው አንቀጽ፣ በ5 ዓመተ አበቅቴ፣ በዘመነ ማርቆስ፣ ጌታችን እሑድ መጋቢት 29 ቀን ትንሣኤው ሆነ ::

ጌታችን የተፀነሰበት ቀን እሑድ፣ የተወለደበትና የተጠመቀበት ቀን ማክሰኞ፣ በዓለ ፍሥሕ የዋለበት ቀን ኀሙስ፣ የተሰቀለበት ዓርብ፣ የተነሣበት እሑድ እንደሆነ በምን ይታወቃል? ብሎ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር፣ ከዚህ በታች የተጻፈውን አስተውሎ በመመልከት መልሱን ያገኛል::

## የትስብእት አበቅቴ ፀሐይ

የትስብእት አበቅቴ ፀሐይ ማለት ጌታችን በተፀነሰበት ዓመት የነበረ ጥንተዮን (መስከረም 1 ቀን) ማለት ነው:: የዓመተ ትስብእትን አበቅቴ ፀሐይ ወይም ሐሳበ ፀሐይ ለማወቅ ከአዳም እስከ ዕለተ ትስብእት ካለው 5500 ዓመት ዕለተ ምርያንና ዕለተ ሠግርን ለይቶ አውጥቶና ደምሮ ለ7 ይከፈላል:: ከ7 የተረፈው አበቅቴ ፀሐይ ይሆናል:: 1 ቢተርፍ አበቅቴ ፀሐይ ሮብ ይሆናል:: 2 ቢተርፍ አሙስ፣ 3 ቢተርፍ ዓርብ፣ 4 ቢተርፍ ቀዳም፣ 5 ቢተርፍ እሑድ 6 ቢተርፍ ሰኞ፣ 7 ወይም አልቦ ቢሆን ማክሰኞ ይሆናል:: ያውም እንዲህ ነው:: የ5500 ዓመተ ዓለም:-

| | |
|---|---|
| ዕለተ ምርያ (5ኛ ጳጉሜን) | 5500 ዕለት |
| ዕለተ ሠግር (6ኛ ጳጉሜን) | 1375 ዕለት |
| ድምር | 6875 ዕለት ይሆናል:: |

ከ6875 ዕለት 1 ሲቀነስ (6875-1) =6874 ዕለት ይተርፋል:: 6874 ዕለት በ7 ዐውደ ዕለት ሲቀመር (6874÷7) =982 ሱባዔ ዕለት ሆኖ 7 ይተርፋል:: ይህ የዓመተ ትስብእት አበቅቴ ፀሐይ ይባላል::



www.ethiopianorthodox.org

## ዕለተ ትስብእት

ዕለተ ትስብእትን ለማወቅ:-

| | |
|---|---|
| የ6 ወር ዐጽፈ አውራኅ | 12 ዕለት |
| የመጋቢት ሠርቀ መዓልት | 29 ዕለት |
| ዕለተ ጠቢባን | 2 ዕለት |
| አበቅቴ ፀሐይ | 7 ዕለት |
| ድምር | 50 ዕለት ይሆናል:: |

50 ዕለት ለ7 ዐውደ ዕለት ሲከፈል 7 ሱባዔ ዕለት ሆኖ 1 ይተርፋል:: ስለዚህ የክርስቶስ ዕለተ ትስብእት እሑድ መሆኑ በዚህ ይታወቃል::

## የልደት አበቅቴ ፀሐይ

የልደት አበቅቴ ፀሐይ ማለት ጌታችን በተወለደበት ዓመት የነበረ ጥንተዮን ማለት ነው:: የዓመተ ልደትን አበቅቴ ፀሐይ ወይም ሐሳበ ፀሐይ ለማወቅ ከአዳም እስከ ልደተ ክርስቶስ ካለው 5501 ዓመት ዕለተ ምርያንና ዕለተ ሠግርን ለይቶ አወጥቶና ደምሮ ለ7 ይከፈላል:: ከ7 የተረፈው አበቅቴ ፀሐይ ይሆናል:: ያውም እንዲህ ነው:-

የ5501 ዓመተ ዓለም:-

| | |
|---|---|
| ዕለተ ምርያ | 5501 ዕለት |
| ሠግረ ዮሐንስ | 1375 ዕለት |
| ድምር | 6876 ዕለት |

ከ6876 ዕለት 1 ሲቀነስ (6876-1)=6875 ዕለት ይተርፋል:: 6875 ዕለት በ7 ዐውደ ዕለት ሲቀመር (6875÷7) =982 ሱባዔ ዕለት ሆኖ 1 ይተርፋል:: ይህ የልደተ ክርስቶስ አበቅቴ ፀሐይ ነው:: ያውም ረቡዕ ዕለት ነው::

## ዕለተ ልደቱ ለክርስቶስ

የክርስቶስን ዕለተ ልደት ለማወቅ:-

| | |
|---|---|
| የ3 ወር ዐጽፈ አውራኅ | 6 ዕለት |
| የታኅሣሥ ሠርቀ መዓልት | 29 ዕለት |





| | |
|---|---|
| ዕለተ ጠቢባን | 2 ዕለት |
| አበቅቴ ፀሐይ | 1 ዕለት |
| ድምር | 38 ዕለት ይሆናል:: |

38 ዕለት በሱባዔ ሲቀመር (38÷7)=5 ሱባዔ ዕለት ሆኖ 3 ይተርፋል:: ስለዚህ የክርስቶስ ዕለተ ልደት ማክሰኞ መሆኑ በዚህ ይታወቃል::

## የጥምቀት አበቅቴ ፀሐይ

የጥምቀት አበቅቴ ፀሐይ ማለት ጌታችን በተጠመቀበት ዓመት የነበረ ጥንተዮን ማለት ነው:: የዓመተ ጥምቀት አበቅቴ ፀሐይን ወይም ሐሳበ ፀሐይ ለማወቅ ከአዳም እስከ ጥምቀተ ክርስቶስ ካለው 5531 ዓመት ዕለተ ምርያንና ዕለተ ሠግርን ለይቶ አውጥቶና ደምሮ ለ7 ዐውደ ዕለት ይከፈላል:: ከ7 የተረፈው አበቅቴ ፀሐይ ይሆናል:: ያውም እንዲህ ነው:: የ5531 ዓመተ ዓለም:-

| | |
|---|---|
| ዕለተ ምርያ | 5531 ዕለት |
| ዕለተ ሠግር | 1382 ዕለት |
| ድምር | 6913 ዕለት ይሆናል:: |

ከ6913 ዕለት 1 ሲቀነስ (6913-1)=6912 ዕለት ይተርፋል:: ይህ በ7 ሲቀመር (6912÷7) =987 ሱባዔ ዕለት ሆኖ 3 ይተርፋል:: ይህ የጥምቀተ ክርስቶስ ዓመት አበቅቴ ፀሐይ ነው::

## ዕለተ ጥምቀቱ ለክርስቶስ

የክርስቶስን ዕለተ ጥምቀት ለማወቅ:-

| | |
|---|---|
| የ4 ወር ዐጽፈ አውራኅ | 8 ዕለት |
| የጥር ሠርቀ መዓልት | 11 ዕለት |
| ዕለተ ጠቢባን | 2 ዕለት |
| አበቅቴ ፀሐይ | 3 ዕለት |
| ድምር | 24 ዕለት ይሆናል:: |



www.ethiopianorthodox.org

24 ዕለት በሱባዔ ሲቀመር (24÷7)=3 ሱባዔ ዕለት ሆኖ 3 ይተርፋል:: ስለዚህ የክርስቶስ ዕለተ ጥምቀት ማክሰኞ መሆኑ በዚህ ይታወቃል::

## የስቅለት አበቅቴ ፀሐይ

የስቅለት አበቅቴ ፀሐይ ማለት ጌታችን በተሰቀለበት ዓመት የነበረ ጥንተዮን ማለት ነው:: የዓመተ ስቅለት አበቅቴ ፀሐይን ለማወቅ ከአዳም እስከ ስቅለተ ክርስቶስ ካለው 5534 ዓመት ዕለተ ምርያንና ዕለተ ሠግርን ለይቶ አውጥቶና ደምሮ ለ7 ዐውደ ዕለት ይከፈላል:: ከ7 የተረፈው አበቅቴ ፀሐይ ይሆናል:: ያውም እንዲህ ነው:- የ5534 ዓመተ ዓለም:-

| | |
|---|---|
| ዕለተ ምርያ | 5534 ዕለት |
| ዕለተ ሠግር | 1383 ዕለት |
| ድምር | 6917 ዕለት ይሆናል:: |

ከ6917 ዕለት 1 ሲቀነስ (6917-1)=6916 ዕለት ይተርፋል:: ይህ በ7 ሲቀመር 988 ሱባዔ ዕለት ሆኖ 7 ይተርፋል ወይም አልቦ ይሆናል:: ይህ የዓመተ ስቅለት አበቅቴ ፀሐይ ነው:: ያውም ማክሰኞ ነው::

የክርስቶስ ዕለተ ስቅለትንና ዕለተ ፍሥሕን ለማወቅ:-

| | |
|---|---|
| የ6 ወር ዐጽፈ አውራኅ | 12 ዕለት |
| የመጋቢት ሠርቀ መዓልት | 26 ዕለት |
| ዕለተ ጠቢባን | 2 ዕለት |
| አበቅቴ ፀሐይ | 7 ዕለት |
| ድምር | 47 ዕለት |

47 ዕለት በ7 ዐውደ ዕለት ሲቀመር 6 ሱባዔ ዕለት ሆኖ 5 ይተርፋል:: ስለዚህ ጌታችን በተሰቀለበት ዓመት በዓለ ፍሥሕ ኀሙስ መጋቢት 26 ቀን መዋሉ በዚህ ይታወቃል:: ሠርቀ ሌሊቱም 14 ነበር:: በማግስቱም ዓርብ መጋቢት 27 ቀን ጌታችን ተሰቅሏል:: ያንጊዜ ሠርቀ ሌሊቱ 15 ነበር::





ጌታችን ከሙታን ተለይቶ የተነሣውም በተሰቀለ በ3ኛው ቀን እሑድ መጋቢት 29 ቀን በ17 ሠርቀ ሌሊት በ6 ሰዓተ ሌሊት ነበር:: በተነሣ በ40 ቀን ግንቦት በባተ በ8 ቀን በ27 ሠርቀ ሌሊት ኀሙስ ዕለት በመላእክት ምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ:: በተነሣ በ50ኛው ቀን ባረገ በ10ኛው ቀን ግንቦት በባተ በ18 ቀን በ6 ሠርቀ ሌሊት ንሑድ በ3 ሰዓተ መዓልት ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው::



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አምስት

## ሐሳበ አቡሻህር

ይህ መጽሐፍ አቡሻህር የተባለ ዮሐንስ የጻፈው ታላቅ የቍጥር መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ የጸሐፊውን ቃል ስለያዘ በጸሐፊው ስም ይጠራል። ይህ መጽሐፍ የፀሐይን፣ የጨረቃን የከዋክብትን ነገር ይናገራል። ከጨረቃ፣ ከከዋክብት አስቀድሞ የፀሐይ ነገር ይናገራል።

አቡሻህር ማለት በዓለ ስብሐት፣ በዓለ አኰቴት ማለት ነው። በዐረቡ እሽኩር አላህ፣ በግእዙ *ስብሐት ይሉና ስብሐት ለአአ* ማለት ነው።

### ጥንታት

ጥንታት አምስት ናቸው። እነርሱም ዓለም የተፈጠረበት ዕለተ እሑድ ጥንተ ዕለት፣ ዕፀዋት፣ አዝርዕት፣ አትክልት የተፈጠሩበት ዕለተ ሠሉስ ጥንተ ቀመር፣ ብርሃናት የተፈጠሩበት ዕለተ ረቡዕ ጥንተዮን፣ ጨረቃ የተወለደችበት ዕለተ ኀሙስ የጨረቃ ጥንተዮን፣ አዳም የተፈጠረበት ዕለተ ዓርብ እንድቅትዮን ናቸው። *ዕለተ ንድቆሙ ለፍጡራን ወነደቃ ለሐዋን እንዲል።*

### ዓመተ ዓለም በፀሐይና በጨረቃ

ይህ ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለ ዘመን ቢቈጠር በፀሐይ 7 ሺሕ 5 መቶ አንድ፣ በጨረቃ 7 ሺሕ 730 ዓመት 8 ወር ከ8 ቀን ነው።

ይህ ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለ ዘመን ቢቈጠር በፀሐይ 5 ሺሕ 5 መቶ፣ በጨረቃ 5 ሺሕ 668 ዓመት 10 ወር 9 ቀን ነው። ከልደተ ክርስቶስ ዠምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለ ዘመን በፀሐይ 2 ሺሕ አንድ፣ በጨረቃ 2 ሺሕ 61 ዓመት 9 ወር 29 ቀን ነው።

ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለ 5 ሺሕ 5 መቶ ዓመተ ፀሐይ በጨረቃ 5 ሺሕ 668 ዓመት፣ 10 ወር፣ 9





ዕለት እንደሆነ ለማጠየቅ ዓመተ ፀሐይን በቀመረ ዐረብ፣ በንኡስ ቀመር ቢቀምሩት 24 ቀመረ ዐረብ 1 ንኡስ ቀመር ሆኖ 9 ዓመተ አበቅቴ ይተርፋል። የቀመረ ዐረብ ልክ 228 ዓመት፣ የንኡስ ቀመር ልክ 19 ዓመት ነው። ከቀመረ ዐረብ 7:7 ዓመት ከንኡስ ቀመር 7:7 ወር፣ ከዓመተ አበቅቴ 11:11 ዕለት ይገኛል። ያውም ከ9ኙ ዓመተ አበቅቴ ምንም ሳይታተትለት 11:11 ቀን ይነግበታል ማለት ነው። ይህስ እንደምን ነው ቢሉ? 5 ሺሕ 5 መቶ ዓመተ ፀሐይን በ228 ቢቀምሩት 24 ቀመረ ዐረብ አንድ ንኡስ ቀመር ሆኖ 9 ዓመተ አበቅቴ ይተርፋል። 24 ቀመረ ዐረብ $24 \times 7 = 168$ ዓመት ይሆናል። 1 ንኡስ ቀመር $1 \times 7 = 7$ ወር ይሆናል። 9 ዓመተ አበቅቴ $9 \times 11 \div 30 = 3$ ወር ከ9 ቀን ይሆናል። ከ24 ቀመረ ዐረብ፣ ከ1 ንኡስ ቀመር፣ ከ9 ዓመተ አበቅቴ የተገኘው 168 ዓመት 10 ወር ከ9 ቀን በ5 ሺሕ 5 መቶ ዓመተ ፀሐይ ላይ ቢደመር 5 ሺሕ 668 ዓመት 10 ወር ከ9 ዕለት ይሆናል ማለት ስለዚህ ነው።

ከልደተ ክርስቶስ ዠምሮ እስከ ዛሬ ያለ 2 ሺሕ አንድ ዓመተ ፀሐይ በጨረቃ 2 ሺሕ 61 ዓመት 9 ወር፣ 29 ዕለት እንደሆነ ለማጠየቅ ዓመተ ፀሐይን በቀመረ ዐረብ፣ በንኡስ ቀመር ቢቀምሩት 8 ቀመረ ዐረብ፣ 9 ንኡስ ቀመር ሆኖ 6 ዓመተ አበቅቴ ይተርፋል። ይህስ እንደምን ነው ቢሉ? 2 ሺሕ አንድ ዓመተ ፀሐይን በ228 ቢቀምሩት 8 ቀመረ ዐረብ 9 ንኡስ ቀመር ሆኖ 6 ዓመተ አበቅቴ ይተርፋል። ከ8 ቀመረ ዐረብ የሚገኝ 7፣7 ዓመት 56 ዓመት ይሆናል። ከ9 ንኡስ ቀመር የሚገኝ 7፣7 ወር 5 ዓመት ከ3 ወር ይሆናል። ከ6 ዓመተ አበቅቴ 1 ቢታተት 5 ይተርፋል። ከ5 ዓመተ አበቅቴ የሚገኝ $5 \times 11 \div 30 = 1$ ወር 25 ቀን ይሆናል። ለጨረቃ ዘመን መሠረት የሆነ 4 ወር 10 ቀን፣ ከትራፋተ ዐውድ የተገኘ 24 ዕለት ይህ ሁሉ ሲደመር 61 ዓመት 9 ወር 29 ዕለት ይሆናል። ከ2001 ዓመት 1 ቢታተት 2000 ዓመት ይሆናል። በ2000 ዓመት ላይ 61 ዓመት 9 ወር 29 ዕለት ሲደመር 2061 ዓመት 9 ወር፣ 29 ዕለት ይሆናል መባሉ ስለዚህ ነው።

ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለ ዘመን ዓመተ ፍዳ፣ ዓመተ ኵነኔ፣ ዘመነ ብሉይ ይባላል። ከክርስቶስ ልደት ዠምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለ ዘመን ዓመተ ምሕረት፣ ዓመተ ሥጋዌ ይባላል። መላው ዓመተ ዓለም መዋዕለ ዓለም ይባላል።



www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

## የቍጥር ቤት

አራቱ ትራፋተ ዐውድ ወይም አምስቱ ትራፋተ ዐውድ ቀመረ ዐረብ፣ በጨረቃ ዓመት ፍጻሜ የጨረቃ ጥንተዮን የሚታወቅባቸውና የሚቈጠርባቸው የቍጥር ቤቶች ስድስት ወይም ሰባት ናቸው:: ምንና ምን ናቸው ቢሉ:- ዕለት፣ ኬክሮስ፣፣ ካልዒት፣ ሣልሲት፣ ራብዒት፣ ኃምሲት፣ ሳድሲት ናቸው:: አቡሻህር በ11ኛው አንቀጽ *ወለእመ ፈቀድከ ታእምር ዘይንእስ እምዝንቱ አኀዝ ዓመተ እልሁጅራ ፍጽምተ በስድስቱ መካናት* እንዲል:: እልሁጅራ ዓመተ አጋራውያን ማለት ነው:: *ዘውእቱ ዓመተ ተንባላት*::

ቍጥሩ ሲከፈልም 1 ዕለት 60 ኬክሮስ፣ 1 ኬክሮስ 60 ከልዒት 1 ካልዒት 60 ሣልሲት፣ 1 ሣልሲት 60 ራብዒት፣ 1 ራብዒት 60 ኃምሲት፣ 1 ኃምሲት 60 ሳድሲት ይሆናል:: *ወሚም በመካን ቀዳማይ ዕለታተ ዓመት ወርኃዊት፣ ወበመካነ ዕለት ትልቁ ኬክሮስ፣ ወበመካነ ኬክሮስ ትልቁ ካልዒት፣ ወበመካነ ከልዒት ትልቁ ሣልሲት፣ ወበመካነ ሣልሲት ትልቁ ራብዒት፣ ወበመካነ ራብዒት ትልቁ ኃምሲት ወበመካነ ኃምሲት ትልቁ ሳድሲት* እንዲል:: ይህ አንድ አርእስት ነው::

ቍጥሩ ሲጠቀለልም 60 ሳድሲት 1 ኃምሲት፣ 60 ኃምሲት 1 ራብዒት፣ 60 ራብዒት 1 ሣልሲት፣ 60 ሣልሲት 1 ካልዒት፣ 60 ካልዒት 1 ኬክሮስ፣ 60 ኬክሮስ 1 ዕለት ይሆናል:: *ወሚም ካዕበ በመካነ ካዕብ ዕለተ፣ ወበመካነ ካልዒት፣ ትልቁ ኬክሮስ፣ ወበመካነ ሣልሲት ትልቁ ካልዒት፣ ወበመካነ ራብዒት ትልቁ ሣልሲት፣ ወበመካነ ኃምሲት ትልቁ ራብዒት፣ ወበመካነ ሳድሲት ትልቁ ኃምሲት ከመ ትኩን ፍጽምተ ትልቁ ዓመት ወርኃዊት ወኬክሮሳቲሃ* እንዲል:: ይህ ሁለተኛ አርእስት ነው::

## የብርሃናት ተፈጥሮ

እግዚአብሔር ዓለምን በፈጠረ ባራተኛ ቀን፣ ሚያዝያ በባተ በ2ኛው ቀን፣ አዳር በባተ በ28ኛ ቀን፣ ጥር በባተ በ15ኛ ቀን፣ *አመ ሰኑዩ ለሚያዝያ አመ ዐሡሩ ወኃሙሱ ለዝልሁጅ* እንዲል:: በጥንተ ሌሊት፣ በጥንተ ሌሊት ባለው በጥንተ እስራ ሌሊት ይላል:: ጥንተ ሌሊት ቢል በመዠመርያው ሰዓተ ሌሊት፣ በጥንተ እስራ ቢል





በዐሥረኛው ሰዓተ ሌሊት ሲል ነው:: ጥንትነቱ ዐሠሩ ለዐሥሩ ነው:: ጥንትነቱ ዐሡሩ ለዐሥሩ ነው ያለው የጨረቃ ዘመን መሠረት ዐሥሩን ዕለት ነው:: በአራተኛው ጥኅት ፀሐይን በምዕራብ፣ ጨረቃን በምሥራቅ በሁለተኛው ሣልሲት ከከዋክብት ጋራ ለዘመን መታወቅያ ሲሆኑ ፈጠረ:: ከኒሳን እስከ አዳር፣ ከመሐረም እስከ ዝልሁጅ ቢቈጥሩ በመጋቢት 29 ሠርቀ መዓልት በ12 ሠርቀ ሌሊት ዓለም እንደተፈጠረ ይታወቃል::

## የጨረቃ የዕለት መንገድና ሕጸጽ

ጨረቃ በ15 ሌሊት በምታበራበት ዐቅም ተፈጥራ የዕለት መንገድዋ በፀሐይ መንገድ ቢሰፍር 59 ኬክሮስ፣ 3 ካልዒት፣ 40 ሣልሲት፣ 16 ራብዒት፣ 18 ኃምሲት፣ 48 ሳድሲት አብርታ ከምዕራብ ሳትደርስ፣ 56 ካልዒት፣ 19 ሣልሲት፣ 43 ራብዒት፣ 41 ኃምሲት 12 ሳድሲት ሲቀራት ፀሐይ 60ውን ኬክሮስ ፈጽሞ በምሥራቅ ታየ:: የጨረቃ የዕለት መንገድዋ፣ የዕለት ሕጸጽዋ በዚህ ይታወቃል:: የወር መንገድዋና የዓመት መንገድዋም በዚሁ መንገድ ሊታወቅ ይችላል::

በምዕራፍ አንድ በስድስቱ ቀናት የተፈጠሩትን ፍጥረታት ዘርዝረናል::በዚህኛው ክፍል በዝርዝር የምናነሣው በአራተኛው ቀን፣ረቡዕ ስለተፈጠሩት ብርሃናት ይሆናል:: ብርሃን ይሁን ብሎ ከፈጠረው ከደገኛው ብርሃን የስንዴን ቅንጣት ያህል ብርሃንን አመጣ:: ይህ ብርሃን ለታላላቅ ብርሃናት ሲሰጥ የሚሰካባቸው ሰባት መስፈርታት አሉ::

እነርሱም ሳድሲት፣ ኃምሲት፣ ራብዒት፣ ሣልሲት፣ ካልዒት፣ ኬክሮስ ዕለት ናቸው:: *ወሶበ ትፈቅድ ዘይንእስ እምዝንቱ አኀዝ ዓመተ እልጉዥራ ፍጽምተ በሰብዓቱ መካናት፤* ማለትም፣ *ከዚህ ያነሰውን መስፈሪያ ለማወቅ ብትፈልግ በሰባት መደብ የተመደበውን ፍጹም የሆነውን የእልጉዥራን ዓመት ያዝ ተመልከት* ይላል (አቡሻህር):: መስፈሪያዎቹ ሲጠቀለሉና ሲዘረዘሩም እንዲህ ነው:-

ሳድሲት 60 ሲሞላ ኃምሲት ይሆናል፤ ኃምሲት 60 ሲመላ ራብዒት፣ ራብዒት 60 ሲመላ ሣልሲት፣ ሣልሲት 60 ሲመላ ካልዒት፣ ካልዒት 60 ሲመላ ኬክሮስ፣ ኬክሮስ 60 ሲመላ ዕለት ይሆናል:: በዚህ ጊዜ በደቂቅነቱ 12 የነበረ ክንትሮስ 6 ይሆናል:: 6



www.ethiopianorthodox.org

ክንትሮስ 1 ኬክሮስ ነው። ስለዚህ 5 ኬክሮስ (5x6) = 30 ክንትሮስ ይሆናል። እነዚህ መስፈርያዎች ፀሐይ በመዓልት፣ ጨረቃ በሌሊት በየምዕዛራቸው የሚያበሩትን የብርሃን መጠን በየሰዓቱ የሚለካባቸው ናቸው። የምዕዛራቸው መከፈትና መዘጋትንም ያመለክታሉ። ምዕዛር ማለት ስቍረት ማለት ነው። ሲበዙም ምዕዛራት፣ ስቍረታት ያሰኛሉ።

## ምዕዛር ወይም ስቍረት

ምዕዛር ወይም ስቍረት ማለት የብርሃን ወንፊት፣ ብርሃን የሚነዛበት ብሱ ነዶላው ነው። የሐሳብ ዘመን መምህራን ለፀሐይ 595፣ ለጨረቃ 105 ምዕዛር አላቸው ብለው ያስተዳራሉ። ይተረጉማሉ። ለማስረጃ የሚጠቅሱት ንባብም እግዚአብሔር ሁለት ታላላቅ ብርሃናትን ፈጠረ። ትልቁ ብርሃን መዓልትን እንዲመግብ፣ ትንሹም ብርሃን ከከዋክብት ጋራ ሌሊትን እንዲመግብ አደረገ፤ (ዘፍ. 1፥16) የሚለውንና እግዚአብሔር ፀሐይ ጨረቃን የፈጠረ ጨልሞት ሲያበሩለት አይደለም፤ ብርሃን ይሁን ካለው የስንዴ ቅንጣት ያህል ማለባቸው እንጂ (ቅዳሴ ግሩም) የሚለውን እነዚህን ሁለት ምንባባት ይጠቅሳሉ። ይህ የስንዴ ቅንጣት የተባለው ብርሃን የሐሳብ ዘመን መምህራን ከሺሕ መጠን ይከፍሉታል። ከሺሑ 595 ለፀሐይ ይደርሳታል። ይህም በምዕዛሯ ልክ ነው። ከሺሕ 595 ሲቀነስ (1000-595) 405 ይተርፋል። ከዚህ ደግሞ 105 ለጨረቃ፣ 100 ለከዋክብት፣100 ለደመናት፣ 100 ለቀላያት ይደርሳቸዋል።

የፀሐይ ድርሻ የሆነው 595 በ98 ቀመር ሲቀመር 6 ክፍል ሆኖ 7 ይተርፋል። (595÷98=6 ሆኖ ቀሪ 7) ስድስቱ ክፍልም ከነግህ እስከ ቀትር በየሰዓቱ ይሰጣታል። እንዲህም ማለት የምዕዛርዋን መከፈት መዘጋት መናገር ነው። 7ቱ ምዕዛሮች ግን መቸም መች አይዘጉም (ኪዳነ ወልድ፣ገጽ 690)። በሠንጠረዥ መደብ ሲተነተንም እንዲህ ነው፡-





## ምዕዛረ ፀሐይ

ከ595 የፀሐይ ድርሻ ከነግህ እስከ ቀትር በሰዓት፣ በክንትሮስ የተለካ በየሰዓቱ ለፀሐይ የሚሰጣት የብርሃን መጠን አንድ መዓርገ ፀሐይ ይባላል። የብርሃኑ መጠን ከመዓርገ ፀሐይ ሲደርስ ምዕዛራት ይከፈታሉ።

## የምዕዛረ ፀሐይ መከፈት

ለፀሐይ የሚሰጣት የብርሃን መጠን በሠንጠረዥ ሲዘረዘርም እንዲህ ነው፡-

| ሰዓት | ኬክሮስ | ክንትሮስ | መዓርገ ፀሐይ | የሚከፈቱ ምዕዛራት መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 5 | 30 | 1 | 98 |
| 2 | 10 | 60 | 2 | 196 |
| 3 | 15 | 90 | 3 | 294 |
| 4 | 20 | 120 | 4 | 392 |
| 5 | 25 | 150 | 5 | 490 |
| 6 | 30 | 180 | 6 | 588 |

ያንጊዜ በጣም ቀትር ይሆናል። ወገጹ ብሩህ ከመ ፀሐይ ዘያስተርኢ በኃይሉ፤ ማለት ፊቱ እጅግ እንደሚያበራ ፀሐይ ብሩህ ነው እንዲል። ወሰበ ይሠርቅ ፀሐይ እምነ ምሥራቅ ይፌኑ ሎቱ ብርሃኖ እግዚአብሔር በበንስቲት እስከ ስድስቱ ሰዓት፤ ማለት ፀሐይ ከምሥራቅ በወጣ ጊዜ እግዚአብሔር እስከ 6 ሰዓት ብርሃኑን በትንሽ በትንሹ ይልክለታል እንዲል። ከዚህ በኋላ የመገመሪያው ስቍረት(ምዕዛር) ይዘጋል።

## የምዕዛረ ፀሐይ መዘጋት

ከስድስት ሰዓት በኋላ መጀመርያው ምዕዛር ይዘጋል። ያውም እንዲህ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

| ሰዓት | ኬክሮስ | ክንትሮስ | መዓርገ ፀሐይ | የሚዘጉ ምዕዛራት መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 7 | 35 | 210 | 7 | 98 |
| 8 | 40 | 240 | 8 | 196 |
| 9 | 45 | 270 | 9 | 294 |
| 10 | 50 | 300 | 10 | 392 |
| 11 | 55 | 330 | 11 | 490 |
| 12 | 60 | 360 | 12 | 588 |

እስከ 6 ሰዓት ሁሉም ፈጽሞ ይዘጋል። ባንድ ዕለት 6 ተውሳክ፣ 6 ሕጸጽ አላት። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር የሰጠውን ብርሃን በመጠን በመጠኑ ይሰበስባል። *ወእምዝ ያስተጋብእ ብርሃና በመድሎተ ዘአመገበ እግዚአብሔር፤ እንዲል፤* መቸም መች በማይዘጉ ሰባቱ ምዕዛሮች እያበራች ትዞራለች።

ምዕዛረ ወርኅ

የጨረቃ ድርሻ የሆነው 105ቱ ደግሞ 15 ሱባዔ ይሆናል። ይህም ከዕለተ ሠርቅ እስከ ዕለተ ገሀህ በየዕለቱ ይሰጣታል። ከ15 ቀን በኋላም በየዕለቱ ሰባት፣ ሰባት እጅ ይነሣታል እስከ 15 ቀን። እንዲህ ማለትም የምዕዛሯን መከፈት መዘጋት መናገር ነው እንጂ ከእፍኘ የሚሰጣት ሌላ ብርሃን አለ ማለት አይደለም። ለፀሐይ ምዕዛር እንዳላት ለጨረቃም አላት ብለው መምህራን ይተረጉማሉ (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ገጽ 690)።

የምዕዛረ ወርኅ መከፈት

ከ105 የጨረቃ ድርሻ ከዕለተ ሠርቅ እስከ ዕለተ ገሀህ በኬክሮስ፣ በክንትሮስ እየተለካ በየዕለቱ ለጨረቃ ብርሃን ሲሰጣት ምዕዛራት ይከፈታሉ። የሚሰጣት የብርሃን መጠንም በሠንጠረዥ ሲዘረዘር እንዲህ ነው።





| ሰዓት | ኬክሮስ | ክንትሮስ | መዓርገ ፀሐይ | የሚከፈቱ ምዕዛራት መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 4 | 24 | 1 እጅ | 7 |
| 2 | 8 | 48 | 4 እጅ | 14 |
| 3 | 12 | 72 | 3 እጅ | 21 |
| 4 | 16 | 96 | 4 እጅ | 28 |
| 5 | 20 | 120 | 5 እጅ | 35 |
| 6 | 24 | 144 | 6 እጅ | 42 |
| 7 | 28 | 168 | 7 እጅ | 49 |
| 8 | 32 | 192 | 8 እጅ | 56 |
| 9 | 36 | 216 | 9 እጅ | 63 |
| 10 | 40 | 240 | 10 እጅ | 70 |
| 11 | 44 | 264 | 11 እጅ | 77 |
| 12 | 48 | 288 | 12 እጅ | 84 |
| 13 | 52 | 312 | 13 እጅ | 91 |
| 14 | 56 | 336 | 14 እጅ | 98 |
| 15 | 60 | 360 | 15 እጅ | 105 |

እንዲህ እያለች በምልዓት እስከ 15፣ በሕጸጽ እስከ 14 ዕለት ትኼዳለች በ15ኛው ቀን ብርሃንዋን ፈጽማ ታገኛለች። ከዚህ በኋላ እየጐደለች ትኼዳለች።

የምዕዛረ ወርኅ መዘጋት

ከ16ኛው ቀን ጀምሮ እስከ 30 በኬክሮስ፣ በክንትሮስ እየተለካ በየዕለቱ ብርሃን ሲነሣት ጨለማ በዝቶ ብርሃን ስለሚያንስ ምዕዛራት ይዘጋሉ። የጨለማው መጠን ማለት ሕጸጽዋ በሠንጠረዥ ሲዘረዘርም እንዲህ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

| ሰዓት | የሚነሣት የብርሃን መጠን | | የሕጸጽዋ ልክ | የሚዘጉ ምዕዛራት መጠን |
|---|---|---|---|---|
| | ኬክሮስ | ክንትሮስ | | |
| 16 | 4 | 24 | 1 | 7 |
| 17 | 8 | 48 | 2 | 14 |
| 18 | 12 | 72 | 3 | 21 |
| 19 | 16 | 96 | 4 | 28 |
| 20 | 20 | 120 | 5 | 35 |
| 21 | 24 | 144 | 6 | 42 |
| 22 | 28 | 168 | 7 | 49 |
| 23 | 32 | 192 | 8 | 56 |
| 24 | 36 | 216 | 9 | 63 |
| 25 | 40 | 240 | 10 | 70 |
| 26 | 44 | 264 | 11 | 77 |
| 27 | 48 | 288 | 12 | 84 |
| 28 | 52 | 312 | 13 | 91 |
| 29 | 56 | 356 | 14 | 98 |
| 30 | 60 | 380 | 15 | 105 |

ይህም ልበ አብድ የሐጸጸ ከመ እንተ ወርኅ፤ የሰነፍ ልቡ እንደ ጨረቃ እየጐደለ ይኼዳል እንደተባለው የጨረቃን ሕጸጽ የሚያመለክት ነው። ይህ 12 መዓርገ ወርኅ ይባላል። 12 መዓርገ ወርኅ ማለት 12 ሰዓተ ሌሊት ማለት ነው። ደግሞም በአምጣነ ጽልመታ ከማሁ ብርሃና፤ እንዲል 12 መዓርገ ፀሐይ ማለት 12 ሰዓተ መዓልት ማለት ነው።

## የጨረቃ ብርሃን

ጨረቃ ከተወለደችበት ቀን ገምሮ እስከ 15 ቀን በኬክሮስና በክንትሮስ እየተለካ በየቀኑ የሚሰጣት የብርሃን መጠን በምታበራበት ጊዜ ብርሃኑ በገዘፉ ጨለማው ብለሚያንስ በየቀኑ የምታተርፈው የኬክሮስና የክንትሮስ መጠን ይታወቃል። የምታበራውና የምታተርፈው በሠንጠረዥ ሲዘረዘርም እንዲህ ነው፡-



www.ethiopianorthodox.org



| ሰዓት | ኬክሮስ | ክንትሮስ | የብርሃን መጠን | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | የምታበራው | የምታተርፈው | |
| 1 | 4 | 24 | 1 እጅ | 56 ኬክሮስ | 336 ክንትሮስ |
| 2 | 8 | 48 | 2 እጅ | 52 ኬክሮስ | 312 ክንትሮስ |
| 3 | 12 | 72 | 3 እጅ | 48 ኬክሮስ | 288 ክንትሮስ |
| 4 | 16 | 96 | 4 እጅ | 44 ኬክሮስ | 264 ክንትሮስ |
| 5 | 20 | 120 | 5 እጅ | 40 ኬክሮስ | 240 ክንትሮስ |
| 6 | 24 | 144 | 6 እጅ | 36 ኬክሮስ | 216 ክንትሮስ |
| 7 | 28 | 168 | 7 እጅ | 32 ኬክሮስ | 192 ክንትሮስ |
| 8 | 32 | 192 | 8 እጅ | 28 ኬክሮስ | 168 ክንትሮስ |
| 9 | 36 | 216 | 9 እጅ | 24 ኬክሮስ | 144 ክንትሮስ |
| 10 | 40 | 240 | 10 እጅ | 20 ኬክሮስ | 120 ክንትሮስ |
| 11 | 44 | 264 | 11 እጅ | 16 ኬክሮስ | 96 ክንትሮስ |
| 12 | 48 | 288 | 12 እጅ | 12 ኬክሮስ | 72 ክንትሮስ |
| 13 | 52 | 312 | 13 እጅ | 8 ኬክሮስ | 48 ክንትሮስ |
| 14 | 56 | 336 | 14 እጅ | 4 ኬክሮስ | 24 ክንትሮስ |
| 15 | 60 | 360 | 15 እጅ | 0 (አልቦ) | 0 (አልቦ) |

እንዲህ እያለ ብርሃንዋ ይፈጸማል። ይህ 12 መዓርገ ወርኅ ነው። 12 መዓርገ ወርኅ ማለት 12 ሰዓተ ሌሊት ማለት ነው። በዚሁ ላይ 12 መዓርገ ፀሐይ ማለት 12 ሰዓተ መዓልት ሲደመር 24 ሰዓት ይሆናል። 24ቱ ሰዓታት የፀሐይንና የጨረቃ ዕለትን

ለማስገኘት በዚህ ሲመላለስ ይኖራሉ:: ወሰመዮ ለጽልመት ሌሊተ ወለብርሃን መዓልተ ኮነ ምሴተ ወጸብሐ ወኮነ አሐደ ዕለተ:: ዕለት ብሂል ዘያስተዛውኃሙ ለመዓልት ወለሌሊት፤ እንዲል:- እግዚአብሔርም ብርሃኑን መዓልት ጨለማውንም ሌሊት ብሎ ጠራው:: ማታም ሆነ፣ ጥዋትም ሆነ፣ አንደኛ ቀን ሆነ:: ዕለት ማለትም መዓልትንና ሌሊትን የሚያዛውግ የሚያዛምድ ማለት ነው:: በዚህም በወዲያኛውም ያሉ መላእክት በዚህ ዓለም ያሉ ቅዱሳን ያመሰግኑበታል:: ከእነዚህም በዚህ ዓለም ያሉ ምእመናን ሊያመሰግኑባቸው 7 ሰዓታት ተለይተዋል:: ሰብዓ ለዕለትየ እሴብሐከ፤ ማለት ለኔ ብለህ በፈጠርህልኝ ቀን ሰባት ጊዜ አመሰግንሃለሁ ማለት ነው:: (መዝ. 188፥165፣ ዘፍ. 1፥5)::

## የከዋክብት ምግብና

የ12ቱ መገብተ አውራኀ ከዋክብት ተከታዮች 28 ንኡሳን ከዋክብት አሉ:: ከአራቱ መገብተ አዝማን አንዱም አንዱም ኮከብ 91፣91 ቀን ይመግባል:: ከ12ቱ መገብተ አውራኀ ከዋክብት ሦስት ሦስቱ ተለይተው አለቆቻቸውን ተከትለው ከ90ው ቀን እያንዳንዳቸው አንዳንድ ወር ይመግባሉ:: ከ28ቱ ንኡሳን ከዋክብት ሰባት ሰባቱ ተለይተው አለቆቻቸውን ተከትለው ከ91 ቀን፣ 13፣13 ቀን ይመግባሉ:: ስማቸውም በአቡሻህር ተጽፎ ይገኛል::

ከ12ቱ መገብተ አውራኀ ከዋክብት ሐመል፣ ተውር፣ ጀውዛ ዕለታቸው 90፣ ኬክሮሳቸው 85 አለቃቸው ምልክኤል ምግብናቸው መሬት ነው:: ሸርጣን፣ አሰድ፣ ሰንቡላህ ዕለታቸው 90 ኬክሮሳቸው 78 አለቃቸው ሕልመልሜሌክ፣ ምግብናቸው ውሀ ነው:: ሚዛን፣ ዐቅራብ፣ ቀውስ፣ ዕለታቸው 90 ኬክሮሳቸው 78፣ አለቃቸው ሚካኤል፣ ምግብናቸው ነፋስ ነው:: ጀደይ፣ ደላዊ፣ ሑት ዕለታቸው 90 ኬክሮሳቸው 74፣ አለቃቸው ናርኤል ምግብናቸው እሳት ነው:: አራቱ 90 ቀን 360 ዕለት ነው:: ኬክሮሱም ሲደመር 315 ይሆናል:: 360ው ዕለት 12 ወር ይሆናል:: 300 ኬክሮስ 5 ዕለት ማለት 5 ጳጉሜን ነው:: 15 ኬክሮስ ባራት ዓመት አንድ ዕለት ይሆናል:: ያውም 6ኛ ጳጉሜን ነው::



www.ethiopianorthodox.org



## የፀሐይና የከዋክብት ምግብና

| ኮከብ | ሐመል | ተውር | ጀውዛ | ሀርጣን | ዐሰድ | ሰንቡላ | ሚዘን | ዐቅራብ | ቀውስ | ጀደይ | ደለዊ | ሑት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዕለት | 30 | 30 | 31 | 31 | 31 | 30 | 30 | 29 | 29 | 29 | 30 | 30 |
| ኬክሮስ | 43 | 12 | 30 | 26 | 10 | 42 | 10 | 40 | 28 | 23 | 41 | 10 |

ድምር 360 ዕለት ከ315 ኬክሮስ ይሆናል::

315፥60= 5 ጳጉሜን፣ 15 ኬክሮስ ነው:: ይህ በ360 ላይ ሲደመር 365 ዕለት ከ15 ኬክሮስ ይሆናል::

የያንዳንዱ ወር መነሻና መድረሻም እንዲህ ይገለጻል:: ሐመል ምግብናውን በመጋቢት በ17 ይጀምራል:: በሚያዝያ በ17 ይፈጽማል:: ከመጋቢት 16 ቢነሣለት 14 ይተርፋል:: በመጋቢት 14 ላይ የሚያዝያን 16 ቢያክሉ 30 ይሆናል:: 17ኛው ዕለት 60 ኬክሮስ ነው:: ከ60 ኬክሮስ 43ቱን ነሥቶ፣ በ30 ዕለት ላይ አክሎ ለሐመል ቢሰጡ ከሚያዝያ 13 ዕለት ከ17 ኬክሮስ ይተርፋል:: በሚያዝያ 13 ላይ የግንቦት 17 ዕለት ቢታከል 30 ዕለት ይሆናል:: ከ17 ኬክሮስ 12ቱን ነስቶ፣ በ30 ዕለት ላይ አክሎ ለተውር ቢሰጡ ከግንቦት 13 ዕለት 5 ኬክሮስ ይተርፋል:: በግንቦት 13 ዕለት ላይ የሠኔ 18 ቀን ቢታከል 31 ቀን ይሆናል:: 19ኛው ዕለት 60 ኬክሮስ ነው:: ይህ በ5 ኬክሮስ ላይ ቢታከል 65 ኬክሮስ ይሆናል:: ከ65 ኬክሮስ 30ውን ነሥቶ በ31 ላይ አክሎ ለጀውዛ ቢሰጡ ከሠኔ 11 ዕለት ከ35 ኬክሮስ ይተርፋል::

እሊህ ሦስቱ አውራኅ ሚያዝያ፣ ግንቦትና ሰኔ ናቸው:: በዕብራውያን ዘመን መፀው፣ በኢትዮጵያ ዘመን ጸደይ ይባላሉ:: የሦስቱ ከዋክብት አለቃም ምልክኤል ይባላል::

በሠኔ 11 ዕለት ላይ የሐምሌ 20 ዕለት ቢታከል 31 ዕለት ይሆናል:: ከ35 ኬክሮስ 26 ኬክሮስ ነሥቶ፣ በ31 ዕለት ላይ አክሎ ለሸርጣን ቢሰጡ ከሐምሌ 10 ዕለት ከ9 ኬክሮስ ይተርፋል:: በሐምሌ 10 ዕለት ላይ የነሐሴ 21 ዕለት ቢታከል 31 ዕለት ይሆናል:: 22ኛው ዕለት 60 ኬክሮስ ነው:: ይህ በ9 ኬክሮስ ላይ ቢታከል 69 ኬክሮስ ይሆናል:: ከ69 ኬክሮስ 10 ነሥቶ በ31 ዕለት ላይ አክሎ ለዐሰድ ቢሰጡ ከነሐሴ 8 ዕለት 59 ኬክሮስ ይተርፋል:: ከነሐሴ 8 ዕለት ላይ 5 ጳጉሜን፣ የመስከረም 17 ዕለት ቢታከል 30 ዕለት ይሆናል:: ከ59 ኬክሮስ 42ቱን ነሥቶ በ30 ዕለት ላይ አክሎ ለሰንቡላህ ቢሰጡ ከመስከረም 13 ዕለት 17 ኬክሮስ ይተርፋል::

እሊህ ሦስቱ አውራኅ ሐምሌ፣ ነሐሴ፣ መስከረም ናቸው:: በዕብራውያን ዘመን ሐጋይ፣ በኢትዮጵያ ዘመን ክረምት ይባላሉ:: የሦስቱ ከዋክብት አለቃ ሕልመልሜሌክ ይባላል::

በመስከረም 13 ዕለት ላይ የጥቅምት 17 ቢታከል 30 ዕለት ይሆናል:: ከ17ቱ ኬክሮስ 10 ነሥቶ፣ በ30 ዕለት ላይ አክሎ ለሚዛን ቢሰጡ ከጥቅምት 13 ዕለት 7 ኬክሮስ ይተርፋል:: በጥቅምት 13 ላይ የኅዳር 16 ዕለት ቢታከል 29 ዕለት ይሆናል:: 17ኛው ዕለት 60 ኬክሮስ ነው:: በ7 ኬክሮስ ላይ ቢታከል 67 ኬክሮስ ይሆናል:: ከ67 ኬክሮስ 40 ኬክሮስ ነሥቶ በ29 ዕለት ላይ አክሎ ለዐቅራብ ቢሰጡ ከኅዳር 13 ዕለት 27 ኬክሮስ ይተርፋል:: በኅዳር 13 ዕለት ላይ የታኅሣሥ 16 ዕለት ቢያክሉ 29 ዕለት ይሆናል:: 17ኛው ዕለት 60 ኬክሮስ ነው:: በ27 ኬክሮስ ላይ ቢታከል 87 ኬክሮስ ይሆናል:: ከ87 ኬክሮስ 28 ኬክሮስ ነሥቶ በ29 ዕለት ላይ አክሎ ለቀውስ ቢሰጡ ከታኅሣሥ 13 ዕለት 59 ኬክሮስ ይተርፋል::

እሊህ ሦስቱ አውራኅ ጥቅምት፣ ኅዳር፣ ታኅሣሥ ናቸው:: በዕብራውያን ዘመን ጸደይ፣ በኢትዮጵያ ዘመን መፀው ይባላሉ:: የሦስቱ ከዋክብት አለቃ ሚካኤል ይባላል::

በታኅሣሥ 13 ዕለት ላይ የጥር 16 ዕለት ቢታከል 29 ዕለት ይሆናል:: ከ59 ኬክሮስ 23ቱን ነሥቶ በ29 ዕለት ላይ አክሎ ለጀደይ ቢሰጡ ከጥር 14 ዕለት 36 ኬክሮስ ይተርፋል:: በጥር 14 ዕለት ላይ





የየካቲት 16 ዕለት ቢታከል 30 ዕለት ይሆናል:: 17ኛው ዕለት 60 ኬክሮስ ነው:: በ36 ኬክሮስ ላይ ቢታከል 96 ኬክሮስ ይሆናል:: ከ96 ኬክሮስ 41 ነሥቶ በ30 ዕለት ላይ አክሎ ለደለው ቢሰጡ ከየካቲት 13 ዕለት 55 ኬክሮስ ይተርፋል:: በየካቲት 13 ዕለት ላይ የመጋቢት 16 ዕለት ቢታከል 29 ዕለት ይሆናል:: በዐረፍተ ሣህል ውስጥ የሚገኝ 15 ኬክሮስ አለ:: በ55 ኬክሮስ ላይ ቢታከል 70 ኬክሮስ ይሆናል:: ከ70 ኬክሮስ 60ውን ኬክሮስ ነሥቶ 1 ዕለት አድርጎ በ29 ዕለት ላይ አክሎ ለሑት 30 ዕለት 10 ኬክሮስ ይሰጠዋል::

እሊህ ሦስቱ አውራኅ ጥር የካቲት መጋቢት ናቸው:: በዕብራውያን ዘመን ክረምት፣ በኢትዮጵያ ዘመን ሐጋይ ይባላሉ:: የሦስቱ ከዋክብት አለቃ ናርኤል ይባላል:: ይህ ሁሉ ተሰብስቦ ቢቈጠር በፀሐይ 365 ዕለት 15 ኬክሮስ ይሆናል:: የሚጐድለው አንዳንድ ሣልሲት ነው:: ፀሐይ ከ12 መንብተ አውራኅ ከዋክብት ጋር የሚመግበው የፀሐይ ዐውደ ዓመት ይህ ነው:: የ12ቱ መንብተ አውራኅ ከዋክብት ነገር ደረሰ ተፈጸመ:: ከዕለታት 360 ዕለት፤ ከኬክሮስ 5 ጳጉሜን 15 ኬክሮስ ይገኛል::

## የከዋክብት ባሕርይና ግብር

የ12 መንብተ አውራኅ ከዋክብት ባሕርይና ግብር እንዲህ ነው:-

| ባሕርይ | ኮከብ | ኮከብ | ኮከብ |
|---|---|---|---|
| እሳት | ሐመል፣ | ዐሰድ | ቀውስ |
| መሬት | ተውር | ሳንቡላህ | ጀይደ |
| ነፋስ | ጀውዛ | ሚዛን | ደለው |
| ውሃ | ሸርጣን | ዐቅራብ | ሑት |

## ዕሪና መዓልትና ሌሊት

ብርሃናት ያልተፈጠሩበት አንዳንድ ሣልሲትም በዓመት 360 ሣልሲት ይሆናል:: ይህም በ60 ቢቀመር (360÷60) 6 ካልዒት ይሆናል:: ይህ እስከ 600 ዓመት ቢሰበሰብ (600×6÷60) 60 ኬክሮስ ይሆናል:: 60ውን 1 ዕለት ብሎ ዕሪና ሌሊት ዕሪና መዓልት ይሆናል:: ዓለም ከተፈጠረ ገርምሮ እስከ ዛሬ ያለ ዘመን ቢቈጠር 7501 ዓመት ነው:: ይህ በ600 ዓመት ቢቀመር 12 ዕሪና ሆኖ 13ኛ ው ዕሪና ከተዠመረ 301 ዓመት ሆኖታል:: ዓለም የተፈጠረ በዕሪና

www.ethiopianorthodox.org

መዓልት በዕሪና ሌሊት ነው:: እስራኤልም ከግብጽ የወጡት በዕሪና መዓልት በዕሪና ሌሊት ነው:: ዓለም ያልፋል ተብሎ የሚጠረጠረውም በዚያን ጊዜ ነው::

## ጥንተ ጨረቃ

ጨረቃ በተፈጠረች በ15 ቀን ረቡዕ ጠፍ ሆነች:: ማክሰኞን ቢያክሉ 16 ይሆናል:: ይህ ከቁጥር አልገባም:: በ17 ቀን ኀሙስ ተወለደች:: ቍጥር ከኀሙስ ተገ[መረ:: ጥንተ ዮንም ተባለ:: ዐውደ ዓመትዋን በፀሐይ በነሐሴ 24 ዕለት ትፈጽማለች:: በጨረቃም ሠኔ (ጀማዲ) 10 ዕለት ትፈጽማለች:: አመ ዕሥራ ወረቡዑ ለነሐሴ፣ አመ ዐሡሩ ለሠርቀ ጀማዲ ቀደማይ እንዲል የጨረቃን ዘመን የሚቄጥር 4ቱን ወር መሠረት አድርጎ ይቈጥራል:: ትራፋተ ዐውድን የሚቈጥር 10ሩን ዕለት መሠረት አድርጎ ይቈጥራል:: ይህ 4 ወር ከ10 ቀን ይሆናል:: ያውም እንዲህ ነው:-

ከረቡዕ እስከ ረቡዕ 15 ቀን ማክሰኞን ቢጨምሩ 16 ዕለት ይሆናል:: ከሚያዝያ 16 ቢነሣ 14 ዕለት ይተርፋል:: በዚህ ላይ የግንቦት 16 ቢታከል 30 ዕለት ይሆናል:: ይህ አንድ ሙሉ ወር ነው:: ከግንቦት 16 ዕለት ቢነሣ 14 ዕለት ይተርፋል:: በዚሁ ላይ የሠኔ 15 ዕለት ቢታከል 29 ዕለት ይሆናል:: ይህ ሕጹጽ ወር ነው:: ሁለት ወር:: ከሠኔ 15 ቢነሣ 15 ዕለት ይተርፋል:: በዚሁ ላይ የሐምሌ 15 ቀን ቢታከል 30 ዕለት ይሆናል:: ይህ ሙሉ ወር ነው:: 3 ወር:: ከሐምሌ 15 ቢነሣ 15 ቀን ይተርፋል:: በዚሁ ላይ የነሐሴ 14 ቀን ቢታከል 29 ዕለት ይሆናል:: ይህ ሕጹጽ ወር ነው:: 4 ወር 10 ቀን ይሆናል:: ስለዚህ የጨረቃን ወር የሚቈጥር 4ቱን ወር መሠረት አድርጎ ይቈጥራል የተባለው ስለዚህ ነው::

## የጨረቃ የ15 ቀን መንገድና ሕጸጽዋ

የጨረቃ የ15 ቀን መንገድዋ በፀሐይ መንገድ ቢለፍር 14 ዕለት፣ 45 ኬክሮስ፣ 55 ካልዒት፣ 4 ሣልሲት፣ 4 ራብዒት፣ 42 ኃምሲት ይሆናል:: ሳድሲት ግን በዕለት መንገድዋ ካልሆነ በቀር በሌላ አትገኝም:: የ15 ቀን ሕጸጽዋም 14 ኬክሮስ፣ 4 ካልዒት፣ 55 ሣልሲት፣ 55 ራብዒት፣ 18 ኃምሲት ነው::



www.ethiopianorthodox.org



## የጨረቃ የወር መንገድና ሕጸጽዋ

የጨረቃ የወር መንገድዋ በፀሐይ መንገድ ቢለፈር 29 ዕለት፣ 31 ኬክሮስ፣ 50 ካልዒት፣ 8 ሣልሲት፣ 9 ራብዒት፣ 24 ኃምሲት ይሆናል:: የወር ሕጸጽዋም 28 ኬክሮስ፣ 9 ካልዒት፣ 51 ሣልሲት፣ 50 ራብዒት፣ 36 ኃምሲት ይሆናል::

## የጨረቃ የዓመት መንገድና ሕጸጽ

የጨረቃ የዓመት መንገድዋ በፀሐይ መንገድ ቢለፈር 354 ዕለት፣ 22 ኬክሮስ፣ 1 ካልዒት፣ 37 ሣልሲት፣ 52 ራብዒት፣ 48 ኃምሲት ይሆናል:: የዓመት ሕጸጽዋም 5 ዕለት፣ 37 ኬክሮስ፣ 58 ካልዒት፣ 22 ሣልሲት፣ 7 ራብዒት፣ 12 ኃምሲት ይሆናል::

ሌሊቱ ነግቶ ፀሐይ እስኪወጣ ድረስ 26 ካልዒት፣ 15 ሣልሲት፣ 30 ራብዒት ይገኛል:: ማታም ፀሐይ ገብቶ እስኪጠፋ ድረስ 26 ካልዒት፣ 15 ሣልሲት፣ 30 ራብዒት ይገኛል::

ይህ በቀን፣ በወር፣ በዓመት ሲታሰብና ሲሰበሰብ ስሌቱ እንዲህ ነው:-

የጥዋትና የማታ በቀን ሲታሰብ 52 ካል፣ 31 ሣል፣ 00 ራብ ይሆናል:: የቀኑ በወር ሲሰላና ሲሰበሰብ 26 ኬክ፣ 15 ካል፣ 30 ሣል፣ 00 ካል ይሆናል:: የወሩ በዓመት ሲሰላና ሲሰበሰብ 5 ዕለት፣ 15 ኬክ፣ 6 ካል፣ 00 ሣል ይሆናል::

የዓመቱ ውጤት 5 ጳጉሜን፣ 15 ኬክሮስ፣ 6 ካልዒት ነው:: 15 ኬክሮስ ባራት ዓመት 1 ዕለት ይሆናል:: ያውም 6ኛ ጳጉሜን ነው:: 6 ካልዒት በ600 ዓመት 1 ዕለት ይሆናል:: ያውም 7ኛ ጳጉሜን ነው::

5 ጳጉሜን በዐረፍተ ሣህል ውስጥ ያለ 15 ኬክሮስ በጨረቃ የዓመት ሕጸጽ ላይ ሲደመርም እንዲህ ነው::

5 ዕለት 37 ኬክ፣ 58 ካል፣ 22 ሣል፣ 7 ራብዒት፣ 12 ኃምሲት (የጨረቃ የዓመት ሕጸጽ)

በ5 ጳጉሜን 15 ኬክሮስ ላይ ሲደመር

10 ዕለት 52 ኬክ፣ 58 ካል፣ 22 ሣል፣ 7 ራብዒት፣ 12 ኃምሢት ይሆናል።

52ቱን ኬክሮስ 1 ዕለት ብሎ በ10ሩ ዕለት ላይ ሲደመር 11 ዕለት ይሆናል። ጉንደ አበቅቴ የሚባለው ይህ ነው።

10 ዕለት 52 ኬክ፣ 58 ካል፣ 22 ሣል፣ 7 ራብ፣ 12 ኃም እስከ 19 ዓመት ቢቈጠር 206 ዕለት 46 ኬክ፣ 29 ካል፣ ሣልሲት ጠፍ፣ 16 ራብ፣ 48 ኃምሢት ይሆናል። ይህ በጨረቃ 7 ወር ሆኖ 3 ኬክ፣ 38 ካል፣ 3 ሣል፣ 11 ራብዒት ይተርፋል። ኃምሢት ጠፍ ነው። ይህ 7 ወር ኋላ በሥፍራው እስኪመጣ ድረስ ይቈያል።

## ቀመረ ትራፋተ ዐውድ

3 ኬክሮስ፣ 38 ካል፣ 3 ሣል፣ 11 ራብዒት ይህ ሁሉ ተሰብስቦ እስከ 16½ ዐውድ ቢቈጠር 59 ኬክሮስ 57 ካል፣ 52 ሣል፣ 31 ራብዒት፣ 30 ኃምሢት ይሆናል። ይህ በጨረቃ የዕለት መንገድ ቢሰፈር 1 ዕለት ሆኖ 54 ካል፣ 12 ሣል፣ 15 ራብ፣ 11 ኃም፣ 12 ሳድ ትርፍ ሆኖ ይገኛል። ትርፉ ደቃይቅ ተብሎ ይቀራል። ይህ 1 ዕለት የተገኘለት 16½ ዐውድ በዓመት ተዘርዝሮ ቢቈጠር (16½×19) 313 ዓመት ተመንፈቅ ይሆናል። ቀመረ ትራፋተ ዐውድ የሚባል ይህ ነው።

7501 ዓመተ ዓለም በቀመረ ትራፋተ ዐውድ፣ በንኡስ ቀመር ቢቀመር 23 ቀመረ ተራፋተ ዐውድ፣ 15 ንኡስ ቀመር ሆኖ 5 ዓመት ተመንፈቅ ይተርፋል። ከ1 ቀመረ ትራፋተ ዐውድ 1 ዕለት 54 ካልዒት፣ ከ23 ቀመር ትራፋተ ዐውድ 23 ዕለት 1242 ካልዒት፣ከ15 ንኡስ ቀመር 45 ኬክ፣ 570 ካልዒት ይገኛል።

በ23 ዕለት በ1242 ካልዒት ላይ 45 ኬክ፣ 570 ካል ቢደመር 24 ዕለት 15 ኬክ፣ 12 ካል ይሆናል። 12 ካልዒት 60 እስከሞላ ድረስ ተቀማጭ ነው። ኬክሮስ 30 ቢመላ ወይም ከ30 ቢተርፍ ይያዛል። ባይመላ ግን ይገደፋል። *ኬክሮስ ለእመ ኮነ 30 አው ተርፈ እም 30 ረስዮ አሐደ ዕለተ ወለእመ ኢኮነ 30 ግድፎ እንዲል።*

የጨረቃ ተውሳክ የተባለ 10 ዕለት በ24 ዕለት ላይ ቢታከል 34 ዕለት ይሆናል። ጨረቃ 28 ቀን አብርታ በ29 ጠፍ ትሆናለች። ከ34ቱ 29ኙ ሕጹጽ ወርኅ ተብሎ ቢገደፍ 5 ይተርፋል። ትራፋተ





ዐውድ 5 መባሉ ስለዚህ ነው። ወይም ጨረቃ 29 ቀን አብርታ በ30ኛው ቀን ጠፍ ትሆናለች። ከ34ቱ ቀን 30ው ሙሉ ወርኅ ተብሎ ቢገደፍ 4 ይተርፋል። ትራፋተ ዐውድ 4 ነው መባሉ ስለዚህ ነው። ትራፋተ ዐውድ 4 ነው ቢባል የታየችበትን 5 ነው ቢባል የተወለደችበትን መናገር ነው።የጨረቃ ተውሳክ 10ሩ ከምን ይገኛል ቢሉ በአቡሻህር በ23ኛው አንቀጽ ይገኛል። *ወትዌስክ ዲበ ዕለታት ዐሠርተ ዘልፈ፤* ብሎ እንደተናገረ የቀመረ ትራፋተ ዐውድ ነገር ተፈጸመ።

**ቀመረ ትራፋተ ዐውድ፡-** 16 1/2 ዐውድ ወይም 313 1/2 ዓመት ነው። ይህም 5ወይም 4 ትራፋተ ዐውድ የሚገኝበት ስሌት ነው። ትራፋተ ዐውድም ከሌሊት ብተት እየተደመረ የጨረቃ ወር ብተትን ያመለክታል።

ከዚህ ቀጥሎ የጨረቃ ወሮች ስም ይነበባል፡-

የጨረቃ ወሮች ስም የ1912 እና የ2004 ዓ.ም. ምሳሌ

| ዐረብ | ግእዝ | ግእዝ | ዕለታቱ |
|---|---|---|---|
| | 1912 | 2004 | |
| መሐረም | የካቲት | ታኅሣሥ | 30 |
| ሰፈር | መጋቢት | ጥር | 29 |
| ረቢዕ ቀዳማይ | ሚያዝያ | የካቲት | 30 |
| ረቢዕ ደኃራይ | ግንቦት | መጋቢት | 29 |
| ጀማጂ ቀዳማይ | ሠኔ | ሚያዝያ | 30 |
| ጀማጂ ደኃራይ | ሐምሌ | ግንቦት | 29 |
| ረጀብ | ነሐሴ | ሠኔ | 30 |
| ሽዕባን | መስከረም | ሐምሌ | 29 |
| ረመዳን | ጥቅምት | ነሐሴ | 30 |
| ሀዋል | ኅዳር | መስከረም | 29 |
| ዝልሁቅዳ | ታኅሣሥ | ጥቅምት | 30 |
| ዝልሁጅ | ጥር | ኅዳር | 29 |



www.ethiopianorthodox.org

የእነዚህ ወሮች ቍጥር የሚቈጠረው በሠርቀ ሌሊት ነው። *ዝልሁጅ ዘውእቱ ጥር ወኑልቆ ዕሥራ ወተሰዓቱ* እንዲል (አቡሻ)።

## ቀመረ ዐረብ

በሥፍራው እስኪመጣ ይቈይ ተብሎ የነበረው 7 ወር እስከ 12 ንኡስ ቀመር ቢቈጠር 7 ዓመት ይሆናል። 7 ዓመት የተገኘበት 12 ንኡስ ቀመር በዓመት ተዘርዝሮ ቢቈጠር 228 ዓመተ ፀሐይ ይሆናል። ቀመረ ዐረብ የሚባል ይህ ነው።7501 ዓመተ ዓለም በቀመረ ዐረብ፣ በንኡስ ቀመር ቢቀመር 32 ቀመረ ዐረብ፣ 10 ንኡስ ቀመር፣ ሆኖ 15 ዓመተ አበቅቴ ይተርፋል።

ያውም እንዲህ ነው። 7501 ዓመት ለ228 ሲከፈል 32 ቀመረ ዐረብ ሆኖ 205 ዓመት ይተርፋል። 205 ዓመት ለ19 ሲከፈል 10 ንኡስ ቀመር ሆኖ 15 ዓመት ይተርፋል። ከ15ቱ ዓመት 1 ሲቀነስ 14 ይተርፋል። ከ14 ዓመት 11፣ 11 ዕለት ተሰብስቦ ለ30 ሲካፈል 5 ወር ከ4 ቀን ይገኛል። ከ10 ንኡስ ቀመር 7፡7 ወር ቢሰበሰብ 70 ወር ይሆናል። ከ32 ቀመረ ዐረብ 7፡7 ዓመት ቢሰበሰብ 224 ዓመት ይሆናል። ይህ ሁሉ ተሰብስቦ ሲደመር 230 ዓመት 3 ወር፣ 4 ቀን ይሆናል። በዚሁ ላይ ለጨረቃ ዘመን መሠረት የሆነ 4 ወር ከ10 ቀን፣ ከትራፋተ ዐውድ የተገኘ 24 ዕለት ሲደመር 230 ዓመት 8 ወር ከ8 ቀን ይሆናል። *እምዓመታት ክልኤተ አእትት ወእምአውራኅ አርባዕተ ወሰክ* የተባለው ተፈጽሞ 230 ዓመት 8 ወር ከ8 ቀን እናገኛለን።

ይህ በ7500 (7501-1) ዓመተ ፀሐይ ላይ ቢደመር በጨረቃ 7730 ዓመት 8 ወር፣ ከ8 ቀን ይሆናል። *ለፀሐይ አሐደ አእትት፣ ለጨረቃ ክልኤተ አእትት* እንዲል፤በዚሁ አሠራር መሠረት የዘመኑ ዐውደ አበቅቴ ሦስተኛ አንቀጽ የሚያበቃበትን 2005 ዓመተ ፀሐይ በጨረቃ 2065 ዓመት፣11 ወር፣13 ቀን ሲሆን፤ 7504 ዓመተ ፀሐይ ደግሞ 7734 ዓመት፣9 ወር፣22 ቀን ይሆናል። የቀመረ ዐረብ ነገር ተፈጸመ።





## የጨረቃ ጥንተዮን .

በጨረቃ ዓመት ፍጻሜ የጨረቃን ጥንተዮን ለማወቅ 354 የጨረቃ ዓመት በሱባዔ ሲቀመር 50 ሱባዔ ሆኖ 4 ዕለት፣ 22 ኬክሮስ፣ 1 ካልዒት፣ 37 ሣልሲት፣ ይተርፋል። በ7200 ዓመት 37 ሣልሲት 1 ዕለት 14 ኬክሮስ ይሆናል። 1 ካልዒት 2 ዕለት ይሆናል። ያውም እንዲህ ነው። 37 ሣልሲት እስከ 7200 ዓመት ቢሰበሰብ ማለት 7200×37 =266,400 ሣልሲት ይሆናል። ይህ ወደ ካልዒት ሲለወጥ ማለት 266400÷60=4,440 ካልዒት ይሆናል። ይህ ወደ ኬክሮስ ሲለወጥ ማለት 4440÷60=74 ኬክሮስ ይሆናል። ይህም ወደ ዕለት ሲለወጥ 1 ዕለት ሆኖ 14 ኬክሮስ ይቀራል።

1 ካልዒት እስከ 7200 ዓመት ቢሰበሰብ ማለት 7200×1=7200 ካልዒት ይሆናል። ይህ ወደ ኬክሮስ ሲለወጥ ማለት 7200÷60=120 ኬክሮስ ይሆናል። ይህ ወደ ዕለት ሲለወጥ 120÷60=2 ዕለት ይሆናል። ይህ በ7200 ዓመት ከካልዒትና ከሣልስት 3 ዕለት ይገኛል ማለት ነው።

## ንኡስ ቀመርና ዐቢይ ቀመር

በዚህ ገጽ ንኡስ ቀመር የሚባለው 8 ዓመት ነው። ዐቢይ ቀመር የሚባለው 30 ዓመት ነው። 4 ዕለት እስከ 8 ዓመት ቢሰበሰብ 32 ይሆናል። 22 ኬክሮስ እስከ 8 ዓመት ቢሰበሰብ ማለት 22×8=176 ኬክሮስ ይሆናል። ይህ ወደ ዕለት ሲለወጥ 2 ዕለት ሆኖ 56 ኬክሮስ ይተርፋል። 56ቱን ኬክሮስ 1 ዕለት ብሎ በ2 ዕለት ላይ ቢደመር 3 ዕለት ይሆናል። ይህ በ32 ዕለት ላይ ቢታከል 35 ዕለት ይሆናል። ይህ በሱባዔ ቢቀመር 5 ሱባዔ ይሆናል።

ዳግመኛም 4 ዕለት እስከ 30 ዓመት ቢሰበሰብ ማለት 4×30=120 ዕለት ይሆናል። 22 ኬክሮስ እስከ 30 ዓመት ቢሰበሰብ ማለት 22×30=660 ኬክ ይሆናል። ይህ ወደ ዕለት ሲለወጥ ማለት 660÷60=11 ዕለት ይሆናል። ይህ በ120 ዕለት ላይ ሲታከል 131 ዕለት ይሆናል። 131÷7=18 ሱባዔ ሆኖ 5 ቀን ይተርፋል።

7730 ዓመተ ጨረቃ በ30 ቢቀመር 257 ዐቢይ ቀመር ሆኖ 20 ዓመት ይተርፋል። ከ1 ዐቢይ ቀመር 5 ዕለት ከተረፈ ከ257 ዐቢይ ቀመር ስንት ይተርፋል 257×5=1285 ዕለት ይሆናል። በዚሁ



www.ethiopianorthodox.org

ላይ ከካልዒትና ከሣልሲት የተገኘው 3 ዕለት ሲደመር 1288 ዕለት ይሆናል:: ይህ በሱባዔ ሲቀመር ማለት 1288÷7=184 ሱባዔ ይሆናል::

ከዐቢይ ቀመር ከተረፈው 20 ዓመት አራት አራት ዕለት ቢሰበሰብ ማለት 20× 4=80 ዕለት ይሆናል:: ዳግመኛም ከ20 ዓመት 22:22 ኬክሮስ ቢሰበሰብ ማለት 20×22= 440 ኬክሮስ ይሆናል:: ይህ ወደ ዕለት ሲለወጥ 440÷60=7 ዕለት ሆኖ 20 ኬክሮስ ይተርፋል:: 20ው ኬክሮስ 60 ኬክሮስ እስኪሞላ ይቀመጣል:: በ80 ዕለት ላይ 7 ዕለት ሲደመር (80+7) =87 ዕለት ይሆናል:: 87 ዕለት በሱባዔ ሲቀመር 12 ሱባዔ ሆኖ 3 ዕለት ይተርፋል:: ከ3 ዕለት 1 ሲቀነስ 2 ይቀራል:: ስለዚህ የጨረቃ ጥንተ ዮን 2 ነው:: በዚሁ ምክንያት የጨረቃ ጥንተ ዮን 1 ቢሆን ኀሙስ፣ 2 ቢሆን ዓርብ፣ 3 ቢሆን ቀዳም፣ 4 ቢሆን እሑድ፣ 5 ቢሆን ሰኞ፣ 6 ቢሆን ማክሰኞ፣ 7 ቢሆን ሮብ ነው:: የፀሐይ ጥንተ ዮን በመገሥረሪያ፣ የጨረቃ ጥንተ ዮን በመጨረሻ ይገኛል::

*ስብሐት ለእግዚአ አዝማን ወዓመታት ወመዋዕል ለዓለም ዓለም አሚን:*





# ምዕራፍ ስድስት

## ሐሳበ ፈለክ

ሚጠተ ብርሃናት ማለት የብርሃናት መመላለስ ማለት ነው:: ብርሃናት የሚወጡባቸው ስድስት ደጃፎች በምሥራቅ አሉ:: እንዲሁም ብርሃናት የሚጠልቁባቸው ስድስት ደጃፎች በምዕራብ አሉ:: እሊህም ልዑል እግዚብሔር የፈጠራቸው በሰማይ ጠፈር ላይም ያደረጋቸው 12 ኃዋኀወ ፈለክ ናቸው::

### ዑደተ ፀሐይ

ዑደተ ፀሐይ ማለት የፀሐይ መዞር ወይም አዟዟር ማለት ነው:: መገሥመርያ ስሙ ፀሐይ የሚባል ታላቁ ብርሃን ወደ ሰሜን ሲጓዝ በስድስቱ ደጃፎች ስድስት ወር ይመላለሳል:: ሔኖክ 72÷3

ወደ ደቡብም ሲመለስ በስድስቱ ደጃፎች ስድስት ወር ይመላለሳል የፀሐይ ዐውደ ዓመትም በ12ቱ መገብተ አውራኀ ከዋክብት አምሳያ በ12 ወሮች ተከፍሏል:: 12ቱም ኃዋኀው በ28 መዓርጋት የሚታዩ 12 ከዋክብት ናቸው:: ከእነዚህ ክፍሎች የተውጣጡ 360 መዓርጋትም በ30:30 መዓርጋት ተከፍለው በያንዳንዳቸው መካከል ተመድበዋል::

ፀሐይም ከደቡብ ወደ ሰሜን ወይም ከመገሥመሪያው ኆኅት ወደ ስድስተኛው ሲዞር ጀደይ፣ ደለው፣ ሑት፣ ሐመል፣ ተውርና ጀውዛ በተባሉ ከዋክብት ደጃፎች የስድስት ወር ዑደት ይፈጽማል:: ወሮቹም ጥር፣ የካቲት፣ መጋቢት፣ ሚያዝያ፣ ግንቦት፣ ሰኔ ናቸው:: እንዲሁም ከሰሜን ወደ ደቡብ ወይም ከስድስተኛው ደጃፍ ወደ መገሥመሪያው ሲመለስ ሸርጣን፣ አሰድ፣ ሰንቡላ፣ ሚዛን፣ ዐቅራብና ቀውስ በተባሉ ከዋክብት ደጃፎች የስድስት ወር ዑደቱን ይፈጽማል:: ወሮቹም ሐምሌ፣ ነሐሴ፣ መስከረም፣ ጥቅምት፣ ኅዳርና ታኅሣሥ ናቸው::



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ፀሐይ ዐውደ ዓመቱን በ12 ወር ይጨርሳል። ፀሐይ ከ12ቱ ደጃፎች ባንዱ በሚቈይበት መጠን የያንዳንዱ የቀን ብዛት ተወስኗል። ከሁለቱ ጾታ ማኅፈድ ባንደኛው በሰሜናዊ ጾታ በሚገኘው በሸርጣን ደጃፍ በሚቈይበት ጊዜ ሰማይን ከሁለት ከፍሎ በአርእስት መካከል ይሆናል። በዚሁ ደጃፍ የሚቈይበት ጊዜ ረዥም ስለሆነ ወሩን በ31 ተኩል ቀን ይፈጽማዋል። ከዚህም በደቡባዊ ጾታ በጀደይ ደጃፍ የሚቈይበት ጊዜ አጭር ስለሆነ ወሩን በ29 ተኩል ቀን ይፈጽመዋል።

ምክንያቱም እስመ ምድር ክቡብ ከመ ኮራ ማለት ምድር እንደ ጋን ክብ ናት እንደተባለ (ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ) የምድር ቅርጽዋ እንደ ደጋንና እንደ ጅማቱ ስለኾነ ፀሐይ ከደቡብ ወደ ሰሜን ወይም ከመገ[ር]መርያው ደጃፍ ወደ ስድስተኛው ደጃፍ ሲሄድ ቀኑ እየረዘመ ይሔዳል።

ከሰሜን ወደ ደቡብ ወይም ከስድስተኛው ደጃፍ ወደ አንደኛው ደጃፍ ሲመለስም ቀኑ ያጥራል። ምክንያቱም ፀሐይ ወደ ሰሜን ሲዞር ደጋን በመሰለው በምድር ደረት አቅጣጫ፣ ወደ ደቡብ ሲመለስም የደጋኑ ጅማት በመሰለው ቅርጽዋ አቅጣጫ ስለሚጓዝ ነው ብለው ሚጠተ ብርሃናትን የሚያስተምሩ ቅዱሳን አበው ያስረዳሉ።

ፀሐይ ከሁለቱ ክፍላተ ዓመት ያውም ከዘመነ ሐመልና ከዘመነ ሚዛን ባንዱ ክፍል በሚቈይበት ጊዜ ጉዞው በመካከል ይሆናል። ከዚያም ፀሐይ በያንዳንዱ ኖኅት በሚቈይበት መጠን ተውሳክና ሕጸጽ ይሆናል። ይህም የሚሆነው ርሱ በሰማይ መካከል ስለሚቈይና በኋላም ከደቡብ ስለሚነሳ ነው።

ስለዚህም 4 ክፍላተ ዓመት እንዳሉ ይታወቃል፣ የአንዱ ክፍለ ዓመት ቀን ብዛትም 91 ዕለት፣ 18 ኬክሮስ፣ 45 ካልዒት ነው። 4ቱን ክፍለ ዓመት የሚመግቡ አራት መገብተ አዝማን አሉ። እነርሱም ምልክኤል፣ ሕልመልሜሊክ፣ ሚካኤል፣ ናርኤል ይባላሉ። ከ12ቱ መገብተ አውራኅ ከዋክብት ሦስት ሦስቱ ከ28ቱ መገብተ ዕለት ከዋክብት ሰባት ሰባቱ ለያንዳንዳቸው ይከተሉዋቸዋል።





የአራቱ ክፍላተ ዓመት ምግብና

ሀ) ጸደይ

አንደኛውን ክፍለ ዓመት የሚመግቡ፦ ሐመል፣ ተውርና ጀውዛ ናቸው። ዕለታቸው 90 ኬክሮሳቸው 85፣ አለቃቸው ምልክኤል፣ ዘመናቸው ጸደይ ነው። ከ91ዱ ዕለታት ዐሥራ ሦስት ዐሥራ ሦስት ቀኖችን የሚመግቡ 7 መገብተ ዕለታት ከዋክብት ይከተሉዋቸዋል።

ለ) <u>ክረምት</u>

ሁለተኛውን ክፍለ ዓመት የሚመግቡ፦ ሸርጣን አሰድና ሰንቡላ ናቸው። ዕለታቸው 90፣ ኬክሮሳቸው 78፣ አለቃቸው ሕልመልሜሊክ ዘመናቸው ክረምት ነው። ከ91ዱ ዕለታት ዐሥራ ሦስት ዐሥራ ሦስት ቀኖችን የሚመግቡ 7 መገብተ ዕለታት ከዋክብት ይከተሉዋቸዋል።

ሐ) መፀው

ሦስተኛውን ክፍለ ዓመት የሚመግቡ፦ ሚዛን ዐቅራብና ቀውስ ናቸው። ዕለታቸው 90፣ ኬክሮሳቸው 78፣ አለቃቸው ሚካኤል፣ ዘመናቸው መፀው ነው። ከ91ዱ ዕለታት ዐሥራ ሦስት ዐሥራ ሦስት ቀኖችን የሚመግቡ 7 መገብተ ዕለታት ከዋክብት ይከተሉዋቸዋል።

መ) ሐጋይ (በጋ)

አራተኛውን ክፍለ ዓመት የሚመግቡ፦ ጀደይ፣ ደለውና ሑት ናቸው። ዕለታቸው 90፣ ኬክሮሳቸው 74፣ አለቃቸው ናርኤል፣ ዘመናቸው ሐጋይ ነው። ከ91ዱ ዕለታት ዐሥራ ሦስት ዐሥራ ሦስት ቀኖችን የሚመግቡ 7 መገብተ ዕለታት



www.ethiopianorthodox.org

ይከተሉዋቸዋል፡፡ የአራቱም ዐበይት ከዋክብት ምግብናቸው እሳት፣ መሬት፣ ነፋስና ውሃ ነው፡፡

የ4ቱ ክፍላተ ዓመት ዕለት ሲደመር 360 ቀን ከ315 ኬክሮስ ይሆናል፡፡ 315ቱ ኬክሮስ 5 ቀን ሆኖ 15 ኬክሮስ ይተርፋል፡፡ 5ቱ ቀን ጳጉሜን ነው፡፡ 15 ኬክሮስም በ4 ዓመት 1 ዕለት ሆኖ 6ኛ ጳጉሜን ይባላል፡፡

4ቱ መገብተ አዝማን ከዋክብት እያንዳንዳቸው 91፡91 ዕለታትን ይመግባሉ፡፡ 12ቱ መገብተ አውራኀ ከዋክብትም በሦስት በሦስት አራት ላይ ተመድበው ከአለቆቻቸው ጋር ሦስት ሦስት ወርን ይመግባሉ፡፡ 28ቱ መገብተ ዕለት በሰባት ሰባት አራት ላይ ተመድበው ከ91 ዕለታት ዐሥራ ሦስት ዐሥራ ሦስት ቀኖችን ይመግባሉ፡፡

ፀሐይ በደቡብ ማዕዘን ካለው ጥንተ ማኅፈድ ከጥር 1 ቀን ገርምሮ ወደ ሰሜን ሲዞር መጋቢት 25 ቀን ዕሪና መዓልትና ዕሪና ሌሊት ይሆናል፡፡ ከሐምሌ 1 ቀን ገርምሮ ከሰሜን ወደ ደቡብ ሲመለስም መስከረም 25 ቀን ዕሪና ሌሊትና ዕሪና መዓልት ይሆናል፡፡

## ዑደተ ወርኅ

ዑደተ ወርኅ ማለት የጨረቃ መዞር ወይም አዟዟር ማለት ነው፡፡ ክብነትዋ እንደ ሰማይ መጠኗ እንደ ፀሐይ የሆነች ስሟ ጨረቃ የምትባል ታናሽ ብርሃን አለች፡፡ ብርሃንም በልክ ይሰጣታል፡፡ በወሮቹ ኹሉ መውጭያዋንና መግቢያዋን ትለውጣለች፡፡ ዕለታትዋም እንደ ፀሐይ ዕለታት ናቸው፡፡ ብርሃንዋ ሙሉ በሚኾንበት ጊዜ ከፀሐይ ብርሃን ሰባተኛ እጅ ይኾናል፡፡ መውጭያዋም በፀሐይ መውጭያ በኩል ነው፡፡ እስከ ዐሥራ አምስት ቀንም ዐሥራ አምስት ክፍለ ብርሃን ይሰጣታል፡፡ ብርሃንዋን በዐሥራ አራት ቀን የምትፈጽምበት ጊዜ አለ፡፡





ከብርሃነ ፀሐይ በምታገኘው ሰባተኛ ክፍለ ብርሃን የሚያገለግሉ አራት ሱባዔዎች አሉዋት፡፡ ከነዚህም ሱባዔዎች ሁለቱ ብርሃን እየተጨመረላት፣ ሁለቱ ብርሃን እየተቀነሰባት ሲሔድ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

ጨረቃ በታወቁ ወሮች ሃያዘጠኝ ሃያዘጠኝ ቀን አብርታ በነጋታው ትታጣለች፡፡ የወሮቹም ብዛት ስድስት ነው፡፡ ዳግመኛም በታወቁ ወሮች ሃያስምንት ሃያስምንት ቀን አብርታ በነጋታው ትታጣለች፡፡ የሊህም ወሮች ብዛት ስድስት ነው፡፡ የዐውደ ቀመርዋ ሥርዓት በዐሥራ ዘጠኝ ዐሥራ ዘጠኝ አንቀጽ የተመደበ ነው፡፡ እንዲሁም እስከ ዘለዓለሙ ጸንቶ ይኖራል፡፡

ጨረቃ በምትወለድበት ጊዜ ፀሐይ ሲጠልቅ በ4 ኬክሮስ ርቀት ከኊላው ትታያለች፡፡ በዚያን ጊዜ ከ15ቱ የራስዋ ክፍለ ብርሃን አንዱን እጅ ከ105 የፀሐይ ክፍለ ብርሃን አንዱን እጅ ታበራለች፡፡ በዚሁ መሠረት በየቀኑ በብርሃንዋ ላይ ብርሃንን እየጨመረች ወደ ምሥራቅ ስትዞር በ15ኛው ቀን በ15ኛው ሰዓት በ60 ኬክሮስ ትታያለች፡፡ ይህም በፀሐይ መንገድ አንድ ቀን ነው፡፡ ያን ጊዜ ጨረቃ 15ቱን ክፍለ ብርሃን በሙሉ ታበራለች፡፡ ከፀሐይ ሱባዔዎች በሰባተኛው ሱባዔ እኩሌታ ፍጹም ብርሃን ትኾናለች፡፡

በዚያች ዕለት ፀሐይ ወደ ምዕራብ ሲጠልቅ ጨረቃ ከምሥራቅ ትወጣለች፡፡ ፀሐይ ወደ ምሥራቅ እስኪመለስ ድረስም ሌሊቱን ኹሉ ብቻዋን ስታበራ ታድራለች፡፡ ከዚያም በየቀኑ ብርሃንዋ እየጐደለ ሲሔድ ከሰባተኛው የፀሐይ ክፍለ ብርሃን የተረፋትን ብርሃን በ15ኛው ቀን ትፈጽማለች፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ጨረቃ ቀድሞ በዕርበተ ፀሐይ ጊዜ ስትወለድ በታየችበት ቦታ አሁንም ሕጸጽዋ በሥርቀተ ፀሐይ ጊዜ በ4 ኬክሮስ ርቀት በዚያው ቦታ ይታያል። ብርሃንዋ በተገመረበት ገጸ ሰማይ ሕጸጽዋን ትገምራለች። ብርሃንዋ በተፈጸመበትም ብርሃንዋን ትፈጽማለች። ሔኖክ 78፥6-17።








## ኬክሮስና ክንትሮስ






www.ethiopianorthodox.org

## ኬክሮስና ክንትሮስ

ኬክሮስ ማለት የሌሊትና የመዓልት ሰዓታት የሚታወቁበት ዐቢይ ክፍለ ጊዜ ሲኾን፣ ርሱም ከደቡብ እስከ ሰሜን የተዘረጋ ነው። ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ያለው የኬክሮስ ብዛትም ስድሳ ነው። ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብት ሁልጊዜ በርሱ ላይ እየኼዱ ስድሳውን ኬክሮስ በአንድ ቀን ይፈጽሙታል።

ክንትሮስ ማለትም ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የተዘረጋ ነው። ክንትሮስ ከኬክሮስ ጋራ እንደ ጥብጣብ አልጋ የተሠራ የረጋ ነፋስ ስለኾነ እንደምድር ኾኖ ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብትም ይኼዱበታል። እነርሱ ሲኼዱ የሚጓዙበት ሠረገላም ነፋስ ነው። የጊዜው አከፋፈል ሥርዓትም እንዲህ ነው፡-

1 መዓልት፡- 12 ሰዓት፣ 60 ኬክሮስ፣ 360 ክንትሮስ ነው።

1 ሰዓት፡- 5 ኬክሮስ፣ 30 ክንትሮስ ነው

1 ኬክሮስ 6 ክንትሮስ ነው።

በምሥራቅ 6 መስኮቶች በምዕራብ 6 መስኮቶች አሉ። ለያንዳንዱ መስኮት 30፡ 30 ክንትሮስ አለው። ፀሐይ አንድ ቀን በአንዱ ክንትሮስ አንድ ቀን በአንዱ ክንትሮስ ይኼዳል። ወር 30 ቀን ተብሎ የሚቈጠረውም በዚያው ልክ ነው።

የፀሐይ የሠሌዳው ስፋት በአንዱ ክንትሮስ ልክ ነው። የአንዱ ክንትሮስ መጠንም 2 ዓመት ከ10 ቀን ያህል የሚያስኬድ ነው። ፀሐይ አንዱን ቀን ሲጓዝ የሚውለው በአንዱ ክንትሮስ ላይ ነው። ከዚህ አይተርፍም ከዚህም አይጐድልም።

የኬክሮስ መጠንም 16 ዓመት ከ8 ወር ያህል የሚያስኬድ ነው። አንዱ ኬክሮስ በድሩ መስፈሪያ ቢሰፈር 6 ክንትሮስ ይኾናል። በዚሁ መሠረት በ6ቱ መስኮቶች ያለ 30፡ 30 ክንትሮስም አንዳንድ ሰዓት ነው። ከመጋቢትና ከመስከረም በቀር በዐሥሩ ወር የአንድ





ሰዓት መትረፍ የአንዲት ሰዓት መጉደል የሚታየውም ከቀኑ መርዘምና ማጠር የተነሣ ነው።

## ፍኖተ መራሒ ወተመራሒ (የመሪ ተመሪ መንገድ)

ፍኖተ መራሒ ወተመራሒ ማለት፣ የመሪና የተመሪ መንገድ ማለት ነው። መሪና ተመሪ የሚባሉት ፀሐይን ተከትለው የሚመግቡ ዐበይትና ንኡሳን ከዋክብት ናቸው። ፀሐይ በተሠራለት መንገድ ሁልጊዜ ይወጣል፤ ይገባል። ፀሐይን ተከትለው የሚመግቡ ከዋክብትም የሚከተሉት ናቸው።

1. መራሕያነ ምቅዋማት የሚባሉ አራት ዐበይት ከዋክብት ናቸው። እነርሱም ምልክኤል፣ ሕልመልሜሌክ፣ ሚላኤል፣ ናርኤል ይባላሉ። እነዚህ አራቱን ወቅቶች እየለዩ የሚመግቡ ናቸው።
2. መራሕያነ ሥርዓታት የሚባሉት ዐሥራ ሁለት መገብተ አውራኅ ከዋክብት ናቸው። እነርሱም ተውር፣ ጀውዛ፣ ሸርጣን፣ አሰድ፣ ሰንቡላ፣ ሚዛን፣ ዐቅራብ፣ ቀውስ፣ ጀደይ፣ ደለው፣ ሑት፣ ሐመል ይባላሉ። እነዚህ አውራኀን እየተለዩ የሚመግቡ ናቸው።
3. በአራቱ ወቅቶች የተመደቡ 28 ንኡሳን ከዋክብት አሉ። እነዚህ እያንዳንዳቸው ዐሥራ ሦስት ዕለታትን እየለዩ የሚመግቡ ናቸው።
4. ሙሉውን ዓመት የሚያገለግሉ 364,000 (ሺሕ) ከዋክብት አሉ። እነዚህም በ364 ዕለታት ተመድበው አንድ አንድ ሺሕ እየሆኑ እያንዳንዱን ዕለት ይመግባሉ። ምግብናቸውም ብርሃን ነው።

የአመራራቸው ሥርዓትም እንዲህ ነው፡-

ፀሐይን ተከትለው የሚመግቡ አራቱ ዐበይት ከዋክብት ከዐሥራ ሁለቱ ከዋክብት እያንዳንዳቸው ሦስት ሦስቱን፣ ከሃያ ስምንቱ ከዋክብት እያንዳንዳቸው ሰባት ሰባቱን፤ ከ364,000 ከዋክብት እያንዳንዳቸው በየቀኑ አንዳንድ ሺሕ እያስከተሉ ዓመቱ



www.ethiopianorthodox.org

እስኪፈጸም ድረስ ይመግባሉ። ያመጋገባቸው ሥርዓትም እንዲህ ነው፡-

1. ምልክኤል መጋቢት በባተ በ26ኛው ቀን ይወጣል። ወሮችን ከሚመግቡ 12 ከዋክብት ሦስት፤ ወቅቶችን ከሚመግቡ 28 ከዋክብት ሰባት ሙሉውን ዓመት ከሚመግቡ 364,000 ከዋክብት አንድ ሺሕ ከዋክብት አስከትሎ፤ ሚያዝያን፣ ግንቦትን፣ ሠኔን ይመግባል። በሠኔ 25 ቀን ምግብናውን ይፈጽማል። ዘመኑም «ቀመረ ፍሥሐ ዕርየተ መዓልት ወሌሊት» ማለት፣ የደስታ ቀመር የመዓልትና የሌሊት እኩልነት የሚሆንበት ማለት ነው። ዘመኑም በዕብራይስጥ መፀው በኢትዮጵያ ጸደይ ይባላል።
2. ሕልመልሚሌክ ሠኔ በባተ በ26ኛው ቀን ይወጣል። ወሮችን ከሚመግቡ 12 ከዋክብት ሦስት፣ ወቅቶችን ከሚመግቡ 28 ከዋክብት ሰባት፣ ሙሉውን ዓመት ከሚመግቡ 364,000 ከዋክብት አንድ ሺሕ አስከትሎ፤ ሐምሌን፣ ነሐሴን፣ መስከረምን ይመግባል። በመስከረም 25 ቀን ምግብናውን ይፈጽማል። ዘመኑም በዕብራይስጥ ሐጋይ በኢትዮጵያ ክረምት ይባላል።
3. ሚላኤል መስከረም በባተ በ26ኛው ቀን ይወጣል። ወሮችን ከሚመግቡ 12 ከዋክብት ሦስት፣ ወቅቶችን ከሚመግቡ 28 ከዋክብት ሰባት፣ ሙሉውን ዓመት ከሚመግቡ 364,000 ከዋክብት አንድ ሺሕ አስከትሎ፤ ጥቅምትን፣ ኅዳርን፣ ታኅሣሥን ይመግባል። በታኅሣሥ 25 ቀን ምግብናውን ይፈጽማል። ዘኑም በዕብራይስጥ ጸደይ በኢትዮጵያ መፀው ይባላል።
4. ናርኤል ታኅሣሥ በባተ በ26ኛው ቀን ይወጣል። ወሮችን ከሚመግቡ 12 ከዋክብት ሦስት፣ ወቅቶችን ከሚመግቡ 28 ከዋክብት ሰባት፣ ሙሉውን ዓመት ከሚመግቡ 364,000 ከዋክብት አንድ ሺሕ አስከትሎ፤ ጥርን፣ የካቲትን፣ መጋቢትን ይመግባል። በመጋቢት 25 ቀን ምግብናውን ይፈጽማል። ዘመኑም በዕብራይስጥ ክረምት፣ በኢትዮጵያ ሐጋይ ይባላል። በዓመቱ የዕለት ምግብና ሳይመደቡ የቀሩ አንድ ሺሕ ከዋክብትም በአራቱ መዓዝነ ዕለት (የዕለት ማዓዝን) ልክ





ከአራት ተከፍለው 250 እየሆኑ አራቱን መዓዝነ ዕለት ይመግባሉ።

ዓመቱም ለአራት መጋብተ አዝማን (የዘመን መጋቢዎች) ሲከፈል ለያንዳንዳቸው ዘጠና አንድ ዕለት ይደርሳቸዋል። የዓመቱም ዕለት በከዋክብት አቈጣጠር 364 ብቻ ነው። ያውም 52 ሱባዔ ነው። የከዋክብት ሥርዓት በዚህ ይፈጸማል። በየዘመናቸው ለሠራቸው፣ በየወገናቸው ለመደባቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል፤ ለዘላለሙ አሜን።

ብርሃን ያላቸው ከዋክብት ሁልጊዜ ያመሰግኑታል፤ አያርፉም። ምስጋናቸውና አገልግሎታቸው ለእነርሱ ዕረፍታቸው ነውና። ጨረቃን በጠፍ ጊዜ እንዳታበራ አትውጭ የሚላት፣ የከዋክብትን ብርሃን የሚሠውር፣ ምስጋናም ለዘለዓለሙ ገንዘቡ የሆነ፤ እግዚአብሔር አይደለምን? «አንተ ይብላ ለወርኅ ኢትሥርቂ፣ ወገጸ ከዋክብት የኀትም አኮኑ እግዚአብሔር ዘሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን።» (ኢዮብ 9+7 ቀመረ ከዋክብት)።

## የአራቱ ዐበይት ከዋክብት ሥርዓት

አራቱ ዐበይት ከዋክብት ከተከታዮቻቸው ጋር ሆነው አራቱን ክፍለ ዓመት የሚያገለግሉበት ሥርዓት ከዚህ በታች ባጭሩ ተገልጿል። ያውም እንዲህ ነው፡-

### ፩ ምልክኤል

| | |
|---|---|
| 1. እስሩጣይን | 13 ቀን ይመግባል |
| 2. እልብጣይን | 13 ቀን ይመግባል |
| 3. እትሩይ | 13 ቀን ይመግባል |
| 4. እድብራን | 13 ቀን ይመግባል |
| 5. እልሀቅዓ | 13 ቀን ይመግባል |
| 6. እልሀንዓ | 13 ቀን ይመግባል |
| 7. እድራዕ | 13 ቀን ይመግባል |
| ድምር 91 ቀን | |



www.ethiopianorthodox.org

ምልክኤል ከ7 ተከታዮቹ ጋር 91 ቀን ይመግባል።

፪ ሕልመልሜሌክ

1. እነትራ 13 ቀን ይመግባል
2. እጠርፍ 13 ቀን ይመግባል
3. እዛብሔ 13 ቀን ይመግባል
4. እልክትራን 13 ቀን ይመግባል
5. እሰርፍ 13 ቀን ይመግባል
6. እልዓዊ 13 ቀን ይመግባል
7. እሴማክ 13 ቀን ይመግባል

ድምር 91 ቀን

ሕልመልሜሌክ ከ7 ተከታዮቹ ጋር 91 ቀን ይመግባል።

፫ ሚላኤል

1. እልቀፍር 13 ቀን ይመግባል
2. እዝብናን 13 ቀን ይመግባል
3. እልአክሊል 13 ቀን ይመግባል
4. እልቀልብ 13 ቀን ይመግባል
5. እስውሌ 13 ቀን ይመግባል
6. እንዓይምን 13 ቀን ይመግባል
7. እልብልድህ 13 ቀን ይመግባል

ድምር 91 ቀን

ሚላኤል ከ7 ተከታዮቹ ጋር 91 ቀን ይመግባል።

፬ ናርኤል

1. ሳዕድ ዕድባህ 13 ቀን ይመግባል
2. ሳዕድ በላዕ 13 ቀን ይመግባል
3. ሳዕድ ሰውድ 13 ቀን ይመግባል
4. ሳዕድ ለክብየ 13 ቀን ይመግባል





5. እልፈር ዕልመቅድም 13 ቀን ይመግባል
6. አልፈር እልመከር 13 ቀን ይመግባል
7. በጥን እልሑት 13 ቀን ይመግባል

ድምር 91 ቀን

ናርኤል ከ7 ተከታዮቹ ጋር 91 ቀን ይመግባል።

በጠቅላላ አራቱ ዐበይት ከዋክብት ከተከታዮቻቸው ጋር ሆነው በአራቱ ክፍለ ዓመት (ወቅት) የሚመግቧቸው ዕለታት (91×4) 364 ናቸው። የከዋክብት ዐውደ ዓመት 364 ቀን ብቻ ነው የሚባለውም ስለዚህ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

## መገብተ ዕለታት ከዋክብት

ሃያ ስምንቱ መገብተ ዕለታት ከዋክብት በነግህና በመንፈቀ ሌሊት በማዕከለ ሰማይ ኹነው የሚታዩባቸው ዕለታትና አውራኅ በዚህ ዐውድ ዙርያ በዝርዝር እንደተጻፈው ነው።

ዐውደ ከዋክብት








## ሐሳበ መናዝል

ሐሳበ መናዝል ማለት የከዋክብትን ሥራና ግብር የሚገልጽ ስሌት ማለት ነው። መናዝል ማለትም የዐሥራ ሁለት ወር ከዋክብት ከእልሐመል እስከ ሑት ያሉ በእንስሳት ስም የሚጠሩ መገብተ አውራኅ ከዋክብት ናቸው።

ዐውደ መናዝል





www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሰባት

## ሐሳበ ነፋሳት

ነፋስ ከአራቱ ባሕርያት መሬትና እሳት፣ነፋስና ውኃ ሦስተኛው ነው። ድምፁ የሚሰማ፣አካሉ የማይታይ ነው።የማይዳሰሰው ነፋስ የፍጥረት ሁሉ ሕይወት አንቀሳቃሽ ነው (ደስታ፣1962)። በቅዱሳት መጻሕፍት ስለነፋሳት ተጽፏል። በተለይ የመጽሐፈ ሔኖክ ሁለት ክፍሎች የነፋሳቱን አቅጣጫና ተጽዕኖ በግእዙ እትም ምዕራፍ 76፣በአማርኛው ከምዕራፍ 34 እስከ 36 ይገልጻል።

ሔኖክ በአራቱ የሰማይ ማዕዘን 12 ነፋሳት የሚነፍሱባቸው 12 ደጃፎች መኖራቸውን ገልጾ፣ በ12ቱ ደጃፎች ከሚወጡ ነፋሳት 4ቱ ነፋሳተ ምሕረት፣ 8ቱ ነፋሳተ መዓት መሆናቸውን አስረድቷል።

ሕዝቅኤልም፡- ነፋስ ሆይ ከአራቱ ነፋሳት ዘንድ ና እነዚህ የተገደሉት በሕይወት ይኖሩ ዘንድ እፍ በልባቸው ብለህ ተናገር ብሎ እግዚአብሔር አምላክ እንዳዘዘኝ ተናገርሁ። እነርሱም ሕያዋን ሆኑ ብሎ ሕይወትን የሚሰጡ 4 ነፋሳተ ምሕረት መኖራቸውን ገልጿል (ሕዝ 37፥9)።

ዮሐንስ ወንጌላዊም፡- በአራቱ የምድር ማዕዘን አራት መላእክት ቆመው ማየቱን ነፋስም በምድርና በባሕር በዛፍም ላይ ቢሆን እንዳይነፍስ አራቱን የምድር ነፋሳት መያዛቸውን አስረድቷል(ራእይ 7፥1፣ ማቴ. 24፥31)።

ሕዝቅኤልና ሆሴዕም ስለ 8ቱ ነፋሳተ መዓት ባሕርይና ግብር ሲያስረዱ፡- የምሥራቅ ነፋስ የተተከለውንና ፍሬውንም ሁሉ ያደርቃል ምንጩና ፈሳሹንም ያጠፋል ብለዋል (ሕዝ.17፥19-12፤ ሆሴ.13፥15)።





ዳንኤልም እንዲህ አለ፤እኔ ዳንኤል ራእይ አየሁ፤እነሆም አራቱ የሰማይ ነፋሳት በታላቁ ባሕር ላይ ይነፍሱ ነበር (ዳን 7፥ 2)።

ሔኖክ ስለ4ቱ ነፋሳተ ምሕረትና ስለ8ቱ ነፋሳተ መዓት ባሕርይና ግብር ለልጁ ለማቱሳላ በዝርዝር ያስተማረውን ትምህርት ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን።

እኔ በምድር ዳርቻዎች ነፋሳት የሚወጡባቸውና በምድርም ላይ የሚነፍሱባቸው ወደ ሰማይ ማዕዘናት ኹሉ የተከፈቱ ዐሥራ ሁለት ደጃፎችን አየሁ።

ከእነርሱም ሦስቱ በገጸ ሰማይ ሆነው የተከፈቱ ናቸው። ሦስቱ በምዕራብ፣ ሦስቱ በሰማይ ቀኝ ሦስቱ በግራ ናቸው።

የመጀመርያዎቹ ሦስቱ እነዚያ በምሥራቅ ያሉት ናቸው። ሦስቱም በሰሜን ሦስቱም በደቡብ ሦስቱም በምዕራብ ናቸው።

ከነዚያም ደጃፎች በ4ቱ የበረከትና የሰላም ነፋሳት ይወጣሉ። ከስምንቱም መቅሠፍትን የሚያመጡ ነፋሳት ይወጣሉ። እነርሱም በተላኩ ጊዜ በምድር ኹሉ ላይ በርሰዋ ላይም ባለው ውሃ ላይ ከዚያም በሚኖሩት ኹሉ ላይ በውሃና በየብስ ባለው ማንኛውም ላይ ድምሳሴን ያመጣሉ።

ስሙ ጽባሐዊ የተባለ የመጀመርያው ነፋስም ከነዚያ ደጃፎች በምሥራቅ፣ በደቡብ አቅጣጫ ከሚገኝ ከአንደኛው ደጃፍ ውስጥ ይወጣል። ከርሱም ድምሳሴና ድርቅ ሞትና ጥፋት ይወጣሉ።

በመካከል ካለች ሁለተኛይቱ ደጃፍ ውስጥም ተስማሚ የኾነ ነገር ይወጣል። ከርሷም ዝናምና ፍሬ ሰላምና ጠል ይወጣሉ። በሰሜን አቅጣጫ ከምትገኝ ሦስተኛይቱ ደጃፍም ውርጭና ድርቅ ይወጣሉ።



www.ethiopianorthodox.org

ከእነዚህም በኋላ የደቡብ ነፋሳት ከሦስት ደጃፎች ውስጥ ይወጣሉ። ከእነርሱም በምሥራቅ አቅጣጫ ከምትገኝ ከአንደኛይቱ ደጃፍ ውስጥ የሞቀ ነፋስ ይወጣል።

አጠገብዋ ካለች ከመካከለኛይቱ ደጃፍ ውስጥም በጎ ሽቱ ጠልና ዝናም፣ ሰላምና ሕይወት ይወጣሉ።

በምዕራብ አቅጣጫ ከምትገኝ ከሦስተኛይቱ ደጃፍ ውስጥም ጠልና ዝናም ኩብኩባና ድምሳሴ ይወጣሉ።

ከእነዚህም በኋላ የሰሜን ነፋሳት በአሉባት በምሥራቅ ከምትገኝ ከሰባተኛይቱ ደጃፍ ጠልና ዝናም ኩብኩባና ድምሳሴ ይወጣሉ።

ከመካከለኛይቱ ደጃፍም ቀጥተኛ በኾነ መንገድ ዝናምና ጠል ሕይወትና ሰላም ይወጣሉ። በምዕራብ ከምትገኝ ሦስተኛይቱ ደጃፍም ጉም ውርጭና ዋግ፣ ዝናምና ጠል ኩብኩባም ይወጣሉ።

ከእነዚህም በኋላ (አራት) የምዕራብ ነፋሳት አሉ። ከሰሜን ጋር ተያይዛ ከምትገኝ ከመገፈመሪያዪቱ ደጃፍ ውስጥ ጠልና ዝናም ውርጭና ብርድ ዋግና ቀቅ ይወጣሉ።

ከመካከለኛይቱ ደጃፍም ጠልና ዝናም ሰላም በረከት ይወጣሉ። ከደቡብ ጋር ተያይዛ ከምትገኝ ከመጨረሻይቱ ደጃፍም ድርቅና ድምሳሴ፣ ዋዕይና ጥፋት ይወጣሉ።

በአራቱ የሰማይ ማእዘን ያሉ ዐሥራ ሁለቱ የሰማይ ደጃፎች በዚሁ ተፈጸሙ። ልጄ ማቱሳላ ሆይ ትእዛዛቸውን ኹሉ መቅሠፍታቸውንም ኹሉ ተድላ ደስታቸውንም ኹሉ ለአንተ አሳይቻለሁ (ሔኖክ 76፥1-14) ።

## በአራቱ ማዕዝን የሚነፍሱ ነፋሳት

የመገፈመሪያው ነፋስ ቀዳማዊ ስለኾነ ስሙ ጽባሐዊ ይባላል። ሁለተኛውም ነፋስ ስሙ አዜብ ይባላል። ምክንያቱም ገናና ልዑል በዚያ ይወርዳልና። ይልቁንም ለዘለዓለሙ የከበረው እግዚአብሔር በዚያ ስለሚወርድ ነው።





በምዕራብ የሚነፍሰውም ነፋስ ስሙ ንቱግ (የጎደለ) ይሉታል። ምክንያቱም የሰማይ ብርሃናት ኹሉ በዚያ ሕጸጽ ስለሚያደርጉና ወደዚያም ስለሚገቡ ነው።

ስሙ መስዕ ተብሎ የሚጠራው አራተኛው ነፋስም በሦስት ክፍሎች ይከፈላል። ከእነርሱ አንደኛው የሰዎችን ማደርያ የሚያጸና ነው። ሁለተኛውም በውሃ ባሕሮችና በቀላያት፣ በደኖችና በወንዞች በጨለማና በደመናት የተሾመ ነው። ሦስተኛው ክፍልም በቸርነቱ በምትወረስ በገነት ጽድቅ የተሾመ ነው (ሔኖክ 77፥1-3)።

ዳግመኛም ከዚሁ ከመስዕ ክረምት ይነሣል። ከዚያም ጨለማ ይመጣል። ሌሊቱና መዓልትም ይኾናል። መዓልት ግን ከንጋት ይወለዳል። የእሊህም ሥርዓታቸው ለዘለዓለሙ እንዲህ ነው።

ሌሎችም ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሔኖክ መዝገበ ነፋሳት መዓዛ ነፋሳት መኖሩን ሲያስረዱ፦ ዐውሎ ነፋስ ከተሰወረ ማደሪያው ብርድም ከሰሜን ይወጣል። ነፋሳትን ከየማጥናቸው የሚያወጣቸው እርሱ ነው። መብረቅን ለዝናም ያደርጋል። ነፋሳትንም ከማጥኑ ያወጣል ብለዋል(ኢዮ. 37፥9፣ መዝ. 13፥57፣ ኤር. 10፥13)።

አራቱ ነፋሳተ ምሕረትም እነሆ ዛሬ መሬቱን ያጸኑልናል። ውሃውን ያቀዘቅዙልናል። እስመ ኃይለ ነፋስ ይስሕብ ለቁመተ ሥጋነ፦ ሰውነታችን እንዲያድግ የነፋስ ኃይል ይስበዋል ተብሎ እንደተጻፈው፦ እኛንም እህሉንም በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የሚያሳድጉ እነርሱ ናቸው (1ቆሮ. 3፥7)።

የሰው ልጅ ኹሉ ኃጢአት ከፋት ሠርቶ እግዚአብሔርን በሚበድልበት ጊዜ 8ቱ ነፋሳተ መዓት የሰው ትንፋሽ ያህል የተነፈሱ እንደሆነ አባር፣ ቸነፈር፣ ሐሩር ፀሐይ፣ ችጋር፣ ድርቅ ይኾናል። ከመከራው ጽናት የተነሣ ሰውም ከብትም በየዱሩ በየመንገዱ ወድቆ ይገኛል።



www.ethiopianorthodox.org

ዳግመኛም በምጽአት ጊዜ እነሆ ዛሬ ገበሬ ፍሬን ከገለባ ለመለየት ዐውድማ እንዲያወጣ ምድርም ጌታ ጻድቃንና ኃጥአንን የሚለይባት ስለኾነች፦ ዘያወጽኦሙ ለነፋሳት እመዛግብቲሆሙ፦ ነፋሳትን ከግምጃቸው የሚያወጣቸው እርሱ ነው ተብሎ እንደተጻፈው እሊህ ነፋሳተ መዓት ዛፉን እየነቀሉ ድንጊያውን እያንከባለሉ ከአድማስ ወዲህ፣ ከናጌብ ወዲያ ወስደው ይጥሉታል።

ተራራውን ከጕድጓዳው ደጋውን ከቈላው ይደለድሉታል። ይመደምዱታል፣ የምሥራቁ ወደ ምዕራቡ የምዕራቡ ወደ ምሥራቅ የሰሜኑ ወደ ደቡብ የደቡቡ ወደ ሰሜን በተመላለሱባት ጊዜ ምድር እንደብራና ትዳመጣለች። እንደ መዳመጫ ትለዝባለች(ራዕ. 20፥11፣ 21፥1፣ ኢሳ. 13፥3)።

ከዚያም በኋላ ፈታሒ በጽድቅ ኰናኒ በርትዕ ጌታ አእላፍ መላእክትን በፊት በኋላ በቀኝ በግራ አስከትሎ ሰማይ በመብረቅ እየታረሰ ከወደምሥራቅ ይመጣል። ማቴ. 24፥27፣ 25፥31 ከሰማይ ዝቅ ከምድር ከፍ ያለ የብርሃን ድንኳን ይተከልለታል። የብርሃን ዙፋን ይዘረጋለታል። የብርሃን ምንጻፍ ይነጸፍለታል። ጌታም ርሱ በፈቀደው ለኹሉ እንዲታይ ኾኖ በርሱ ላይ ተቀምጦ ጻድቃንን ኑ ያባቴ ብሩካን መንግሥትን ውረሱ ይላቸዋል። ኃጥአንን ከእኔ ሒዱ እላንት ርጉማን ወደ ዘለዓለም እሳት ብሎ ያስናብታቸዋል ብለው ኢትዮጵያውያን መተርጉማን ያትታሉ(ማቴ. 25፥31፣ 34፥41)።

ቅዱሳን አበውና ነቢያትም ስለኀልፈተ ዓለምና ኑ ያባቴ ቡሩካን የተባሉ ምእመናን ስለሚወርሱት አዲስ ሰማይ አዲስ ምድር ሲያስረዱ የመዠመሪያው ሰማይ ይጠፋል። ፈጽሞ ያልፋል። አዲስ ሰማይም ይገለጻል። የሰማይ ሠራዊት ኹሉም ሰባት እጽፍ ብርሃንን ያበራሉ ብለው አስተምረዋል (2ጴጥ. 3፥3-13፣ ራዕ. 21፥1)።



ባሕረ ሐሳብ

፬. የ12ቱ ነፋሳት መስኮቶች






www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ስምንት

## ሐሳበ ሰዓታት

መዓልትና ሌሊት 24 ሰዓት ናቸው። በመስከረምና በመጋቢት ሁለቱም ዕኩል ይሆናሉ። በቀረው መዓልት ሲያንስ ሌሊት እየበዛ፣ ሌሊት ሲያንስ መዓልት እየበዛ ሌሊትም ቢበዛ ከ15 በላይ አይወጣም፤ ቢያንስ ከ9 በታች አይወርድም። ከ15 እስከ 9 ከ9 እስከ 15 ይመላለሳሉ።

1. መስከረም መዓልቱ 12፣ ሌሊቱ 12 ሰዓት ነው።
2. ጥቅምት መዓልቱ 11፣ ሌሊቱ 13 ዓሰት ነው።
3. ኅዳር መዓልቱ 10፣ ሌሊቱ 14 ሰዓት ነው።
4. ታኅሣሥ መዓልቱ 9፣ ሌሊቱ 15 ሰዓት ነው።
5. ጥር መዓልቱ 10፣ ሌሊቱ 14 ሰዓት ነው።
6. የካቲት መዓልቱ 11፣ ሌሊቱ 13 ሰዓት ነው።
7. መጋቢት መዓልቱ 12፣ ሌሊቱ 12 ሰዓት ነው።
8. ሚያዝያ መዓልቱ 11፣ ሌሊቱ 13 ሰዓት ነው።
9. ግንቦት መዓልቱ 14፣ ሌሊቱ 10 ሰዓት ነው።
10. ሠኔ መዓልቱ 15፣ ሌሊቱ 9 ሰዓት ነው።
11. ሐምሌ መዓልቱ 14፣ ሌሊቱ 10 ሰዓት ነው።
12. ነሐሴ መዓልቱ 13፣ ሌሊቱ 11 ሰዓት ነው።

መንፈቀ ሌሊትም በዶሮ ጩኸት ይታወቃል።

ሰዓታት በየወሩ እንዴት እንደሚመላለሱ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን። አንተ በትክክል ቁመህ የራስህ ጥላ በደረሰበት ላይ ምልክት ታደርጋለህ። ሰዓቱንም ለማወቅ እግርህን በማፈራረቅ እየሰፈርህ ትቈጥራለህ። ከመገፕመርያው ሰዓተ መዓልት እስከ ሠርክ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ነው። ከታኅሣሥ ወር እስከ ሠኔ ወር 1½ ጫማ በየወሩ ትቀንሳለህ። ዳግመኛም ከሠኔ ወር እስከ ታኅሣሥ ወር 1½ ጫማ በየወሩ ትጨምራለህ።





በታኅሣሥም ወር መገፕመርያው ሰዓት 29 ጫማ እንደሆነ በዚህ ታውቃለህ። ሰዓቱ በጥር ወር 27½ ጫማ ነው። በየካቲት ወር 26 ጫማ፣ በመጋቢት ወር 24½ ጫማ፣ በሚያዝያ ወር 23 ጫማ፣ በግንቦት ወር 21½ ጫማ፣ በሠኔ ወር 20 ጫማ፣ ከዚህ በኋላ ፀሐይ ይመለሳል፤ ሰዓታትም ይተካከላሉ። ያውም እንዲህ ነው።

ሐምሌ ከግንቦት ጋር፣ ነሐሴ ከሚያዝያ ጋር፣ መስከረም ከመጋቢት ጋር፣ ጥቅምት ከየካቲት ጋር፣ ኅዳር ከጥር ጋር ሰዓታቸው አንድ ነው።

የታኅሣሥ ሰዓት ግን የሚለፈረው ብቻውን ነው። ያንጊዜ የመዓልት ስፍረ ሰዓት አንሶ፣ የሌሊት ስፍረ ሰዓት ይበዛልና። ዳግመኛም የሠኔ ሰዓት የሚሰፈረው ብቻውን ነው። ያንጊዜ የመዓልቱ ስፍረ ሰዓት ረዝሞ፣ የሌሊቱ ስፍረ ሰዓት ያጥራል።

ዳግመኛም አንድ ሰዓት ካገኘህ፣ ከርሱ ዐሥር ቀንሰህ ሁለት ሰዓት ታገኛለህ። ሁለት ሰዓት ካገኘህ፣ ከእርሱ አራት ቀንሰህ ሦስት ሰዓት ታገኛለህ። ሦስት ሰዓት ካገኘህ፣ ከርሱ ሦስት ቀንሰህ አራት ሰዓት ታገኛለህ። አራት ሰዓት ካገኘህ፣ ከርሱ ሁለት ቀንሰህ አምስት ሰዓት ታገኛለህ። አምስት ሰዓት ካገኘህ ከእርሱ አንድ ቀንሰህ፣ ስድስት ሰዓት ታገኛለህ። ስድስተኛው ሰዓት የሚሰፈረው ብቻውን ነው። ያውም የቀትር ጊዜ ነው። ከዚህ በኋላ ጥላ ይመለሳል፤ ሰዓቶችም ይተካከላሉ። ያውም እንዲህ ነው፡-

7 ሰዓት ከ5 ሰዓት ጋር አንድ ነው፣ 8 ከ4 ሰዓት ጋር፣ 9 ከ3 ሰዓት ጋር፣ 10 ከ2 ሰዓት ጋር፣ 11 ከ ሰዓት ጋር እኩል ነው። 12 ሰዓት ግን የሚሰፈረው ብቻውን ነው። ያውም 70 ጫማ ነው። ይህም የፀሐይ መግባት ጊዜ ነው።

አንተ ግን፣ ይህን የጾም ሥርዓት ስተውለህ ጠብቅ። ጠይቀህም ተረዳ። ሰነፎች ሰዎች አሉና ጾም በ፤ በኝ ሰዓት ይፈታል የሚል ከመጻሕፍት በሰሙ ጊዜ፣ በዘጠኝ ጫማ ያለ መስሏቸው ጾማቸውን በዚያን ጊዜ ይፈታሉ። ስለዚህ እነርሱ ይህ ስፍረ ሰዓት



www.ethiopianorthodox.org

በየወሩ እንዴት እንደሚመላለስ ባለማወቃቸው፣ ታላቅ በደልን ይበድላሉ። አንተ ግን ተሳስተህ እንዳትበድል ይህን ተረድተህ እወቅ። ዳግመኛም በየወሩ የሚሆነው የሰዓታት ዑደት ይህ ነው። ከታኅሣሥ ወር እስከ ሠኔ ወር 1½ ጫማ በየወሩ ይቀንሳል። ከሠኔ ወር እስከ ታኅሣሥ ወር በየወሩ 1½ ጫማ ይጨምራል።

## ስፍረ ሰዓት

ተመሳሳይ የሆኑ ወሮችን በሁለት በሁለት መድበን ስፍረ ሰዓታቸውን ከዚህ በታች እናሳያለን።

1. የመስከረምና የመጋቢት ስፍረ ሰዓት እንዲህ ነው፡- 1 ሰዓት 24 ጫማ ነው። 2 ሰዓት 14 ጫማ፣ 3 ሰዓት 10 ጫማ፣ 4 ሰዓት 7 ጫማ፣ 5 ሰዓት 5 ጫማ ነው። የ6 ሰዓት ስፍሩ ብቸኛ ነው። ያውም የቀትር ጊዜ ነው። ከዚህ በኋላ ጥላ ይመለሳል። ሰዓቶችም ይተካከላሉ። ያውም 7 ከ5 ሰዓት ጋር፣ 8 ከ4 ሰዓት ጋር፣ 9 ከ3 ሰዓት ጋር፣ 10 ከ2 ሰዓት ጋር፣ 11 ከ1 ሰዓት ጋር እኩል ናቸው ማለት ነው። የ12 ሰዓት ስፍር ግን ብቸኛ ነው። ያውም 70 ጫማ ነው። ይህም ፀሐይ የምትገባበት ጊዜ ነው።

2. የጥቅምትና የየካቲት ስፍረ ሰዓትም እንዲህ ነው፡- 1 ሰዓት 26 ጫማ ነው። 2 ሰዓት 16 ጫማ፣ 3 ሰዓት 12 ጫማ፣ 4 ሰዓት 9 ጫማ፣ 5 ሰዓት 7 ጫማ፣ 6 ሰዓት 6 ጫማ ነው። ከዚህ በኋላ ጥላ ይመለሳል። ሰዓቶችም ይተካከላሉ። ያውም 7 ከ5 ሰዓት ጋር፣ 8 ከ4 ሰዓት ጋር፣ 9 ከ3 ሰዓት ጋር፣ 10 ከ2 ሰዓት ጋር፣ 11 ከ1 ሰዓት ጋር እኩል ናቸው ማለት ነው። የ12 ሰዓት ስፍር ግን ብቸኛ ነው። ያውም 70 ጫማ ነው።
3. የኅዳርና የጥር ስፍረ ሰዓትም እንዲህ ነው፡- 1 ሰዓት 27 ጫማ ነው። 2 ሰዓት 17 ጫማ፣ 3 ሰዓት 13 ጫማ፣ 4 ሰዓት 10 ጫማ፣ 5 ሰዓት 8 ጫማ ነው። 6 ሰዓት 7 ጫማ ነው። ከዚህ በኋላ ጥላ ይመለሳል። ሰዓቶችም ይተካከላሉ። ያውም 7 ከ5 ሰዓት ጋር፣ 8 ከ4 ሰዓት ጋር፣ 9 ከ3 ሰዓት ጋር፣ 10 ከ2 ሰዓት ጋር፣ 11 ከ1 ሰዓት ጋር እኩል ናቸው ማለት ነው። የ12 ሰዓት ስፍር ግን ብቸኛ ነው። ያውም 70 ጫማ ነው።





4. ታኅሣሥ ብቸኛ ወር ነው። የርሱ ስፍረ ሰዓትም እንዲህ ነው፡- 1 ሰዓት 29 ጫማ ነው። 2 ሰዓት 19 ጫማ፣ 3 ሰዓት 15 ጫማ፣ 4 ሰዓት 12 ጫማ ነው። 5 ሰዓት 10 ጫማ ነው። 6 ሰዓት 9 ጫማ ነው። ከዚህ በኋላ ጥላ ይመለሳል። ሰዓቶችም ይተካከላሉ። ያውም 7 ከ5 ሰዓት ጋር፣ 8 ከ4 ሰዓት ጋር፣ 9 ከ3 ሰዓት ጋር፣ 10 ከ2 ሰዓት ጋር፣ 11 ከ1 ሰዓት ጋር እኩል ናቸው ማለት ነው። የ12 ሰዓት ስፍር ግን ብቸኛ ነው። ያውም 70 ጫማ ነው።
5. የሚያዝያና የነሐሴ ስፍረ ሰዓትም እንዲህ ነው። 1 ሰዓት 23 ጫማ ነው። 2 ሰዓት 13 ጫማ፣ 3 ሰዓት 9 ጫማ ነው። 4 ሰዓት 6 ጫማ ነው። 5 ሰዓት 4 ጫማ ነው። 6 ሰዓት 3 ጫማ ነው። ከዚህ በኋላ ጥላ ይመለሳል። ሰዓቶችም ይተካከላሉ። ያውም 7 ከ5 ሰዓት ጋር፣ 8 ከ4 ሰዓት ጋር፣ 9 ከ3 ሰዓት ጋር፣ 10 ከ2 ሰዓት ጋር፣ 11 ከ1 ሰዓት ጋር እኩል ናቸው ማለት ነው። የ12 ሰዓት ስፍር ግን ብቸኛ ነው። ያውም 70 ጫማ ነው።
6. የግንቦትና የሐምሌ ስፍረ ሰዓትም እንዲህ ነው። 1 ሰዓት 21 ጫማ ነው። 2 ሰዓት 11 ጫማ ነው። 3 ሰዓት 7 ጫማ ነው። 4 ሰዓት 4 ጫማ ነው። 5 ሰዓት 2 ጫማ ነው። 6 ሰዓት 1 ጫማ ነው። ከዚህ በኋላ ጥላ ይመለሳል። ሰዓቶችም ይተካከላሉ። ያውም 7 ከ5 ሰዓት ጋር፣ 8 ከ4 ሰዓት ጋር፣ 9 ከ3 ሰዓት ጋር፣ 10 ከ2 ሰዓት ጋር፣ 11 ከ1 ሰዓት ጋር እኩል ናቸው ማለት ነው። የ12 ሰዓት ስፍር ግን ብቸኛ ነው። ያውም 70 ጫማ ነው።
7. ሠኔ ብቸኛ ወር ነው። የርሱ ስፍረ ሰዓትም እንዲህ ነው፡- 1 ሰዓት 20 ጫማ ነው። 2 ሰዓት 10 ጫማ ነው። 3 ሰዓት 6 ጫማ ነው። 4 ሰዓት 3 ጫማ ነው። 5 ሰዓት 1 ጫማ ነው። 6 ሰዓት አልቦ ወይም ዜሮ ነው። ከዚህ በኋላ ጥላ ይመለሳል። ሰዓታትም ይተካከላሉ። ያውም 7 ከ5 ሰዓት ጋር፣ 8 ከ4 ሰዓት ጋር፣ 9 ከ3 ሰዓት ጋር፣ 10 ከ2 ሰዓት ጋር፣ 11 ከ1 ሰዓት ጋር እኩል ናቸው ማለት ነው። የ12 ሰዓት ስፍር ግን ብቸኛ ነው። ያውም 70 ጫማ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

## የወሮቹ ጥላ ስፍር በጫማ

| የዕለቱ ክፍለ ጊዜያት | ሰዓት | መስከረም መጋቢት | ጥቅምት የካቲት | ኅዳር ጥር | ታኅሣሥ | ሚያዝያ ነሐሴ | ግንቦት ሐምሌ | ሰኔ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዐቢይ ነግህ | 1 | 24 | 26 | 27 | 29 | 23 | 21 | 20 |
| ንኡስ ነግህ | 2 | 14 | 16 | 17 | 19 | 13 | 11 | 10 |
| ዐቢይ ሠለስት | 3 | 10 | 12 | 13 | 15 | 9 | 7 | 6 |
| ማእከላዊ ሠለስት | 4 | 7 | 9 | 10 | 12 | 6 | 4 | 3 |
| ንኡስ ሠለስት | 5 | 5 | 7 | 8 | 10 | 4 | 2 | 1 |
| ዐቢይ ቀትር | 6 | 4 | 6 | 7 | 9 | 3 | 1 | አልቦ |
| ማእከላዊ ቀትር | 7 | 5 | 7 | 8 | 10 | 4 | 2 | 1 |
| ንኡስ ቀትር | 8 | 7 | 9 | 10 | 12 | 6 | 4 | 3 |
| ዐቢይ ተሰዓት | 9 | 10 | 12 | 13 | 15 | 9 | 7 | 6 |
| ማእከላዊ ተሰዓት | 10 | 14 | 16 | 17 | 19 | 13 | 11 | 10 |
| ንኡስ ተሰዓት | 11 | 24 | 26 | 27 | 29 | 23 | 21 | 20 |
| ሠርክ | 12 | 70 | 70 | 70 | 70 | 70 | 70 | 70 |

## የሌሊትና የመዓልት ጥላ ስፍር መበላለጥ ባጭሩ

| | መስከረም መጋቢት | ጥቅምት የካቲት | ኅዳር ጥር | ታኅሣሥ | ሚያዝያ ነሐሴ | ግንቦት ሐምሌ | ሰኔ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሌሊቱ | 12 | 13 | 14 | 15 | 11 | 10 | 9 |
| የመዓልት | 12 | 11 | 10 | 9 | 13 | 14 | 15 |





## መክደኛ

፩. ሰም ለበስ ሰደፌ ግጥም፣
የመጽሐፉን ምሥጢር የሚተረጉም ፤

እነ ድሜጥሮስ የሠሩት ቤት
ተቀይሷል ሲመሠረት
ባራቱ ማዕዘን ክፍለ ሰንበት፤
በመሐንዲሱ በድሜጥሮስ
የሚተረጉም ብሉይ ከሐዲስ
መነሻው ብሉይ መድረሻው ሐዲስ
ጽንፍ ከጽንፍ የሚያመላልስ፤
የመግቢያው አንቀጽ ሃያ ስምንት
አምስት መቶ ነው የክፍሉ ብዛት
ከነበረንዳው ሠላሳ ሁለት
የክፍሉም ብዛት ዞሮ ለማየት
አይጨረስም በአንድ ሰንበት
ሦስቱን ሰንበት ካልጨመሩበት
የሰንበትን ትርጉም እንረዳው
መቶ ሠላሳ ከሦስት ነው።
በሌላ መንገድም ብንመረምረው
ሰባት ጊዜ አሥራ ዘጠኝ ነው፤
ማኽል የቆመው ተቅዋመ ማኅቶት
ሰባ ስድስት ነው ያምፖሉ ብዛት
ሲያበራ ይኖራል እስካለም ኅልፈት፤
ከዚህ ይታያል የብርሃን ጮራ
ጽንፍ እስከ ጽንፍ የሚያበራ፤
ይህን ብርሃን ማየት የማይችል
የዓይኑን ብሌን የሀገር ባህል፤
ይታከም ተግቶ በየዕለቱ



www.ethiopianorthodox.org

ባገር ሐኪሞች በሊቃውንቱ፤
የዓይን ሕመም ለሚጋርደው
እንዲታከም የተዘጋጀው
የመጽሐፍ ስሙ መርሐ ዕዉር ነው፡፡
ከዓይን ሕመም እንድትድኑ
ይህንን መጽሐፍ ተግታችሁ አጥኑ፤
ዳፍንት ከኾነ የዓይኑ ሕመም
አሻግሮ እንጂ የግሩን አያይም፤
የሚያስናክለውን የግሩን ካላየ
እገደል ገብቶ ይላል እየየ፤
ከዚህ አደጋ ለመጠንቀቅ
ያገሩን መንገድ ቀድሞ ይወቅ፡፡
ከመንገዶቹም አንዱ ይኸው ነው
ከፍጥረት እስከ ምጽአት የተዘረጋው፤
ይህንም መንገድ ብንለካው
ባገር መስፈርያ በተዘጋጀው
ለስምንት ሺሕ ሃያ ፊሪ ነው፤
ያለሙም ዕድሜ አለጥርጥር
ተወስኗል በስምንት ቁጥር
ሐሰት እንደኾነ ዳዊት ይመስክር
ባሥር ቢበዛ ስምንቱ ቁጥር
ሰማንያ ይሆናል እንዳለው መዝሙር፤
ሰማንያም ማለት ስምንት ሺሕ ነው
የስምንተኛው ሺሕ ትርጉም ይህ ነው፤
የሚልም ቢገኝ እንዴት ታወቀ
ብዙ መልስ አለ የተራቀቀ፤
እንደሚታወቅ ዛፍ በፍሬው
ስምንተኛም ሺሕ ታውቋል በሥራው፤
ፍቅርም ጠፍቷል ከሰው መንፈስ
እንደተጻፈው በማቴዎስ፤
ወዳዳራሹ አሁን እንመለስ





ከባለቤቱ ከድሜጥሮስ፤
ምንም ጨለማ የለ በቤቱ
ኹላችኁ ጉብኙት በየዕለቱ፤
የቤቱ ወለል ቀድሞ ቢሠፈር
በነቢያት ዘንግ በሐዋርያት በትር
በሊቃውንትም በነአቡሻህር
አሥራ አምስት ሜትር በ15 ቀመር
መጠኑ ኾናል አለጥርጥር
ከዚያም አይበልጥ ከዚያም አያጥር፤
ግድግዳው ንኡስ ጣራው ዐቢይ
ሰማየ ሰማያት ዕመቀ ዕመቃት የሚያሳይ፤
እንድትረዱ የቀመር ምሥጢር
በዚሁ ያለው የዘመን ቁጥር
የተረጋገጠ በሰባት ምስክር
ሒዳችኁ እዩት በማለብ እግር፤
ያንቀጹ መግቢያ እንየው አሁን
የተከፈለ በሰባት እርከን፤
በዚህ እርከን ካልተራመዱ
አይታወቅም ዙርያ መንገዱ፤
እየተባዛ ደግሞም ቢቈጠር
ስድሳው ሱባኤ በዐሥራ አምስት ቀመር
ከዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሜትር
ሰባት ሺሕ ነው የቊጥሩ ድምር፤
የግጥሙን ምሥጢር ለመረዳት
እንብቡት ዛሬ መጽሐፉን ከቤት፤
ብዙ ጥያቄ እያሰባችኁ
ቢወጣ ቢወርድ ከኅሊናችኁ
መጽሐፉን እዩት ተመልሳችኁ
መልሱን ለማግኘት ትችላላችኁ፤
ቀርቦላችኋል የአዝማን ቀመር
ከፍጥረት እስከ ምጽአት የሚያበሥር



www.ethiopianorthodox.org

የሰማይና የምድርን ነገር
የቤቱ አናጢ የቤቱ መምህር
ሠርቶላችኋል መባጃ ሐመር፤
በጾም በጸሎት በወንድም ፍቅር
እየዋኛችሁ በዘመን ባሕር
ተሻግራችሁ የባሕሩን ድንበር
ባዲሱ ሰማይ ባዲሲቱ ምድር
እንድትኖሩ ከአብርሃም ጋር፤
የዘመኑ ቁጥር ሐሳበ ባሕር
የጾሙም ማውጫ መባጃ ሐመር
ተሠይሟል በነአቡሻህር
ስሙን ከግብሩ ለማስተባበር
እያቈራኙ ንባብ ከምሥጢር።

*፪. ሐተታዊ ወዳጅ ግጥም፤*
*የሚተረጉም የዘመናት ሕልም ፤*

ዳዊት በመዝሙሩ ቀንና ሌሊት
አድኅነኒ ብሎ የጸለየው ጸሎት
ለዚሁ ጊዜ ነው ለሌለው ሃይማኖት
የሚነጋገረው በከናፍረ ጉኅሉት፤
ከናፍረ ጉኅሉት ፖለቲካ ነው
የሚናገርበት የዘመኑ ሰው
በስምንተኛ ሺሕ የተፈጠረው፤
የስምንተኛ ሺሕ መለያ ሥዕል
ከናፍረ ጉኅሉት መሆኑ ታውቋል
እንዲሁም ጦርነት ረኃብና በቀል
እንደተጻፈው በማቴዎስ ወንጌል፤
ቀዳማዊ አዳም የመጣበት ቀን
ሲታወቅ ተችሏል በእንድቅትዮን፤
የእንድቅትዮን ትርጉም የእንድቅትዮን ምሥጢር





እንደሚታወቀው በአሥራ አምስት ቁጥር
ኅልፈትም ታውቋል በ15 ቀመር፤
እንድቅትዮን ማለት ዓርብ ዕለት ናት
ቀዳማዊ አዳም የተፈጠረባት፤
ኅልፈትም ማለት ዕለተ ምጽአት ናት
ዳግማዊ አዳም ፍርድ የሚሰጥባት፤
ጳውሎስ በላከው ለጢሞቴዎስ
ፍቅር የሌለበት መሐላም የሚያፈርስ፤
በኋለኛው ዘመን ይመጣል ትውልድ
ከራሱ በስተቀር ወንድሙን የማይወድ
በክሥተት አምኖ አምላኩን የሚክድ
ተብሎ ተጽፏል በዚሁ ምዕላድ፤
የኋለኛው ዘመን ስምንተኛ ሺሕ ነው
ብለው ተርጉመውታል የቀድሞ አበው፤
‹‹ ንዑና ሑሩ›› የሚለው አዋጅ
ያን ጊዜ ይሰማል በክርስቶስ ደጅ፤
በሰባቱ ዕለታት የተሠራው ዓለም
ምሥጢሩ ታወቀ በሰባት ማኅተም
በዮሐንስ ራዕይ በዳንኤል ሕልም
ከፍጥረት እስከ ምጽአት የሚተረጉም፤

*፫. ወርቃ ወርቅ ሰደፌ ግጥም፤*
*ላዲሱ ትውልድ እጅግ የሚጠቅም ፤*

የቀድሞ አባቶች የፈለሰፉት
ባሕረ ሐሳብ ነው ባሕረ ጥበባት
ተዘጋጅቷል በአዲስ ሥርዓት
አዲሱ ትውልድ እንዲማርበት፤
ይህን መጽሐፍ ተግተን እናንብብ
እንዳይረሳ የአበው ጥበብ
ተዘግቶ ያለው ከጥንቱ መዝገብ

www.ethiopianorthodox.org

በገዳምና በአድባራት ግንብ፤
የአበው ጥበብ የተበደለ
አዲሱን ትውልድ ስማኝ እያለ
ያቀርባል ዛሬ አቤቱታውን
በሰማይ ላለ ለአምላካችን፤
ወጣቶች ሁሉ ይኸንን ተማሩ
በሀገር ባህል እንድትኮሩ፤
ያገሩን ታሪክ ያገሩን ባህል
የማይረዳ የማያስተውል
ይባል የለም ወይ ማወቅ የማይችል
የወለደችው እናቱን በገድል
ተቀምጣ ሳለች በሴቶች ማኻል፤
የእናቱን መልክ ለማያውቅ ሰው
ሁሉም ይለዋል የእንጀራ ልጅ ነው፤
በተውሶ ልብስ የሚኰራ ወንድ
ይናቅ የለም ባሰተዋዮች ዘንድ፤
ሲመለከቱት ያንን ይመስላል
በባዕድ ቋንቋ በባዕድ ባህል
የሚኰራ የሚያፌችል
ያልተረዳውን ባህል ለሚንቅ
ይተረትበታል ተብሎ በሊቅ
አባቱን አያውቅ አያቱን ናፈቅ፤
ያገርን ባህል ኹሉም ይወቀው
ለሀገር ፍቅር መሠረቱ ነው፤
በአረንጓዴ በብጫ በቀይ
በኹሉም አገር አጊጦ ሚታይ
ያገር ባህል ነው ከኹሉም በላይ፤
ቀይና ብጫ አረንጓዴማ
የምነት የተስፋ የኪዳን አርማ
ቀድሞ የመጣ ለኖኅ ከራማ
በመስቀለ ወልድ ሰንደቅ ዓላማ





ተሰቅሎ ታየ በመፍርህ ግርማ
በአዲሲቱ ወንጌል ከተማ፤
በዚህ ከተማ በዚህ መንደር
መኖር የሚሻ በሰላም በክብር
የአምላክና የወንድም ፍቅር
የቁጥሩ ተራ የኾነ ዐሥር
መታወቂያው ነው ይዞ ይሞክር
መግባት ይችላል በጠባብዋ በር፤
እንደ ኀምስቱ ደናግል ጠባባት
እንድንችል ቀድመን ለመግባት፤
ይዘን እንቅረብ መታወቂያውን
ሰዓቱ ሳይደርስ በሩ ሳይዘጋብን፤
ወጣቱ ትውልድ የአገር ልጅ
በዕውቀት በሥራ እንዲደረጅ
ትምህርቱ ሲሰጥ ከዚህም ከዚያም
ከወጭው በፊት ያገሩ ይቅደም፤
ከአገር ትምህርት ካቆዩት አበው
አስትሮኖሚ የሚባል ይኸ ነው፤
በግእዝ ቋንቋ ተጽፎ ያለው
ፈለክ ፈለካት የሚያሳየው፤
አንርሳቸው አባቶችን
ይህንን ቅርስ ያቈዩልን
እናስባቸው በኀሊናችን
መርገመ ጌባል እንዳይደርስብን፤ (ዘዳ.27፥13)
ለሚያከብር ያባቱን ቃል
በረከተ ገሪዛን ይሰጠዋል፤
አባትና እናት አክብር የሚለው
ከዐሥሩ ትእዛዝ ከተወሰነው
የአምላክን ሕግ ከሚያስረዳው
በመዓርግ አራተኛ ነው፤
ከትእዛዛቱም መገመርያ



www.ethiopianorthodox.org

ለኤፌሶን ሕዝብ እንደተጻፈው
በጳውሎስ በሐዋርያው፤
አባት እናቱን የሚያከብር
ዕድሜው ይረዝማል በዚሁ ምድር፤
እንዲህ የሚለው የተስፋ ቃል
በብሉይ በሐዲስ ተጽፏል፤
የተስፋው ፍሬ እንዲሰጠን
እናክብራቸው ወላጆችን፤
አባትና እናት የሚለው ቃል
ይተረጐማል በብዙ ክፍል፤
በሥጋ ብቻ የወለዱን አባትና
ማለት አይደለም የትርጓሜው ስልት፤
ሁሉንም በዕድሜ የሸመገለው
እንዳባት እናት አክብር ማለት ነው፤
ወጣቶች ሁሉ በኀሊናችሁ
ይህንን ምሥጢር ተገንዘባችሁ
አባት እናትን እርዱ እባካችሁ ፤
በዚህ ዓለም ላይ ለምንሠራው
ይከፈለናል ሲደርስ ቀጠሮው
አይለወጥም ቁናው አንድ ነው፤
ወደ ጥንተ ነገር እንመለስ
ያገርን ባህል ለማስታወስ፤
ይህ ብቻ አይደለም ያበው ትምህርት
ተዘግቶ ያለው በዕቃ ቤት
እጅግ ብዙ ነው ሒዳችሁ እዩት፤
ትምህርቱን አጥኑት ከዚያም ሒዳችሁ
ኢትዮጵያዊ ለመሆናችሁ
እርሱ ነውና መታወቂያችሁ፤
በዓለም ኹሉ እንድትፈሩ
በሀብት በጸጋ እንድትከብሩ
በተዋሕዶ ጸንታችሁ ኑሩ፤





ስብሐት ለእግዚአብሔር በአርያም
በምድርም ሰላም፤
በጎ ፈቃዱም ለሰው ልጆች ይሁን። አሜን።
(ያሬድ ፈንታ ወልደ ዮሐንስ፤ 1975 ዓ.ም.)



www.ethiopianorthodox.org

## ስምዓት

መሠረት ስብሐት ለአብ፤ ትውፊታዊ ኅሳበ ዘመንና ታሪኩ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አቋም፤ሆንግ ኮንግ፤ ኒው ላይፍ ሊትሬቸር፣1981 ዓ.ም.።

መጽሐፍ ቅዱስ– የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፤ አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣1953 ዓ.ም.።

ማኅበረ ሐዋርያት፤ዘሄኖክ ነቢይ፤በመጽሐፈ ነገሥት፤ አሥመራ፣ኮከበ ጽባሕ ቤት ማኅተም፣1983 ዓ.ም.።

ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (ሊቀ መዘምራን)፤ሥነ ፍጥረት ምስለ ኀምስቱ አዕማደ ምሥጢር፤አሥመራ፣ኮከበ ጽባሕ ዘማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት ማተሚያ ቤት፣1957 ዓ.ም.።

ማኅበረ ሐዋርያት፤ብሉይ ኪዳን ሰመንቱ ብሔረ ኦሪት፤ አሥመራ፣ኮከበ ጽባሕ ዘማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት ማተሚያ ቤት፣1959 ዓ.ም.።

አባ ቴዎፍሎስ ሊቀ ጳጳስ፤መዝሙረ ዳዊት ንባቡ ከትርጓሜው ከጥንት የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣ፤አዲስአበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1950 ዓ.ም.።

አባ ዮሲማስ ዘውእቱ በኀይለ ሚካኤል፤ነገር ወዜና ሕይወት ትርጓሜ ራእዩ ለዮሐንስ፤በPatrologia Orientalis No.28, Tunhout/Belgique,1980. Das Hexaëmeron,Munchen,1882.

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ.ም.።

--------------------፤መጽሐፈ ሕዝቅኤል ከትርጓሜው ጋራ ንባቡ በግእዝ ትርጓሜው በአማርኛ፤1916 ዓ.ም.።

ወንጌል ቅዱስ ንባቡ ከትርጓሜው ከቀድሞ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ፤አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም





ማተሚያ ቤት፣1959 ዓ.ም.

ያሬድ ፈንታ፤ የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር፤ውስተ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም.(2000)፤ አዲስ አበባ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ 2000 ዓ.ም.።

ያሬድ ፈንታ ወልደ ዮሐንስ፤መጽሐፈ ግጻዌ ሐዲስ ዘተሰንአወ በአርባዕቱ ክፍላተ አዝማን፤አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣7489 ዓ.ዓ. (1989 ዓ.ም.)።

--------------------------፤ፍኖተ ግእዝ (ዘመናዊ)፤አሥመራ፣ ፍራንቸስካና ማተሚያ ቤት፣7486 ዓ.ዓ. (1986 ዓ.ም.)።

----------------------------፤ባሕረ ሐሳብ፤ውስተReview Of Ethiopian Culture, CFIPT, 1995.

---------------፤አርእያና አምሳል፤ውስተ ፈለገ ጥበብ መጽሔት፤3ኛ ዓመት፣ቍጥር 9፣ሐምሌ-ነሐሴ 1993 ዓ.ም.።

----------------፤ሐሳበ ዘመን ዘኢትዮጵያ፤ውስተ ሰዋስወ ብርሃን መጽሔት፤1ኛ ዓመት፣ቍጥር 2፣1988ዓ.ም.።

---------------፤የዘመን አቈጣጠር-ዓመተ አዳም ወኖኅ፤ውስተ ፈለገ ጥበብ መጽሔት፤ 2ኛ ዓመት፣ቍጥር 2፣መስከረም 1992 ዓ.ም. ።

ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ፤አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣1959 ዓ.ም.።

ጌራ ወርቅ ጥበቡ (መጋቤ ምሥጢር)፤ዳንኤልና አሥራ ሁለቱ ደቂቀ ነቢያት፤ አዲስ አበባ፣ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣1998 ዓ.ም.።



www.ethiopianorthodox.org

--------------------- ፤ መጻሕፍተ ብሉያት፦ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘፀአት አንድምታ ትርጓሜ፤ አዲስ አበባ፣ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ 1999 ዓ.ም.።

ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው፤አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣1958 ዓ.ም.።

## ያልታተሙ

- መጽሐፈ ሔኖክ ዘግእዝ፡ በስመ እግዚአብሔር ሥሉስ ዘእንበለ ፍልጠት ዘሔኖክ ነቢይ ብሎ የሚጀምር።
- ትርጓሜ ወንጌል ዘመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል፣ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደተረጐመው።
- ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ
- መርሐ ዕዉር
- አቡሻኽር





## ስለ ደራሲው

አለቃ ያሬድ ፈንታ ወልደ ዮሐንስ ሐረቀ ማርያም፣ሕንጣሎ ወረዳ፣እንደርታ አውራጃ ትግራይ ጠቅላይ ግዛት በ፸፬፻፲፭ (7415) ዓመተ ዓለም፣፲፱፻፲፭ (1915) ዓመተ ሥጋዌ፣ ፲፱፻፳፫(1923) ዓመተ ምሕረት፣በዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ፣ሚያዝያ መባቻ ተወለዱ።

ከፊደል እስከ ድጓ በተወለዱበት አካባቢ፣ ከዚያም ቅኔን ከመምህር ጌራ ወርቅ ገብረ እግዚአብሔር፣ ባሕረ ሐሳብን ከአለቃ ወልደ ኪሮስ ገብረ መድኅን ተምረዋል። በጨለቆት ደብረ ምሕረት ቅድስት ሥላሴ ከመምህር ቀለመ ወርቅ ድጓ፣ ምሥራቅ አዲጉደም አራ በምትገኘው ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ከመምህር ስብሐተ ሥላሴ መዋሥዕት፣ በመቀጠልም ወደ ጎንደር ሔደው ከመምህር ክፍሌ ትግሬው አቋቋም ተምረዋል። ዝማሬ መዋሥዕት በመምህርነት አስመስክረዋል።

እንዲሁም በአዲስ አበባ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ አራት ዓመት ተምረው ተመርቀዋል።በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በቅድስት ሥላሴ ኮሌጅ ሳሉ በ1940ዎቹ በኢትዮጵያ ሬዲዮ በየሳምንቱ እሑድ ቃለ ወንጌል አስተምረዋል። በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅም ከ1976 እስከ 2000 ዓ.ም. ለ24 ዓመታት ባሕረ ሐሳብን አስተምረዋል። ካሳተሟቸው የአማርኛና እንግሊዝኛ ሰዋስው፣ የግእዝና የግጻዌ መጻሕፍት ሌላ በነገረ መለኮትና ነገረ ማርያም፣ባሕረ ሐሳብ ዙርያ በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎች በተለያዩ መጽሔቶች ላይ አውጥተዋል።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት፣

1. በግእዝ ቋንቋና ሰዋስው፣ቅኔም ከነአገባቡ፤
2. ጸዋትወ ዜማ (ጾመ ድጓና ምዕራፍ፣ዝማሬና መዋሥዕት፣ድጓም)
3. ሥርዓተ ማሕሌት (ጸዋትወ ዜማውና ቅኔው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውልበት ይትበሃል ወይምየአቋቋም አደራረስ)



www.ethiopianorthodox.org

**4.ባሕረ ሐሳብ** (በአዕዋዳት፣በአቅማራትና በሱባዕያት እየቀመረ የዘመናትን ምሥጢር እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ቈጥሮና ሰፍሮ የሚያስረዳ)

በእነዚህ ትምህርቶች አገልግሎት ለመስጠት በቂ ሙያ አላቸው።



www.ethiopianorthodox.org